# የመንፈስ ቅዱስ ባሕሪና አገልግሎት

## የአስተምህሮ መንፈስ ቅዱስ ጥናት

ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በዊሊያም ፋራድ እና ካንኢንግሃም ብላክበርን ተዘጋጅቶ በ"ሥነ መሰኮት በቤቴ" አማካኝነት ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ የአስተምህሮ መንፈስ ቅዱስ የመማርያ መጽሐፍ።

**Counselor, Teacher, & Guide**
**A study of The Holy Spirit**

የመጀመርያ እትም
ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
1995 - አዲስ አበባ



ማውጫ ገጽ

መግቢያ ........ 5
1. የመንፈስ ቅዱስ ምሉዕ አካላዊነት ........ 7
2. መለኮታዊ አካል ........ 26
3. የሚረዳን አካል ........ 44
4. የመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ........ 61
5. መልዕክት የሚያስተላልፍ መንፈስ ........ 77
6. ዳግም ልደት የሚያስገኘው መንፈስ ........ 97
7. ኃይልን የሚሰጥ መንፈስ ........ 116
8. በመንፈስ ማምለክ ........ 135
9. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ........ 154
10. የመንፈስ ፍሬ ........ 175
የሙከራ ፈተና መልሶች ........ 190

## መግቢያ

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ አገልግሎቱ ማብቂያ ላይ ከደቀ መዛሙርቱ የሚለይበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ እንዲህ በማለት ተናገረ

> እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው። ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም። እናንተ ግን አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ።

ኢየሱስ የተናገረው ስለ ሥላሴ ሦስተኛው አካል፣ ስለመንፈስ ቅዱስ ነበር። እግዚአብሔር አብ ልጁን ኢየሱስን ወደዚህ ምድር በመላክ እርሱ ምን እንደሚመስል አስታወቀን። ኢየሱስም ወደ አባቱ ወደ ሰማይ ሲያርግ፣ በአማኞች ልብ ውስጥ እንዲኖር መንፈስ ቅዱስን ላከው። መንፈስ ቅዱስም ክርስቶስን ለእኛ ይገልጽልናል። ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስን በአይናችን ባናየውም፣ እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑ ሊሰማን ይችላል፤ ራሳችንንም ለእርሱ ባስገዛን መጠን በሕይወታችን ውስጥ ሲመራን እናስተውላለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ እንደ ምሳሌ ወይም ምልክት ሆነው የቀረቡ የተለያዩ ነገሮች አሉ፡- ንፋስ (የሐዋ. 2:2)፣ እርግብ (ማቴ. 3:16-17)፣ እሳት (ማቴ. 3:11)፣ ውሃ (ዮሐ. 7:37-39)። እነዚህ ምልክቶች መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ያለውን የተለያየ የአገልግሎት ገጽታዎች የሚወክሉ ናቸው። እርሱ ከአጠገባችን አብሮን የሚጓዝና በገርነት የሚረዳን ወዳጃችን በመሆኑ፣ በእርግብ ይመሰላል። በውስጣችን የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ነው። መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያጠራና በክርስቶስ ካገኘነው አዲስ ሕይወት ጋር አብሮ ስለማይሄደው ነገር ሁሉ የሚወቅስን ቅዱስ እሳት ነው። በመንፈስ በተሞሉ አማኞች ውስጥ ታምራታዊና ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የሚገለጥና የሚሠራ ታላቅ ንፋስ ነው።

በዚህ ኮርስ ከወዳጅህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንድትተዋወቅ እንፈልጋለን። እርሱ የሚያመዛዝን፣ የሚሰማውና ውሳኔ የሚያደርግ የግል ወዳጅህ ሊሆን የሚችል ነው፤ የእግዚአብሔር ባሕርያት ሁሉ ያሉት መለኮታዊ ወዳጅ ነው፤ እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በአጠገብህ ቆሞ የሚረዳህ ወዳጅ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ታላቅ ኃይል ያለው ወዳጅም ነው፤ በፍጥረት ሥራ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው፤ የእግዚአብሔርንም መልዕክት ወደ ሰው የሚያስተላልፍና ለጠፉት ዳግም ልደት የሚሰጥ ነው። በአምልኳችን ይረዳናል፣ አንዱ ሌላውን እንዲያገለግል በማድረግና የክርስቶስን መልክ በእኛ ውስጥ በመሥራት በተግባር የሚሠራ ወዳጅ ነው።

ይህን ኮርስ ስታጠና ልብህ እንዲነሳሳና መለኮታዊ ወዳጅ ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የቀረበና የግል ግንኙነት እንዲኖርህ ጸሎታችን ነው። ከዚህም የተነሳ ወደ መንፈሳዊ ብስለት ልትገሰግስና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት የሚያስገኘውን ወሰን የሌለው በረከት ልትለማመድ ትችላለህ።

***የመንፈስ ቅዱስ ባህሪና አገልግሎት*** የሚለው ይህ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስን ባህሪና ከፍጥረት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ያለውን ሥራውን የሚያስተምር የመግቢያ ኮርስ ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደ ግል ወዳጅ ሆኖ ቀርቧአል። ታላቅ ኃይሉንና ተግባራዊ ዕርዳታውንም እንማራለን። ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም ይገልጻል። የጴንጤቆስጤ ልምምድ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፣ አማኝ ለመመስከር፣ ለማገልገልና የተቀደሰ ኑሮ ለመኖር ኃይል እንዲሞላ ያደርጋል። ይህ ትምህርት በመንፈስ ስለተሞላ ሕይወት መማር ለሚወድ ተማሪ ተግባራዊ መመርያ ሆኖ ያገለግላል።

## የትምህርቱ አዘገጃጀትና የአጠናኑ ስልት

እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ይይዛል።

1. ርዕስ
2. መግቢያ
3. የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
4. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች
5. የትምህርቱ ዝርዝር
6. ለጥናቱ የሚረዱ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
7. የሙከራ ፈተና (ከትምህርቱ በስተመጨረሻ)
8. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስና በመጽሐፉ መጨረሻም የሙከራ ፈተናዎች መልስ ቀርበዋል።

የትምህርቱ አከፋፈልና ዓላማዎች በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ሃሳብ ይሰጣሉ፤ ጥናቱን በምታጠናበት ወቅት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነጥቦች ላይ እንድታተኩር ይረዱሃል።

በትምህርቱ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ክፍት ሥፍራዎችን በመሙላት ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም ረዘም ያሉ መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ መጻፍ ይገባል። መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ የምትጽፍ ከሆነ የጥናቱን ቁጥርና ርዕሱን መመዝገብህን እርግጠኛ ሁን።

የራስህን መልሶች ከመስጠትህ በፊት በመጽሐፉ የቀረቡትን መልሶች አትመልከት። የራስህን መልሶች የምትሰጥ ከሆነ ያጠናኸውን ጥናት በተሻለ ሁኔታ ትረዳዋለህ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ከመለስህ በኋላ በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። ከዚያ በኋላም በትክክል ያልመለስካቸውን አርማቸው። የቀረቡትን መልሶች በድንገት ተመልከተህ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳትችል መልሶቹ የቀረቡት በቁጥር ቅደም ተከተል አይደለም። እነዚህ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በጥናቱ የቀረቡትን ዋና ዋና ሃሳቦች እንድታስታውስ ከመርዳቱም በላይ ከትምህርቱ ያገኘሃቸውን የሕይወት መርሆዎች ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዱሃል።



# 1

## ትምህርት

# የመንፈስ ቅዱስ ምሉዕ አካላዊነት

ለአንድ ሰው በሚደረግ የእቀባበል ግብዣ ላይ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ከሚቀበሉት ሰው ይልቅ ምግብና መጠጡን ወይም የሚቀርበውን የተለያየ ዝግጅት ዋነኛ ጉዳይ ያደርጉታል። የመንፈስ ቅዱስንም ጥምቀት መቀበል ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው ብዙ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ የተቀበሉትን በረከት በሥራው ያወራሉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አካል ያለው መሆኑን ፈጽሞ ይረሳሉ።

መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ አንደኛው በመሆኑ ምሉዕ አካላዊነት አለው። ፍጹም አካል ስለሆነም ጥልቅ የሆነ ፍላጎታችንን ሙሉ በሙሉ የሚያረካና በእግዚአብሔር መንግሥት ሥፍራችን እኛን የሚያዘጋጅ ስለሆነ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ እንችላለን። በዚህ ክፍለ ትምህርት የምንከታተለው ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት የሚናገሩትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችንና እነዚህም ማስረጃዎች ለእኛ ስላላቸው አስፈላጊነት ይሆናል።

## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- አካላዊ ባሕርያቶቹ
- አካላዊ አገልግሎቶቹ
- አካላዊ ስያሜዎቹ
- ግላዊ ግንኙነታችን

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፦

- የመንፈስ ቅዱስን የግል ስያሜዎች፣ ባሀርያቶችና የግል ተግባሮች በመረዳት መንፈስ ቅዱስ ምሉዕ አካላዊነት ያለው መሆኑን ማስረጃ መስጠት
- አካል በመሆኑ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊኖረን የሚችለው የአንድ ለአንድ ግንኙነት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ መግለጽ።

---

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የክፍለ ትምህርቱን ዓላማ መገንዘብ ትምህርቱን በሚገባ ለመከተል ስለሚረዳህ የመጽሐፉን መግቢያ በጥንቃቄ አንብብ፤
2. የመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት የቀረበበትን አከፋፈልና ዓላማዎች በጥንቃቄ ተመልከት፣ ትምህርቱን ስታጠና ማወቅ የሚገባህን ነገሮች እንድትለይ ስለሚረዳህ በጥንቃቄ አንብብ።
3. የክፍለ ትምህርቱን ዝርዝር አንብብና በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩትን መልመጃዎች አጠናቅ። መልሶቹን ለመስጠት ደግሞ ማስታወሻ ደብተርህን ተጠቀም። በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶቹ ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸው ካሉ አስተካክል።
4. በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሰፈረውን የሙከራ ፈተና ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን በጥንቃቄ አስተካክል።

---



## የትምህርቱ ዝርዝር

# አካላዊ ባሕርያቶቹ

***ዓላማ 1 ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት የሚገልጹ ማስረጃዎችን ለይቶ ለመምረጥ።***

### መግቢያ

ስለ አካላዊነት በምታስብበት ጊዜ ምናልባት የምታስበው እንደ አንተው የሚያስብና ስሜት ያለው እንደዚሁም ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ስላለው ሰው ይሆናል። የማወቅና የስሜት እንደዚሁም የመምረጥ ችሎታ ለእኛ የተሰጠን ከእግዚአብሔር ነው። እኛም በእርሱ አምሳል የተፈጠርን ነን።

የተሟላና ፍጹም አካላዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፥ እውነተኛ ምሳሌ የሚሆነን እርሱ ነው። እኛ የእርሱ ቅጅዎች ነን። ዓላማችን መንፈስ ቅዱስ እኛን ስለሚመስል አካላዊነት አለው ብለን ለመናገር አይደለም። ይልቁንም የእኛ ባሕርይ ከመለኮታዊው ምሳሌ ጋር እንዲመሳሰል የተሠራ በመሆኑ ተመሳሳይና መሠረታዊ የአካላዊነት ባህርያቶች አሉን። እነዚህም የማሰብ፣ የስሜትና የመወሰን ችሎታዎች ናቸው።

እነዚህ አካላዊነትን የሚያሳዩ ባሕርያት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የሚገኙ ናቸው። እርሱ ሕያው የነበረ ነው። በእርግጥ እንደምናስተውለው እርሱ የሕይወት ምንጭና ሕይወት ሰጭ በመሆኑ ለእርሱ ከተሰጡት ስሞች አንዱ "የሕይወት መንፈስ" የሚል ነው (ሮሜ 8:2)።

ሁልጊዜ አካል እንደ አንድ የሚታይና የሚዳሰስ ቁሳዊ ወይም ገላ አድርገን በማሰባችን ምክንያት "አካል" የሚለውን ቃል እውነተኛ ትርጉም እንስታለን። የአካልን እውነተኛ ባሕሪና ችሎታዎችን የሚያመለክቱትን እንደማወቅ ችሎታ፥ የስሜትና የመምረጥ ችሎታ የመሳሰሉትን ማየት ይሳነናል። መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው ኃይል ብቻ ቢሆን - የእርሱ ባሕርይ በዕለት ኑሮህ ትርጉም ይሰጥህ ነበርን? ማሰብ የሚችል፣ ሊሰማውና ለመምረጥ የሚችል ፍጹም አካል ስለሆነ የአንተን ፍላጎቶች ወደ እግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ደግሞ ወደ አንተ ለማስተላለፍ ፍጹም መንገድ የሆነ እርሱ ነው።

(1). መንፈስ ቅዱስ አካል ነው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ የሚያመለክተው የትኛው ነው?

ሀ. እንደ እኛ ነው።
ለ. የአካላዊነት አስፈላጊ ባሕርያት አለው።
ሐ. መንፈሳዊና ሥጋዊ ሀልው ነው።
መ. መንፈሳዊ ሀልው ነው።

ከዚህ ቀጥለን የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ባሕርያት በመመልከት ለእኛ ያላቸው አስፈላጊነት ምን እንደሆነ እንመረምራለን።

## የማወቅ ችሎታ

*ዓላማ 2 ስለ መንፈስ ቅዱስ የማወቅ ችሎታ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚናገር ለመረዳት የተሰጡትን ክፍሎች ለማገናዘብ።*

ከአካላዊነት ባህርያቶች አንደኛውና የመጀመሪያው የማወቅ ችሎታ ነው። ይህንም ችሎታ የሚያያዘው ከአእምሮ ጋር ነው። መንፈስ ቅዱስ በማስተዋልና በጥበብ እንደሚሠራ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል።

> "ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳል (ሮሜ 8:2)።
>
> "መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል፣ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው። በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም" (ቆሮ. 2:10-11)።

በዚሁ በሁለተኛው ምንባብ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያነጻጽረው ሰው ሰውን ለማወቅ ያለውን አካላዊ ችሎታ መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ካለው አካላዊ ችሎታ ጋር ነው፤ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ይህ አካላዊ ችሎታ ግንኙነቱ ዘለቄታ ካለው ከሰው መንፈስ ጋር እንጂ ከሚሞተው ገላው ጋር አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድና የሰዎችን ፍላጎቶች የማወቅ ችሎታው በተግባራዊ መንገድ ውጤታማ ረዳትና አማካሪአችን በመሆን እንዲያገለግለን ያስችለዋል። ይህ እውነት በተሻለ መንገድ ተብራርቶ የቀረበው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለገጠማት ችግር መፍትሔ ለመፈለግ በኢየሩሳሌም ስብሰባ ባካሄደችበት ወቅት ነበር። ታሪኩን ተጽፎ የምናገኘው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሲሆን የቤተ ክርስቲያኒቱን አንድነት ሊያጠፋ የሚችል ቀውስ በገጠማቸው ጊዜ ሐዋርያቱና ሽማግሌዎቹ መንፈስ ቅዱስ የምሪትና የመጽናናት ምንጭ ሆነላቸው። የመንፈስ ቅዱስ መኖር ከሁለቱም ወገን መደረግ ያለበትን አስፈላጊውን ነገር ስላሳያቸው ሐዋርያቱ፦ መንፈስ ቅዱስና እኛ መልካም ሆኖ አግኝተነዋል በማለት ለመጻፍ ቻሉ (የሐዋ. 15:28)። እዚህ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥበብና መለኮታዊ እውቀት አይሁዶችን የሚያረካ፣ አሕዛብንም የሚያበረታታ መፍትሔ ለቤተ ክርስቲያን በማስገኘት ውጤታማ በሆነ መንገድ ይበልጥ ወንጌል እንዲስራጭ አደረገ።



እንግዲህ አካል ማወቅ የሚችልና ራሱም የሚታወቅ ነው። እንደ ተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ ሁለቱን ባሕርያት የያዘ ነው። እርሱ እኛን ከማንም ይልቅ በተሻለ መንገድ ያውቀናል። ምን ያህል ደህና አድርገህ እንደምታውቀው የሚወስነው ከእርሱ ጋር ባለህ ዕለታዊ ሕብረት ስለ እርሱ ምን ያህል እንደምትማር በማወቅ ነው። በሩቅ እንደሚታወቅ ወይም እንደ ቅርብ ጓደኛ አድርገህ ትይዘው ይሆናል። ብዙዎች "አውቀዋለሁ" ብለው ሲናገሩ በሩቅ ብቻ እንደሚያውቁት ያስታውቃል። እንደ ቅርብ ጓደኛ አድርገው የሚያውቁት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው። በተሻለ ቅርበት እርሱን ለማወቅ ትፈልጋለህ? እርሱን በተሻለ መንገድ የምታውቀው ይበልጥ ጊዜህን ከእርሱ ጋር በመሆን ስታጠፋ ነው።

(2). የማወቅ ችሎታ የመንፈስ ቅዱስ____________ ባሕርይ ነው።

(3). በሮሜ 8:27 እና በ1ቆሮ. 2:10-11 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት መግለጫውን በተሻለ መንገድ የተሟላ የሚያደርገውን ምረጥ፦ መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እኛን ሊያገለግል የሚችለው . . .

ሀ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ፍላጎት ስለሚያውቅ ነው።
ለ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሕዝቡ ምን እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው።
ሐ. ሕዝቡ የሚፈልጉት ነገሮች ምን እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው።
መ. ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ሀ፣ ለ፣ እና ሐ ትክክል ናቸው።
ሠ. ከላይ በ"ሀ" እና በ"ለ" ላይ የተጠቀሱትን ትክክል ናቸው።

(4). ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ባህሪ የሚገልጠው እንዴት ነው? "መንፈስ ቅዱስና እኛ መልካም ሆኖ አግኝተነዋል?"

## የስሜት ችሎታ

*ዓላማ 3 ስለ መንፈስ ቅዱስ የስሜት ችሎታ የሚገልጹትን ቀጥሎ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስመግለጽ።*

ሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት መግለጫ ባሕርይ የስሜት ወይም ስሜትን የመለማመድ ችሎታ ነው። ስሜት የመውደድን ችሎታ፣ የሀዘንና የመጎዳትን እንደዚሁም ቁጣን የሚያካትት ነው። መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን ሲሰራ ሳለ እነዚህን ስሜቶች ሁሉ የማስተናገድ ችሎታ እንዳለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች እንረዳለን።

ፍቅር፣ እንደ እውቀት ሁሉ፣ ሰው ለሰው ወይም - አካል ከአካል ጋር ባለው ግንኙነት የሚገለጥ ነው። ፍቅርን ለመግለጽ አካላዊነት ሊኖርህ ይገባል፤ ፍቅርህንም የምትገልጸው አካላዊነት ላለው ካልሆነ በቀር ምንም ትርጉም አይኖረውም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ በሮሜ 5:5 ላይ ሲገልጽ፦ "እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና" ይላል። በሮሜ 15:30 ላይ ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ሊወደድ የሚችል፣ እኛንም መውደድ የሚችል፣ ሌሎችንም በእኛ ውስጥ አልፎ ሊወድድ የሚችል አካል ነው።

ፍቅር የአንድን ሰው ስሜቶች ወደ ሌላው ማስተላለፍ ነው። ይህ ፍቅር ትርጉም ያለው እንዲሆን መልዕክቱን በደስታ ተቀብሎ ምላሽ የሚሰጥ ያስፈልገዋል።

መንፈስ ቅዱስ የተሟላ አካላዊነት ስላለው የእግዚአብሔርን ፍቅር መግለጽ ይችላል። ከጥንት ጀምሮ ከሰው ዘር ጋር ባለው ግንኙነት የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ማስረጃ በግልጽ የሚታይ ነበር። በኖኅ ዘመን ኃጢአትና ክፋት በምድር ላይ እየተስፋፋ በመሄዱ መንፈስ ቅዱስ አዘነ። የሀዘን ስሜቱን እጅግ ትልቅ ነበር። በዚህም ምክንያት በዘፍ. 6:3 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚነግረን፡ "እግዚአብሔርም . . . መንፈሴ እያዘነ ከእርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም" በማለት ተናገረ። መንፈስ ቅዱስ የስሜት ችሎታ ስላለው የሰዎች ኃጢአትና አመጽ ሊያሳዝነው ይችላል። በዚህም ረገድ የእርሱ ፍቅር በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ነበር ማለት ነው።

ብዙ ሰዎች ለመንፈስ ቅዱስ ፍቅርና ትዕግሥት ተገቢውን ምላሽ አልሰጡም። ከዚህ እንደምናየው ለእነርሱ ባህርይ እርሱ የሚሰጠው ምላሽ ሌላ የአካላዊነቱና የስሜት ችሎታውን ያመለክታል። እርሱ በሚያሳዝኑት ጊዜ የሚሰማው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በማያምኑ ሰዎችና ክርስቶስን በተቀበሉ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ይናገራል። የማያምኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር አይደሉም። በኃጢአተኛ ባሕሪያቸው ቁጥጥር ስር ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ አማኞች በለውጥ ሂደት ውስጥ ያሉና ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ነው። አማኙ ክርስቶስን በመምሰል አዲሱን መንፈሳዊ ሕይወት እያሻሻለ የሚሄድበትን መንገድ የሚወስነው ሕይወቱን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በመስጠቱ እንደሆነ በግልጽ የሚታወቅ ነው (ሮሜ 8:5-15ን፣ ከኤፌ. 4:17-32 አነጻጽር)። አዲሱ አማኝ ከጊዜ በኋላ ወደ አሮጌው ሕይወቱ በመመለስ ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር አስፈላጊውንና ተገቢውን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ እንደሚያዝን በኤፌ. 4:30 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

አንድ የምትወደው ሰው ባሳዘንህና ባስቀየምህ ጊዜ እንዴት እንደተሰማህ ታስታውሳለህ? መንፈስ ቅዱስም ስናሳዝነው የሚሰማው እንደዚያ ነው።

(5). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ስለማሳዘን ወይም ስለ ማስቀየም የተጠቀሰውን በተሰጠው ስፍራ አስፍር።



ሀ. የሐዋ. 5:3
ለ. የሐዋ. 7:51
ሐ. ዕብ. 10:29
መ. ሉቃ. 12:10
ሠ. ማቴ. 12:31-32

(6). ኤፌ. 4:25-32፣ እና 5:1-7 ላይ የተጻፈውን ቃል ካነበብህ በኋላ "እነዚህን ነገሮች በማድረግ ወይም ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠት እርሱን አሳዝኜ ይሆን?" በማለት ራስህን ጠይቅ። አመለካከትህን ወይም ባህርይህን መለወጥ እንደሚያስፈልግህ ከተሰማህ እነኛን ነገሮች በመዘርዘር በማስታወሻ ደብተር ላይ ጻፍ።

## የመምረጥ ችሎታ

*ዓላማ 4 ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች መንፈስ ቅዱስ ሉዓላዊ ፈቃዱን የሚፈጽምባቸውን መንገዶች ለመምረጥ።*

የአካላዊነት ሌላው ዋና ባህርይ የመወሰን ችሎታ ነው። የሥነ ምግባር ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ያለው በፈጣሪው አምሳል የተፈጠረ ፍጡር ሰው ብቻ ነው። ዘላለማዊ ፍጻሜውን የሚወስን ምርጫ የመምረጥና የማድረግ ችሎታ አለው። አንድ ሰው ነጻ ፈቃዱን ሊለማመድ የሚችለው ምርጫ በማድረግ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባሕርያት አንዱ ፍጹም የሆነ ኃይሉን ወይም ፈቃዱን በሥራ ላይ የማዋል ችሎታው ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በተግባር ላይ የዋለውን የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ያሳየናል።

በርናባስና ሳኦል ለተጠሩበት አገልግሎትና እርሱ ለመረጣቸው ሥራ እንዲለዩ ማድረጉ መንፈስ ቅዱስ በምርጫ ችሎታው እንዴት እንደሚሠራ የሚያመለክት ጥሩ ምሳሌ ነው (የሐዋ. 13:1-4)። በርናባስና ሳኦል መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ያለው መሆኑን በምንም መንገድ ሊጠራጠሩ አልቻሉም። ለጠራቸውና ለመረጣቸው አገልግሎት በይፋ እንዲለዩ ያደረጋቸው እርሱ ነበር። ለእነርሱ የሰጠው የግል ጥሪ መልእክት እርሱ እግዚአብሔር እንዲያከናውኑ ለጠራቸው አገልግሎት ሊቀባቸው የመጣ መለኮታዊ ኃይል ብቻ ሳይሆን ከዚያም የበለጠ መሆኑን የሚያመለክትና የሚገልጥ ነው። እንደ ሥልጣኑ ፈቃድ በፈለገ ጊዜ ለይቶ የሚመርጥ መለኮታዊ አካል ያለው ነው።

(7). በሮሜ ምዕራፍ ፰ ላይ የተጻፈውን ካነበብህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፈቃዱን እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውል ለማሳየት እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር የተሟላ አድርግ።

ሀ. በሮሜ 8:5 ላይ የተጻፈው የሚያስተምረን መንፈስ ቅዱስ __________
ለ. በሮሜ 8:9 ላይ የተጻፈው የሚያሳየን መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን _____
ሐ. በሮሜ 8:26 ላይ የተጻፈው መንፈስ __________ ይገልጻል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ በቂ ግንዛቤ ካለህ ይህ በእርግጥ ለአንተ አዲስ አይሆንም። ጳውሎስ ሲያስተምር መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቹን እንደፈቃዱ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ያከፋፍላል (1ቆሮ. 12፡7-11)። በሌላ አባባል መንፈስ ቅዱስ ራሱ ስጦታዎቹን የሚገልጥባቸውንና የሚሰራባቸውን ሰዎች ይመርጣል ማለት ነው። ይህ ሆን ተብሎ የሚደረግ ምርጫ የመንፈስ ቅዱስ የግል ውሳኔ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተገለጠ ቁጥር የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባሕርይ እየተገለጠ ነው።

(8). የሚከተሉት መግለጫዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ባሕርይ ማስረጃዎች ናቸው። መግለጫው እውነት ከሆነ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ የአካላዊነት ባሕርያት ያለው ሕያው ሀልው ነው።
ለ. በዚህ ክፍለ ትምህርት እንደተገለጠው የአካል አስፈላጊ ባህርያቶች የማወቅ፣ የስሜትና የመወሰን ችሎታዎች ናቸው።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ተዳሳች ገላ ስለሌለው ፍጹም አካል ከመሆን ያግደዋል።
መ. መንፈስ ቅዱስ የአካልን ስሜታዊ ባሕርያት ያሳያል።
ሠ. የመንፈስ ቅዱስ የስሜት ችሎታ የሚገለጠው ለእኛ ባለው ስሜቶችና ለእኛ ስሜቶች ባለው ምላሽ ነው።
ረ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት የአካል ለአካል ግንኙነት ነው።
ሰ. መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ስጦታዎቹን የሚያከፋፍለው እንደ ስጦታው ተቀባዮች አባላት ምርጫ ነው።
ሸ. በ1ቆሮ. 2፡10-11 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚያስረዳን የማወቅ ችሎታ የእግዚአብሔርም መንፈስ ሆነ የሰው መንፈስ ሁለቱም ያላቸው ችሎታ ነው።

## አካላዊ አገልግሎቶቹ

### *ዓላማ 5 መንፈስ ቅዱስ እንደ አስተማሪና እንደ አስተዳዳሪ እንደዚሁም እንደ አጽናኝ በመሆን የሚሠራባቸውን መንገዶች ለመግለጽ።*

በሰው ሳይታቀድ የተቋቋመ መሥሪያ ቤት ሊኖር ይችላል ብለህ ማሰብ ትችላለህ? መሥሪያ ቤቶች ዘወትር የሚያዙት በሠራተኞች ነው። መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ስላለው እንደ አስተማሪና እንደ አስተዳዳሪ እንደዚሁም እንደ አጽናኝ ሆኖ ሊሠራ ይችላል።

### የማስተማር አገልግሎት

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ብዙ ነገር ለማስተማር ፈልጎ ነበር፤ እነርሱ ግን ትምህርቱን ለመቀበል ዝግጁዎች አልነበሩም። ስለዚህ ሌላ አስተማሪ እንደሚልክላቸው ቃል ገባላቸው።



የመንፈስ ቅዱስ የግል የማስተማር አገልግሎት ባይጨመርበት ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው መንፈሳዊ ኃይል እንደማይኖረው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በሚገባ ይረዳሉ። እርሱ እውነቱን በማብራራት ትምህርቱ በዕለት ኑሮ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

ኢየሱስ ስለሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሲያስተምር፣ "አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፣ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል" በማለት ተናግሯል (ዮሐ. 14:26)። በዮሐ. 15:26 ላይ ደግሞ እሱ ስለኔ ይመሰክራል በማለት ተናግሮአል። በመጨረሻም ኢየሱስ በዮሐ. 16:13-15 ስለ መንፈስ ቅዱስ ተግባር የበለጠ ገለጻ በመስጠት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

> "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል . . . ወደፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድ ያከብረኛል፤ የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው። እንግዲህ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል።"

የክርስቶስን ቃል በዕለት ኑሮአችን በተግባር ላይ ለማዋል መንፈስ ቅዱስ ግልጽ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያብራራልን ዝግጁ ሆነን መጠበቅ ይኖርብናል። በችግር ጊዜያት የክርስቶስን የማበረታቻ ቃላት ለማስታወስ እንድንችል የማስታወስ ችሎታችንን ይቀሰቅሳል (ማር. 13:11)። ከዚህም በላይ ወደ እውነት ሁሉ በመምራት ወደ መንፈሳዊ እድገት እንድንደርስ ያደርገናል። በመጨረሻም የወደፊቱን ለእኛ በመግለጽ ክርስቶስን የሚያከብር ሕይወት በመኖር ተገቢውን ምላሽ እንድንሰጥ ይረዳናል (ቲቶ. 2:11-14)።

አንዳንድ ጊዜ በአስተማሪና በተማሪ መካከል ያለው ግንኙነት በቤተሰብ አባላት መካከል እንዳለ ግንኙነት የተቀራረበ ይሆናል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት እንደ አስተማሪና ተማሪ የተቀራረበ ሊሆን ይችላል። አስተማሪያችን መንፈስ ቅዱስ ከእያንዳንዳችን ጋር የግል ግንኙነት ያለው ፍጹም አካል ነው።

(9). መንፈስ ቅዱስ ሁሉን እንደሚያስተምረን የሚናገረው ቃል ትርጉም፦

ሀ. ከመንፈስ ቅዱስ ከምናገኘው በስተቀር ሌላ ትምህርት አያስፈልገንም ማለት ነው።
ለ. መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል ሁሉን ነገር እንረዳለን ማለት ነው።
ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና መንፈስ ቅዱስ ይመራናል፥ እውነቱንም ደግሞ ይገልጽልናል።

## የማስተዳደር አገልግሎት

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ "የሐዋርያት ሥራ" ተብሎ ከሚሰየም "የመንፈስ ቅዱስ ሥራ" ተብሎ ቢሰየም የበለጠ ተስማሚ ርዕስ ይሆን ነበር። መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ቀን በወረደ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ተቆጣጣሪና መሪ ሆነ። የሐዋርያት ሥራ መንፈስ ቅዱስን የሚያቀርበው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴዎች የሚቆጣጠር መሪ አድርጎ ነው። የእርሱ የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች ምን ምን ነበሩ?

በምድረ በዳ ለሚጓዝ ለአንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፥ ፊልጶስ ወንጌል እንዲሰብክለት መሪ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነበር። ወደ ጃንደረባው ሰረገላ ገብቶ እንዲመሰክርለት ፊልጶስን ያዘዘው መንፈስ ቅዱስ ነው (የሐዋ. 8:26-40)።

(10). ፊልጶስ ለጃንደረባው የሰጠው ምስክርነት ወዲያው ያስከተለው ውጤት ምን ነበር?

ጴጥሮስ ምንም እንኳን ሊያደርገው የሚፈልገው ነገር ባይሆንም ለአንድ የአህዛብ መቶ አለቃ የወንጌል አገልግሎት እንዲያበረክት መንፈስ ቅዱስ እንደመራውና እንደላከው እንመለከታለን (የሐዋ. 10:19-48)።

(11). የጴጥሮስ አገልግሎት በመቶ አለቃውና በቤቱ መልእክቱን በሰሙት ሁሉ ላይ ወዲያው ያስከተለው ውጤት ምን ነበር?

መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን በአንጾኪያ ከነበራቸው አገልግሎት ለይቶ በየአገሩ እየተዘዋወሩ የሚሲዮናዊነት አገልግሎት እንዲሰጡ (የሐዋ. 13:1-3)፤ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ አንድነት በማምጣት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለአይሁድና ለአሕዛብ ወንጌል እንደሚገባ እንዲሰበክ አድርጎአል (የሐዋ. 15)። ይህ ድርጊት ወንጌል ዓለም አቀፋዊ መልዕክት እንዲኖረው አድርጓል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ እስያ ገብቶ ወንጌል ለመስበክ በሞከረ ጊዜ ወደዚያ እንዳይሄድ መንፈስ ቅዱስ ከለከለው (የሐዋ. 16:6-7)። ይህን ምዕራፍ ስታነብ በዚያን ወቅት መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያው ጳውሎስ ሌላ እቅድ እንደነበረው ትረዳለህ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች የሾማቸውና ቤተ ክርስቲያንን በእነርሱ ስር ያደረገ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ባሳሰባቸው ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን አስተዳደር በደንብ አሳውቆአል (የሐዋ. 20:28)። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ የማስተዳደር ተግባራት ሁሉ የሚያጸኑት የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ይመራ ዘንድ በኢየሱስ የተላከው መንፈስ ቅዱስ ምሉዕ ስብዕና እንዳለው ነው።



(12). ለሚከተለው ጥያቄ የተሻለውን መልስ ምረጥ። ከላይ እንደተመለከትነው ፊልጶስ፣ ሳውልና ጴጥሮስ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዲታዘዙ ያደረጋቸው ምን ነበር?

ሀ. ከእርሱ ጋር የርስ በርስ ግንኙነት ስለነበራቸውና እርሱን ስላመኑ።
ለ. እርሱን እንዲታዘዙ ስለተገደዱ።
ሐ. ውጤቶቹ ምን እንደሚሆኑ ስላወቁ

## የማጽናናት አገልግሎት

ኢየሱስ ዓለምን ትቶ ወደ ሰማይ በሄደበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ታውከው ነበር። ያለ እርሱ ተስፋቢሶች ስለነበሩ በዮሐ. 14:16 ላይ፦ "እኔም አብን እለምነዋለሁ፣ እርሱም ለዘላለም ከእናንተ ጋር የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው። ይህ አጽናኝ የሚለው ቃል ጰራቅሊጦስ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ረዳት፣ አጽናኝ ወይም አማካሪ ማለት ነው። "ሌላ" የሚለው ቃል የእርሱ ዓይነት የሆነ ሌላ ማለት እንደሆነ የግሪክ ምሁራን ያመለክታሉ። መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ የተለየ አካል ሲሆን በዓይነቱ እርሱን የሚመስል እንደርሱ ምሉዕ አካላዊነት ያለው ነው። ክርስቶስ ተስፋ የሰጠው ምክር፣ መጽናናት ወይም እርዳታ ለመስጠት ሳይሆን፣ ምሉዕ ስብዕና ያለው ረዳት፣ አጽናኝ ወይም አማካሪ ለመስጠት ነው።

(13). ከዚህ ቀጥሎ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብክ በኋላ መግለጫዎቹን የተሟላ አድርግ። ዮሐ. 14::15-18፣ 26፤ 15:26፣ 16:12-15።

ሀ. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ______________ እንደሌላቸው፣ ብቻቸውን እንደማይተዋቸው ቃል ገባላቸው።
ለ. የእርሱን ስፍራ ለዘላለም እንዲወስድ አባቱ ሌላ__________ እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ።
ሐ. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ምንን የሚያካትት ነው?
መ. ሌላው አጽናኝ ሲመጣ የሚከተሉትን እንደሚያደርግ ኢየሱስ ተናገረ። የእርሱ የሆኑትን ወደ ____ ______________ ይመራቸዋል። እንዲሁም ለ ____________________ ክብርን ያመጣል።

(14). በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በመሙላት አብሮ የሚሄደውን አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ___ሀ. ስለ ኢየሱስ ቃል ያስታውሰናል፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል፤ ቃሉን ግልጽ ያደርግልናል። | 1. አስተማሪ |
| ___ለ. የእኛ ረዳት፣ መካሪና አጽናኝ በመሆን የሌላውን ስፍራ ይወስዳል። | 2. አስተዳዳሪ |
| ___ሐ. ለቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ምሪትንና መሪዎችን ይሰጣል። | 3. አጽናኝ |

# አካላዊ ስያሜዎች

*ዓላማ 6 የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት የሚያሳዩ ስያሜዎችን ምሳሌ ለመስጠት።*

የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ከሚያሳዩት ባህርያትና ተግባራት በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ አካላዊ ስሞችንና ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም ይጠራዋል። መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ90 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ እናገኛለን። ይህ አካላዊና አስፈላጊ ባሕርዩን የሚገልጽ ስሙ ነው። አሁን ደግሞ ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት እንዴት እንደገለጠ እንመለከታለን። መንፈስ ቅዱስም ራሱን እንዴት እንደ አካል እንደገለጸ እንረዳለን።

## በኢየሱስ የተገለጠው

ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት በተናገረ ጊዜ በዮሐ. 14፣ 15 እና 16 ላይ የሰጠውን ተስፋ በደብልጥ ጠለቅ ብለን እንመልከት። ኢየሱስ ስመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ስም በመስጠትና ተውላጠ ስም በመጠቀም በግልጽና በማያሻማ መንገድ ለመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ይሰጠዋል።

> "እኔ አብን እለምናለሁ፥ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ *አጽናኝ* ይሰጣችኋል" (ዮሐ. 14:16)። "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚወጣው *አጽናኙ* የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ *እርሱ* ስለ እኔ ይመሰክራል" (ዮሐ. 15:26)። የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። *እርሱ ከራሱ* አይናገርም የሚሰማውን ብቻ ይናገራል። እንዲሁም ወደፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል (ዮሐ. 16:13)።

ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደምንረዳው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲያውቁ የፈለገው በእርሱ ፋንታ የሚልከው አካላዊነት ያለው እንደሆነ ነው። *አጽናኝ* የሚለውን ስያሜ ሦስት ጊዜ ተጠቅሞአል። በተጨማሪም በአንድ አጭር የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ ሰባት ጊዜ "እርሱ" በሚል ተውላጠ ስም ተጠቅሞአል። እነዚህን ተውላጠ ስሞች ለመተው ወይም ያታዊ ባልሆነ ግዑዝ ስያሜ መጠቀም ይችል ነበር። እርሱ ግን እየደጋገመ የተጠቀመው እርሱ የሚለውን ተውላጠ ስም ነበር። ኢየሱስ እዚህ ላይ ትኩረት ለመስጠት የፈለገው አካላዊነት እንዳለውና እንደ አካል ሆኖም እንደሚሠራ ነው።

## በራሱ የተገለጠው

የመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳቦች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ ናቸው (2ጴጥ. 1:20-21)። ይህም ማለት ከተጻፈው ሁሉ በስተጀርባ መገለጥን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ መኖሩና እርሱም ምሉዕ አካላዊነት ያለው



መሆኑ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ድርጊቶችን አስመልክቶ የሚጠቀምበት አካላዊ መጠርያዎች አካላዊነት ስለመላበሱ የበለጠ ማስረጃ ይሰጣሉ።

ቀደም ሲል የተጠቀምንበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለራሱ የተናገራቸው መግለጫ በቀጥታና በግልጽ ስለዚሁ ያስረዳሉ። መንፈስ ቅዱስ እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስና ሳውልን ለዩልኝ በማለት ተናገረ (የሐዋ. 13:2)።

## በሐዋርያው ጳውሎስ የተገለጸው

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 8:1-27 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ስለሚገኘው ሕይወት በጻፈው መልዕክቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲጠቅስ የሚጠቀመው አካላዊነቱን የሚያመለክት ስያሜ ነው እንጂ በግዑዝ ስያሜ አልተጠቀመም (ሮሜ 8:16፣ 26)። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን የሚ መሰክረውና በድካማችን ጊዜ የሚረዳን አካል እንደሆነ በሚያመለክተው ስያሜ ተጠቅሷል። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንድንረዳ የፈለገው አእምሮአችንን የሚቆጣጠረው፣ መንፈሳዊ ሕይወትን በእኛ የሚያስገኘውና ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት እውነተኛ የሚያደርገው እንደዚሁም በድካማችን ጊዜ የሚረዳን እኛ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችል የአካላዊነት ባሕርያት እንዳለው ነው።

(15). በተሰጠው ስፍራ ቁጥጥሩን በማስገባት አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. ስለሚመጣው *አጽናኝ* በመናገር ሰባት ጊዜያት *እርሱ* በማለት በሰው ስያሜ ስለ እርሱ ጠቀሰ። | 1. ኢየሱስ |
| ____ለ. በርናባስና ሳውልን ለጠራኋቸው አገልግሎት ለዩልኝ በማለት ተናገረ። | 2. *መንፈስ ቅዱስ* |
| ____ሐ. *አጽናኙ* ሲመጣ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል በማለት ተናገረ። | |

(16). አካላዊነት ላለው ብቻ ሊሰጡ የሚችሉትን የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ስያሜዎች ዘርዝር።

# ግላዊ ግንኙነቶችን

*ዓላማ 7 መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል ስናውቀው የሚኖረንን የግል ግንኙነት ለመግለጽ።*

መንፈስ ቅዱስ አካል ስብዕና እንዳለው ማወቅ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስረዱ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ምክንያቶች አንደኛው በዚህ መልክ ስናውቀው ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ጥልቅ እንዲሆን ማድረግ ነው።

የእርሱን ስጦታዎች ተቀብለን በተግባር ላይ ለማዋል ከመፈለጋችን በፊት፣ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ለማወቅ ብንፈልግ ኖሮ የጸጋ ስጦታዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመለማመድ በኩል በጉልህ የሚታዩ ብዙዎች ችግሮች በተወገዱ ነበር። መንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ማወቅ እርሱን ለማስደሰትም ሆነ እርሱ እንዲጠቀምብን ጥልቅ የሆነ ፍላጎት እንዲያድርብን ያደርጋል። ይህም እውቀት የጸጋ ስጦታዎችን አሠራር ሊወስን አይገባውም፤ አይወስንምም።

## ትክክለኛ ግንኙነት

መንፈስ ቅዱስ የማወቅ ችሎታ ያለው አካል እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይህም ችግሮቻችንን ከእርሱ ጋር በመካፈል እንዴት እንደምንፈታቸው እንዲያሳየን ለማድረግ ጠንካራ መሠረት ሊሆነን ይገባል።

እርሱ ስሜት ያለው ሕልው እንደሆነም በማስረጃ ተመልክተናል፤ ይህም ማስረጃ እርሱ የሚፈልጋቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ በጥልቀት እንድናውቅ ያደርገናል። የእርሱን ፍላጎት ለማከናወን እንዲጠቀምብን መፍቀድ አለብን እንጂ የራሳችንን ፍላጎት ለመፈጸም እኛ በእርሱ ለመጠቀም ማሰብ የለብንም። እርሱን ልናየው የሚገባን አፍቃሪና በእኛ ክፉ አድራጎት ሊያዝን የሚችል፣ አድርገን ነው። እርሱን ከማስደሰት የበለጠ ራሳችንን ማስደሰት የለብንም።

> በመጨረሻም እርሱ የመምረጥና የመወሰን ችሎታ እንዳለው የሚያሳየውን ማስረጃ ተመልክተናል። የማወቅ ችሎታው ወሰን ወይም ገደብ የሌለው በመሆኑ ለእኛ የሚሻለው የቱ እንደሆነ ያውቃል። ከዚህም በላይ እርሱ እኛን መርጦናል። የእርሱም ምስክሮች እንድንሆን ኃይል ሰጥቶናል። እነዚህን ስጦታዎች ትልቅ ሥፍራ እንደምትሰጣቸው ተስፋ አደርጋለሁ። ቢሆንም ከስጦታዎቹ ሁሉ በላይ ለሰጪው ትልቅ ክብርና ዋጋም እንድትሰጥ ላሳስብህ እወዳለሁ።

## ትርጉም ያለው ግንኙነት

መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል በማወቅ ረገድ ከልምምድ ይልቅ ግንኙነት ለአማኙ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ማወቅ ወደሚያስደስቱ፡ ልምምዶች ሊያመጣን ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው እርሱን እንደ አካል ወደማወቅ ደረጃ ሲደርስ ብቻ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እውነተኛ ትርጉም ወዳለው ግንኙነት ሊገባ ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ ግንኙነት እያደገ የሚሄድ ነው። ይህ ዓይነቱ ግንኙነት መንፈሳዊ መብታችን እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ኀላፊነቶቻችንም ምን እንደሆኑ ደግሞ እንድናቅ ያደርገናል። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 3፡18 ላይ የዚህ ግንኙነት በየጊዜው እያደገ የመሄድን ባሕርይ ሲገልጽ፦ "የጌታን ክብር እንደ



መስታወት እያበሰጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።"

በሐዋ. 2:4 ላይ የተጻፈው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአንድ በኩል የዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው በስጦታዎች ልምምድ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንደ መጨረሻ ነገር አድርጎ ይወስዳል ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በተቀበለ ጊዜ ዓላማውን ከግቡ እንዳደረሰ ይስማማል። በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አካል የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ወደ ሕይወቱ እንደሚያስገባ አድርጎ ከተመለከተው እያንዳንዱ ቀን ይህን ግንኙነት ለማጠናከር በሚችል ተስፋ የተሞላ እንደሆነ ለመረዳት ይችላል። በሕይወት እስከለ ድረስ በመንፈስ ለመሞላት የሚፈልግ ከሆነ ይህ ግንኙነት ሳያቋርጥ እየተስፋፋ ሊሄድ የሚችል ነው (ኤፌ. 5:18)። በዮሐ. 14:16 ላይ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው ለዘላለም ከእኛ ጋር ሊኖር እንደሆነ ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ አስታውስ።

እስከ አሁን ድረስ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ብቻ በመሻትና ልምምድ ላይ ብቻ በማተኮር ከኖርህ፥ መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል ልታውቀውና ከእርሱ ጋር ያለህን የግል ግንኙነት ለይተህ የምታውቅበት ጥሩ አጋጣሚ ጊዜ አሁን ነው። በእርሱ መገኘት በኃይል እንድትሞላና ዋንኛ ፍላጎትህም እርሱን ማስደሰትና የእርሱን ፈቃድ ማድረግ እንዲሆን ይፈልጋል።

(17). ከዚህ በታች የተሰጡትን ምሳሌዎች በማጥናት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለህን ግንኙነት መርምር። በግል ግንኙነት ላይ በሚያተኩሩት ምሳሌ ዎች ቁጥር "1" ጻፍ። በልምምድ ላይ ብቻ በሚያተኩሩት ምሳሌዎች ደግሞ ቁጥር "2"ን በተሰጠው ባዶ ስፍራ በመጻፍ አመልክት።

___ሀ. የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ስቀበል የመንፈሳዊ እድገት መጨረሻ ላይ እንደደረስኩ ይሰማኛል።
___ለ. መንፈስ ቅዱስን ከተቀበልኩ ወዲህ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቴ አድጌአለሁ። እያንዳንዱም ቀን ደስ የሚልና ጥልቀት ያለው ሕብረት ከእርሱ ጋር እንዲኖረኝ እያደረገ ነው።
___ሐ. በረከትን ለማግኘት ስለምፈልግ ለመንፈሳዊው መነቃቃት ስብሰባ እስከሚቀጥለው ሳምንት መቆየት አላስችል ብሎኛል። በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኜ ለእሮጌው ሕይወቴ ስፍራ ስጥቼ እንኳን ቢሆን፤ መንፈስ ሲንቀሳቀስና መሥራት ሲጀምር ደግሞ ሁሉን ነገር ረስቼ የማተኩረው በረከቴ ላይ ብቻ ነው።
___መ. የብርታቴና የኃይሌ ምንጭ በሕይወቴ የመንፈስ ቅዱስ መኖር ነው። በሙላተ ጥምቀት ወደ ሕይወቴ ከመጣ ጀምሮ መንፈሳዊ እድገት አግኝቻለሁ። አሁን ያለኝ እቅድ እርሱን ማስደሰት ብቻ ነው።

(18). በዚህ ክፍለ ትምህርት በተከታተልነው መሠረት መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል ስናውቀው ከእርሱ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት የተሻለ መግለጫ የትኛው ነው? እርሱን እንደ አካል ካወቅነው ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር የምንፈቅድለትን የሚኖረንም ዝንባሌ የትኛው ነው?

ሀ. ባለን መንፈሳዊ ልምምዶቻችንና በሚሰጡን ስሜቶች ላይ ይሆናል።
ለ. እርሱን ማስደሰትና በይበልጥ በእርሱ ቁጥጥር ስር ለመሆንና በየዕለቱ ለንጽሕናዊ ባሕርይ እለመገዛት ላይ ነው።
ሐ. የብርታታችንና የኃይላችን ምንጭ በመሆኑ የእርሱ በሕይወታችን መኖር ላይ ነው።
መ. እንዲኖሩን የምንፈልጋቸውን የጸጋ ስጦታዎች ለመምረጥ የተሻለ ችሎታ ላይ ነው።



## የሙከራ ፈተና

የመጀመሪያውን ክፍለ ትምህርት በሚገባ ካጠናህ በኋላ የሙከራ ፈተናውን ውሰድ። ከዚያም መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸው ካሉ አስተካክል፣ መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል በተሰጠው ስፍራ በማስፈር አመልክት።

____1. መንፈስ ቅዱስ አካል አለው የተባለው ተለሚነትና ኃይል ስላለው ነው።

____2. መንፈስ ቅዱስ ያለው ሦስት የአካላዊት ችሎታዎች የማወቅ፣ የስሜትና የመምረጥ ችሎታዎች ናቸው።

____3. መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊገልጥ ይችላል፥ ይገልጥማል።

____4. የመምረጥ ችሎታ ፈቃድ ተብሎ የሚጠራው የአካል መግለጫ ክፍል ነው።

____5. መንፈስ ቅዱስ በቅድሚያ የሚሠራው በፍርድ ቤት ውስጥ ነው።

____6. ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ዋና አገልግሎቶች አስተማሪ፣ አስተዳዳሪና አጽናኝ መሆን ነው።

____7. አንድ ነገር ስም ስላለው አካል እንዳለው ይገመታል።

____8. መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን የሚጠቅሰው አካላዊነት በሌለው ስያሜዎች ነው።

____9. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን የጠቀሰው እንደ አካል አድርጎ በስምና በተውላጠ ስም በመጠቀም ነው።

____10. ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቶቹ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲጽፍ እንደ አካል አድርጎ በወንድ ተውላጠ ስም በመጠቀም ነው።

ከዚህ በታች ከተሰጡት ቃላት በመምረጥ ባዶ ቦታዎችን እየሞላህ መግለጫዎቹን የተሟላ አድርግ።

| | | |
|---|---|---|
| ምሉዕ | ግንኙነት | ልምምድ |
| ፍላጎቶች | መንፈሳዊ ብስለት | ችግሮች |

11. መንፈስ ቅዱስን አካል እንዳለው ለይተህ ካወቅህ የአንተን  ከእርሱ ጋር በመካፈል እንዴት መፍትሔ ለማግኘት እንደምትችል እንዲያ ሳይህ ማድረግ ትችላለህ።

12. መንፈስ ቅዱስ ስሜት ያለው ህልው እንደሆነ ስትረዳ  እን ዳለው ደግሞ በመረዳት ራስህን ሳይሆን እርሱን ለማስደሰት መፈለግ አለብህ።

13. የስጦታዎች  ላይ የሚያተኩሩ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የመጨረሻ ግብ አድርገው የማየት ዝንባሌ አላቸው።

14. በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል በሕይወታቸው የሚያውቁት በ  ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

15. አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በእርግጥ ከተረዳ እያሳየ የሚሄድ ግንኙነት መጀመር አለበት።

16. መንፈስ ቅዱስ  አካል ነው ስንል እኛ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖረን የሚያስችል ችሎታዎችን ሁሉ ይዟል ማለታችን ነው።

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ።

17. በዚህ ክፍለ ትምህርት ያጠናነውን ሃሳቡን የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባህርያትን ዘርዝር።

18. የፍቅር ግንኙነት እንዴት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንደሚሠራ ግለጽ።

19. መንፈስ ቅዱስ ስሜቶች እንዳሉት የሚገልጡትን፥ እርሱም ሊያዝን የሚችልባቸውን ሃሳቡን መንገዶች ጥቀስ።

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

10. ጃንደረባው መልእክቱን ተቀብሎ ተጠመቀ፣ ደስ እያለውም መንገዱን ቀጠለ።

1. ለ

11. መልእክቱን ተቀበሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ ወዲያውም ተጠመቁ።

2. አካላዊ



12. ሀ

3. ሠ

13. ሀ. ወላጆች
ለ. አጽናኝ ወይም ረዳት
ሐ. ማስተማርና ኢየሱስ የተናገረውን ማስታወስ
መ. እውነት ሁሉ፣ ኢየሱስ

4. መፍትሔ ለመስጠት እውቀት እንደነበረውና ያንን እውቀት ለሐዋርያት ማስተላለፍ ይችል እንደነበረ ያሳያል።

14. ሀ. 1  ለ. 3  ሐ. 2

5. መንፈስ ቅዱስን
ሀ. መዋሸት
ለ. መቃወም
ሐ. መስደብ
መ. ስሙን በከንቱ ማንሳት፣ እርሱን መድፈር(ይህ ከሁሉም አጅግ አደገኛ ነው)
ሠ. በእርሱ ላይ መናገር ኃጢአት መሥራት

15. ሀ. 1  ለ. 2  ሐ. 1

6. የአንተ መልስ።

16. መንፈስ ቅዱስ (የግል ስም) አጽናኝ እርሱ፣ እኔ

7. ሀ. ይፈልጋል  ለ. ይቆጣጠራል  ሐ. በመቃተት እንደሚጸልይልን

17. ሀ. 2  ለ. 1  ሐ. 2  መ. 1

8. ሀ. እውነት  ሐ. ሐሰት  ሠ. እውነት  ሰ. ሐሰት
ለ. እውነት  መ. እውነት  ረ. እውነት  ሸ. እውነት

18. ለ እና ሐ

9. ሐ

# 2

ትምህርት

# መለኮታዊ አካል

መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል የሆነ፥ ከሦስቱ ስላሴ አንዱ አባል ነው። ባጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዘፍጥረት አንሥቶ እስከ ዮሐንስ ራዕይ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ መንፈስ ቅዱስን የምናየው፥ በሰው ታሪክ ውስጥ ከሌሎቹ የሥላሴ አባላት ጋር ሆኖ ሲሠራ ነው። ክርስቶስ ወደአባቱ ቀኝ ካረገ በኋላ በሰዎች ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአዲስ መልክ መንቀሳቀስ ጀመረ (የሐዋ. 1:1-9)።

እኛ ሰዎች እውቀታችን የተወሰነ በመሆኑ የሥላሴን ምስጢር ሙሉ በሙሉ ልንረዳ አንችልም። ሥላሴ በፍጹም በአንድነትና በመተባበር የሚሠሩ፣ ሦስቱም ለየራሳቸው አካላዊነት ያላቸው ነገር ግን አንድ አምላክ የመሆናቸው ምስጢር ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር አብ በተመረጡ በጥቂት ሰዎች በኩል በመንፈስ ተናገረ። ልጁ ኢየሱስ፥ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ በምድራዊ አገልግሎቱ እግዚአብሔር አብን ለእኛ ገለጠ። መንፈስ ቅዱስ የተላከው ደግሞ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ሲሆን፥ የተላከውም የክርስቶስ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን በኩል እንዲሠራ ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርት የምንመለከተው መንፈስ ቅዱስ ክብርና መታዘዝ የሚገባው፥ የሥላሴ ሦስተኛው አባልና መለኮታዊ አካል እንደሆነ ነው። እርሱ በየዕለቱ በሕይወታችን ውስጥ ለማገልገል የሚናፍቅ፣ በእኛ ውስጥ እንዲታይና የሚያደርገን እርሱን ወደ ማገልገል የሚመራን ነው። መንፈስ ቅዱስ ዘወትር የሚያመለክተን ወደራሱ ሳይሆን፥ ወደ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ መለኮታዊ አካል በአንተ ውስጥ እንዲኖር ፈቅደህለታልን? እርሱ አጽናኝህ፣ ጓደኛህና መሪህ ነው? ይህን ክፍለ ትምህርት በመከታተል ላይ ሳለህ እርሱ ለልብህ እንዲናገር ራስህን አዘጋጅ።



### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መለኮታዊ ኅብረት
- መለኮታዊ ባሕርያት
- መለኮታዊ አድናቆት
- መለኮታዊ ብቃት

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- መለኮታዊ ሕብረት፣ ባሕርያትና አድናቆትን መሠረት በማድረግ ስለ መንፈስ ቅዱስ አምላክነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መስጠት።
- የመንፈስ ቅዱስን አምላክነትና ማንኛውንም የለው ችግር ለመፍታት ያለውን ብቃት በራስህ ሕይወት ላይ በመተግበር።

### የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ክፍለ ትምህርቱን በቅደም ተከተል በሚገባ በመከታተል የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስም ንባቦች በሙሉ በጥንቃቄ አንብብ። የክፍለ ትምህርቱን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችንም መልስ።
2. ክፍለ ትምህርቱን በጥንቃቄ ተከታትለህ ከጨረስክ በኋላ የሙከራ ፈተናውን ውሰድ። ከዚያም በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

## መለኮታዊ ሕብረት

***ዓላማ 1 በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረት መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር ያለውን ሕብረት የሚያሳየውን ገለጻ ለመስጠት።***

በአብና በወልድ እምላክነት የምናምንበት ማንኛውም ምክንያት ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። በሐዋ. 5:3-4 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ማመጽ ወይም ኃጢአት ማድረግ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንደማድረግ እንደሆነ ይናገራል። እዚህ ላይ የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ያለ ምንም ስህተት የተረጋገጠ ነው። እርሱ የተለየ አካል ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ከሌሎቹ የሥላሴ አባላት ጋር ያለው ሕብረት በጣም የተቀራረበ በመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት የአባታችሁ መንፈስ፤ እንዲሁም ደግሞ የክርስቶስ መንፈስ ተብሎ ተጠርቷል (ማቴ. 10:20፤ ሮሜ 8:9)።

መንፈስ ቅዱስ ከሌሎቹ የሥላሴ አባላት ጋር ያለው ሕብረት የተለየና መለኮታዊ አካል ሆኖ ከአብና ከወልድ ጋር ፍጹም የሆነ አንድነትና እኩልነት እንዳለው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ይገኛሉ። አንዳንዶቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

### የጥምቀት መመሪያ

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ይህን ትእዛዝ በሰጠ ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ የሰጠው እኩል እውቅና ነበር።

> "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28:19-20)።

ከዚያን ጊዜ እንሥቶ ብዙ አማኞች ይህንን መመሪያ በመከተል፥ በሦስቱ ሥሉሴ፥ በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀዋል። በዚህ ትእዛዝ ላይ ኢየሱስ የተጠቀመው "ስም" በሚለው ነጠላ ቁጥር እንጂ "ስሞች" በሚል በብዙ ቁጥር እንዳልሆነ አስተውል። በአማርኛችን ይህ በጣም ግልጽ ባይሆንም፤ አዲስ ኪዳን በመጀመርያ በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ሕግ "አብ፤ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የብዙ ቁጥር እንደመሆኑ "ስም" የሚለውም ቃል በብዙ ቁጥር "ስሞች" ተብሎ መጻፍ ነበረበት። ይህ በሥላሴ ውስጥ የሚታየው ኅብረት ሦስትነትና አንድነት በተጨማሪ በግልጽ የታየው ኢየሱስ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ነው።

(1). በዮሐ. 1:25-34 እና ሉቃ. 3:15-16፣ 21-22 ላይ የተጻፈውን ቃል በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።



ሀ. መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ጥምቀት ጋር የተባበረው በየትኞቹ ሁለት መንገዶች ነው?

ለ. ከኢየሱስ ጥምቀት ጋር እግዚአብሔር አብም ተባባሪ መሆኑን የሚያመለክተው የትኛው ጥቅስ ነው?

### ሐዋርያዊ ቡራኬ

ከሁሉም ይበልጥ ተወዳጅነት ያለውና ብዙ ጊዜ ከሚጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን ቡራኬዎች አንዱ ለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ሌላ ምስክር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 13:14 ላይ ለቆሮንቶስ አማኞች የጻፈውን መልእክት ሲደመድም፦

> "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን" ይላል።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ ጋር በስም ብቻ ሳይሆን በአገልግሎትም የሚያስተባብር ጭምር ነው። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ሦስቱ የሥላሴ አካላት የተጠቀሰው ሦስቱ ባሕርያት የሚያሳስበን እያንዳንዱ ሕይወታችንን የነካበትን በጣም አስፈላጊ የሆነውን መንገድ ነው። እነሆም አንድ ልጁን ስለ እኛ አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ የወደደን የማይሞተው የአብ ፍቅር፥ ገና ኃጢአተኞች ሳለን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በመሞቱ የተሰጠን ለሁሉ የሚበቃ ጸጋ የመለኮታዊ ወዳጃችን የመንፈስ ቅዱስ ዘወትር የሚጸና ሕብረት ናቸው። የሥላሴን ፍቅር፣ ጸጋና ሕብረት ስንቀበል መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለመጠበቅ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ አለን ማለት ነው። ይህም መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለመጠበቅና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጽጽት ያስችለናል።

## ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች

(2). ዘፍ. 1:1-2 እና 26ን አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ መንፈስ ቅዱስ በምን መንገድ በፍጥረት ሥራ ላይ ተባበረ?

(3). ማቴ. 1:18-19 አንብብ። መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ልደት ጋር የተባበረው እንዴት ነበር?

(4). ኢሳ. 61:1-2 እና ሉቃ. 4:14-21 አንብብ። መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ጋር ሕብረት ያደረገው እንዴት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ ካለህ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር ያለውን ሕብረት በግልጽ የሚያሳዩ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካገኘህ ዘርዝረህ ብታሰፍራቸው ስለዚሁ ሕብረት ጠለቅ ያለ ማስተዋል እንድታገኝ ይረዳሃል።

(5). ከመጽሐፍ ቅዱስ ባገኘነው ማስረጃ መሠረት ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ስጥ። ለጥምቀት የተሰጠው መመሪያ፥ ሐዋርያዊ ቡራኬ፣ የዘፍጥረት ታሪክና የኢየሱስ ልደት፥ መንፈስ ቅዱስ ምን መሆኑን ለመግለጽ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ክፍሎች ናቸው?

ሀ. ከእግዚአብሔር አብ ወይም ወልድ ከፍ ያለ ሥልጣን ያለው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው።
ለ. ፍጹም ሕብረትና አንድነት ያለው፥ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሆነ ከሦስቱ ሥላሴ አንደኛው አባል እንደሆነ ለመግለጽ ነው።
ሐ. ከአብ ወይም ከወልድ ዝቅ ያለ ሥልጣን ያለው አምላክ እንደሆነ ለመግለጽ ነው።
መ. አምላክ ሳይሆን እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማከናወን የሚጠቀምበት መንፈሳዊ ኃይል እንደሆነ ለመግለጽ ነው።

## መለኮታዊ ባሕርያት

*ዓላማ 2 የእግዚአብሔር ባሀርያትን በሠንጠረዥ ውስጥ በመሙላት ስለ መንፈስ ቅዱስ አምላክነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ለመስጠት።*

ስለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ሌላ ማስረጃ ሊሆነን የሚችለው አምላክ ብቻ ሊኖረው የሚችለውን ባህርያት መያዙ ነው። ባለፈው ክፍለ ትምህርት ስለ መንፈስ ቅዱስ እውነት የሆኑትን አንዳንዶቹን ባሕርያት ተመልክተናል፤ በዚያ ክፍለ ትምህርት ላይ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር አካላዊ ጠባያት ውስጥ የሕይወት ምንጭና ሰጭ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (የሐዋ. 17:24-25)።

እነዚህ የሕይወት ስጪነት ባሕርያት የመንፈስ ቅዱስም እንደሆኑ በርከት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያስረዳሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ አንደኛው የመንፈስ ቅዱስ ስያሜ "የሕይወት መንፈስ" የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ከሞት እንዳስነሣው ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ ይናገራል (ሮሜ 8:11)። በዮሐ. 6:63 እንደተገለጸው ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ እንደሆነ ያንኑ በማጽናት ያመለክታል። በ2ቆሮ. 3:6 ላይ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፈው መልእክቱ ላይ መንፈስ ሕይወት እንደሚሰጥ ተናግሮአል። ሐዋርያው ጴጥሮስም እርሱ በሥጋ ሞተ፥ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ በማለት በ1ጴጥ. 3:18 ላይ ይናገራል።

(6). በስተቀኝ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ በስተግራ ከሚገኘው ከእግዚአብሔር ባህርያት ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ስብዕና | 1. ዮሐ. 4:24 |
| ለ. ዘላለማዊ | 2. 1ቆሮ. 8:6 |
| ሐ. ሦስቱ ስላሴ | 3. ዘፍ. 2:18፣ ኢሳ. 1:14፣ 55:8 |



| | |
|---|---|
| ___መ. መንፈስ | 4. ዮሐ. 14:23-26 |
| ___ሠ. አለመለዋወጥ | 5. መዝ. 90:1-2 |
| ___ረ. አንድ አምላክ | 6. መዝ. 33:11፣ 102:25-27፣ ሚል. 3:6 |

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ መንፈስ ከአብና ከወልድ ጋር የሚጋራቸውን አንዳንዶቹን ባሕርያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጠው እንመልከት።

## እርሱ ቅዱስ ነው

በመጽሐፍ ቅዱስ በብዛት እንደተጠቀሰው የሥላሴ ሦስተኛው አካል ለሆነው የተሰጠው የግል ስም መንፈስ ቅዱስ የሚለው ነው። የፍጹም ቅድስናን ባሕርይ የያዘ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ስሙ አምላክነቱን ያረጋግጣል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1:4 ላይ "የቅድስና መንፈስ" ብሎ በመጥራት ፍጹም የሆነ የቅድስና ባሕርዩን አጥብቆ ይናገራል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚያመለክቱት በኢሳ. 6:3 ላይ እና በራዕ. 4:8 ላይ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፥ ተብሎ የተጠቀሰው የእግዚአብሔርን አንድም ሦስትም መሆን ለማመልከት ነው።

## እርሱ ዘላለማዊ ነው

በዕብ. 9:14 ላይ መንፈስ ቅዱስ የተጠራው *"የዘላለም መንፈስ"* በመባል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *ዘላለም* የሚለው ቃል በሌሎች ስፍራዎች የእግዚአብሔር አብንና የእግዚአብሔር ወልድን ዘላለማዊ ባሕርይ ለመግለጥ የሚያገለግል ቃል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *ከዘላለማዊው መንፈስ* በተቃረነ መልኩ የሚታዩትና የማይታዩት ሌሎች ነገሮች ሁሉ በአንድ ወቅት የተፈጠሩ መሆናቸውን ይናገራል (በቆላ. 1:15-16)። መንፈስ ቅዱስ ግን በራሱ ዘላለማዊ የሆነ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ የነበረ፣ ያለና ዘወትርም የሚኖር ነው። ዘላለማዊ ባሕርይው የመለኮታዊነቱ ማስረጃ ነው።

## እርሱ ከሁሉ በላይ ነው

በክፍለ ትምህርት 1 ላይ አንዱ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት የሚገልጸው የእርሱ ፈቃድ እንደሆነ ተመልክተናል። የእርሱ ፈቃድ ፍጹም የሆነው የአምላክነቱ መግለጫ ነው።

በዮሐ. 3:8 ላይ ኢየሱስ "ነፋስ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይነፍሳል" ብሎ በመናገር መንፈስ ቅዱስን በነፋስ ይመስለዋል። ደስ ያሰኘውን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ይህም ሌላ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚገልጽ ማስረጃ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 12 ላይ ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም ሲያስረዳ ከሁሉ በላይ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን ባሕሪ ያመለክታል። እንደፍላጎቱ ለእያንዳንዱ ሰው

የተለየ ስጦታ እንደሚሰጥ በመግለጽ፥ ከሁሉ በላይ የመሆኑን መለኮታዊ ባሕርይ በተግባር ላይ እንደሚያውል ይናገራል "ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ቆሮ. 12፡11)።

መንፈስ ቅዱስ ከሁሉ በላይ ሥልጣን አለው። ከእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን የበለጠ ሌላ ኀይልና ሥልጣን የለም። መንፈስ ቅዱስ ያለው ከሁሉ በላይ የሆነ ሥልጣን እግዚአብሔር ብቻ የያዘው ሥልጣን ነው። እኛን ፈቃድና ምርጫ የማድረግ ሥልጣን ሰጥቶ የፈጠረን እርሱ እንደዚህ እንድንሆን ስለመረጠ ነው። እርሱን ለማገልገል ከሚያስገድደን ይልቅ በነዛ ፈቃዳችን በመጠቀም እንድናገለግለው ፈጠረን። የእኛ ፈቃድ ሲሠራ የሚችለው ከሁሉ በላይ በሆነው በእርሱ ፈቃዱ ምክንያት ነው።

(7). የሐዋ. 13፡2 እና 1ቆሮ. 2፡4 ካነበብህ በኋላ ባዶ ቦታውን በመሙላት መግለጫውን የተሟላ አድርግ።

ሀ. በሐዋ. 13፡2 ላይ ከሁሉ በላይ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የታየው በአንጾኪያ ለነበሩ ነብያትና መምህራን__________በመስጠት በርናባስና ሳውልን____________ በመናገር ነው።

ለ. በ1ቆሮ. 2፡4 ላይ በጳውሎስ ሕይወት ጎልቶ የታየው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል____________ በላይ በመሆን ነበር።

## እርሱ በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ ይገኛል

እርሱ በሁሉ ስፍራ እንደሚገኝ መዝሙረኛው ዳዊት ሲገልጽ፦ "ከመንፈስህ ወዴት እሔዳለሁ? . . . ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ" ይላል (መዝ. 139፡7-8)። እርሱ በማንኛውም ጊዜ በሁሉ ስፍራ ስለሚገኝ፥ ከመንፈስ ቅዱስ መሸሽ የሚቻልበት ስፍራ የለም።

በሁሉ ስፍራ የመገኘት ችሎታ አለኝ ለማለት የሚችል ሌላ መንፈስ የለም። ሰይጣን እንኳ በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ ለመሆን ችሎታ የለውም። የክፋት ተግባሩን ለማከናወን እንዲረዱት የሚመካው በሌሎች በወደቁ መላእክት ነው።

የእግዚአብሔር መለኮታዊ መንፈስ የእግዚአብሔርን የድነት ፕሮግራም ለማከናወን በድርጅት ወይንም በሌሎች ትናንሽ መንፈሶች ላይ መደገፍ የለበትም። ከእያንዳንዱ ኃጢአተኛ ጋር ለመታገል በራሱ ይኖራል (ዮሐ. 16፡7-11)፤ እያንዳንዱን ጻድቅ ያጽናናል (ዮሐ. 16፡13፣ 14፡16-17)። እርሱ ከአብና ከወልድ ዘንድ የተላከው በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ እንዲኖርና እያንዳንዱን አማኝ በመለኮታዊ ኃይል እንዲሞላ ነው (የሐዋ. 1፡8)። ዛሬ የምንኖረው ኢዮኤል በተነበየው በመጨረሻው ዘመን ነው።



እግዚአብሔር በሚቀበለው አማኝ ሁሉ ላይ መንፈሱን አፍስሷል (የሐዋ. 2፡16-18)። መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ሲሠራ መለኮታዊ ኃይሉን ተለማምደሃልን?

## እርሱ ሁሉን ያውቃል

ከመንፈስ ቅዱስ የሚደበቅ ምንም ነገር የለም፣ እርሱ ሁሉን የሚያውቅ ነው። ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶና ከዚያም በፊት የተፈጸመ ነገር ሁሉ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው። በአሁኑም ጊዜ በየትም ስፍራ የሚፈጸመውና ወደፊትም ሊፈጸም ያለው ሁሉ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር አዋቂ እንደሆነ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ ሲገልጽ፦

> ይልቁን እንጂ እንደ ተጻፈው፣ "ዐይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶል" እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል (1ቆሮ. 2፡9-11)።

## እርሱ ሁሉን ቻይ ነው

ኃይል ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ነው። በሉቃ. 1፡35 ላይ የልዑል እግዚአብሔር ኃይል ተብሎ የተጠራው እርሱ ነው። በሌላ አነጋገር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ኃይሉም ወሰን የለውም። ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻለዋል (ማር. 10፡27)።

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለተመረጡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደተሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ለምሳሌ፥ ለዳዊት ተሰጥቶአል (1ሳሙ. 16፡13) ለሚክያስ (ሚክ. 3፡8)፣ ለደቀ መዛሙርቱ (ዮሐ. 20፡19-23)፣ ለሚቀበሉ ሁሉ (የሐዋ. 1፡8) ተሰጥቷል።

በዘካ. 4፡6 ላይ ለዘሩባቤል የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል "በመንፈሴ እንጅ በኃይልና በብርታት አይደለም" የሚል ነበር። ይህ በሰው ኃይልና ብርታት ሳይሆን ድል የሚነሣው በእርሱ ኃይል እንደሆነ የሚገልጽ ነው። ይህም ኀይል ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው። ድል የሚነሣው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በሰው ኀይልና ጉልበት እንዳልሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መገንዘብ አለባቸው።

(8). እያንዳንዱን በስተቀኝ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ባህሪያት በስተግራ ካለው ማብራሪያ ጋር አዛምድ፤ የመረጥከውን ቁጥር በባዶው ስፍራ ላይ ሙላ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ፍጹም ንጹሕ | 1. ከሁሉ በላይ የሆነ |
| ለ. መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ለዘለዓለም የሚኖር | 2. ሁሉን የሚያውቅ |
| ሐ. እንደ ፈቀደው ለማድረግ የሚችል ኃይል ሁሉ ያለው | 3. ቅዱስ |
| መ. ሁሉን የሚያውቅ | 4. ሁሉን ቻይ |
| ሠ. በሁሉ ስፍራ የሚገኝ | 5. ዘለዓለማዊ |
| ረ. ኃይል ሁሉ የእርሱ የሆነ | 6. በሁሉ ስፍራ ያለ |

(9). ከዚህ በታች የተጠቀሱትንና የእግዚአብሔር አምላክነት በአብና በወልድ እንዴት እንደተገለጠ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አንብብ። ከዚያም እንደመለኮታዊ ባሕርያቱ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያረጋግጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አስፍር።

| የእግዚአብሔር ባሀርያት | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| ሀ. ቅድስና | መዝ. 22:3<br>ዘሌ. 19:12-25 | የሐዋ. 3:14 | |
| ለ. ዘላለማዊነት | መዝ. 90:2<br>መዝ. 102:27 | ሚክ. 5:2<br>ዮሐ. 1:1 | |
| ሐ. ከሁሉ በላይ የሆነ | ኢዮ. 42:2 | ማቴ. 28:18<br>1ጴጥ. 3:22 | |
| መ. በሁሉ ስፍራ የሚገኝ | መዝ. 139:7-12 | ማቴ. 18:20<br>ኤፌ. 1:22-23 | |
| ሠ. ሁሉን የሚያውቅ | መዝ. 139:1-6 | ዮሐ. 2:24-25<br>ቆላ. 2:2-3 | |
| ረ. ሁሉን የሚችል | መዝ. 139:19<br>ማቴ. 19:26 | ሉቃ. 7:11-12 | |

## መለኮታዊ አድናቆት

*ዓላማ 3 በ2ጴጥ. 1:20-21 በተጻፈው መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በተመለከተ የሰጡትን መግለጫዎች ለመቀበል የምንችልበትን ምክንያት ለመግለጽ።*

የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች በቀጥታ አምላክ ብለው በመጥራታቸው አምላክነቱን የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህን መግለጫዎች ከተናገሩት ሰዎች ምሳሌ የሚሆኑን ስምዖን፣ ጴጥሮስና ሐዋርያው ጳውሎስ ናቸው።



## የስምዖን መግለጫ

በሉቃስ ወንጌል ከተጻፈው ታሪክ ውስጥ እንደምንረዳው ስምዖን የተባለ በኢየሩሳሌም የኖረ ጻድቅና ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሰጠ ሰው ነበር። ስምዖን የመሲሑን መምጣት የሚጠባበቅ አይሁድ ነበር። ስለዚህም ድርጊት ከመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ እንደተቀበለ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

> በዚያን ጊዜ ጻድቅና ትጉሕ የሆነ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረ ሰው ነበር። ደግሞም የጌታን መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር፤ እርሱም በዚህ ጊዜ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ የልጁም ወላጆች በሕጉ ልማድ መሠረት ተገቢውን ሊፈጽሙለት ሕፃኑን ኢየሱስን ይዘው በገቡ ጊዜ፣ ስምዖን ተቀብሎ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ፤ ቃል በገባኸው መሠረት አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤ ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና" (ሉቃ. 2:25-30)።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚያውቅ መሆኑ የታየው በስምዖን ዘንድ ሊታወቅ የማይችል የነበረውን የእግዚአብሔር ሃሳብ በመግለጡ ነው። እንደ ጴጥሮስ አስተሳሰብ ይህ ከእግዚአብሔር የመነጨው ትንቢት የተላለፈው ኃይል ሁሉ የእርሱ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው (2ጴጥ. 1:20-21)። በሦስቱ ሥላሴ አካል ዘንድ አንድነትና ሕብረት በመኖሩ፥ ለአንዱ አካል በተግባር ላይ የሚውለው ለሌሎቹም እንደዚያው ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት እንደገና በማስረጃ እየታየ ነው።

## የጴጥሮስ መግለጫ

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹ አማኞች ንብረታቸውን በመሸጥ ለሚያስፈልጋቸው ነገር እንዲከፋፍል ገንዘቡን ወደ ሐዋርያት ያመጡ ነበር (የሐዋ. 4:32-36)። ከነዚህም አማኞች መካከል ሐናንያና ሰጲራ የተባሉ ባልና ሚስት ነበሩ። እነርሱም ንብረታቸውን ሸጠው ገንዘብ በመቀበል ያስረከቡትን አስረክበው ሌላውን በመሸሸግ ሁሉንም ገንዘብ ለቤተክርስቲያን የሰጡ አስመስለው ገዝም አሉ። ሐዋርያው ጴጥሮስ እነዚህ ባልና ሚስት ምን አድርገው እንደነበር በመንፈስ ቅዱስ ተረዳ።

(10). የሐዋ. 5:1-4 ላይ የተጻፈውን ካነበብህ በኋላ ጴጥሮስ ለሐናንያ የሰጣቸውን መግለጫዎች የተሟላ አድርግ።

ሀ. ሐናንያ ሆይ! በ                    ላይ እንድትዋሽና ከመሬቱም ሽያጭ ክፊሉን
እንድታስቀር ያደረገህ ሰይጣን፥ ስለምን ወደ ልብህ ገባ?
ለ. የዋሸኸው በ                    ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጴጥሮስ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስን መዋሸት እግዚአብሔርን መዋሸት እንደሆነ ነው።

## የጳውሎስ መግለጫዎች

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በሁለቱም መልእክቶች ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ አምላክነት የበለጠ ማስረጃ የሚሰጡ መግለጫዎችን ሰጥቶአል። የመጀመሪያው መግለጫ የተሰጠው በ1ቆሮ. 2:4-5 ላይ ሲሆን መግለጫውም እንደዚህ የሚል ነው። "ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይልን በመግለጥ እንጂ፤ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም። ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው።" እዚህ ላይ ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያደንቀው የመንፈስን ኃይል ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር እኩል አድርጎ በማየት ነው። በ1ቆሮ. 3:16 ላይ ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ ማስረጃ ሲሰጥ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን?" በማለት ይጠይቃል። እዚህ ላይ የሚያመለክተው አማኞች የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆናቸውን ነው።

እንደገና ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳያስተውሉ መሸፈኛ የሆነባቸው ወደ ጌታ ቢመለሱ እንደሚወገድላቸው ካስረዳ በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን ቃላት አስፍሮአል። "ጌታ መንፈስ ነው፣ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነፃነት አለ። እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያንጸባረቅን የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው።" (2ቆሮ. 3:17:18)።

(11). በ2ጴጥ. 1:20-21 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት የስምዖን፥ የጴጥሮስና የጳውሎስ መግለጫዎች ለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ለምን ተጨማሪ ማስረጃ ሲሆኑ እንደሚችሉ ግለጽ።

### መለኮታዊ ብቃት

*ዓላማ 4 መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገንን ነገር ሊሰጠን የሚችለው በምን መንገድ እንደሆነ ለመግለጽ።*

በመንፈሳዊ ማስተዋል እየጠነከርን ስንሄድ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚገልጡትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችና በሥላሴ ውስጥ የእርሱን



መለኮታዊ ባሕርይና የያዘውን ስፍራ መመርመርና ማስተዋል በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንን ካላደረግን እርሱ በየዕለቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም የማንችል መሆናችን ብቻ ሳይሆን፥ ለእርሱ የሚገባውን የክብር ስፍራ ለመስጠት የማንችል እንሆናለን። በሕይወታችን አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚያመልጡን መረጃ ስናጣ ነው። በሆሴዕ 4:6 ላይ እግዚአብሔር ዘሆሴዕ በኩል ስለዚሁ ሲናገር፦ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቶአል" ይላል። በሆሴዕ 4:1 ላይ ደግሞ "በምድሪቱ ላይ ታማኝነትና ፍቅር እግዚአብሔርንም ማወቅ ጠፍቶአል" ይላል። መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነና ለእኛ ምን ሊያደርግልን እንደሚችል እንደዚሁም ለሰዎች ሁሉ ምን ሊያደርግላቸው እንደሚችል፣ ካላወቅን፥ ከመለኮታዊ ብቃቱ ሙሉ በሙሉ መጠቀም አንችልም።

ስለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት የተማርናቸው ብዙዎቹ ነገሮች በዕለት ሕይወታችን በተግባር ላይ ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። የእኛን ችግሮች ለመፍታት በእርሱ በኩል ምንም የሚጎድል ነገር የለም። አምላክ ስለሆነ የእኛን ችግሮች ሁሉ ለመፍታት እርሱ በቂ ነው። በሕይወታችን ለመሥራት የሚፈልጋቸውን አንዳንድ መንገዶች በአጭሩ ብንመለከት እርሱ ከሥላሴ አንደኛው አካል በመሆኑ፥ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊያደርግልን ሙሉ በሙሉ በቂ ነው።

## እርሱ መንፈሳዊ ሕይወት ይሰጣል

ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር የተላከ አስተማሪ በመሆኑ ከእርሱ ለመማር አስቦ ነበር። እንደገና ልትወለድ ይገባሃል ባለው ጊዜ ኒቆዲሞስ በጣም ተገረመ። ከዚያም በመቀጠል ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ "ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው" አለው።

ከመንፈስ መወለድ ማለት የእግዚአብሔርን ሕይወት መቀበል ነው። ያለ መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ነገሮችን ፈጽሞ ለማድረግ አይቻልም።

ጳውሎስ "የሕይወት መንፈስ" ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ እንዲያወጣው ከመፍቀዱ በፊት ስለነበረው ተስፋ ቢስ ትግል ለሮም ክርስቲያኖች ይነግራቸዋል። የእርሱ ልምምድ የእኛም ልምምድ ስለሆነ የእርሱ ንግግር ለማንኛችንም ግር አይለንም።

> "ዘእኔ ማለትም ኃጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ ውስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር አውቃለሁ፤ በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም። የማደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም፤ ዳሩ ግን ለማድረግ የማማፈልገውን ክፉ ነገር ነው።" (ሮሜ. 7:18-19)።

(12). የዚህ ችግር መፍትሔ የሚገኘው በሮሜ 8:5-9 ላይ ነው። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካነበብህ በኋላ በምንባቡ መሠረት የሚከተሉት መግለጫዎች "እውነት" ወይም "ሐሰት" መሆናቸውን አመልክት። እውነት የሆኑትን መግለጫዎች ፊደሎቹን ክበብ።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲሰጠን ብንፈቅድ፥ እርሱ የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንፈልጋለን።
ለ. እንደራሳችን ባሕርይ ከኖርን፥ ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ፥ አብዛኛውን ጊዜ የኀጢአት ምኞታችንን ለመቆጣጠር እንችላለን።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ለእኛ መንፈሳዊ ሕይወት በሚሰጠንና አእምሮአችንን በሚቆጣጠርበት ጊዜ የአእምሮ ሰላም ደግሞ ይሰጠናል።
መ. ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም።
ሠ. መንፈስ ቅዱስ ለእኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሲሰጥ፥ ከመንፈሳዊ ሕይወት ኃላፊነታችን ነጻ በማውጣት፥ እርሱ በውስጣችን ሆኖ ሕይወታችንን ይቆጣጠራል።

(13). በዚህ ክፍለ ትምህርት ያጠናናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው። የሐዋ. 17:24-25፣ ሮሜ 8:11፣ ዮሐ. 6:63፣ 2ቆሮ. 3:6፣ 1ጴጥ. 3:18። ለግል ችግሮችህ መፍትሔ እንዲሆኑ በተግባር ላይ ስታውላቸው አስፈላጊነታቸው ምን ያህል ነው?

## ቅድስናን ያሳድጋል

መጽሐፍ ቅዱስ በዕብ. 12:14 ላይ፡- "ያለ ቅድስና ማንም እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልም" ይላል። በሮሜ 8:5-9 ላይ እንደተመለከትነው፥ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ይሆን ዘንድ ሕይወታችንን ለእርሱ ስናስረክብ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ንቁ እንድንሆን ከማስቻሉም በላይ በእግዚአብሔር ፊት በትክክለኛው መንገድ ለመኖር እንድንችል ያደርገናል። በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ኃይል፡- በኑሮአችን ሁሉ ቅዱሳን እንድንሆን የተሰጠንን የመጽሐፍ ቅዱስ ምክር ለመታዘዝ ያስችለናል (1ጴጥ. 1:14-15)።

የአዲስ አማኝ ሃላፊነት ምን እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 6:22 አስፍሮታል። ከኃጢአት ነጻ ከወጣ በኋላ አዲሱ አማኝ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን አለበት። የዚህም ተግባር አንደኛው ጥቅም ቅድስና ነው። ሐዋርያው ሲገልጽ በዚህ ሂደት የእኛ ድርሻ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ከሚበክሉ ነገሮች ራሳችንን በማንጻት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተባበር ነው (ሮሜ 8:5-11፣ ከ2ቆሮ. 7:1 እና ኤፌ. 4:22-24 ጋር አወዳድር)። መንፈሳዊ ግዴታችንን መወጣት ሲያቅተን (ሮሜ 8:12-14)፣ ማለትም በመንፈስ መመራት ሲያቅተን (ገላ. 5:25) እንድንታረም የሚያረገው ለአንድ ተቀዳሚ ዓላማ ነው። "የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለጥቅማችን ይቀጣናል" (ዕብ. 12:10)። ስለሆነም ሕይወታችን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሲሆን ብቻ ነው፥ በቅድስና እያደግን የምንሄደው።



(14). ሮሜ 8:5-17 አንብብ፤ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውጤታማ የሆነ ክርስቲያናዊ ኑሮ ለመኖር ቁልፉ ምን እንደሆነ ይነግረናል። ይህ ቁልፉ ምንድነው?

## ኃይል ይሰጠናል

ሕይወትህን በአንተ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር እንዲሆን አሳልፈህ ስትሰጥ፥ እርሱ ደግሞ ኃይል ይሰጥሃል።

1. ለመመስከር ኃይል ይሰጥሃል (የሐዋ. 1:8)
2. ድል አድራጊ እንድትሆን ኃይል ይሰጥሃል (1ዮሐ. 5:4-5)
3. ለአገልግሎት ኃይል ይሰጥሃል (1ቆሮ. 12:4-11)
4. መናፍስትን እንድትመረምርና ድል እንድታደርግ ኃይል ይሰጥሃል (1ዮሐ. 4:1-4)።
5. በፍርሃት ላይ፤ በጭንቀት ላይና በፈተናዎች ላይ ድል እንድታደርግ ኃይል ይሰጥሃል (2ጢሞ. 1:7፣ 2ቆሮ. 6:4-10)።

መንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሚሰጥህ ሕይወትን በሙሉ የፍርሃት ባርያ ሆነህ መኖር የለብህም። የሕይወትን ትግል ለመቋቋም እንድትችል እርሱ ድፍረት ይሰጥሃል። በኃጢአትም ላይ ድል እንድታደርግ ኃይል ይሰጥሃል። በሉቃ. 1:35 ላይ እንደተጻፈው ካንተ ጋር ያለው የልዑል እግዚአብሔር ኃይል ክፋትን የምትቃወምበትን ማስተዋል ይሰጥሃል። የዲያብሎስንም ሽንገላ ድል እንድታደርግ እምነት ይሰጥሃል (ያዕ. 4:7፣ 1ዮሐ. 4:4)። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ የተላከው የአንተ ጠባቂና ረዳት እንዲሆን ስለሆነ፥ በማንኛውም በሚያጋጥምህ ሁኔታ ሰላምና እረፍት ሊኖርህ ይችላል (ዮሐ. 14:25-27)።

(15). ትክክለኛውን መልስ ምረጥ። በተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት ያለፍርሃት የድል ሕይወት ለመኖር እንደሚቻል ለመደምደም የምንችለው፡-

ሀ. ክርኩሳን መናፍስት ውጊያ ክርስቲያኖች ሁሉ ነጻ እንደሚሆኑ ተስፋ ስለተሰጠ ነው።
ለ. ርኩሳን መናፍስት ፈጽሞ ኃይል እንደሌላቸው አማኞች ለይተው ስለሚያውቁ ነው።
ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወሰን የሌለው በመሆኑ፥ በእምነት በእርሱ ኃይል፥ አማኙ ፍርሃትን በማሸነፍ በድል አድራጊነት መኖር ይችላል።

## ከእርሱ ጋር ባልንጀራ መሆንን ያስገኛል

ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ በቅርበት ከእርሱ ጋር የመሆን መብት ነበራቸው። ይህ ግንኙነት በጊዜያዊነት

እንዲሆን የታሰበ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግና የእርሱን አገልግሎት ለመቀጠል ዝግጁ ሲሆኑ፥ እንዲሁም የእርሱ የድነት ተልእኮ ሲፈጸም በቅርበት አብሮ የመሆኑ ግንኙነት ያቆማል። ኢየሱስ ወደ አገልግሎቱ መጨረሻ ሲመጣ ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ መገኘት በጣም እንደተደገፉ አወቀ። ያለ እርሱ ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች እንደሚሆኑ ተገነዘበ። ከእነርሱ ሲለይ እነርሱን ለማዘጋጀት፥ እርሱ የሚተወውን ቦታ ወይም ባዶ ስፍራ እንዲሞላ፥ የእርሱን ቦታ እንዲወስድ፥ መንፈስ ቅዱስን እንዲልክ አብን ጠየቀ።

> "እኔ አብን እለምናለሁ፣ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" (ዮሐ. 14:16)። በዮሐ. 16:7 ላይ ደግሞ "እኔ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃችኋል። እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ" (ዮሐ. 16:7)።

በልባችን እንዲኖር እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን የእኛ አጽናኝና መሪ እንዲሆን ስለላከ ብቸኝነት ሊሰማን አያስፈልግም። በሁሉ ስፍራ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ፥ በአንድ ጊዜ በዓለም ላይ ለእያንዳንዱ አማኝ አብሮ የሚሆን ጓደኛ ሊሆን ይችላል። እኛን ሊያስተምረን፣ ሊያበረታታንና በማንኛውም ሁኔታ ከእኛ ጋር ሊሆን ዝግጁ ነው። ኢየሱስ ለተከታዮቹ የእኔ መሄድ ለእናንተ ይጠቅማችኋል በማለት መናገሩ ምንም የሚያስገርም አይደለም። እርሱ በሌለበት አጽናኙ በቅርብ አብሮ በመሆን በእያንዳንዳችን ውስጥ ይኖራል (1ቆሮ. 3:16)።

(16). ትክክለኛውን ቃላት በመምረጥ የተሟላ አድርግ።

| | |
|---|---|
| ሁሉን ቻይ | በሁሉ ቦታ በአንድ ጊዜ የሚገኝ |
| ሁሉን የሚያውቅ | ጻድቅ |
| ሕይወት | |

ሀ. መንፈስ ቅዱስ የ_______________ መንፈስ ስለሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ሊሰጠኝ ይችላል።
ለ. መንፈስ ቅዱስ ሕይወቴን ሲቆጣጠርና የእግዚአብሔርን__________ ሲሰጠኝ ቅዱስ መሆን እችላለሁ።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ_____________ በመሆኑ ለክርስትና ሕይወቴና ለመመስከር መንፈሳዊ ኃይል መቀበል እችላለሁ።
መ. መንፈስ ቅዱስ_____________ ስለሆነ እርሱ የማያቋርጥ ጓደኛዬ ነው።

ስለ መንፈስ ቅዱስ አምላክነት አስፈላጊውን ግንዛቤ በማግኘት ከአንተ ጋር በቅርብ አብሮ በመሆን ሊመራህ እንደሚናፍቅ ተረድተሃል። እነዚህን ጥያቄዎች ራስህን በመጠየቅ ወደ ሕይወትህ እንዲመጣ ጋብዘው፥ በመለኮታዊ ኃይሉም እንዲጠቀምብህ ፍቀድለት።



- ክርስቶስ ስለ እኔ ባቀረበው መሥዋዕት በኩል የእግዚአብሔር መንፈስ፥ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲሰጠኝ ፈቅጀለታለሁን?
- ቅድስናዬን ፍጹም ለማድረግና፣ ክርስቶስን እንድመስል በሕይወቴ እየሰራ ነውን?
- በዕለት ሕይወቴ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእኔ ውስጥ እየሠራ ነውን? መለኮታዊ መጽናናት፣ ጥበብና ብርታት ለመስጠት በሕይወቴ ይገኛልን?

---

## የሙከራ ፈተና

መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" መግለጫው ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል ጻፍ።

1. መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሦስተኛ አካል አድርገን የምንጠራው በደረጃ ከአብና ከወልድ ዝቅ ያለ በመሆኑ ነው።

____2. ሥላሴ የሚለው ቃል የሚጠቀሰው አንድ አምላክ የሆኑትን በፍጹም አንድነትና ሕብረት ያላቸውን ሦስት አካላት ነው።

____3. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ መሆኑን የምናውቅበት አንደኛው መንገድ የአምላክነት ባሕርያትን በመያዙ ነው።

____4. ሁሉን በዋቂ የመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ባሀሪ የሚገልጸው ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ያለውን ኃይል ነው።

____5. ባለንበት ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የፈሰሰው ለተመረጡ ጥቂት ሰዎች፥ ለአጭር ጊዜ ነው።

____6. ኢየሱስ ራሱ በምድራዊ አገልግሎቱ ኃይል የተቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ ነበር።

____7. መንፈስ ቅዱስን ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር የሚያመሳስሉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

____8. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በሰዎች ሕይወት የጀመረው ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ነበር።

____9. የኢየሱስ ጥምቀት፥ በሥላሴ መካከል ላለው ፍጹም አንድነትና ሕብረት ምሳሌ ነው።

____10. መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወት የመስጠቱ እውነት ለእርሱ አምላክነት ማስረጃ ነው።

____11. መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ የተወሰነ ነው።

____12. የመንፈስ ቅዱስ ስም ከመለኮታዊ ባሕርያቱ አንደኛውን የሚገልጥ ነው።

____13. ምርጫ፦ ለመንፈስ ቅዱስ የሚያገለግሉትን ቃላት ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ዘላለማዊ
ለ. ሥጋ ለብሶ መምጣት
ሐ. ከሁሉ በላይ የሆነ
መ. ውሱን
ሠ. የማይለወጥ
ረ. ቅዱስ
ሰ. ሁሉን ቻይ
ሸ. በሁሉ ስፍራ በአንድ ጊዜ የሚገኝ
ቀ. ሁሉን የሚያውቅ
በ. መልአክ መሰል
ተ. ሕይወት ሰጪ

አጭር መልስ፦ እያንዳንዱን ጥያቄ በተቻለ መጠን በአጭሩ መልስ።

14. የጥምቀት መመሪያና የሐዋርያት ቡራኬ ለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ማስረጃ የሚሰጡት በምን መንገድ ነው?

15. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አካል ያለው መሆኑን በማወቅህ ልትጠቀም የምትችለው እንዴት ነው?

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

9. የአንተ መልስ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ማንኛቸውም ሊሆኑ ይችላሉ።

ሀ. ሮሜ 1:4
ለ. ዕብ. 9:14
ሐ. ዮሐ. 3:8፤ 1ቆሮ. 2:4፤ የሐዋ. 10:38
መ. መዝ. 139:7-8፤ ዮሐ. 16:7-13፤ ዮሐ. 14:16-17
ሠ. 1ቆሮ. 2:9-11
ረ. ሉቃ. 1:35፤ የሐዋ. 1:8፤ ዘካ. 4:6

1. ሀ. ዮሐንስ መጥምቁ፣ እርሱ በውሃ እንደሚያጠምቅ፤ ኢየሱስ ግን በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት እንደሚያጠምቃቸው ለሕዝቡ ነገራቸው። በሁለተኛ ደረጃ፤ በቁጥር 22 ላይ እንደሚናገረው መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በኢየሱስ ላይ ወረደ።
   ለ. ሉቃ. 3:22፤ "የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል" የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ።

10. ሀ. መንፈስ ቅዱስ    ለ. እግዚአብሔር

2. እርሱ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ ተግባሩን ለማከናወን ዝግጁ ሆኖ ነው የታየው። ቁጥር 26 ላይ ሥላሴ ነጠላ ቁጥርን ሳይሆን የብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ይህ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ጉልህ ተሳትፎና አስተዋጽዖ ማድረጉን ነው።

11. በ2ጴጥ 1:20-21 የተጻፈው ቃል የሚገልጠው እነዚህ መግለጫዎች ሰዎች በእግዚአብሔር ተመርተው የተጻፉ መሆናቸውንና የሰው ማስተዋል ውጤት አለመሆናቸውን ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያመለክተው 'ሌላው ነገር ደግሞ የትንቢት እነሳሽነት፥ አተረጓጎሙንና በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ መካል ያለው እኩልነት የሚያመለክት ነው። እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

3. ኢየሱስ በማርያም ውስጥ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

12. ሀ. እውነት    ሐ. እውነት    ሠ. ሐሰት
    ለ. ሐሰት    መ. እውነት

4. ኢሳይያስ እንደተነበየው፥ አባቱ የላከውን አገልግሎት እንዲፈጽም መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ወረዶ በኃየል ቀባው።

13. የእንተ መልስ። እኔ እንዲህ በማለት እመልሳለሁ። የዘላለም ሕይወት ሊኖረኝና ከኃጢአት እስራት ነጻ ልሆን የምችለው ከእግዚአብሔር መንፈስ መለኮታዊ ኃይል ነው።

5. ለ

14. ቁልፉ የሚገኘው በቁጥር 13 ላይ ነው። የሥጋ ሥራን በመንፈስ ቅዱስ በኩል መግደል አለብን። ይህንን ብናደርግ በሕይወት እንኖራለን።

6. ሀ. 3    ሐ. 4    ሠ. 6
   ለ. 5    መ. 1    ረ. 2

15. ሐ

7. ሀ. ትእዛዝ፥ ለሥራ እንዲለዩለት
   ለ. ከሰው ጥበብ

16. ሀ. ሕይወት    ሐ. ሁሉን ቻይ
    ለ. ጽድቅ    መ. በሁሉ ቦታ በአንድ ጊዜ የሚገኝ

8. ሀ. 3    ሐ. 1    ሠ. 6
   ለ. 5    መ. 2    ረ. 4

# 3
ትምህርት

# የሚረዳን አካል

ኢየሱስ የምድራዊ አገልግሎቱን ስመፈጸም በተቃረበበት ወቅት ፈሪዎቹና ጽናት የጎደላቸው ደቀ መዛሙርቱ ያለ እርሱ እርዳታ የመቀጠሉ ነገር የማይቻል ተግባር ሆነባቸው። እርሱ በተሰቀለ ጊዜ ተስፋቸው ሁሉ ከእርሱ ጋር አብሮ የሞተ መስላቸው። ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣ ወደ ዓሣ ማጥመድ ሥራቸው ተመለሱ። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠላቸውና ሌላ ረዳት እንደሚልክላቸው የተስፋ ቃሉን በድጋሚ አስማቸው።

በመጨረሻም ረዳታቸው መንፈስ ቅዱስ የሚመጣበት ቀን በደረሰ ጊዜ ተስፋ ቆርጠው የነበሩት ተስፋቸው እየለመለመ መጣ። ክርስቶስ የሰጣቸውን ተግባር ለማከናወን እንዲረዳቸው የሚያስፈልጋቸውና ሁሉ በሁሉ የሆነ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነበር።

ባለፈው ክፍለ ትምህርት መንፈስ ቅዱስ ሙሉዕና መለኮታዊ አካል እንደሆነ ተመልክተናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የምናጠናው እርሱ የጸና እምነት እንዲኖረን በማድረግ፣ ዳግም ልደትን በማስገኘት፣ በማስተማርና በመምከር እኛን የሚረዳባቸውን መንገዶች ይሆናል። በእነዚህ አቅጣጫዎች የበለጠ የእርሱ እርዳታ ያስፈልግሃል? ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠና መንፈስ ቅዱስ የግል ረዳትህ እንዲሆን ልብህን ለእርሱ ክፈት።



የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይወቅሳል
- መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ያስገኛል
- መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል
- መንፈስ ቅዱስ ይመክራል

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በዮሐ. 16:7-11 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት የመንፈስ ቅዱስ *የመውቀስ ሥራ* ማለት ምን እንደሆነ መግለጽ።

- *በዳግም ልደት* ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን እንደሆነ ማስረዳት።

- የመንፈስ ቅዱስን *የማስተማርና የመምከር* አገልግሎት የተለያዩ አሠራሮችን መግለጽ።

- ለመንፈስ ቅዱስ *የዕርዳታ* አገልግሎት ራስህን መስጠት።

---

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለክፍለ ትምህርቱ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በሙሉ አንብብ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን መልስ።

2. የሙከራ ፈተናውን ከወሰድህ በኋላ የተሳሳትካቸውን መልሶችህን አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

## መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይወቅሳል

### ዓላማ 1 ዓለምን ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ በመውቀስ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ምን እንደሆነ ለመግለጽ።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ረዳት እንደሚልክላቸው በነገራቸው ጊዜ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የመጀመሪያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን እንደሆነ የተገለጠው ያን ጊዜ ነበር። ያላቸው ይህንን ነበር፦

"ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃችኋል። እኔ ካልሄድኩ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፤ ከሄድኩ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ፤ በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት ሲባል፣ ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅ ወደ አብ ስለምሄድና ከእንግዲህ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም፣ የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው።" (ዮሐ. 16፡7-11)።

ዓለም የራሷ የሆነ የኃጢአትና የጽድቅ መለኪያ ስለፈጠረች ለእግዚአብሔር የፍርድ ማስጠንቀቂያ ጆሮዋን ዘግታለች። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ብቻ ለኃጢአተኞች ስህተታቸውን እንዲያስረዳ መንፈስ ቅዱስን ላከው። ሰው ወደ ጌታ እንዲመለስ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ በማያምነው ሰው ልብ ይሠራል፣ ነገር ግን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመሰክሩና በሚኖሩት የቅድስና ሕይወት እንዲማርኩ የሚጠቀመው አማኞችን ነው። ስለዚህ ዓለም ስህተት እንደሆነች በማረጋገጥ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ የሚወቅሰው በአማኝ በኩል ነው። ዓለምን ወደ ክርስቶስ ስናመጣ የእኛ ረዳት እርሱ ነው።

## ስለ ኃጢአት ይወቅሳል

በአንድ ወቅት ወንጌል ከሰበክሁ በኋላ ሰዎች በጌታ እንዲያምኑና እርሱን እንዲቀበሉ ጥሪ ሳደርግ፣ አንዲት የምታምር የስምንት ዓመት ልጅ ከጉባዔው ተነስታ መጣች። በመድረኩ አጠገብም ተንበርክካ እንባዋ በጉንጮችዋ ላይ እየወረደ "እምላኬ ሆይ እጅግ ክፉ ኃጢአተኛ ነኝ" በማለት ትናገር ነበር።

ዓለም ክፉ ኃጢአት የሚለውን ተግባር መፈጸሟን እጠራጠራለሁ፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ቅዱስ ሕይወት ስላሳያትና መዳን እንደሚያስፈልጋት ስለገለጸላት ነበር በዚያ መልክ ንስሐ የገባችው። በእግዚአብሔር ያለማመንን ትልቅ ኃጢአት ከቁም ነገር አትቆጥረውም፤ የልጁንም ታላቅ ስጦታ ዋጋ ታሳጣለች። ሆኖም ከኃጢአቶች ሁሉ በላይ የሆነው ኃጢአት ይህ ነው። የማያምንን ሰው የኃጢአቱን ይቅርታ መቀበል እንዳለበት የሚያስረዳውና በንስሐ ወደ ክርስቶስ እንዲመጣ የሚያደርገው



መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኞችን የሚወቅሰውና ስለ ኃጢአታቸው የሚያስረዳው በርሱ ኃይል የሚሰበከውን ወንጌል ሲሰሙ ነው (የሐዋ. 2፡14-41)። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ኃጢአተኛ ስለ ኃጢአቱ ሊረዳ የሚችለው ክርስቶስን እንደ አዳኙ ከተቀበለው አማኝ በመንፈስ የተቀባ ምስክርነት ሲሰማ ነው።

(1). መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ስለ ኃጢአት የሚወቅሰው

ሀ. በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ለማያምነው ሰው ምሪት በመስጠት ነው።
ለ. እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኝ ሕይወት ኢየሱስን ምሳሌ አድርጎ በማቅረብ ነው።
ሐ. የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመቀበል የማይገባቸው መሆናቸውን ኃጢአተኞች እንዲያውቁ በማድረግ ነው።

## ስለ ጽድቅ ይወቅሳል

መንፈስ ቅዱስ ስለ ጽድቅ ዓለምን እንደሚወቅስ ኢየሱስ ተናገረ፤ ምክንያቱም እርሱ ወደ አብ ስለሚሄድ ነው። ስለ ራሱ የተናገረው ሁሉ እውነት መሆኑን በማስረጃ የሚረጋገጠው የእርሱ ወደ አባቱ በመመለስ ነበር። እርሱ ጻድቅ ባይሆን ኖሮ ይሞት የነበረው ስለእኛ ሳይሆን ስለራሱ ኃጢአት ነበር። እንደሌሎቹ ኃጢአተኛ ሰዎች በመቃብር ውስጥ በስብሶ ይቀር ነበር። እርሱ ግን ጻድቅ ስለነበር የእኛን የኃጢአት ዋጋ ከፈለ፤ ከሞት ተነሥቶ፥ ወደ አባቱ አረገ። በበዓለ ሃምሳ ዕለት እነዚህን እውነቶች ጴጥሮስ ከእርሱ ጋር ለነበሩት በግልጽ ያስቀመጠላቸው በዚህ ምክንያት ነበር (የሐዋ. 2፡14-41)።

በሮሜ 1፡4 ላይ፦ "በቅድስና መንፈስ ደግሞ ከሙታን በመነሳቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኃይል ስለተገለጠው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል። ስለ ኢየሱስ ጻድቅነት የሚመሰክረው የቅድስና መንፈስ ነው። የክርስቶስን ነገሮች ለዓለም በማሳወቅ ለእርሱ ክብር ያስገኛል (ዮሐ. 16፡14)።

(2). በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ በተጻፈው መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅነት ማስረጃ የሆኑት ሁለት መልሶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ያስተማረው ትምህርት
ለ. በመስቀል ላይ መሞቱ
ሐ. ከሞት መነሣቱ
መ. ወደ አብ ማረጉ
ሠ. በሰዎች መካከል ያገለገለው አገልግሎት

## ስለ ፍርድ ይወቅሳል

ስለ ፍርድ እርግጠኛነት ለሰዎች ለማስረዳት መንፈስ ቅዱስ እንደ ምሳሌ የሚጠቀምበት የሰይጣንን ፍርድ ነው። የሰይጣን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ መሸነፍ፣ ክርስቶስ በሲኦልና በሞት ላይ የተቀዳጀው ድል፣ የመጨረሻ ፍርድ ስለመኖሩ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ናቸው።

ስለ ፍርድ የሚሰበክ ስብከት የመንፈስ ቅዱስን ፍቅርና ርኅራኄ እንዲሁም የክርስቶስን ድል መንሳት ላይ ጨምሮ የማይቀርብ ከሆነ፥ ለዎች ከእግዚአብሔር እንዲሸሹ የሚያደርግ ብቻ ይሆናል። ኢየሱስ ስለሚመጣው ፍርድ ኢየሩሳሌምን ባስጠነቀቀ ጊዜ እጅግ እንዳዘነ እንጂ፣ እርሱን አልቀበል ያሉት በመቀጣታቸውም ደስ ሲለው አንመለከትም (ማቴ. 23:37-38)።

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ለሰዎች ለማስረዳት ሐዋርያትን እንዴት እንደተጠቀመባቸው የሚያስረዱ ብዙ ምሳሌዎችን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እናገኛለን። በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ የተናገራቸው ነገሮች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. ባለማመናቸው ምክንያት በኢየሱስ ላይ ስላደረጉት ነገር በኃጢአታቸው ተወቀሱ (የሐዋ. 2:22-23)።

2. እግዚአብሔር ልጁን መበስበስን እንዲያይ በመቃብር እንዳል ተወው፣ ነገር ግን ከሞት እንደተነሳና በቀኙ እንዳስቀመጠው ሰዎቹ በተረዱ ጊዜ ስለ ጽድቅ ተወቀሱ (የሐዋ. 2:27፣ 30-33፣ 36)።

3. ስለ ፍርድም እንዲወቀሱ አደረገ። "በሌላ ብዙ ቃል እየመሰከረላቸው "ከዚህ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ" በማለት አስጠነቀቃቸው" (የሐዋ. 2:40)።

4. በውጤቱም በመጀመሪያ ሕዝቡ ተስፋ መቁረጥ ታየባቸው። ከዚያም ንስሐ በመግባት የጴጥሮስን መልእክት ተቀበሉ። በዚያም ዕለት ወደ 3000 ሰዎች በአማኞቹ ቁጥር ላይ ተጨመሩ።

ሌሎች ምሳሌዎች በሐዋ. 3:14-21፣ 4:10-12፣ 10:39-42፣ 13:27-41 ላይ ይገኛሉ። ዛሬም ቢሆን ለዓለም የድነት መልእክት ለማምጣት ረዳታችን መንፈስ ቅዱስ ነው። እኛንም፣ ሰዎች ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ እንዲወቀሱ ይጠቀምብናል።

(3). ባጠናነው መሠረት ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ በመውቀስ መንፈስ ቅዱስ ስለሚሰጠው አገልግሎት ከሚያስረዳው እውነተኛ መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. የዘላለም ፍርድ የሚያስከትለው ኃጢአት፥ ያለማመን ኃጢአት ነው።



ለ. መንፈስ ቅዱስ ስለ ፍርድ የሚወቅሰን በኃጢአተኛ ሰዎች ፍርድ ነው።
ሐ. የክርስቶስ ትንሣኤ የጻድቅነቱ ማስረጃ ነው።
መ. መንፈስ ቅዱስ ለዓለም የሚያበረክተው አገልግሎት በይበልጥ የሚከናወነው በሕይወታቸውና በአንደበታቸው ምስክርነት በሚሰጡ አማኞች ነው።
ሠ. ኢየሱስ በፍርድ ላይ ያተኮረው ለኃጢአተኞች የሚገባቸው ስለሆነ ነው።

### መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ያስገኛል

*ዓላማ 2 ድነት በምንቀበልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚያደርግ ልንን ሦስት ነገሮች ለመጥቀስ።*

የመንፈስ ቅዱስን ዳግም ልደት የማስገኘት ተግባር ወደፊት በምንማረው ክፍል ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ እንወያይበታለን። በዚህ ክፍል ትምህርት ላይ የተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እንደረዳትና እንደ ወዳጅ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ከመውቀስ ጀምሮ በቋሚነት በአጠገባችን በመሆን የአስተማሪነትና የመሪነት ተግባሩን እንደሚወጣ ለማሳየት ነው። የአጽናኙን የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በሕይወታችን ከመለማመዳችን በፊት ከመንፈስ ዳግሞ ልደትን ማግኘት ይገባናል።

ዳግም ልደትን የምናገኘው ከኃጢአታችን በንስሐ ተመልሰን ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችን ጌታና አዳኝ አድርገን ስንቀበል ነው። ንስሐ ለሚገባው ኃጢአተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመስጠት፥ በአብና በወልድ ስም የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. 3:3-8፣ 6:63፣ ቲቶ 3:4-5)።

በዳግም ልደት ወቅት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያድራል። ይህም ማለት በውስጣችን ሆኖ ሲረዳን በእኛ ያድራል ማለት ነው (ዮሐ. 14:16-17)።

(4). ሮሜ 8:9-11፣ 1ቆሮ. 3:16፣ 6:19 በማንበብ ይህን ዓረፍተ ነገር ሙሉ ለማድረግ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚናገሩትን እውነት ተጠቀም። ክርስቶስን እንደ አዳኛችን አድርገን በምንቀበልበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ

ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ካመጣን በኋላ መንፈስ ቅዱስ መኖሪያውን በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ያደርጋል። በውስጣችን ሲኖርም ስለወደፊቱ መንፈሳዊ ርስታችን መያዣ የእግዚአብሔር ማህተም ነው። "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም፣ በእርሱ በመሆን ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል። ለክብሩ ምስጋና ለመሆን የእግዚአብሔር የሆኑት እስኪዋጁ ድረስ እርሱ ለርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው" (ኤፌ. 1:13-14)።

(5). በዮሐ. 14:1-3፣ ኤፌ. 1:12-13 እና 2ቆሮ. 1:22 ላይ በተጻፈው መሠረት መንፈስ ቅዱስ ዋስትናችን የሚሆን መያዣ የሆነበት ምክንያት______

የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም እርሱ ሕይወታችንን ሲቆጣጠር በእርሱ ያለንን ዋስትና የሚያመለክት ነው። የሰማይ አባታችንም ርስት ተካፋይ እንድንሆን ልጆች መሆናችንን ደግሞ ይመሰክራል (ሮሜ 8:15-17፣ ገላ. 4:6)።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደትን በማስገኘት በእኛ ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወትን ይጀምራል። በውስጣችንም በማደር የሕይወታችንን ሂደት መቆጣጠር ይጀምራል። የልጅነት መብታችንን እውነተኝነት በመመስከርና (ሮሜ 8:16) የልጅነት መብት ወደፊት የሚያስገኘውን ጥቅሞች በማሳየት በውስጣችን ተስፋ እንዲኖር ያደርጋል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንጸልይ ስለ እኛ በመማለድ ይቃትታል (ሮሜ 8:26-27)። ተቀባይነት ያለው መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖርና በሕይወታችን የሚያደርገው እንቅስቃሴ እግዚአብሔር በየዕለቱ እኛን ለመርዳት ከእኛ ጋር የመሆኑ ዋስትናችን እንደሆነ ያሳስበናል።

(6). በዳግም ልደት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚያደርጋቸውን ሦስት ነገሮች ዘርዝር።

## መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል

*ዓላማ 3 መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር እንደሚያስተምረን ኢየሱስ የተናገረው ምን ማለት እንደሆነ ለመግለጽ።*

መንፈስ ቅዱስ ረዳት ከሆነባቸው ዋና ዋና መንገዶች አንዱ እውነትን ለአማኞች ማስተላለፍ ነው። በዮሐ. 14:16-17 ላይ አጽናኝ ብሎ በጠራበት መግለጫ ላይ *የእውነት መንፈስ* ብሎ የጠራው ስለዚህ ነው። በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውስጥ ማስተማርና መምከር በቅርበት የተያያዙ ናቸው። የማስተማር አገልግሎቱ ለአማኞች ነው፤ የዚህን አገልግሎት ሦስት ሁኔታዎች እንመለከታለን።

### አስተማሪ

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ባህርይና ፈቃድ ለማሳወቅ እንደመጣው፥ መንፈስ ቅዱስም የኢየሱስን ባሕርይና ፈቃድ ለማሳወቅ መጣ (ዮሐ. 14:20-21፣ 23-26)። ባለፉት ጊዜያት ይህንን ያደረገበት አንደኛው መንገድ የኢየሱስን ሕይወትና አገልግሎት ታሪክ እንዲጽፉ የእርሱን ተከታዮች በመምራት ነበር፤ የእርሱን ሕይወትና አገልግሎት ታሪክ ያሰፈሩት አራቱ ወንጌላት ሲሆኑ እነርሱም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ናቸው።



መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረው እንዴት ነው? *በመጀመሪያ እርሱ ክርስቶስን ያከብራል፤* ከእርሱ ጋር ግንኙነት የሌለውና አዲስ የሆነ እውቀት አያስተምርም። ነገር ግን ክርስቶስ ያስተማራቸውን ነገሮች ወስዶ እድማጮቹ የሚፈስገውን እውነት እንድንይዝ ብርሃን ያበራልናል። አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉና እየጠነከሩ ሲሄዱ የበለጠ ኃላፊነት ለመሸከም ይችላሉ። ወተት ከመመገብ ይልቅ ጠንካራ የሆነ ምግብ መመገብ ይጀምራሉ (1ቆሮ. 3:2፣ ዕብ. 5:11-14) መንፈሳዊ ምግቡ ቢለወጥም የትምህርቱ ርዕስ ጉዳይ ኢየሱስ፣ የማይለወጥ ሆኖ ይቆያል።

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልታውቀው ከሚገባህ አስፈላጊ ነገሮች ውስጥ የሚያስቀረው ምንም ነገር የለም። "እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል" በማለት ኢየሱስ በዮሐ. 14:26 ላይ ተስፋ ሰጥቶአል። ስለ ሥራዬ፣ ስለ ቤተሰቤና ስለ ገንዘቤ ሁኔታ አይገደውምን? በማለት በመገረም ትጠይቅ ይሆናል። አዎን እግዚአብሔር ስለነዚህ ነገሮች ይገደዋል። ዳሩ ግን ቅድሚያ ልንሰጣቸው ስለሚገቡ ነገሮች ሲገልጽ፦ "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመርላችኋል" በማለት በማቴ. 6:33 ላይ ኢየሱስ ተናግሮአል። መንፈሳዊ ነገርን በተመለከተ ሕይወታችንን እንዴት በሥርዐት እንደምንመራ መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል። ከዚያም ሕይወታችንን በመቆጣጠር በሌላው ነገር ሁሉ ውስጥ በአግባቡ እንድንመራ ያደርገናል። የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች የሚገልጥልንና መንፈሳዊ ኑሮአችንን እንድናስተውል የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ነው (1ቆሮ 2:10-15)። በዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ ክርስቶስን ለማክበር ነው።

*በሁለተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ በሚያስተምረው ውስጥ ወደፊት የሚፈጸሙ ነገሮችንም ያካትታል።* በዮሐ. 16:13 ኢየሱስ ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "ወደፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል" በማለት ተናግሮአል። ይህ ተስፋ በጣም ግልጽ የሆነው ሐዋርያው ዮሐንስ በጌታ ቀን በመንፈስ በነበረ ጊዜና የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ በተሰጠው ጊዜ ነበር (ራዕ. 1:10)። እነዚህ በቅርብ ሊፈጸሙ የሚገቡ ነገሮች እንደሆኑ ዮሐንስን ተናግሮት ነበር። የተሰጠው መገለጥ የሚያካትተው ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እስከ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ድረስ የሚፈጸመውን ድርጊት ነበር (ራዕ. 21)። በዚሁ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጌታ መገለጥና በመገለጡ ዙሪያ የሚፈጸሙ ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ ተናግሮአል (1ተሰ. 4:13-18፣ 5:1-11)። በማያምኑ ሰዎች ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድና አስቀድሞ የአመጽ ሰው እንደሚገለጥ ተናግሮአል (2ተሰ. 1:5-12፣ 2:1-12)። ጴጥሮስም ዳግም ስለሚመጣው የጌታ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተናግሮአል (2ጴጥ. 3:1-13)። በእነዚህ ድርጊቶች ሁሉ የምናየው የጋራ የሆነ መሠረታዊ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ መምጣቱ ነው።

(7). በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ዋና ሃሳብ ምንድነው?

ሀ. የኃጢአተኞች ፍርድ

ለ. የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር
ሐ. የሰይጣን የመጨረሻ ድሎች

(8). ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር እንደሚያስተምረን ሲናገር ምን ማለቱ ነበር? ፊደሉን በመክበብ የመረጥከውን መልስ አመልክት።

ሀ. እግዚአብሔር ስለ ራሱ እንድናውቅ የሚፈልገውን ሁሉ
ለ. ስለ ሥራችን ማወቅ የሚያስፈልገን ሁሉ
ሐ. በምድር ላይ ወደፊት በሕይወታችን ስለሚፈጸሙ ነገሮች
መ. እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናውቅ የሚፈልገውን ሁሉ
ሠ. ክርስቶስን እንድናከብር የሚረዳን የመንፈስ ቅዱስ ነገሮች
ረ. በክርስቶስ ካለን መንፈሳዊ ሕይወት ጋር የተዛመዱ የወደፊት ጉዳዮች
ሰ. በገንዘብ በኩል የተሳካልን እንዴት እንደምንሆን
ሸ. ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ዓለምን እንዴት እንደምናሳውቅ

## ተርጓሚ

### *ዓላማ 4 ቅዱሳት መጻሕፍት መጻፋቸውን በተመለከተ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን እንደነበር ለመግለጽ።*

ወንጌላቱ እንደተጻፉ መንፈስ ቅዱስ ፍቺ የመስጠት ወይም የመተርጎም አገልግሎቱን ጀመረ። ወንጌልን በዝርዝር ለቤተ ክርስቲያን ለመግለጽ የተመረጠው ሐዋርያው ጳውሎስ ነበር። ከአራቱ ወንጌላትና ከሐዋርያት ሥራ ቀጥሎ የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ከፍ ያለውን ክፍል የያዙት፣ ጳውሎስ ለአብያተ ክርስቲያናት የጻፋቸው መልእክቶች ናቸው። ሌሎች ሐዋርያትና የአዲስ ኪዳን አማኞችም የክርስቶስን ነገሮች ወስደው ለማሳወቅ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ነበር (ዮሐ. 16:14)። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ምን እንደሆነ በ2ጴጥ. 1:20-21 እና በ2ጢሞ. 3:16 ላይ የተጻፈው ቃል ያሳየናል። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተሰጣቸው እንዲጽፉ መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው ያሳያሉ። እነርሱ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጣቸው ምሪት የእግዚአብሔርን መልእክት ተናገሩና ጻፉ እንጂ የሂደቱ ጀማሪዎች እነርሱ አልነበሩም። መልእክቱ የመነጨው ከእግዚአብሔር ዘንድ ቢሆንም የግለሰቡ የግል የአጻጻፍ ስልትና ቃላት አጠቃቀም እንደዚሁም በአንዳንድ በኩል የልምምድ ችሎታውን በማንጸባረቅ የተጻፈ መሆኑን ማንም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነ ሁሉ የሚረዳው ነው። ጸሐፊዎቹ ዝም ብለው እንደ መኪና የሚነዱ መሣሪያዎች አልነበሩም። እራሳቸውን ለዚህ ሂደት መሳካት አሳልፈው በመስጠት እግዚአብሔር የፈለገውን መልእክት በትክክል ለማስፈር የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ቶሎ የሚሰማቸው ነበሩ።



የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና የተፈጸመና የተዘጋ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ሊገልጥ የወደደው በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረ ቢሆንም፣ የመንፈስ ቅዱስ የመተርጎም ወይም የማብራት አገልግሎት መስራቱን እንደቀጠለ ነው። የተጻፉትን ነገሮች በመውሰድ ለአማኞች ልብና አእምሮ ግልጽ እንዲሆኑ አብርሆት ይሰጣል (ያበራቸዋል)።

ማንኛውንም መጽሐፍ በሚገባ ለመረዳት የተሻለው መንገድ ደራሲው በጻፈው ጊዜ ምን ለማለት እንደፈለገ ደራሲውን ራሱን መጠየቅ ነው። ችግሩ አብዛኞቹ ደራሲዎች ለእኛ ለማስረዳት የማይገኙ መሆናቸው ነው። መንፈስ ቅዱስ ግን ዘወትር ከእኛ ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ሁሉ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ሞተዋል። መለኮታዊው ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ግን ከእኛ ጋር መሆኑን ማወቅ ምን ዓይነት መጽናናት ነው። መጽሐፍ ቅዱስህን በምትከፍትና በምታነብበት ጊዜ እውነቱን እንድትረዳ ሊያደርግህ የግል ረዳትህ በዚህ ነው።

(9). ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ምን እንደሆነ በተሻለ መንገድ የሚያስረዳው የትኛው መግለጫ ነው።

ሀ. እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሌላው ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ሰዎች መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸውን በአንድ ዓይነት የአጻጻፍ ስልትና ቃላት እንደዚሁም የሥነ ጽሑፍ ጾታ በመጠቀም እንዲጽፉ አደረገ።
ለ. መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ሲንቀሳቀስ ራሳቸውን የማያውቁ ስለነበሩና እንዲጽፉ የተደረጉትን ብቻ ስለጻፉ የሰዎቹን የአጻጻፍ ስልት፣ የቃላት አጠቃቀምና ልምምድ መንፈስ ቅዱስ አልተጠቀመም።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ የተመረጡ የእግዚአብሔር ሰዎችን ትንቢት እንዲናገሩ አነሳሳቸው። መንፈስም እንዳነሳሳቸው የእግዚአብሔርን መልእክት በታማኝነት ጻፉ፣ የእግዚአብሔርን መልእክት በማስተላለፉ ሂደት መንፈስ ቅዱስ የሰዎቹን የአጻጻፍ ስልትና ቃላት እንደዚሁም ልምምድ ተጠቀመ።

## ምሥክር

### *ዓላማ 5 ምሥክር የሚለውን ቃል ከኢየሱስ፣ ከመንፈስ ቅዱስና ከአማኙ አገልግሎት ጋር ለማዛመድ።*

ኢየሱስ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላ አጽናኙ የእግዚአብሔር ምሥክር ሆኗል። ምሥክር ማለት ሌላውን ወክሎ የሚናገር ማለት ነው። ኢየሱስ ራሱም ምስክርና የእግዚአብሔር አፍ ነበር። አባቱ የሰጠውን ተግባር አከናውኖ ፈጸመ። ኢየሱስ እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እንደሚናገር ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው (ዮሐ. 16:13)።

በዮሐ. 7:16 ላይ ኢየሱስ የአብ ምሥክር እንደመሆኑ፦ "የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን ከላከኝ የመጣ ነው" በማለት ተናገረ። ስለአጽናኙ መንፈስ ቅዱስም የተነገረው ተመሳሳይ እውነት ነው "እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል" (ዮሐ. 16:13)።

ልዩነቱ፡ ኢየሱስ የተናገረው በራሱ በተዳሰሸ ሰውነቱ፡ ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው በአማኞች በኩል ነው። ስለ እርሱ ሆነን የምንናገረው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ስናጠና የሰጠንን መልእክት ነው። ቃሉን በምናጠናበት ጊዜ ያበራልናል፤ ደግሞም የእርሱ ምሥክሮች ሆነን እንድንናገር በቅባቱ ይቀባናል። በዚህም መንገድ ረዳታችን መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በምድር ሁሉ ላይ ምሥክሮች ሊኖሩት ይችላሉ። እርሱን ስንሰማውና በእኛ በኩል እንዲናገር ስንፈቅድለት እርሱ በእያንዳንዳችን በኩል ሊናገር ይችላል።

እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በኩል በቀጥታ መንፈስ ቅዱስ የሚናገርበትም ጊዜያት ይኖራሉ፤ ስጦታው በተግባር ላይ በሚገለጥበት ጊዜ የምንናገረው እኛ ብንሆንም ቃላቱን የሚሰጠን ግን እርሱ ነው። ማንኛውም አማኝ የእግዚአብሔር አፍ ሆኖ መናገር የሚችለው መልእክቱን ከመንፈስ ቅዱስ ሲቀበል ብቻ ነው (1ቆሮ. 12:1-10)።

(10). ዮሐ. 14:7 እና 26 ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለእኛ የገለጠልን የትኛው ምሥክር ነው?
ለ. ኢየሱስ ምን እንደሚመስል ለእኛ የገለጠልን የትኛው ምሥክር ነው?
ሐ. መንፈስ ቅዱስ በእኛ በኩል ሲናገር የሚያሳስበን ስለምንድነው?
መ. ተወካይ ወይም ምሥክር መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

## መንፈስ ቅዱስ ይመክራል

*ዓላማ 6 የመንፈስ ቅዱስን የመምከር አገልግሎት የተለያዩ ገጽታዎች ለመግለጽና ትርጉማቸውን ለማብራራት።*

በዮሐ. 14:16 ***ጰራቅሊጦስ*** የሚለው የግሪክ ቃል አጽናኝ ወይም ረዳት ወይም ***አማካሪ*** ተብሎ እንደሚተረጎም ቀደም ሲል በክፍለ ትምህርት አንድ ተመልክተናል። ቃሉ በጥሬው ያለው ትርጉም "ለመርዳት በአጠገብ እንዲሆን የተጠራ" የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስን እንደ አማካሪያችን አድርገን ስናስብ ትርጉሙ ለመማለድ፣ ለመምራት ወይም ለማጽናናት የሚመጣ ጓደኛን ይመስላል። መንፈስ ቅዱስ ለእኛ በግል የሚሰጠው አገልግሎት፥ ለመርዳት በአጠገብ እንዲሆን የተጠራ፥ ከሚለው ሃሳብ ጋር በደንብ የሚስማማ ነው። እነዚህን አገልግሎቶች በግል ሕይወታችን ልንጠቀምባቸው የምንችለው እንዴት ነው?



## ስለ እኛ ይማልዳል

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጽ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል። ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና (ሮሜ 8:26-27)።

እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚጠቅሰው በእኛ ቦታ ሆኖ ስለ እኛ ስለሚጸልየው ወይም ስለሚማልደው መንፈስ ነው። በድካማችን ጊዜ ምን እንደምንጸለይና እንዴት እንደምንጸልይ አናውቅም። በምንደናገርበት ጊዜ ምን እንደሚያስ ፈልገን ለማስተዋል ይሳነናል። ተስማሚውን መፍትሔም እንዴት መፈለግ እንደምንችል ግራ ይገባናል። በሕይወታችን ከሁሉም በላይ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግና እርሱን ማስደሰት እንፈልግ ይሆናል፥ ዳሩ ግን ያሁኑ ችግራችንን እኛን ወደ መንፈሳዊ እድገት ለማምጣት ዘለቄታ ካለው ከእግ ዚአብሔር ዓላማ ጋር እንዴት እንደምናስማማው አናውቅም። በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜያት እኛን ለመርዳትና በቃላት ሊገለጥ በማይቻል መቃተት ለመጸለይ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል። በልባችን ምን እንዳለና በመንፈስ ቅዱስም ሀሳብ ምን እንዳለ እግዚአብሔር አብ ያውቃል። በእግዚአብሔር አብና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ፍጹም የሆነ ግንኙነት ስላለ መልእክት ለማስተላለፍ ቃላት አያስፈልጉም። መንፈስ ቅዱስ የአብን ሃሳብና ፈቃድ ስለሚያውቅ እርሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚጸልይልን በመረዳት ልንታመን እንችላለን። ይህም ግንዛቤ ጸሎታችን በእግዚአብሔር መንገድና በእግዚአብሔር ጊዜ እንደሚመለስ እንድናምን ሊረዳን ይገባል።

ከእኛ ጋር በቅርብ ሆኖ የሚረዳን ጓደኛ እንዳለን ማወቅ፥ በተለይም እንዴት እንደምንጸልይ ግራ በተጋባንበት ወቅት ስለ እኛ በመቃተት የሚጸልይ መኖሩን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የእኛ ስለሆኑት ነገሮች በማስታወስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንማልድ ይረዳል (1ቆሮ. 2:12)። ያለ እርሱ እርዳታ ጸሎታችን ባዶና ከንቱ ይሆናል።

(11). ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ የሚረዳን በምን ሁለት መንገዶች ነው?

(12). የመንፈስ ቅዱስን ስለ እኛ የመማለድ አገልግሎት የሚያመለክቱት የትኞቹ እንደሆኑ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. "የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ሁሉ ምን እንደሆኑ ዝርዝር በማውጣት በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አቀረብሁ"
ለ. "ወንድሜ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ችግር እንዳለበት ተረድቻለሁ፤ ዳሩ ግን ለዚሁ ችግር እንዴት እንደምጸልይ አላውቅም። ላደርግ የቻልኩት

በውድ ወንድሜ ስም ወደ እግዚአብሔር መድረስ ለሚችለው ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፌ መስጠት ነበር"

ሐ. "ቤተሰቤ የሚበላው ምንም ምግብ አልነበረውም። ስለዚሁ በመጸለይ ላይ ሳለን የቤታችን በር ተንኳኳ። በቤተ ክርስቲያን ያለ አንድ ወዳጃችን በአገልግል ምግብ ይዞ ከበራፉ ቆሞአል። ከመጸለያችን በፊት መልሱን እግዚአብሔር አስቀድሞ ለጥቶን ነበር"

መ. "እግዚአብሔር እኔ ከማውቀው አብልጦ ስለ እኔ ችግሮች ስለሚያውቅ በጸሎት ብዙ ጊዜ ማባከኑ አስፈላጊ አይደለም"

## ይመራናል

በየትኛው ሥራ ላይ ልሰማራ? ማንን ላግባ? የት ልኑር? የሚሉት ጥያቄዎች በየዕለቱ የሚያጋጥሙህ በመሆናቸው ውሳኔ ለማድረግ ታማኝ የሆነ መሪ ያስፈልግሃል። የነገሮች የሚወሰነው በምትከተለው ምሪት ነው።

እያንዳንዱ ከሁሉ የተሻለ ነው የተባለለትን ምክር የሚሰጡ ብዙ ድምጾች አሉ። ነገር ግን ለመከተል በፍጹም የሚያስተማምን አንድ አማካሪ ብቻ አለ። እርሱም ወደኛ ለመላክ ኢየሱስ ተስፋ የሰጠው አማካሪ ነው። በእውነትና በሐሰት መካከል መወሰን ሲኖርብህ እርሱ የእውነት መንፈስ በመሆኑ፥ በእውነት መንገድ ይመራሃል (1ዮሐ. 4:1-6)።

"እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም" (ገላ. 5:16፣ 18)። "በመንፈስ የምንኖር ከሆንን፥ በመንፈስ እንመመላለስ" (ገላ. 5:25)። በመንፈስ ለመመላለስ ወይም ለመመራት እርሱ በሚመራን መንገድ ለመሄድ ፈቃደኞች መሆን አለብን። እንደ ፈቃዱ ከኖርን፥ እርሱ ይመራናል (ሮሜ 8:5)። ከሁሉ በላይ የሆነ የመሪነቱን ሥልጣን ስንቀበል፣ ቀስ በቀስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል (ዮሐ. 16:13)። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ያደርግ እንደነበረው፥ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ሞገስ እንድናገኝ፥ እኛንም ደግሞ ይመራናል። ማንኛውም ችግር ሲገጥመን፥ ለእነርሱ እንዳደረገው ለእኛም በችግራችን ይረዳናል (የሐዋ. 2:42-47)።

ወደ እውነት ሁሉ ከመምራት ተግባሩ በተጨማሪም፣ በዕለት ኑሮአችን ካልተለወጠው ባህሪያችን የሚመነጨውን የተሳሳቱ ድርጊቶች በጉልህ ያሳየናል። ኤፌ. 4:20-32 እና ሮሜ 8:12-14 በማነጻጸር ተመልከት። በአሮጌው ሰው ቁጥጥር ውስጥ እየተንሸራተተ የሚገባ ሰው በመንገዱ ላይ የሚጠብቀውን ጉድጓድ ከመግለጡም ሌላ፣ መንፈስ ቅዱስ ከአዲሱ ሰው ጋር አብሮ የማይሄደውን ማንኛውንም መጥፎ ባህሪይ ለማስወገድ ይረዳዋል።

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አብሮ የማይሄድ ድርጊት እንዳንከተል መንፈስ ቅዱስ ይቆጣጠረናል። ለጳውሎስና አብረው ለነበሩት በእስያ ወንጌል እንዳይሰብኩ የተከለከሉት ኃጢአት ስለሆነ ሳይሆን፥ ወቅቱ የእግዚአብሔር ጊዜ ስላልነበረ ብቻ ነው (የሐዋ. 16:6-10)። በኋላም ይህ መከልከል



ተነሥቶ ጳውሎስ በእስያ ምድር ታላቅ የወንጌል አገልግሎት እንደነበረው በሐዋ. 19:10 ላይ ማንበብ እንችላለን፤ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ የመሪነት ተግባሮች ለመንፈሳዊ እድገታችን በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

(13). የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦቹን ከተመለከትክ በኋላ ቁጥሩን በተሰጠው ክፍት ቦታ በማስፈር አብሮ የሚሄደውን አመልከት።

| | |
|---|---|
| _____ ሀ. ውሳኔ ማድረግ | 1. የሐዋ. 8:29 |
| _____ ለ. መከልከል | 2. የሐዋ. 13:2 |
| _____ ሐ. ሹመት | 3. የሐዋ. 15:28 |
| _____ መ. ምሪት | 4. የሐዋ. 16:6 |

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ምን ማድረግ እንዳለብን ምሪት ብቻ ሳይሆን፣ ማድረግ በሌለብን ጉዳዮችም ምሪት ይሰጠናል። ከእርሱ አስቀድመን እንዳንሄድና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን የሚያ ስንቅፉ ድርጊቶች እንዳናደርግም ይመራናል (ሮሜ 8:12-16፣ 1ዮሐ. 3:2-3)። እርሱ እንዲመራን ወደ እርሱ መመልከትና ድምጹን መታዘዝ ይገባናል።

## ያጽናናል

ቀደም ሲል እንደተናገርነው ጰራቅሊጦስ የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ የሚተረጎመው አጽናኝ ተብሎ ነው። "በአጠገብ ሆኖ ለመርዳት የተጠራ" በሚለው አስተሳሰብ መሠረት መንፈስ ቅዱስ አጽናኛችን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ማጽናናት መለኮታዊ ሐዘን ማዘን አይደለም። እርሱ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙንን ሐዘናችና ችግሮችን ስለሚያውቅ ከፍ ያለ ርኅራኄ አለው። የእርሱ ማጽናናት ግን ሐዘንን ተካፋይ ከመሆን በላይ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ከሚያሳምርባቸው ባህርያት መካከል፣ ሰላምን ማስገኘቱ ሊጠቀስ ይገባል (ገላ. 5:22)። የእርሱ ሰላም ሕይወታችን በእርሱ ቁጥጥር ስር እንዲሆን አሳልፈን የመስጠታችን ውጤት ነው (ሮሜ 8:6)። እርሱ የሕይወታችን ተቆጣጣሪ መሆኑን በይበልጥ እየተረዳን ስንሄድ የእግዚአብሔር የመሆናችን እውነት አብልጦ ይገባናል። ይህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የመሆናችንን የማወቅ ስሜት ይፈጥርልናል። ይህ እውቀትም ታላቅ የዕረፍትና የሰላም ስሜት ሊሰጠን ይገባል።

የመንፈስ ቅዱስ መጽናናት ተስፋንም የሚያካትት ነው። ሌሊቱ የፈሰገውን ያህል ቢጨልምም የወደፊቱን በትክክልና በደንብ የሚያውቀው አጽናኝ ንጋት እንደሚኖርና፣ "ተመልሼ እመጣለሁ" በማለት ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም እንድታውቅ ያደርግሃል (ዮሐ. 14:28)።

(14). በስተቀኝ የተሰጡትን የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ የመምከር አገልግሎት ገጽታዎች ከበስተግራ ካሉት ማብራሪያዎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ሀ. በማስጠንቀቅ፣ በመከልከል፣ በመሾም፣ ውሳኔ በማድረግ መንፈስ ቅዱስ ይመራናል። | 1. የሚማልድ |
| ለ. በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆን እንኳ መንፈስ ቅዱስ ሰላም ይሰጠናል። | 2. መሪ |
| ሐ. ችግራችንን ለማወቅና በቃላት ለመግለጽ በማንችል በት ጊዜ ችግራችንን እንድናውቅና ስለ እኛ በመጸለይ መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል። | 3. አጽናኝ |

(15). በእነዚህ በሦስት አቀማመጦች የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ አግኝተሃልን? ካገኘህ የሚማልድ፣ መሪና አጽናኝ የሚሉትን ሦስት ቃላት በማስታወሻ ደብተርህ ላይ እንደ ርእስ በማስፈር የተለማመድከውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከጻፍክ በኋላ፣ በየዕለቱ በሚገጥመህ በማንኛውም መንፈሳዊ ችግሮች ሊያገለግልህ ከአንተ ጋር በመሆኑ አመስግነው።

---

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ፦ትክክለኛውን መልስ ከመረጥህ በኋላ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

1. *ጰራቅሊጦስ* ለሚለው የግሪክ ቃል ትርጉም ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አጽናኝ ለ. አማካሪ ሐ. ፈጣሪ መ. ረዳት

2. *ጰራቅሊጦስ* ለሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም የትኛው ነው?

ሀ. የሚያስረዳ
ለ. ሊፈርድ የተጠራ
ሐ. የሚያስተዛዝን
መ. በአጠገብ ሆኖ ለመርዳት የተጣራ

3. የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ አገልግሎት ያልሆነው የትኛው ነው? ከአንዱ በስተቀር በሌሎቹ ሁሉ ዓለምን ይወቅሳል።

ሀ. ፍርድ ለ. ዳግም ልደት ሐ. ጽድቅ መ. ኃጢአት

4. *ዳግም ልደት* ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጋር በተያያዘ መልኩ የሚገልጸው፡-

ሀ. መንፈሳዊ ልደት
ለ. የሥጋ ልደት
ሐ. የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ
መ. የተሻለ ሕይወት ለመኖር መሞከር



5. መንፈስ ቅዱስ ስለ ፍርድ ዓለምን የሚወቅሰው ምንን አስመልክቶ ነው?

ሀ. አማኞች ስለተፈረደባቸው ነው
ለ. የማያምኑት ስለተፈረደባቸው ነው
ሐ. ሰይጣን ስለተፈረደበት ነው

6. ድነት በምንቀበልበት ጊዜ ከነዚህ መካከል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የታረመ ሕይወት ያኖረናል
ለ. ያትመናል
ሐ. ዳግም እንድንወለድ ያደርገናል
መ. በውስጣችን ይኖራል

7. ማኅተሙን በእኛ ላይ ሲያኖር ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር አብሮ የማይሄደው የትኛው ነው።

ሀ. ባለቤትነት ለ. ጥበቃ ሐ. ዋስትና መ. ፍጹምነት

8. ልንጸልይበት ስለሚገባን ችግር መንፈስ ቅዱስ ያሳስበናል። እርሱም በቃላት ሊገለጥ በማይቻል መቃተት የእኛን ችግሮች ወደ እግዚአብ ሔር ያቀርባል። ይሀ ለእኛ ያለው አገልግሎት ምን ይባላል?

ሀ. ማስተማር
ለ. ማጽናናት
ሐ. መማለድ
መ. መተርጎም

9. ውሳኔ ማድረግ፣ መከልከል፣ መሾምና መምራት ከየትኛው የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ጋር የተዛመዱ ናቸው?

ሀ. መምራት
ለ. ማጽናናት
ሐ. ማማለድ
መ. መውቀስ

**አጭር መልስ**፡- እያንዳንዱን ጥያቄ ባጭሩ መልስ።

10. መንፈስ ቅዱስ በማስተማር አገልግሎቱ ለእኛ ምን ሁለት ነገሮች እንደሚያደርግ ኢየሱስ ተናገረ?

11. የእግዚአብሔር መገለጥ ወደ ሰዎች የሚያደርሱት ምስክሮች እነማን እንደሆኑ በትክክለኛው ቅደም ተከተል ዘርዝር።

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. መከበብ ያለባቸው ፊደሎች፡- ሀ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ እና ሸ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሆኑትን በዝርዝር መልኩ ያስረዳሉ። በርግጥ ተግባራዊ ሆነ መንፈሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ጥበብን ይሰጠናል።

1. ለ

9. ሐ

2. ሐ እና መ

10. ሀ. ኢየሱስ — ሐ. ኢየሱስ ያስተማረው ነገር ሁሉ
ለ. መንፈስ ቅዱስ — መ. ስለሌላው ወይም በሌላው ስም ሆኖ መናገር

3. ሀ. እውነት — ሐ. እውነት — ሠ. ሐሰት
ለ. ሐሰት — መ. እውነት

11. አንዳንድ ጊዜ እንድንጸልይባቸው ችግሮችን ወደ አእምሮአችን ያመጣል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እኛ በቃላት ልንገልጻቸው በማንችልበት ወቅት ችግሮቹን በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባቸዋል።

4. (በራስህ ቃላት)። በውስጣችን ይኖራል፣ በውስጣችን ሊኖር ይመጣል።

12. "ለ" እና "ሐ" ላይ የሰፈሩት መልሶች የመንፈስ ቅዱስን የምልጃ ጸሎት የሚያብራሩ ናቸው።

5. ኢየሱስ በዮሐንስ 14 ላይ በሰጠው ተስፋ መሠረት የእርሱ ለሆኑት እንደሚመለስ ማኅተሙ ወይም ዋስትናው እርሱ ነው። የወደፊቱ ርስት ዋስትናችን መንፈስ ቅዱስ ነው።

13. ሀ. 3 — ለ. 4 — ሐ. 2 — መ. 1

6. ዳግም ልደትን እንድናገኝ ያደርጋል፣ በውስጣችን ይኖራል፣ እንደገናም ያትመናል።

14. ሀ. 2 — ለ. 3 — ሐ. 1

7. ለ

15. የአንተ መልስ።



# 4
### ትምህርት

# የመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት

አንድ ክርስቲያን አስትሮኖመር (የጠፈር ተመራማሪ) ትምህርት ለማስተማር ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር በባቡር ይጓዝ ነበር። ራሱ የሰራውና ገለጻ በሚሰጥበት ጊዜ እንደ ትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚጠቀምበት በባትሪ ኃይል የሚሠራ ሥርዐት ፀሐይን (Solar System) በምሳሌነት የሚያሳይ በሸራ የተሸፈነ ሞዴል ይዞ ነበር። በባቡሩም ውስጥ በአጠገቡ ስለ እግዚአብሔር ህልውና የማያምን ሰው ተቀምጦ ነበር። በጭውውታቸው መካከል የእግዚአብሔርን መኖር የሚክደው ሰወ ዩኒቨርስ ወይም ህዋ በእግዚአብሔር ተፈጥሮአል የሚለው ነገር የሞኞች ሐሳብ ነው በማለት መሳለቅ ጀመረ።

የጠፈር ተመራማሪውም በጽሞታ ካዳመጠው በኋላ ለማስተማርያነት የያዘውን ተሽከርካሪ መኪና መሰል የማስተማርያ ሞዴል እንዲመለከት ጋበዘው። ሸራውን ከገለጠ በኋላ ማብሪያና ማጥፊያውን ተጫነው። ትናንሾቹ ፕላኔቶች በፀሐይ ዙሪያ በምህዋራቸው ላይ መሽከርከር ጀመሩ። እንቅስቃሴው ድንቅ በሆነ ሁኔታ፣ ያለ ምንም መዛባትና ግጭት ይካሄድ ነበር። እግዚአብሔር የለም ባዩ ሰው በጣም በመገረም፣ "እንዴት አስደናቂ ነገር ነው! ማነው ለመሆኑ የሠራው?" በማለት ጠየቀ። ተመራማሪውም "ማንም አልሠራውም። እነዚህ ሁሉ በአጋጣሚ የተፈጠሩና እንዲህ ሆነው የተገኙ ናቸው" ብሎ መለሠለት። እግዚአብሔር የለም ባዩ ሰው እንደበቱን ለጉሞ ጸጥ አለ። ተመራማሪው ሰው የሰራውን የሥርዓተ ፀሐይ ሞዴል በማስደገፍ፣ የሥሥዓተ ፀሐይ ጅማሬ ምን እንደነበረ ገለጸለት። ይህ ሞዴል ወይም ምሳሌ ሰሪ ካስፈለገው፣ ባስደናቂ ጥበብ የሚመራው ፀሐይና በፀሐይ ዙሪያ ያሉት ተሽከርካሪ አካላትና ፕላኔቶች ሁሉ፣ ምድርን ጨምሮ ምን ያህል ፈጣሪ ሊኖራቸው የሚገባ እንደሆነ ገለጸለት።

ምድርና ሰማይ፣ እንደዚሁም በውስጣቸው ያሉት ሁሉ የመለኮታዊ ፈጣሪ ሥራዎች ናቸው። እግዚአብሔር ቃሉን ሲናገር በሥራ ላይ የዋለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። በዚህ ክፍል ትምህርት የምናጠናው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በፍጥረት ውስጥ ምን እንደሆነ ነው። ዓለም በተፈጠረ ጊዜ በግል ወዳጃችን የሆነው መንፈስ ቅዱስ በዚያ ነበረ። ዛሬም በፈጣሪነት ኃይሉ በሕይወታችን ውስጥ በትጋት ይሠራል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- በመተባበር መፍጠር
- ዓለምን መፍጠር
- ሰውን መፍጠር
- ሁሉን ጠብቆ ማኖር

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በፍጥረት ሥራ ውስጥ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ምን እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን መግለጽ።
- የሰው አፈጣጠር ሌላው ፍጥረት ከተፈጠረበት የሚለይበትን መንገዶች መግለጽ።
- መንፈስ ቅዱስ ፍጥረትን በመፍጠርና ጠብቆ በማቆየት ያለውን ኃይል የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ማስተዋል።

---

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ክፍለ ትምህርቱ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በጥን ቃቄ አንብብ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹንም መልስ።
2. ለክፍሰ ትምህርቱ መነሻ ይሆንህ ዘንድ፥ ዘፍ. 1 እና 2፣ እንደዚሁም ዮሐ. 1 በቅድሚያ አንብብ።
3. ክፍለ ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለህ ስትጨርስ የሙከራ ፈተናውን ወስደህ መልሶችህን አመሳክር።



የትምህርቱ ዝርዝር

## በመተባበር መፍጠር

## የፍጥረት ዕቅድ አውጪዎች

***ዓላማ 1 በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ የሰፈረው የፍጥረት አፈጣጠር ታሪክ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ተሳትፎ በይበልጥ ዝርዝር በሆነ መልኩ ለምን እንዳላስቀመጠ ለመግለጽ።***

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር . . ." (ዘፍ. 1:1) እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ቃላት በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚጠቀሙት የእግዚአብሔርን የብዙ ቁጥር ስም ነው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ ባይጠቀሱም ሥላሴ አካላት በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቅሰዋል።

የሥላሴ ትምህርት በመጽጽፍ ቅዱስ ውስጥ የበለጠ እያደገና እየጎላ የመጣና እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን በግልጽ የተቀመጠ ነው። ሙሴ የመጀመሪያዎቹን አምስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በጻፈበት ጊዜ ብዙ ሰዎች በብዙ አማልክት የሚያምኑ ነበሩ። በዚያን ጊዜ የሥላሴ መገለጥ መደናገር ሊያመጣ ይችል ነበር። ሕዝቡ ይህንን እውነት ለመቀበል ዝግጁ እንዳልነበረ ስላወቀ እግዚአብሔር ይህን መገለጥ አልሰጠም። በእያንዳንዱ ጊዜ የቱን ያህል ራሱን መግለጥ እንደነበረበት እግዚአብሔር ያውቅ ስለነበረ፣ የሰጠው መገለጥ በጊዜ ውስጥ የሚያድግ ነበር። ስለዚህ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረው የፍጥረት ታሪክ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ተግባር ሁሉንም በዝርዝር በማቅረብ አይነግረንም። ሌሎች የመጽጽፍ ቅዱስ ክፍሎች እያንዳንዱ የሥላሴ አባል በእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራና የመዋጀት ዕቅድ ውስጥ ምን ድርሻ እንደነበረው ያስረዳናል።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ብዙ ጅማሬዎች ይነግረናል። ስለ ፍጥረት፣ ስለ ሰው፣ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ፍርድና ስለ ድነት ጅማሬዎች ይነግረናል። ስለ ፍጥረት የሚናገሩት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ብቻ ናቸው። የፍጥረት አፈጣጠር በአጭሩ የተጻፈው በሰው ልጅ ታሪክ ጅማሬ አካባቢ የተፈጸመውን በማመልከት ለምን መዋጀት እንደሚያስፈልገው ለማሳየት ነው።

ከፍጥረት በፊት እንኳ በፍጥረቱ ላይ ምን እንደሚሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ሰው በኃጢአት እንደሚወድቅ አስቀድሞ ስላወቀ ለሰው የድነትን መንገድ እንዳቀደ በርከት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይነግሩናል።

1. በራዕ. 13:8 ላይ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስሞቻቸው በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስለተጻፉ ሰዎች ይናገራል።

2. በኤፌ. 1:4 ላይ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደመረጠን ይነግረናል።

3. በማቴ. 25:34 ላይ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታማኞች ለሆኑት የተዘጋጀላቸው መንግሥት እንዳለ ይጠቅሳል።

በርከት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሥላሴን ዘላለማዊነት በማረጋገጥ አጠንክረው ይናገራሉ። ስለዚህ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ዘወትር አብረው በፍጹም አንድነት የሚሠሩት ሁሉን ነገር ለመፍጠር አቅደው፥ በተግባር ላይ አዋሉ። አንዳንዶቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከዚህ ቀጥለን እንመልከት።

1. በመዝ. 90:2 ላይ፡- "ገና ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድርንና ዓለምን ከመፍጠርህ በፊት፣ አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላክ ነህ።" በማለት ዳዊት ይናገራል። *ይህ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የአብን መኖር የሚገልጽ ነው።*

2. ሐዋርያው ዮሐንስ *የወልድን ቀደም ሲል መኖር* ሲገልጽ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" በማለት ይናገራል (ዮሐ. 1:1)። ከዚያም በመቀጠል በቁጥር 14 ላይ፡- "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን" በማለት ይናገራል። ወልድ ከአብ ጋር በእኩልነት በፍጥረት ጊዜ አብሮ ነበር።

3. የመንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ መኖሩ የተገለጠው *ዘላለማዊ መንፈስ* ተብሎ በተጠራበት በዕብ. 9:14 ላይ ነው። እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም፤ በፍጥረት ሥራ ከአብና ከወልድ ጋር አብሮ ነበር። *የመንፈስ ቅዱስ ቅድመ መኖር* የተገለጠው ለዘላለማዊ ባሕርይው በተሰጠው መግለጫ ነው።

አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ ነበሩ። ሌላውን ማንኛውንም ነገር ወደ መኖር ያመጡት ሥላሴ ያሉና የነበሩም፣ ወደፊትም ለዘላለም የሚኖሩ ናቸው። ውስን የሆነው አእምሮአችን ይህንን እውነት ሙሉ በሙሉ ሊረዳው አይችልም። እኛ በጊዜ የተወሰንን ስንሆን፣ እግዚአብሔር ብቻ ጊዜ የማይወስነው ነው። በዘፍ. 1:1 ላይ በመጀመሪያ ተብሎ ከተነገረው በፊት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም በሆነ አንድነትና ሕብረት የፍጥረትን እቅድና የድነትን መንገድ ይነግገዋል።

(1). ከላይ በተመለከትነው መሠረት የዘፍጥረት ታሪክ የሥላሴ ተሳትፎ በይበልጥ ግልጽና ዝርዝር ያላደረገበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግለጽ።

(2). ዘፍ. 1 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።



ሀ. በዚህ ምዕራፍ የእግዚአብሔር ስም ስንት ጊዜ ተጠቅሷል?
የመንፈስ ቅዱስስ? የወልድስ?

ለ. ቁ. 1 ላይ የተጻፈው ቃል እግዚአብሔር የተጠራው በብዙ ቁጥር ስም ስለሆነ፣ በውስጠ ታዋቂነት ሥላሴ ያመለክታል። ሥላሴን የሚያመለክት ሌላው ጥቅስ የቱ ነው?

## በአንድነት መፍጠር

*ዓላማ 2 አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ተግባር ውስጥ የነበራቸውን ተሳትፎ ለመግለጽ።*

መጽሐፍ ቅዱስ የፍጥረት አፈጣጠር ተግባር የሥላሴ አባላት ሁሉ እንደሆነ ያሳያል።

1. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባላት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ፡- "ሰማይንና ምድርን፤ ባሕርንም፤ በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ልዑል ጌታ ሆይ አንተ ፈጥረሃል፤" በማለት ተናገሩ (የሐዋ. 4:24)። ወደ አብ ይጸልዩ እንደነበር ግልጽ ነው።

2. እንደገና በዮሐ. 1:3 ላይ ስለ ወልድ ሲገልጽ "ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠረው ሁሉ፥ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም" በማለት ይናገራል። ኢየሱስ በመፍጠር ሥራ ተሳትፎ እንደነበር በግልጽ የሚያሳይ ነው።

3. ውበ በሆነ የምስጋና መዝሙር ፍጥረት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሆኖ ተገልጿል። በመዝ. 104:30 መዝሙረኛው ሲናገር፡- "መንፈስን ስትልክ፣ እነርሱ ይፈጠራሉ፤ የምድርንም ገጽ ታድሳለህ።" በማለት ይገልጻል። ይህ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ተግባር ስለነበረው ተሳትፎ የሚናገር ብቻ ሳይሆን፥ በመንከባከቡና በመጠበቅም እንደነበረው የሚገልጽ ነው።

ፍጥረት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም የሆነ ትብብር ውጤት ነው። ይህ እንዴት እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ሊገባን አይችልም። ስታንሊ ሆርቶን የተባለ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ስለዚህ ሲገልጽ፡- "አብ ፈጣሪና ሠሪ ነው። የፈጠረውም በወልድ በኩልና በመንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ እንዴት እንደሆነ ምስጢሩ በመጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር አልተገለጠም። ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው እርሱ ፈጣሪ፣ እኛ ደግሞ የእርሱ ፍጡሮች የመሆናችን እውነት ነው" በማለት ተናገረ (ሆርቶን፣ *መንፈስ ቅዱስ* ገጽ 52)።

በፍጥረት ሥራ ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው እንመለከታለን። እርሱ በተለይ የተጠቀሰው ከተግባሮቹ ሁሉ ትልህ በሆነው በፈጣሪነት ኃይሉ በተለየ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ ነው። እርሱ ሕይወት የሚሰጥ

ኃይል እንዳለው ኢዮ. 33:4፥ መዝ. 10:30፣ ዮሐ. 6:63 እና ሮሜ 8:11 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

(3). የዘፍጥረት መጽሐፍ የፍጥረትን አፈጣጠር ታሪክ ሲናገር የሥላሴን አካላት የነበራቸው ተሳትፎ አጉልቶ ባያሳየንም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እኩል ተሳትፎ እንደነበራቸው የምናውቀው እንዴት ነው?

## ዓለምን መፍጠር

*ዓላማ 3 ስለ ፍጥረት ድርጊቶች እውነት የሆኑትንና ያልሆኑትን መግለጫዎች ለይቶ ለማስረዳት።*

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ከሌሎች ጋር በመሆን የፍጥረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ምድርን ስለሸፈነው ጨለማና ባዶ ሁኔታ ለመግለጽ ብዙ አስተያየቶች ሰጥተዋል። የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ ምክንያቱን ስለማይገልጥልን ምን እንዳመጣው ከመገመት በስተቀር እዚህ ላይ በዝርዝር ለማስረዳት እንሞክርም። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የባዶነትንና ቅርጽ የሌለውን ሁኔታ በእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ወደ ሙላት እንደመጣ፣ መልክና ቅርጽ በማግኘት ውበት ያለው እንደሆነ እናውቃለን።

### በውሃው ላይ መስፈፍ

> "ምድርም ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች፤ የምድርን ጥልቅ ሥፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር። የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር" (ዘፍ. 1:2)።

እዚህ ላይ የምንመለከተው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ከፍጥረት በፊት በነበረው ሀዋ ላይ ይሰፍ እንደነበር የሚያሳይ ነው። በዘዳ. 32:11 ላይም ንስር "ጫጩቶቿን፥ በክንፍ የመብረርን ጥበብ እንደምታለማምድና በተዘረጉ ክንፎቿ ተጠንቅቃ እንደምትይዛቸው ሲገልጽ የሚጠቀመው ይህንኑ "መርበብ" በሚለውን ግስ ነው። (የ1956 ትርጉም "መስፈፍ" የሚለውን ግስ ሲጠቀም፣ የ1993 አዲሱ መደበኛ ትርጉም "መርበብ" የሚለውን ግስ ይጠቀማል።) የሥላሴ ሦስተኛው አካል የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እዚህ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔርን የመፍጠር ድንጋጌዎች ለማከናወን ዝግጁ በመሆን ነው። በተከታታይ የተሰጡት የመፍጠር ትዕዛዞች እርሱ የሚያከናውናቸው ነበሩ። እርሱ የተገለጠው የፍጥረት ሙሉ ወኪልና አነግሽ በመሆን ነው።

በዘፍ. 1:3 ላይ፦ "ብርሃን ይሁን" በማለት የመጀመሪያው ትእዛዝ መጣ። ወዲያው ብርሃን ሆነ፤ ብርሃኑም መልካም ነበር። በዘፍ. 1:6 ላይ "ውሃውን ከውሃ የሚለይ ጠፈር በውሆች መካከል ይሁን" የሚል ሁለተኛው ትእዛዝ



መጣ። ጭጋጋማ የነበረው በመንፈስ ቅዱስ ድርጊት ተገፎ ከውሃው በላይ ደመና ሆነ። የኢዮ. 26:13 አንድ ትርጉም ምን እንደሆነ ሲገልጽ፦ "በእስትንፋሱ (መንፈስ) ሰማያትን አጠራ" ይላል።

ሦስተኛው ትዕዛዝ "ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ስፍራ ይከማች፤ ደረቁ ምድር ይገለጥ" የሚል ነበር (ዘፍ. 1:9)። ኃይል ሁሉ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡና በላዩ ሆኖ ሲሠራ ውቅያኖሱ በአንድ ስፍራ ተሰበሰበ፤ ደረቅ ምድርም ከውሃው ተለይቶ ብቅ አለ።

(4). ውሃውን ከውሃ የመለየት የመንፈስ ቅዱስን ተካፋይ መሆን በተሻለ መንገድ የሚገልጠው የትኛው ቃል ነው?

ሀ. ዕረፍት ለ. መጠባበቅ ሐ. ማዘዝ መ. ኃይለኛ

### በምድር ላይ መንቀሳቀስ

የሚቀጥለው ትእዛዝ የተሰጠው ስለ ምድር ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስን የሚገልጸው እንደ ሕይወት መንፈስ አድርጎ ነው (ዘፍ. 1:11-13፥ 20-25)። የሕይወት መንፈስ የሚለው መጠሪያ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል።

እርሱ በሰፊው ምድር ላይ ሲንቀሳቀስ ምድር አትክልትን፥ በየዓይነቱ የእህል አዝዕርትንና ፍራፍሬ የሚያስገኙ ተክሎችን ማብቀል ጀመረች (ዘፍ. 1:12)። ከዚያም ታላላቅ የባሕር እውሬዎችን፣ ሌሎችንም በውሃ ውስጥ የሚኖሩና የሚንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ ወፎችን ፈጠረ (ዘፍ. 1:20-22)። ከዚያም እንደገና በምድር ላይ በመንቀሳቀስ አራዊትን በየዓይነቱ፥ እንስሳትን በየዓይነቱና በምድር ላይ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታትን ፈጠረ (ዘፍ. 1:24-25)።

መዝሙረኛው ስለነዚህ ፍጥረታት እግዚአብሔርን በተለይ ሲያመሰግን "መንፈስህን ስትልክ እነርሱ ይፈጠራሉ" ይላል (መዝ. 104:30)፥ "እነርሱ ይፈጠራሉ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምድርንና ባሕርን እንዲሞሉ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ነው (መዝ. 104:24-25)።

የተለያዩና የተዋቡ አትክልቶች፣ እንስሳት፣ አሶችና የሰማይ ወፎች የእነዚህ የፈጣሪያቸውን ችሎታ እንድናደንቅ ከማድረጋቸውም በላይ የአክብሮት መንፈስ ያሳድርብናል። በአንድ ሙዚየም እጅግ ብዛትና ትልቅ ውበትን የተጎናጸፈ ከመላው አፍሪካ አህጉር የተሰባሰቡ የተለያዩ ተክሎችና እንስሳትን ተመልክቻለሁ። ከነዚህም ውስጥ በጣም ደስ የሚያሰኘው በመቶዎች የሚቆጠሩ እጅግ ውስብስብ የሆነ ሥራና የሚያምሩ ቀለማት የሚታይባቸው ትናንሽ ነፍሳት የሚገኙበት ክፍል ነው። አንዳንዶች የፀሐይ ብርሃን ሲያርፍባቸው የሚያንጸባርቁ ትናንሽ ፈርጦች ያላቸው ናቸው። ይህ እንግዲህ እጅግ ብዛትና ልዩነት ባለው በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ

የሚገኝ ትንሹ ክፍል ነው። በፈጣሪነት ኃይሉ የእግዚአብሔርን እቅድ በሥራ ላይ ያዋለው መንፈስ ቅዱስ ነው።

(5). ዘፍ. 1:11-12 እና 20-25 የተጻፈው የሚያሳየን፣ እግዚአብሔር. . .

ሀ. እያንዳንዱ ዓይነት አታክልትን፣ በባሕር የሚኖሩ ፍጥረታትን፣ አእዋፋትንና እንስሶ ችን እንደፈጠረ ነው።
ለ. የተለያዩ ፍጥረታትን ያስገኙትን የተወሰኑ ተክሎችን፣ አእዋፍንና እንስሳትን እንደፈጠረ ነው።
ሐ. ሌሎች ዓይነቶችን የሚያስገኙ ከየዓይነቱ ጥቂት ቁጥር ያላቸውን ህያዋንን እንደፈጠረ ነው።

## በሰማይ መንቀሳቀስ

> በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተሠሩ፣ በአፉም እስትንፋስ የከዋክብት[14] ሰራዊት (መዝ. 33:6)።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መዝሙረኛው ያሰፈረው የሰማይ ሠራዊት በእግዚአብሔር መንፈስ (እስትንፋስ) እንደተፈጠረ የሚገልጽ ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ የተጻፈው ታሪክ የሚያተኩረው በምድር ላይና በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ ስለተፈጠሩት ጸሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ነው (ዘፍ. 1:14-18)።

ስለ ፕላኔቶች፣ ስለ ጨረቃ፣ ስለ ጸሐይና ስለ ከዋክብት ከሚያጠናው አስትሮኖሚ ከተባለው ጥናት የተሻለ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚገልጥ ሌላ ጥናት የለም። የጠፈር በህዋ ውስጥ የሚገኘው እጅግ የተለያየ ነገር አእምሮአችን ሊያስበው ከሚችለው ነገር እጅግ የሚያልፍ ነው። እኛ ሰዎች በምድር ላይ እንደ ጥራጊ አዋራ ነን፣ ምድርም ራሷ በህዋ ስፋት ውስጥ በአንጻራዊነት ስትታይ እንዲሁ የአዋራ ያህል ናት።

በሕዋ ውስጥ ርቀትን ለመለካት በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ በምድር ላይ ያለው የርቀት መለኪያ ብቃት የለውም። በሕዋ ውስጥ ርቀት የሚለካው በብርሃን ፍጥነት ነው፣ ብርሃን በአንድ ሰከንድ 186,000 ማይልስ (299,270 ኪሎ ሜትር) ይጓዛል። የህዋ ርቀት በሴኮንዶች፣ ወይም በደቂቃዎች፣ ወይም በሰዓታት፣ ወይም በቀናት የሚለካ ሳይሆን በብርሃን ዓመታት የሚለካ ነው።

ለምሳሌ፦ ከጸሐይ ሥርዓት ውጪ ለምድራችን ከሁሉ የበለጠ ቅርብ የምትባለው ኮከብ አራት ዓመት ተኩል የብርሃን ዓመት ያህል ትርቃለች። በሌላ አባባል ከእርስዋ የሚወጣው ብርሃን በሰከንድ 186,000 miles እየተጓዘ እኛ ጋር ለመድረስ አራት ዓመት ተኩል ይፈጅበታል ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት ስለ ከዋክብት ምርምር የሚያደርጉ ሳይንቲስቶች



እንደሚነግሩን ከሆነ፣ ከዋክብት 3 ቢሊዮን የብርሃን ዓመታት ያህል ከመሬት እንደሚርቁ ተገንዝበዋል።

እነኚህ በእግዚአብሔር እስትንፋስ (መንፈስ) የተፈጠሩት ከዋክብት ቁጥራቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ከተፈለገ፣ መቶ ቢሊዮን የሚሆኑ ከዋክብቶች በእኛ ጋላክሲ ውስጥ ብቻ ይገኛሉ። (ጋላክሲ ማለት የብዙ ከዋክብቶች ክምችት ሆኖ እጅግ ብዙ ከሆኑት ሥርዓቶች አንዱ ነው።) የከዋክብት ተመራማሪዎች ከቢሊዮን በላይ የሚሆኑ የከዋክብት ጋላክሲዎች እንዳሉ ተገንዝበዋል።

"ኤርምያስ ብዛታቸው ሊቆጠር እንደማይችል እንደ ባሕር አሸዋና እንደ ሰማይ ከዋክብት ይሆናል" የሚለውን አገላለጽ የተጠቀመው ስለሰዎች ብዛት ሲገልጽ ነው (ኤር. 33:22)። በመዝ. 19:1 ላይ ደግሞ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይ ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" በማለት ዳዊት የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ በማድነቅ ይናገራል። እኛ የምናገለግለው አምላክ ምንኛ ኃያል አምላክ ነው። የፍጥረት ወኪል በመሆን የአብን ድንጋጌ በተግባር ላይ ያዋለው ያው መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በእኛ ሕይወት ይሠራል። በሚያስገርም ሁኔታ በሠራት ዓለም ውስጥ የሰማይ አባታችንን ፈቃድ ለማከናወን እንድንችል የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለእኛ ማግኘት የሚቻል ነው።

(6). ስለ ፍጥረት እውነት የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ለተለያየ የፍጥረታት ክፍል ኃላፊነት ነበረው።
ለ. ከፍጥረት በፊት የመንፈስ ቅዱስ በውሃ ላይ መስፈፍ (መርበብ) የእግዚአብሔርን የፈጠራ ድንጋጌ በተግባር ላይ ለማዋል የእርሱ ኃይል ዝግጁ እንደሆነ ሃሳብ የሚሰጥ ነው።
ሐ. ሀዋ እኛ ከምናስበው በላይ እጅግ በጣም ትልቅ ቢሆንም፣ እያንዳንዱ ክፍል ከሌሎቹ ጋር ፍጹም በሆነ ስምምነት ይሠራል።
መ. እግዚአብሔር ምድርን፥ እጽዋትን፥ እንስሳትን፥ አእዋፋትንና የባሕር የፈጠረው ከምንም ተነስቶ ነው።
ሠ. በዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ፍጥረት የሚናገረው ታሪክ ስለ ሰማያትና እንዴት እንደተሠሩ ትኩረት የሚሰጥ ነው።
ረ. ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት በእግዚአብሔር የተፈጠሩ የሰማይ አካሎች ናቸው።
ሰ. መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ የነበረው አንድ ድርሻ ሕይወት ላላቸው ፍጥረታት የሕይወት እስትንፋስ መስጠት ነው።

## ሰውን መፍጠር

*ዓላማ 4 ሰው እንዴት ሕይወት እንዳገኘና አፈጣጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት በምን እንደሚለይ ለመግለጽ።*

## በእግዚአብሔር የታቀደ

በዘፍ. 1:26 ላይ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር፦ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ" በማለት ተናገረ። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ስምም ሆነ "እንሥራ" የሚለው ግስ የብዙ ቁጥር ሆኖ ነው የተጠቀሰው። የሥላሴን መለኮታዊ ፍቅር የሚገልጥ ዕቅድ ሲያቅዱ ነው የሚታዩት።

ሰው ከህዋ ጋር ሲነጻጸር ብናኝ አዋራ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል። ሰው ለእግዚአብሔር "ልዩ የሆነ ብናኝ አዋራ" ነው። ሰው እግዚአብሔር የተለየ የፍቅር ዓላማውን የሚገልጥበት ከፍተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍጡር ነው።

በራዕይ 13:8 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚነግረን የሰው ድነት የታቀደው ከፍጥረት በፊት መሆኑን ለመረዳት እንችላለን። ይህ መለኮታዊ ውሳኔ የተደረገው ጊዜ የሚባል ነገር ከመጀመሩ በፊት መሆን አለበት (ዘፍ. 1:26)። በሥላሴ ዘንድ በሰው የአፈጣጠር ሂደት ውስጥ ምን እንደተደረገ እንመልከት። "እኛን የሚመስል ሰው እንፍጠር" ሲል እግዚአብሔር አብ ተናገረ። "ማሰብ የሚችል፥ ሊሰማውና ውሳኔ ሊያደርግ የሚችል፣ ከእርሱ ጋር ተግባቦትና ሕብረት እንዲኖረን እንድንችል፥ ሰውን በአምሳላችን እንፍጠር አለ"።

ይህን እቅድ በማውጣት ሰው የፈጣሪውን ፍቅር ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ሙሉ ነጻነት እንዲኖረው ለማድረግ ወሰነ። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ሰው በኃጢአት እንደሚወድቅና ከፈጣሪው ጋር ያለውን ሕብረት የሚያድስበትን መንገድ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልገው ያውቅ ነበር። ይህን ከፍተኛ መሥዋዕት ለመክፈል የእግዚአብሔር ልጅ ተላከ። እርሱም ራሱን በፈቃደኝነት መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እቅዱንም በተግባር ላይ በማዋል የሚያከናውነው መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱን በፈቃዳቸው ለመከተል የሚፈልጉ ጥቂት የተመረጡ ሰዎች እንደሚኖሩ እግዚአብሔር አወቀ። እነዚህም አማኞች የእርሱን ባሕርይ ተካፋዮች ይሆናሉ። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነበር እግዚአብሔር የድነትን እቅድ ያወጣው። ስለዚህ እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ሰውን ፈጠረ። ሰው በእግዚ አብሔር አምሳል ተፈጠረ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው (ዘፍ. 1:27)።

(7). ሰው ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር የድነት እቅድ ያወጣው ለምን ነበር?

## በእግዚአብሔር የተሠራ

"እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር ወስዶ፥ ሰውን አበጀው" (ዘፍ. 2::7)። ሌሎች ፍጥረታት እግዚአብሔር ቃሉን ሲናገር በምድር ላይ ህልውናን አገኙ፤ መንፈስ ቅዱስም በምድር ገጽ ላይ ይንቀሳቀስ ነበር።



ሰው ግን ልዩ ፍጡር ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ከመሬት አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው። የሰው አፈጣጠር ከሌሎች መፍጠር ድርጊቶች ሁሉ የተለየ ነበር። በዘፍ. 2 ላይ፥ በምዕራፍ 1 ውስጥ የሚገኙትን የፍጥረት ሥራዎች አንዳንዶቹን በጥልቀት ይዘረዝርልናል። በዘፍ. 2:21-22 ላይ እንደተጻፈው የሰው ፍጥረት የተሟላ የሆነው እግዚአብሔር ከሰው ጎን አጥንት ወስዶ ባዶውን ስፍራ በሥጋ በመሙላት ከሰው በወሰደው አጥንት ሴትን በሠራ ጊዜ ነበር።

## በእግዚአብሔር ሕይወትን ያገኘ

> "በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት" (ዘፍ. 2:7)። "የእግዚአ ብሔር መንፈስ ፈጥሮኛል፤ ሁሉን የሚችለውም አምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጥቶኛል።" (ኢዮ. 33:4)።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሰውን አካል አበጀ። ከዚያም በሰውነቱ ውስጥ የሚኖረውን መንፈሳዊ አካል ለማስገኘት የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወት የሚሰጥ እስትንፋስ ሰጠው። በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተገኘው ሕይወት በይበልጥ የሚያመለክተው ከአፈጣጠሩ ይልቅ መንፈስ ቅዱስን መቀበሉን ነው። የአፈጣጠሩ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች መታየታቸው እውነት ነው። ሕይወት የማግኘቱ ነገር የመጣው ግን ከኃያሉ አምላክ እስትንፋስ ነው።

እዚህ ላይ ለማስተዋል ከእኛ ሰብዓዊ ችሎታ በላይ የሆነውን የተፈጸሙትን ሁኔታዎችና ኃይሎች ስንመለከት፥ የሰው አፈጣጠር ሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረታት ያላገኙትን በማግኘቱ ከፈጣሪው ጋር የቅርበት ስፍራ እንዲኖረው ያደርገዋል ብንል አንሳሳትም።

(8). ሰው ሲፈጠር ሕይወት የተቀበለው በየትኛው ነጥብ ላይ ነው?

(9). የሰውን አፈጣጠር ከቀሩት ፍጥረታት ልዩ የሚያደርገው በምን መንገድ ነው?

(10). ይህ ልዩነት የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ ሰው...

ሀ. አካላዊ (ተዳሳሽ) ፍጡር እንደሆነ ነው።
ለ. መንፈሳዊ ፍጡር እንደሆነ ነው።
ሐ. በፈጣሪው ፊት ከሌላው የተለየ ፍጡር አለመሆኑን ነው።

### ሁሉን ጠብቆ ማኖር

*ዓላማ 5 ፍጥረትን በመደገፍ፡ በኩል የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ተግባራት ለመግለጽ።*

ሁሉን በመፍጠር ሦስቱም የሥላሴ አካላት ተሳትፎ እንደነበራቸው፣ ፍጥረትንም ጠብቆ በማኖር በኩል ጉልህ የሆነ ተሳትፎ ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚያድግፍና እንደሚጠብቅ ቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ስፍራ ይናገራሉ (ዘዳ. 6:24፣ መዝ. 31:23፣ ምሳ. 2:8፣ 2ጢሞ. 4:18)።

መዝ. 121 እንዲህ ይላል፦

> ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሳሁ፤ ረድኤቴ ከወዴት ይመጣል? ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል። እግርህ እንዲሸራተት አይፈቅድም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።
>
> እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፤ እግዚአብሔር በቀኝህ በኩል ይከልልሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም፤ ጨረቃም በሌሊት ጉዳት አታመጣብህም። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤ ነፍስህንም ይንከባከባታል። እግዚአብሔር ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣ መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።

በዮሐ. 14:16 ላይ፦ "እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" በማለት ኢየሱስ ተናገረ። በቀንና በሌሊት እኛን የሚጠብቅ እርሱ ነው፥ በእርሱ ጥበቃ እስከሆንን ድረስ ምንም አያስጋንም። የእርሱ ጥበቃ እኛን ብቻ ሳይሆን መላውን ፍጥረት ያካትታል።

(11). ኢዮ. 12:7-10 አንብብ። እንስሳት፥ አእዋፍ፥ ምድርና የባሕር አሶች የሚያስተምሩን ምንድን ነው?

(12). ኢሳ. 40:7 እና 13 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ለአንተ ምን ማለት እንደሆኑ በራስህ ቃላት ግለጽ።

(13). በስተቀኝ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብና በስተግራ ካለው ማብራሪያ ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ኢየሱስ ዓለምን ሁሉ ደግፎ ይይዛል። | 1. መዝ. 104:30 |
| ለ. እግዚአብሔር ስለሚያበረታንና ደግፎ ስለሚይዘን መፍራት የለብንም። | 2. ዕብ. 1:1-3 |
| ሐ. ሁሉን የፈጠረው መንፈስ፣ ሁሉን ነገሮች ደግሞ ያድሳል። | 3. ኢሳ. 41:10 |

(14). እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችስ የሚገልጹት ፍጥረትን የመፍጠርና ጠብቆ የማኖር ተግባር

ሀ. በይበልጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ነው።



ለ. በይበልጥ የእግዚአብሔር አብ ተግባር እንደሆነ።
ሐ. የሚከናወነው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ነው።

የእግዚአብሔርን ፍጥረት በማድነቅ ስንመለከት፣ እርሱ በፈጸማቸው አስደናቂ ነገሮች መገረማችን የማይቀር ነው። በእርግጥ ክብርና ምስጋና የሚገባው እርሱ ነው። ሥራውን በስድስተኛው ቀን ፈጽሞ ሲመለከት ያደረገው ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለክብሩ ፈጠረ። "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይ ጠፈሮችም የእጁን ሥራ ያወራሉ" ይላል (መዝ. 19:1)። የፈጠራቸው ፍጥረታት የእርሱን ክብር የሚገልጡ ናቸው። እኛን የፈጠረን እርሱን እንድናከብረው ነው። እርሱን እንድናከብር የሚያሳስቡን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ (1ዜና. 16:29፣ መዝ. 29:1፣ ሮሜ 15:6-9)። ፈጣሪ አምላክህን ታከብራለህን? ኢየሱስንና በአንተ ውስጥ ለመኖር የመጣውን መንፈስ ቅዱስን ታከብራለህ?

በራዕይ 4:11 ላይ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ለዘላለም በሚኖረውና በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት በግንባራቸው ተደፍተው በመስገድ አክሊሎቻቸውን በዙፋኑ ፊት አኑረው ከተናገሩ ቃላት በስተቀር ለዚህ ትምህርት የተሻለ መደምደሚያ አይኖርም። ሃያ አራቱ የተናገሩት እንዲህ የሚል ነበር።

> "ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ ክብርና ሞገስ፣ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤ ሆነዋልምና።"

# የሙከራ ፈተና

ምርጫ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሻለውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

1. በዘፍጥረት መጽሐፍ ሦስቱ የሥላሴ አካላት በመፍጠር ተግባር ውስጥ ስላደረጉት ተሳትፎ የተሟላ መግለጫ የሚሰጠው የትኛው ነው?

ሀ. ሦስቱም አካላት ሙሉ በሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውን በመግለጽ፣ ዝርዝሮቹን በግልጽ ያሰጠናል።
ለ. ስለ እያንዳንዱ ተሳትፎ በትንሹ በመግለጽ፣ በአጽንኦት የሚናገረው ግን በብዙ ቁጥር የተጠቀሰው አንዱና ዘላለማዊው አምላክ የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ነው።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከሁሉም የበለጠ ተሳትፎ እንደነበረው ይገልጣል።

2. በዘፍጥረት ከሁሉ በላይ ትኩረት የተሰጠው የትኛው ነው?

ሀ. የዓለማት መፈጠር
ለ. የኃጢአትና የፍርድ ጅማሬ
ሐ. የሰው የመዋጀት አስፈላጊነት
መ. የሰው መፈጠር

3. እግዚአብሔር የድነት ዕቅድን የወሰነው

ሀ. ጊዜ ከመጀመሩ በፊት
ለ. ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ
ሐ. ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ
መ. በፍጥረት ጊዜ

4. በመዝ. 90:2፣ ዮሐ. 1:1 እና ዕብ. 9:14 ላይ የተጻፈው ዘላለማዊ የሆነውን አምላክ ባሕርይ የሚያጸናው. . .

ሀ. በፍጥረት ወቅት የሥላሴን ተሳትፎ በመጥቀስ ነው።
ለ. ከፍጥረት ጊዜ አንጻር የሥላሴን ቅድመ ህልውና በመጥቀስ ነው።
ሐ. የአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከፍጥረት በፊት ያለው ህልውና ከጊዜ በኋላ መገለጡን በመጥቀስ ነው።
መ. በፍጥረት ጊዜ የነበረውን ጨለማና ባዶነት ሁኔታ በመጥቀስ ነው።

5. ፍጥረት የማን ሥራ ነው?

ሀ. የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ
ለ. የአብና የመንፈስ ቅዱስ
ሐ. የእግዚአብሔርና የሰው

6. ዓለምን በመፍጠር የመንፈስ ቅዱስ ተግባር

ሀ. ቃል መናገር ነበር።
ለ. ምን መደረግ እንዳለበት መወሰን ነበር።
ሐ. መለኮታዊ ድንጋጌውን በተግባር ላይ ለማዋል በሐይል መንቀሳቀስ ነበር።



7. ሰውን በመፍጠር ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ምን ነበር?

ሀ. ሰውን ከአፈር ማበጀት ነበር።
ለ. ከሰው አጥንት ወስዶ ሴትን መፍጠር ነበር።
ሐ. ሰው መንፈሳዊ ህልውና እንዲኖረው ያደረገውን የሕይወት እስትንፋስ መስጠት ነበር።
መ. በመፍጠር ኃይሉ በሰው ላይ መሰፈፍ

8. ከፍጥረት ሥራ በኋላ በፍጥረት ላይ የመንፈስ ቅዱስን ተሳትፎ በትክክል የሚገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. ፍጥረትን ጠብቆ ማኖር
ለ. እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ
ሐ. ምድርን ቀስ በቀስ በአዲስ የሕይወት ዓይነቶች መሙላት

9. እግዚአብሔር ሰውንና ዓለምን ለመፍጠር የፈለገው፦

ሀ. የተሟላ ለመሆን
ለ. ክብሩን ለመግለጥና ክብር ለመቀበል
ሐ. የሚቆጣጠረው እንዲኖረው ለማድረግ

10. እግዚአብሔር ላደረገው ሁሉ በተሻለ መንገድ ልናከብረው የምንችለው በምን መንገድ ነው?

ሀ. የተፈጥሮን ቁንጅና በማድነቅ
ለ. እርሱን በማምለክና በመታዘዝ
ሐ. ለፍጥረታት በሙሉ ደግነትን በማሳየት
መ. ፍጥረታትን ሁሉ በተቻለ መጠን በቁጥጥር ሥር በማድረግ

11. የሰው መፈጠር ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው በምን መንገድ ነው?

ሀ. እርሱ ብቻ ጎልማሳ ወይም ሙሉ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ
ለ. ሌሎቹ ፍጥረታት የተፈጠሩት በተናገረው ቃል ሲሆን፣ ሰው ግን እግዚአብሔር ከአፈር ካበጀው በኋላ የሕይወትን እስትንፋስ "እፍ" ስላለበት።
ሐ. ሰው ሌሎቹን ነገሮች ሁሉ ጠብቆ እንዲያኖር ኃይል ስለተሰጠው

12. ሙሴ የመጀመሪያዎቹን አምስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በጻፈበት ወቅት እግዚአብሔር ራሱን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ቀስ በቀስ የገለጸበት ምክንያት ለምን ነበር?

ሀ. ምክንያቱም በጊዜው መለኮታዊ ባሕርይው ሙሉ በሙሉ ስላልጎለበተ
ለ. ሕዝቡ የእግዚአብሔር በሥላሴ መገለጥ ለመቀበል ዝግጁ ስላልነበሩ

ሐ. የሥላሴን መገለጥ ሌሎች በሚገባቸው መንገድ ለማስረዳት ሙሴ ራሱ በደንብ ስላልገባው

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ በአፍንጫው እፍ ባለበት ጊዜ

1. የሥላሴ ሙሉ መገለጥ ለማስተዋል በዚያን ጊዜ ሕዝቡ ዝግጁ ስላልነበሩና ግራ የሚያጋባቸው ስለነበረ ነበር።

9. ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በእግዚአብሔር ቃልና መንፈሱ በምድር ላይ በመንቀሳቀሱ ሀልውና አግኝተዋል። ሰውን ግን ከአፈር አበጀውና እስትንፋሱ ሕይወት ሰጠው።

2. ሀ. ቢያንስ 30፣ አንድ ጊዜ፣ ምንም አልተጠቀመም
ለ. ቁጥር 26 (የብዙ ቁጥር ግስ በመጠቀም)

10. ለ

3. ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ፍጥረትን በተመለከተ ምስጋና የሚያቀርቡት ለሥላሴ ነው።

11. ሕይወትና እስትንፋስ በጌታ እጅ መሆናቸውን።

4. መ

12. የአንተ መልስ። የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወት እንደሰጠንና፣ የሕይወታችንንም መጀመሪያና መጨረሻ እንደሚቆጣጠር የሚያመለክቱ ናቸው።

5. ሀ

13. ሀ. 2    ለ. 3    ሐ. 1

6. ሀ. ሐሰት    ሐ. እውነት    ሠ. ሐሰት    ሰ. እውነት
ለ. እውነት    መ. እውነት    ረ. እውነት

14. ሐ

7. ሰው ከእርሱ ጋር ያለውን ሕብረት እንደማያጠብቅና ሕብረቱንም ለማደስ ወደፊት መንገድ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ያውቅ ስለነበረ።



# 5

ትምህርት

# መልእክት የሚያስተላልፍ መንፈስ

ከፍጥረት ጀምሮ እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ለሕዝቡ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለነቢያት መልእክት በማስተላለፍ የእርሱ መልእክት ወደ ሕዝቡ እንዲደርስ ያደርግ ነበር። አንዳንድ ነቢያትና ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፉ ዘንድ ስለመረጣቸው መልእክቱን በጽሑፍ አስፍረው አኖሩ።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕያው ቃልና፣ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነበር። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለእኛ ለማሳየት ወደ ዓለም መጣ። የእርሱን ትምህርትና በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎት ዝርዝር በመጻፍ አራቱ ወንጌላት አስፍረዋል። በጽሑፍ የሰፈረው ያህ ቃል የመጣው ከእርሱ ጋር በተመላለሱና በተነጋገሩ ሰዎች፣ እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና መሪነት ነበር።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ ሐዋርያት የእግዚአብሔርን መልእክት ማስተላለፍ ቀጠሉ። ከእነርሱም ብዙዎቹ ቃሉን ለመጻፍ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሲሆን የቅዱሳት መጻሕፍትም መሰኪያ (ቀኖና) ሰጥተውናል። ቃሉን በማስተላለፍ ወንዶችና ሴቶች እርሱን አውቀው እንዲታዘዙት፣ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሠርቶአል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት የምንመለከተው ቃሉ እንዲጻፍና ለኛም ቅባት ያለው ህያው ቃልና ህያው መልዕክት እንዲሆንልን በማድረግ በኩል የነበረውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ነው። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሌሎች የሚያስተላልፈው በእኛ በኩል ስለሆነ መልእክቱን የማስተላለፍ ኃላፊነት አለብን።

## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የተጻፈው ቃል
- ሕያው ቃል
- ሕያው መልእክቶች

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- መገለጥ፣ እስትንፋስ እግዚአብሔርና አብርሆት የሚሉትን ቃላት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በተመለከተ ትርጉማቸውን መግለጽ።
- መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ምሪት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለማወቅ የምንችልበትን መንገዶች መግለጽ።
- በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ መግለጽ።
- መንፈስ ቅዱስ በአንተ በኩል እንዲሠራ በመፍቀድ ህያው መልእክት የመሆንን አስፈላጊነት ግንዛቤ ማግኘትህን በተግባር ማሳየት።

---

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርት አንድ የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ትምህርቱን አጥና። ትምህርቱን በማስተዋል አጥና፣ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አንብብ፤ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹንም መልስ።
2. የሙከራ ፈተናውን ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከው ካለ እንደገና ተመልከት።





# የተጻፈው ቃል

## የተጻፈው ቃል አስፈላጊነት

***ዓላማ 1 በመገለጥ፣ በእስትንፋስ እግዚአብሔርና በአብርሆት መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ።***

እግዚአብሔር ለሰው ያለው መልእክት የሞትና የሕይወት ጉዳይ ነው። በመዝ. 119፡11 ላይ መዝሙረኛው ዳዊት፡- "አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ" በማለት ይናገራል።

እግዚአብሔር ለሰዎች ለመናገር የፈለገው መልዕክት በብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል። "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ወይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው አባባሎች ከ3800 ጊዜ በላይ ተጽፈው ይገኛሉ። የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በማድረግ ነው ከዘላለም ሞት የምንድነው።

> ሙሴም ሁለቱን የምሥክር ጽላቶች በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ፤ ጽላቶቹም ከፊትና ከኋላ በሁለት ወገን ተጽፎባቸው ነበር። ጽላቶቹ የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፤ በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸ ጽሕፈትም የእግዚአብሔር ነበር (ዘጸ. 32፡15-16)።

ሙሴ የሕዝቡን ኃጢአት በተመለከተ ጊዜ እነዚያን ጽላቶች ሰበራቸው። እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ አሥርቱን ትእዛዛት ለሙሴ በሰጠ ጊዜ መመሪያዎች ጭምር አክሎ ሰጠው። እግዚአብሔር ሙሴን "እነዚህን ቃሎች ጻፋቸው፤ በእነዚህ ቃሎች መሠረት ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና" አለው (ዘጸ. 34፡27)። በቁ. 28 እንደተገለጸው "ሙሴ . . በጽላቶቹ ላይ የቃል ኪዳኑን ቃሎች ዐሥርቱ ትእዛዛትን ጻፈ" ይላል።

በቃል ከማስተላለፍ ይልቅ መልእክትን በጽሑፍ ማስተላለፍ የተሻለ የሚሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም በቃል የሚተላለፍ መልእክት ከሰው ወደ ሰው በተላለፈ ቁጥር ስለሚለወጥ ነው። በጽሑፍ የሚተላለፍ መልእክት ግን የመጀመሪያው ሰው የተቀበለውን ተመሳሳይ መልዕክት የመጨረሻው ሰው ይቀበላል። ሳይከለስና ሳይበረዝ ምንም ሳይቀየጥበት በንጹህ መልኩ ሊደርስ ይችላል።

እግዚአብሔር ወደሰው የሚያስተላልፈው መልእክት እርሱ እንደ ሰጠው በትክክል መድረስ አለበት። ትንሽ ስወጥ አድርጎ ለማቅረብ እንኳ ማንም ፈቃድ የለውም። ስለዚህ ነው *ስህተት የሌለበትን* የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉውን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጠን ያስፈለገው። ከሰው ወደ ሰው በቃል ሲተላለፍ እንዳይለወጥ የእግዚአብሔር መልእክት መጻፍ ነበረበት። ማንም

እንደመሰለው እንዳይጨምርበት፣ ወይም ከመልእክቱ ቀንሶ እንዳያስቀር የተሟላ መሆን ነበረበት። እንዲሁም ያለስህተት ደግሞ መሆን አለበት። ያሁኑንና የወደፊቱን እያንዳንዱን የእኛን ሁኔታ በጥልቀትና በስፋት ባይነግረንም፥ ስለ ድነት፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንን፣ እንዴት እንደምንጠብቅ ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ስላለለን ኃላፊነት፣ የኃጢአተኛንና የጻድቅን ሰው የወደፊት ዕድል እንድናውቅ የፈለገውን እግዚአብሔር ገልጦአል። መጽሐፍ ቅዱስ እምነትንና ተግባርን በተመለከተ ሙሉ ብቃት ያለው የበላይ ባለ ሥልጣን ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ማስተላለፍ የፈለገውን ሙሉ መገለጥ የያዘና ፍጹም ሊታመን የሚገባ ነው። ከዚህም የተነሳ ያለ ምንም ማመንታትና መቆጠብ ልንታመንበት እንችላለን።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ መናገር ሲፈልግ፣ ይህን የሚያደርገው በመንፈስ ቅዱስ እማካኝነት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች መልእክት የሚያስተላልፍበት ሦስት መንገዶች አሉ። እነዚህም ሦስት መንገዶች *መገለጥ፣ እስትንፋስ እግዚአብሔርና አብርሆት ናቸው።*

1. *መገለጥ፦* ቀደም ሲል ያልታወቀው ነገር መግለጥና እንዲታወቅ ማድረግ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው በቀጥታ ሲናገርና የሚያውቅበት ሌላ መንገድ የሌለውን ነገር ሲነግረው *መገለጥ* ይባላል።

2. *እስትንፋስ እግዚአብሔር፦* የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማሳወቅ በሰው እእምሮና ስሜት ላይ የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት የሚያመለክት ነው። እንዲያስፍሩ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ጸሐፊዎች ስህተት የሌለበትን እውነት በተጠቀመባቸው ጊዜ በእስትንፋስ እግዚአብሔር ጻፉ፤ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጻፉ እንላለን። ይህም እውነት ከዚህ በፊት ያውቁት የነበረውን ወይም በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠላቸው ሊሆን ይችላል (2ጢሞ. 3:16)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ *በሙሉ እስትንፋስ እግዚአብሔር* (plenary inspiration) የተጻፈ ስለመሆኑ ብዙ ጊዜ ይጠቀሳሉ። ሙሉ የሚለው ቃል በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በሙሉ እስትንፋስ እግዚአብሔር ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጻፉን የሚያመለክት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ *የቃል እስትንፋስ እግዚአብሔር* እንዳለው ብዙ ጊዜ ይጠቀሳል። መንፈሳዊ እውነቶች የሚገለጡት በመንፈሳዊ ቃላት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (1ቆሮ. 2:13)። *የቃል እስትንፋስ እግዚአብሔር* ማለት ሃሳቡ ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትም ጭምር በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወይም አነሳሽነት የተጻፉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

3. *አብርሆት፦* በአንድ ነገር ላይ ብርሃን በማብራት በግልጽ እንዲታይ ማድረግ ነው። *የአብርሆት* ተግባር የሚከናወነው መንፈስ ቅዱስ ጸሐፊዎቹን ወይም አንባቢዎችን የተጻፈው እንዲገባቸው በሚያደርግበት ጊዜ ነው።



መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ሁሉ መንገዶች በመጠቀም የእግዚአብሔር መልእክት ወደ እኛ እንዲደርስና በልባችን ህያው እንዲሆን ያደርጋል። የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል፥ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለእኛ የተሰጠን፥ በጽሑፍ የቀረበ መልእክት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

(1). ኢሳ. 9:6-7 አንብብ። እዚህ ላይ ኢሳይያስ ስለ ኢየሱስ መወለድ አስቀድሞ ይናገራል። ይህ የምን ምሳሌ ነው?

ሀ. የአብርሆት — ሐ. የእስትንፋስ እግዚአብሔር
ለ. የመገለጥ

(2). በማቴዎስ 8 ላይ ኢየሱስ ስለፈወሰው ለምጻም ሰውና ሌሎችም ኢየሱስ ስለ ፈወሳቸው ሰዎች ስታነብ፥ እርሱ አንተንም ሊፈውስ እንደሚችል ትገነዘባለህ። እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ የሰጠህ ምንድነው?

ሀ. መገለጥ — ሐ. አብርሆት
ለ. የቃል እስትንፋስ እግዚአብሔር

(3). በባዶው ስፍራ ትክክለኛውን ቃል ሙላ።

ሀ. በ2ጢሞ. 3:16 ላይ የተጻፈው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በ ______ እስትንፋስ እግዚአብሔር ወይም በመንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን የሚደግፍ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈው ነው ማለት ነው።
ለ. 1ቆሮ. 2:13 ላይ የተጻፈው ቃል መጽሐፍ ቅዱስን በ ______ እስትንፋስ እግዚአብሔር ወይም በመንፈስ መሪነት ነው። ይህም ማለት ቃላቶቹ ራሳቸው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተገኙ ናቸው ማለት ነው።

(4). በጽሑፍ የቀረበው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ለምን እንዳስፈለገ በራስህ አባባል ግለጽ።

## የተጻፈው ቃል መጠበቅ

*ዓላማ 2 በጽሑፍ የቀረበው የእግዚአብሔርን ቃል በዘመናት ውስጥ ከስህተት ነጻ እንዲሆን የጠበቀው ምን እንደሆነ ለመግለጽ።*

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ጢሞ. 3:16 ላይ "ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው" ብሎ ለጢሞቴዎስ ይነግረዋል። ይህም በቀላል አባባል ሲገለጽ መጽሐፍ ቅዱስ በጽሑፍ ሲሰፍር በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ነበረ ማለት ነው። ጳውሎስ የተናገረው ቃል በ2ጴጥ. 1:20-21 ላይ በሐዋርያው ጴጥሮስ በይበልጥ ተብራርቶ ሰፍሯል።

"ከሁሉ አስቀድሞ ይህንን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጉመው አይደለም። ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።"

በሌላ አነጋገር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ነብያትና ሐዋርያት እግዚአብሔር እንዲጽፉ የፈለገውን ይጽፉ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥርና ምሪት ስር ነበሩ። ያስፈሩአቸው በሙሉ ያለ ስህተት ስለነበሩ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው ይጠራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ብለን የምንጠራው ታምራዊ መጽሐፍ 40 በሚያህሉ ጸሐፊዎች የተጻፈ ነው። እነዚህ ጸሐፊዎች በተለያዩ ስፍራዎች በ1600 ዓመታት የጊዜ ክፍተት ውስጥ የኖሩ ናቸው። በአገላለጻቸውና በአጻጻፍ ስልታቸው ቢለያዩም መልእክታቸው ፍጹም የሆነ አንድነትና ስምምነት ነበረው። ምክንያቱም ከጀርባ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነበረበት።

መጽሐፍ ቅዱስን ይጽፉ ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች ብዛትና የጻፉበትን ዘመን ስንመለከት ያለው አንድነት የሚያስገርም ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ እንዳመለከተው መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ዓይነት የዶክትሪን ወይም የአስተምህሮ አመለካከት፥ አንድ የሥነ ምግባር መለኪያ፥ አንድ የድነት እቅድ፥ አንድ የጊዜ ሰሌዳና አንድ አተያይ አለው ብሏል (ቲይሰን፡ 1979፣ ገጽ 67)። ይህ ሊሆን የቻለው በጻፉት ሰዎች ላይ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስለነበረ ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመለኮታዊ ምሪት ለመጻፉ ጸሐፊዎቹ ራሳቸው ያረጋገጡት ነገር ነው። በ2ሳሙ. 23:2 ላይ ዳዊት ለእስራኤል ባቀረበው የመጨረሻ መዝሙሩ ላይ የተናገረው ቃል እንደሚነግረን፦ "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ አማካኝነት ይናገራል፤ ቃሉም ከከንፈሮቼ ይወጣል" በማለት ይገልጻል። በሳሙኤል መጽሐፍ ላይ እንደሰፈረው የዳዊትን በመንፈስ ቅዱስ መመራት በማረጋገጥ ኢየሱስ በማር. 12:36 ላይ፦ "ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ" በማለት ይናገራል። እንደገናም በዕብ. 3:7 ላይ ጸሐፊው ከመዝሙር 95 በመጥቀስ፦ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚለው" የሚሉትን ቃላት አስፍሯል። እነዚህ ምሳሌዎች የሚያረጋግጡት የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ምሪት እውነት መሆኑን ሲሆን፤ የኢየሱስ ምስክርነትም በዚህ ላይ ተጨምሮ የነገሩን እውነትነት ያጠናክረዋል።

በጽሑፍ የቀረበው የእግዚአብሔር ቃል ቅጂ በየጊዜው እየተዘጋጀ ሲሄድ በጥንቃቄ ተጠብቆ፥ ከአንዱ ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ ተደርጎአል፤ ይህም እንደገና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። መንፈስ ቅዱስ በኩረ ጽሑፎቹ (ቅጅ ያልሆኑት የመጀመርያዎቹ ጽሑፎች) ሲዘጋጁ በጥንቃቄ ከመራና ከተቆጣጠረ በኋላ፣ ወደ እኛ እስኪደርስ ድረስ ቅጂዎች ሲዘጋጁ ተአማኒነት የጎደላቸው እንዲሆኑ ዝም ብሎ አልተዋቸውም።



እዚህ ላይ እንደገና አሁን ያለን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ይጠራ ዘንድ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መልዕክት በጥንቃቄ እንደጠበቀው እናምናለን። መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል እንዳልሆነ ወይም ስህተቶችን የያዘ መጽሐፍ እንደሆነ ለማረጋገጥ ብዙ ሰዎች ሞክረዋል፤ ያደረጉት ሙከራ ግን ከንቱ ሆኖ ቀርቶአል። የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ ሲጻፍ እንደነበረው ዛሬም ልንታመነው የምንችለው ነው።

(5). የእግዚአብሔር ቃል በዘመናት ከስህተት ነጻ ሆኖ የተጠበቀበትን ምክንያት በራስህ አባባል ግለጽ።

## የተጻፈው ቃል ተቀባይነት ማግኘት

*ዓላማ 3 መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነና ዛሬም መለኮታዊ ደራሲነቱን እንደሚያረጋግጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ለመስጠት።*

ኢየሱስና ሐዋርያት ብዙ ጊዜ በትምህርታቸው ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሱ ስለነበረ ተገቢውን ተቀባይነት አግኝቷል። ስለዚህም ብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነ ስይተው አውቀዋል።

(6). በስተቀኝ ያሉትን የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በስተግራ ካሉት የብሉይ ኪዳን ንባቦች ጋር የሚስማሙትን አዛምድ። ቁጥሩን በተሰጠው ባዶ ቦታ አስፍር።

| | |
|---|---|
| _____ ሀ. ማቴ. 22:43-44 | 1. ምሳ. 25:21-22 |
| _____ ለ. ሉቃ. 4:18-19 | 2. ኤር. 31:33 |
| _____ ሐ. የሐዋ. 2:17-21 | 3. ኢሳ. 61:1-2 |
| _____ መ. ሮሜ 12:20 | 4. መዝ. 110:1 |
| _____ ሠ. ገላ. 3:11 | 5. ዕን. 2:4 |
| _____ ረ. ዕብ. 10:15-16 | 6. ኢዩ. 2:28-32 |

በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሰባሰብና በጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተቀባይነትና እውቅና ሲያገኙ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ተጽጽኖ ይስተዋላል።

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ የምዕራብ በሚል ተከፍላ የነበረ ሲሆን፤ ይህም የግሪክና የላቲን ባህል ተጽዕኖ የነበረበት ነበር። በሁለቱም ወገን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን 27ቱን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስትቀበል የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንደነበር በግልጽ የሚታይ ነው። ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ለየብቻቸው የወሰኑ ሲሆን፣ ይህም የሆነው በሦላሣ ዓመታት ውስጥ ነው።

ከዚህ በኋላ በነበሩት 16 ክፍለ ዘመናት፥ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሺህ ጊዜያት ቅጅ ከመዘጋጀቱም በላይ በእያንዳንዱ ቋንቋ ተተርጉሞአል። በተሰበከበት ስፍራ ሁሉ አማኞች እንደ እግዚአብሔር ቃል ይቀበሉታል። መንፈስ ቅዱስም ሰዎች እውነቱን እንዲገባቸው በማድረግ የሰዎችን ሕይወት እንዲለወጥ ያደርጋል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1778 አንድ ቮልቴይር የተባለው የፈረንሳይ ጸሐፊ፥ በመቶ ዓመት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ተቀባይነቱን ፈጽሞ እንደሚያጣና የእርሱ ጽሑፎች ግን በሰፊው እንደሚታተሙ ተናገረ። ዛሬ በዓለም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከማንኛውም መጽሐፍ ይልቅ በሰፊው የሚዳረስ፣ በብዙ ቋንቋዎች የሚተረጎምና መልእክቱም በየስፍራው የሚሰበክ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በሚሰበክበት ስፍራ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የቃሉን እብርሆት በመስጠት ሥራውን ይሠራል። የሰዎች ልብ እንዲነካ፣ ወደ ንስሐ እንዲመጡና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል። መጸሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ለይተን የምናውቀው የሚሰሙትንና የሚቀበሉትን ሰዎች ሕይወት ስለሚለውጥ ነው።

(7). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስህ ካነበብህ በኋላ ከመግለጫው ጋር የሚሄደውን ጥቅስ ከጎኑ አስፍር።

| | | |
|---|---|---|
| 1ጴጥ. 1:22 | ማር. 4:14-20 | መዝ. 126:6 |
| መዝ. 119:89 | 1ነገ. 8:56 | ኢሳ. 40:8 |
| ዮሐ. 15:3 | መዝ. 119:103 | መዝ. 119:9 |
| ሮሜ 15:4 | ዮሐ. 17:17 | ማቴ. 5:18 |
| 1ጴጥ. 2:2 | ዘዳ. 8:3 | 1ዮሐ. 5:13 |
| ማር. 16:15-20 | 1ጴጥ. 1:25 | ኤፌ. 5:25 |

| በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተጻፈው ቃል የሚነግረን የእግዚአብሔር ቃል | |
|---|---|
| ሀ. ይጸናል | |
| ለ. ለነፍሳችን ምግብ ነው። | |
| ሐ. ያነጻናል። | |
| መ. ተስፋ ይሰጠናል። | |
| ሠ. ፍሬ ያፈራል። | |
| ረ. የታመነ ነው። | |





## ቃሉን ማዘጋጀት

*ዓላማ 4 መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ለምድራዊ አገልግሎቱ በማዘጋጀት አኳያ የነበረውን ድርሻ ለመግለጽ።*

ከሁሉም በላይ ትልቅ ትርጉም ካላቸው መግለጫዎች አንዱ በዮሐንስ 1:14 ላይ የተጻፈውና "ቃልም ሥጋ ሆነ" የሚለው ነው። አምላክ በስው ደረጃ ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርግ ዘንድ የእግዚአብሔር ወልድን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም መምጣት ይገልጻል። ቃል ሥጋ ከመሆኑ በፊት እግዚአብሔር ለብዙ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች በነብያት በኩል ተናግሮአል። አሁን ግን በልጁ በኩል ከሰው ጋር በቀጥታ ሰመገናኘት ይችላል።

መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ የእግዚአብሔር ወኪል እንደነበረ፥ በድንግል ማርያም ላይ በፈጠራ ኃይሉ በመንቀሳቀስ ሥራውን ጀመረ። መልአኩ ገብርኤል ኢየሱስ እንደሚወለድ አስቀድሞ ለመንገር ወደ ማርያም መጥቶ ስላደረገው ጉብኝት ሉቃስ ይነግረናል። መልአኩም የነገራት

> "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ የሚወለደው ቅዱሱ ሕጻን፣ የእግዚአብሔርም ልጅ ይባላል" በማለት ነበር (ሉቃ. 1:35)።

በኋላም ሉቃስ እንደሚነግረን ማርያም ዘመዷን ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ሄደች። ሰላምታም በሰጠቻት ጊዜ፣ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ስለነበር፥ በታላቅ ድምጽ አንቺ "ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፣ የማህጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው" በማለት ተናገረች።

የማቴዎስ ወንጌል በዚሁ ላይ ተጨማሪ ኃሳብ በመስጠት ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ መንፈስ ቅዱስ የተጫወተው ሚና ምን እንደሆነ ሲገልጽ፦ "የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እንዲህ ነው፦ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች" በማለት ይናገራል (ማቴ. 1:18)። በፊል. 2:6-7 ላይ የተጻፈው ቃል ደግሞ፦ "እርሱ በባህርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ" ይላል። ፍጹም አምላክ የሆነው ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሥራ ሥጋ ለብሶ በመካከላችን ኖረ (ዮሐ. 1:14)። በኋላም ስለዚሁ ዝግጅት ኢየሱስ "መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም፥ ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ" (ዕብ. 10:5) በማለት የተናገረውን እንመለከታለን።

መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ለምድራዊ አገልግሎቱ የማዘጋጀት ድርሻውን ማከናወን ቀጥሏል። በኢየሱስ እድገት ላይ መንፈስ ቅዱስ ያደረገውን ንቁ ተሳትፎ በሚገባ ባይናገርም፥ ኢየሱስ እንዲወለድ ካደረገው አንጻር መንፈስ የጀመረውን በመንከባከብ እንደቀጠለ ለመረዳት እንችላል። ሉቃስ ሲናገር፦ "ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ" ይላል።

መጥምቁ ዮሐንስ፥ በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት በልዩ መንገድ የመንፈስ ቅዱስን መገኘት በዮሐ. 1:32 ላይ ሲገልጽ፦ "መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ከሰማይ ወርዶ በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ" በማለት ይናገራል። በቁ. 33-34 ላይ ምስክርነቱን በመቀጠል ሲናገር፦ "መንፈስ ሲወርድና በርሱ ላይ ሲያርፍበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው ሲል ነግሮኛል" በማለት ይገልጻል። በኢየሱስ ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ መኖር ኢየሱስን ለአገልግሎት ለመቀባት እንደሆነ መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል።

የመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በኢየሱስ ላይ መውረድ ማንም ሊመለከተው የሚችል መገለጥ ነበር። ከዚህም ቀጥሎ ወዲያው የእግዚአብሔር ድምጽ "የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል" (ሉቃ. 3:22) የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ።

ስታንሊ ሆርቶን ይህን ሲገልጸው፦ "ርግብ ለአይሁዶች ከጨዋነት ከሰላም ምልክት በላይ ነች። ለድሆች በበግ ፈንታ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ ርግብ ነበር (ዘሌ. 5:7)። ኢየሱስ ለድሆች፣ ለችግረኞችና በዚህ ዓ ለም ላሉ ኃጢአተኞች ምትክ ሆኖ የተሰጠ የእግዚአብሔር በግ ነው" (ሮሜ 3:23)። (ሆርቶን፡ 1976፡ ገጽ 90)።

ሉቃስ በምዕራፍ 4 ላይ ኢየሱስን ለምድራዊ አገልግሎቱ ሰማዘጋጀት የመንፈስ ቅዱስን መገኘት አበክሮ ይነግረናል።

(8). በቁጥር 1 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ተግባር የሚነግረን ምንድነው?

ኢየሱስ ለ40 ቀናት ያህል በዲያብሎስ ተፈተነ። የተፈተነውም በመንፈስ በሚመራት ጊዜ እንደነበር ግልጽ ነው። እያንዳንዱ የኢየሱስ ሥልጠናና ዕድገት የተካሄደው መንፈስ ቅዱስ በትጋት በሚያደርገው እንክብካቤ ውስጥ ነበር። በምዕ. 4 ላይ እንደሚነግረን ዲያብሎስ ኢየሱስን ከፈተነውና ሊያሸንፈው ባልቻለ ጊዜ ኢየሱስ *በመንፈስ ቅዱስ ኃይል* ወደ ገሊላ ተመለሰ።

(9). መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ለአገልግሎቱ ለማዘጋጀት በንቃት ያደረገውን ተሳትፎ በተመለከተ በሉቃስ ካነበብካቸው ምንባቦች ውስጥ ሦስት ሁኔታዎች ጥቀስ።



## ቃሉን መቀባት

### ዓላማ 5 መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን አገልግሎት የቀባበትን መንገዶች ለመግለጽ።

ኢየሱስ ወደ ገሊላ ከተመለሰ ከአጭር ጊዜ በኋላ፥ ወዳደገበት ወደ ናዝሬት ተመልሶ ምኩራቡን ጎበኘ። በዚህ ጊዜ የኢሳይያስ መጽሐፍ ጥቅልል ተሰጠውና ከትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ. 61 ስለ እርሱ አገልግሎት የሚናገረውን ትንቢታዊ ምዕራፍ መርጦ እንዲህ የሚለውን አነበበ።

> "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፥ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንዳወጣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል" (ሉቃ. 4:18-19)።

(10). ኢየሱስ ቃሉን አንብቦ እንደጨረሰ ምን ተናገረ? (ቁ. 21)።

አገልግሎቱ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባቱ የተናገረውን ያረጋግጣል። በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን አስወጣ (ማቴ. 12:28)። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደገለጠው የኢየሱስ የፈውስና ነጻ የማውጣት አገልግሎት በሕይወቱ ላይ ከመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተገኘ ውጤት ነበር (የሐዋ. 10:33)። በመንፈስ ቅዱስ ቅባት አደርጋለሁ ያለውን ሁሉ ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ፈጽሞአል።

አራቱን ወንጌላት በማንበብ ኢየሱስ የፈወሳቸውን ሰዎች ዝርዝር ማግኘት ትችላለህ። እውሮች ሲበሩ፣ በሁለት አሳና በአምስት እንጀራ ከአምስት ሺህ ሰዎች በላይ ሲመግብ፣ ደንቆሮዎች ሲሰሙ፣ ሙታን ሲነሡ፣ በአጋንንት የተያዙ ነጻ ሲወጡ፤ እነዚህ ሁሉ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መገለጥን የሚያመለክቱ ናቸው።

(11). ሉቃስ 8 እና 9ን ካቃኘህ በኋላ በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች የተጠቀሱ የኢየሱስ ተግባሮችን በዝርዝር አስፍር። በኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆናቸው ማረጋገጥ ትችላለህን?

በማቴ. 12:34 ላይ "በልብ ውስጥ የሞላውን አንደበት ይናገረዋል" ሲል ኢየሱስ ተናገረ። በልብህ ያለው በቃላት ተገልጦ ይወጣል። በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለው ምን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋለህን? መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን የሚያቀርበው እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርጎ ነው። ስለዚህም የእርሱን ቃልና ተግባር አጥና። እርሱ የእግዚአብሔርን ልብ ፍጹም በሆነ መንገድ ይገልጻል።

## ቃሉን ከፍ ማድረግ

***ዓላማ 6 መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን አገልግሎት በምን መንገድ ከፍ እንዳደረገና ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዲኖረው እንዲቻል እንዴት እንዳደረገ ለመግለጽ።***

የእግዚአብሔር የፍቅር መልእክት ከስብከት፥ ከማስተማር፥ በሽተኞችን ከመፈወስ ወይም አጋንንትን ከማስወጣት በላይ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ማለት ደግሞ የእግዚአብሔር በግ ስለ ዓለም ኃጢአት መሞት ማለት ነው። መስቀሉ አሰቃቂ የሆነ የመከራና የስቃይ ጊዜ ቢሆንም፥ ኢየሱስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በስቃዩ ውስጥ አለፈበት። ምንም ኃጢአት የማያውቀው የዓለምን ኃጢአት በመሸከም ሕይወቱን ስለኃጢአት ፍጹም መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። የዕብራውያን ጸሐፊ በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ራሱን ለእግዚአብሔር እንደቀረበ ይገልጻል (ዕብ. 9:14)። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ለአይሁዶች ሲመሰክር፡- “ስለዚህ ነገር እኛ ምስክሮች ነን፤ እግዚአብሔር ለሚታዘዙት ሁሉ የሰጣቸው መንፈስ ቅዱስም ምስክር ነው” በማለት ይናገራል (የሐዋ. 5:32)።

ኢየሱስ ሥጋ በለበሰበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በፈጠራ ኃይሉ አብሮ ነበረ፤ በክርስቶስ የአገልግሎት ጊዜ ሁሉ በቅባት ኃይሉ ከእርሱ ጋር ነበር፤ በኃይሉ ያበረታው ነበር፤ በመስቀል ላይ በችግሩ በመከራውና በስቃዩ ወቅት እርሱን ለማበረታታት ከእርሱ ጋር ነበር። በሞትም ላይ ድል ለመስጠት በትንሣኤ ኃይሉ ከእርሱ ጋር ነበር። ኢየሱስን ከሞት ያስነሣ መንፈስ እርሱ ነው (ሮሜ 8:11)።

ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት በእርሱ ያመኑት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ሕብረት ሙሉ በሙሉ እንደሚታደስ አሳየ። “መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ” በማለት በደቀ መዛሙርቱም ላይ እፍ አለባቸው (ዮሐ. 20:22)።

ሰውን በመጀመሪያ ሕያው ነፍስ ያደረገው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነበር። አሁን ደግሞ ወደ አባቱ ከመመለሱ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተነጋገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ወልድ እንደገና በሰው ላይ እፍ አለበት። ይህን ያደረገው በኢየሱስ ለሚያምኑና ቃሉን ለሚታዘዙ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ እንደሚታደስ ለማመልከት ነበር። ይህ በትንሣኤው ምክንያት በኃጢአትና በሞት ላይ ድል ስለነሣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቅ በመቻሉ ይህ የአገልግሎቱ መክበር ነው። አሁን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መንፈሳዊ ሞት ድል ሊነሳ ቻለ ማለት ነው።

(12). ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ስለ እኛ ኃጢአት ሕይወቱን እንዲሰጥ ያስቻለው ምን ነበር?



(13). *መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን አገልግሎት ከፍ ያደረገውና ሰውም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕብረት ሙሉ በሙሉ እንዲታደስ ያደረገው በየትኛው መንገድ ነው?*

ሀ. በፈጠራ ኃይሉ
ለ. በቅባት ኃይሉ
ሐ. በማበረታታት ኃይሉ
መ. በትንሣኤ ኃይሉ

## ሕያው መልእክቶች

***ዓላማ 7 በተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሀያው መልእክቶች፣ የምንማር፥ ኃይል የምንቀበልና የምንገዛ ቅዱስ መሆናችንን በምሳሌዎች ለመግለጽ።***

### በመንፈስ ቅዱስ መማር

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን ድክመትና ብርታት ደህና አድርጎ ያውቅ ነበር። ብዙ ጊዜ ስለ አለማመናቸውና ትክክል ስላልሆነ አስተያየታቸው ይገስጻቸው ነበር። ሆኖም ሁልጊዜ ያስብ የነበረው እርሱ ከሄደ በኋላ ወንጌልን እንዲሰብኩ ያስብ ነበር። በምድር ላይ የወደፊት ጠቅላላ ሥራው በእነርሱ ላይ የተጣለ ነበር፤ እርሱን ለሌሎች የሚያሳውቁት እነርሱ ናቸው። ከእርሱ በማይሆንበትና በማይመራቸው ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ኃላፊነት ደቀ መዛሙርቱን እንዴት ሊያምናቸው ይችላል? መልሱ ቀላል ነው። እርሱን በመተካት ረዳታቸው ሊሆን በሚመጣው መለኮታዊው አካል ላይ ያተኮረ ነው። በእርሱ ላይ የወረደው ያው መንፈስ በእነርሱም ላይ ይመጣል። ኢየሱስ ሥራውን ከፈጸመና ከከበረ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። እርሱም እነርሱን ያስተምራቸዋል፣ ታማኝ ምስክሮችም እንዲሆኑ ኃይል ይሰጣቸዋል።

እርሱ አጽናኝ ወይም አማካሪ እንደመሆኑ የጌታን ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስተምራቸው ኢየሱስ ተናግሯል። ጌታ ያስተማራቸውን ትምህርት ማስታወስ ብቻ ሳይሆን፥ የተወሳሰቡና የተለያዩ ብዙ የሰዎችን ችግር በመፍታት ተወዳዳሪ የለውም (ዮሐ. 14:26፣ 15:26)። ከዚህም በላይ በሚማሩበት ወቅትም መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ኢየሱስ ተናግሮአል። ይህም የሚያመለክተው በእውነትና በሐሰት መንፈስ መካከል የመለየት ችሎታ እንደሚሰጣቸው ነው (ዮሐ. 16:13፣ ከ1ዮሐ. 4:1-6 ጋር በማነጻጸር ተመልከት)። ወደፊት ስለሚሆነውም ያውቁ ዘንድ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል። በአሁኑ ኃላፊነቶቻቸውና ወደፊት ስለሚያገኙት ሽልማት ሚዛናዊ ዕውቀትና የጠለቀ መረዳት ይሰጣቸዋል።

የኢየሱስ ተከታዮች የተቀበሉት ትምህርትና ለሌሎች የሚያስተላልፉት፥ ሙሴ በሲና ተራራ ላይ እንደተቀበለው በጽላት ላይ የተጻፈ አልነበረም። እንዲሁ ዝም ብሎ በተግባር የማይገለጥ “የአእምሮ እውቀት” ብቻ

አልነበረም፤ እንደ ጳውሎስ መልእክቶችም በብዕርና በቀለም የተጻፈ አይደሉም። የተቀበሉት ትምህርት በውስጣቸው ከእነርሱ ጋር የተዋሐደ በመንፈስ ቅዱስ በልባቸው ጽላት የተቀረጸ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል።

> እናንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ፣ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን በሰው ልብ ጽላት ላይ የተጻፋችሁና በእኛ የተገለገላችሁ የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ፤ (2ቆሮ. 3:3)።

መልእክቱ የመልእክተኛው ክፍል የሚሆነው በልብ ጽላት በመንፈስ ቅዱስ ሲቀረጽ ነው። ያን ጊዜ ያ ሰው ሕያው መልእክት ይሆናል።

አንተስ ሕያው መልእክት ነህን? የእግዚአብሔር መልእክት በመንፈስ ቅዱስ በልብህ ተቀርጿልን? የእርሱን መልእክት በታማኝነት ለሌሎች ታስተላልፋለህን?

(14). በስተቀኝ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በስተግራ ካሉት የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ተግባር ማብራሪያ ጋር አብሮ የሚሄደውን አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ሀ. በመንፈስ ቅዱስ የተማረ ሰው በመንፈስ መመዘንን ወይም መለየትን ያጎለብታል። | 1. 1ቆሮ. 2:13 |
| ለ. አማኙ መንፈሳዊ እውነትን በመንፈስ ስለተማረና በመንፈሳዊ ቃላት ስለሚገልጽ የሚናገረው በመንፈሳዊ ደረጃ ነው። | 2. የሐዋ. 1:8 |
| ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ተግባር የክርስቶስ የሆነውን ማስተማርና ማሳሰብ ነው። | 3. ዮሐ. 14:26 |
| መ. ስራ የሆነውን መንፈሳዊ እውቀትና ልምድ የማወቅ ችሎታ የሚመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። | 4. 1ቆሮ. 2:12 |
| ሠ. መንፈስ ቅዱስ ድካማችንንና ስህተታችንን በማስተማር፥ እንድናሸንፋቸው ይረዳናል። | 5. 1ቆሮ. 2:14 |
| ረ. መንፈስ ቅዱስ ኃላፊነታችንን በማሳሰብ ያሰንን ልምድ ለሌሎች እንድናካፍል ያደርጋል። | 6. ሮሜ 8:13 |

## በመንፈስ ኃይል መሞላት

ውጤታማ ሕያው መልእክት ለመሆን እንደ አማኝ በውስጡ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊኖረው ይገባል። ኢየሱስ ይህን በመረዳት "መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" (ማቴ. 5:16) በማለት ምክር ይሰጣል። ደግሞም ደቀ መዛሙርቱ ንስሐን ለአህዛብ ሁሉ እንዲሰብኩ ሲያዛቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈላጊ እንደሆነ ስላወቀ፣ ኃይልን ከላይ



እስኪለብሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ እንዲቆዩ ነገራቸው (ሉቃ. 24:49)። ይህም ኃይል የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀውም ስጦታውንም ሲቀበሉ ነበር (የሐዋ. 1:4-5)። መንፈስ በሚሰጠው ኃይልና ምሳሌያዊ ክርስትና ኑሮ መኖር መካከል ያለውን ግንኙነት ጳውሎስ ለይቶ በማወቁ፥ ለሮም ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ኃይል ረዳት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን እንዲቆጣጠር እንዲፈቅዱና በእርሱ ኃይል ለክርስቲያን በማይገቡ ባህሪያት ላይ ድል እንዲያደርጉ ይነግራቸዋል (ሮሜ. 8:6፣ 13)። በመንፈስ እርዳታ የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆናችንም በተጨማሪ ወደፊትም የእርሱ ወራሾች ለመሆናችን እምነት ይኖረናል (ሮሜ 8:15-17)። ይህ እውቀት በሕይወት ውስጥ ያለውን ውጣ ውረድ መንፈሱ በሚሰጠው ሰላምና ጸጥታ ለመጋፈጥ እንድንችል ያደርገናል፣ ምክንያቱም ፍርሃት በሰላምና በእረፍት ተተክቶአልና (ሮሜ 8:15)። ከአጽናኙ ርዳታ የተነሳ የሕይወት ማዕበል ቢገጥመን እንኳ ጭንቀትና ሃሳብ ላይ ሳንወድቅ ሕያው መልእክቶች በመሆን የእርሱን ሰላምና ፍቅር ማንጸባረቅ እንችላለን።

(15). በ1ጴጥ. 3:8-16 ላይ በተጻፈው መሠረት በክርስትና ሕይወት ላይ ክፉ ንግግር በሚናገሩ ሰዎች ላይ፣ ህያው መልዕክት የሆነው ክርስቲያን ምን ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል?

## በመንፈስ መገዛት

ሐዋርያው ጳውሎስ ህያው መልዕክት ስለሆናችሁ ማንም ሰው የሚያውቃችሁና የሚያነባችሁ ናችሁ ይላል (2ቆሮ. 3:2)። በልብህ መልዕክት የጻፈው መንፈስ ቅዱስ የልብህን ሐሳብና አመለካከትህን ሁሉ መቆጣጠር መቻሉ ትልቅ ነገር ነው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለዓለም መግለጥ መቻል አለብህ። ዓለም ባህሪህን እንደሚመለከትና መልዕክትንም እንደሚያዳምጥ እወቅ። ድርጊትህ ደግሞ ከቃልህ የበለጠ ከፍ ባለ ድምጽ ይናገራል።

ገላ. 5:13-26 ያለው ክፍል በመንፈስ የምንኖረው ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት በግልጽ ይናገራል። በመንፈስ ስንመራ ደስ ያሰኘንን ሁሉ እናደርግም። በክርስቶስ ያለን ነጻነት በኃጢአት የሚገኝ ደስታን ሁሉ ለመለማመድ የተሰጠ ነጻነት ሳይሆን፣ የክርስቶስን ፍቅር ለኃጢአተኛው ዓ ለም ለመግለጽ የሚያስችል ነው።

ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትልቅ ተቃርኖ የሚታይባቸውን ሁለት ዝርዝሮች ያቀርብልናል። አንዱ ዝርዝር የኃጢአተኛው ባህሪ ድርጊቶችን የሚያሳይ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ በመንፈስ የተገዛ የሚኖረውን ባህሪያት የሚዘረዝር ነው። የኃጢአተኛው ሰው ባህሪይ ለሌላው የማያስብና ራስ ወዳድነት ገንኖ የሚታይበት ሲሆን፤ በመንፈስ የተገዛው ሰወ የሚታይበት ደግሞ ሌሎችን መውደድ ወይም የፍቅር ባህሪ

ነው። የእግዚአብሔርን መልዕክት በሚገባ ለሌሎች የምናደርስበት ብቸኛ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥርና ምሪት ውስጥ ስንሆን ብቻ ነው።

(16). ከታች በተሰጠው ሰንጠረዥ የኃጢአተኛው ሰው ባህሪያትና በመንፈስ የተገዛውን ሰው ባህሪያት ዘርዝር።

| ገላትያ 5:19-23 | |
|---|---|
| የኃጢአተኛ ባህሪ ድርጊቶች | በመንፈስ የተገዛ ሰው ባህሪ |
| | |

(17). ሮሜ 8:1-8 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. በኃጢአተኛ ባህሪይ የተገዛን ስንሆን ምን ዓይነት ሰዎች እንደ ምንመስል ግለጽ።
ለ. በመንፈስ ስንገዛ ይህ ሁኔታ እንዴት ይለወጣል?

ይህን ትምህርት ለማጠቃለል ከሉቃ. 4:18-19 እንደገና አንብብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ ህያው ቃል የሆነው ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ሊያደርግ የመጣውን ይናገራል። በሕይወቱና በድርጊቱ መታዘዙን ያሳያል። ዮሐንስ በእውነት እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆንና የኢየሱስን ጌትነት ከተቀበልን፣ በእምነታችን ዓለምን እንደምናሸንፍ ይነግረናል። ይህም በእግዚአብሔር ፊት ያለንን ማንነት የሚያሳይ ነው። በመንፈስ የተገዛ ሕይወት ስንኖር በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለን። ዮሐንስ እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆን፣ ትዕዛዙን እንደምንጠብቅ ይነግረናል። ፍቅራችንን ተግባራዊ በሆነ መንገድ ገልጸን እናሳያለን። እያንዳንዳችን እግዚአብሔር እንድንሆንና እንድናደርገው የሚፈልገውን ለመሆንና ለማድረግ እንመኝ። በዚያን ጊዜ ለስሙ ክብር እናመጣለን።



## የሙከራ ፈተና

ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

1. ከዘላለም ሞት የዳንነው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና

ሀ. ስለሰማነው ቃል ለሌሎች በመንገር ነው።
ለ. የሰማነውን በማስታወስ ነው።
ሐ. በሰማነው ቃል ላይ እርምጃ በመውሰድ ነው።

2. እግዚአብሔር ቃሉ እንዲጻፍ የፈለገበት ምክንያት ቃል በቃል የሚተላለፍ መልዕክት

ሀ. ብዙ ሰዎችን መድረስ ስለሚችል ነው።
ለ. ከአንዱ ወደ አንዱ ሲተላለፍ ሊለወጥ ስለሚችል ነው።
ሐ. ሁልጊዜ የማይለወጥ ስለሆነ ነው።
መ. ይበልጥ አስተማማኝ ስለሆነ ነው።

3. ቀደም ሲል ያልታወቀውን አንድ ነገር ማሳወቅ ማለት

ሀ. እስትንፋስ እግዚአብሔር
ለ. መገለጥ
ሐ. አብርሆት
መ. ሐሳብን ማስተላለፍ

4. በሙሉ እስትንፋስ እግዚአብሔርን እናምናለን ማለት

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተጽፏል ማለት ነው።
ለ. መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች የሚጽፉት ምን እንደሆን ለእነርሱም አይታወቃቸውም ነበር።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለጻፉት ለሰዎች የሰጣቸው በሚረዱት መጠን ነው።
መ. አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተጽጽዋል ማለት ነው።

5. አማኞች በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት

ሀ. የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመንፈስ ምሪት እንደተጻፈ ያውቃሉ።
ለ. ስሜታቸውን ለእግዚአብሔር ለመግለጽ ይችላሉ።
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት ይረዳሉ።

6. መጽሐፍ ቅዱስን ከጻፉት ሰዎች ቁጥርና ከተጻፈበት ጊዜ አንጻር አስደናቂ ነበር

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት ነው።
ለ. የአፃፃፍ ስልቱ ተመሳሳይነት ነው።
ሐ. የሚገልጻቸው የባህል ለውጥ ነው።
መ. በሁሉም ጽሑፎች ውስጥ የሚታየው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።

7. በዘመናት ውስጥ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ያለ ስህተት እንዲጠበቅ ያደረገው

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር
ለ. የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ኢየሱስ የሰጠው ማረጋገጫ
ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ምሪት

8. መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለመሆኑ አንድ ዋና ማረጋገጫ

ሀ. ወደ ብዙ ቋንቋዎች መተርጎሙ
ለ. በማያምኑ ሰዎች ዘንድ እንኳ እንደ እግዚአብሔር ቃል መታወቁ
ሐ. ዛሬም በሰዎች ሕይወት አደርጋለሁ የሚለውን ስለሚያደርግ

9. በኢየሱስ ላይ መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ የታየው መቼ ነበር

ሀ. በልደቱ
ለ. በጥምቀቱ
ሐ. በፈተናው
መ. በትንሣኤው

10. ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባቱ የተናገረው የተረጋገጠው

ሀ. በአገልግሎቱ
ለ. በሞቱ
ሐ. በትንሣኤው
መ. ሁሉም መልስ ነው
ሠ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

11. ሕያው መልእክት ልንሆን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ

ሀ. በመንፈስ በመገዛት
ለ. በራሳችን መንፈስ በመገዛት
ሐ. ሰባኪዎች ወይም ወንጌላውያን በመሆን



# የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

9. በልደቱ፣ በጥምቀቱና በፈተናው

1. ለ. መገለጥ እስትንፋስ እግዚአብሔር ብለህ ብትመልስ ልክ ነው። ወደፊት የሚከናወን እውነት በመገለጥ ይሰጣል፤ እንዲሁም በመንፈስ በመመራት ደግሞ ነቢይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን መልዕክት በትክክል ማስፈር ይችላል።

10. ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

2. ሐ

11. ከክፉ መናፍስ የተፈወሰችው ሴት፥ ምሳሌዎችና የሰጠው ትምህርት፣ ማዕበሉን ጸጥ ማድረግ፣ በዲያብሉስ የተያዘ ሰው መፈታት፣ የታመመች ሴት መፈወስ፣ አንድ ሴት ልጅ ከሞት ማንሳት፣ ወንጌል እንዲሰበኩና የታመሙ ሰዎችን እንዲፈውሱ አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መላክ፣ አምስት ሺህ ሰዎች መመገብ፣ የኢየሱስ መልክ መለወጥ፣ በርኩስ መንፈስ የተያዘ ልጅ መፈወስ።

3. ሀ. ሙሉ
ለ. ቃል

12. የመንፈስ ቅዱስ ብርታትና ኃይል መስጠት

4. የአንተ መልስ - እኔ የምለው በቃል ከተላለፈ መልእክት ይልቅ የተጻፈ መልእክት ይበልጥ አስተማማኝ ነው። ከዚህም በላይ ደግሞ የተጻፈ መልእክት የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉም እንዲደርስ ያደርጋል። ቃሉም ፍጹምና የማይለወጥ ነው።

13. መ

5. ቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፉ ጊዜ የተቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ፥ በቅጅ መልክ ከአንዱ ትውልድ ወደሚቀጥለው ሲተላለፉም ጠብቆአቸዋል።

14. ሀ. 5
ለ. 1
ሐ. 3
መ. 4
ሠ. 6
ረ. 2

6. ሀ. 4
ለ. 3
ሐ. 6
መ. 1
ሠ. 5
ረ. 2

15. ጴጥሮስ እንዳለው ክፉ ተናጋሪዎች በተግባራቸው ያፍራሉ። ይህ የክርስትና ባህርይ ወንጌልን ኃይል ባለው መንገድ በተግባር እንዲታይ ከማድረጉም በላይ ብዙ ሕይወት እንዲለውጥ ምክንያት ይሆናል።

7. ሀ. መዝ. 119:89፣ ኢሳ. 40:8፣ ማቴ. 5:18፣ 1ጴጥ. 1:25
ለ. ዘዳ. 8:3፣ መዝ. 119:103፣ 1ጴጥ. 2:2
ሐ. መዝ. 119:9፣ ዮሐ. 15:13፣ ዮሐ. 17:17፣ 1ጴጥ. 1:22፣ ኤፌ. 5:25-26
መ. ሮሜ 15:4፣ 1ዮሐ. 5:13
ሠ. መዝ. 126:6፣ ማር. 4:14-20፣ ማር. 16:15-20
ረ. 1ነገ. 8:56 (ተጨማሪ ማቴ. 5:18)

16. ክፍል ሀ

ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅንአት፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነትና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው።

ክፍል ለ

ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ደግነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው።

8. ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር፥ ከዚያም መንፈስ ወደ በረሃ እንዲሄድ አነሣሣው።

17. ሀ. ሃሳባችን ሁሉ ኃጢአታዊ ባህሪያችንን ማስደሰት ይሆናል።

ለ. ሃሳባችን ሁሉ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይሆናል።



# 6
## ትምህርት

# ዳግም ልደት የሚያስገኘው መንፈስ

በጣም ትንሽ ሕፃን ተመልክተህ የመወለድን ነገር በማሰብ ተዓምር ሆኖብህ ተደንቀህ ታውቃለህ? ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ፍጡር በዓይን በማይታይ በሁለት ሴል ውህደት ተጀምሮ ለማደግ፣ ለመብሰልና ሃላፊነት የሚሰማው ጎልማሳ ለመሆን የሚያስችል ነገር በውስጡ አለ። ከሁሉ ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ እነዚህ ሁለት ሴሎች በአንድነት ሲዋሃዱና አዲስ ሕይወት ሲፈጠር፣ ህጻኑ የእናቱን ቀይ ጸጉር፣ የአባቱን ቅርጽ፣ የወንድ አያቱን ጸባይና ዝንባሌ፣ የሴት አያቱን ዓይነት ጥርስ፣ እንዲሁም የአጎቱን ሳቂታነት ይዞ ለመውጣት የሚያስችለውን ነገር ሁሉ ማግኘቱ ነው። ቢሆንም ልጁ አንድ ግለሰብ እንዲሆን የሚያደርገውን የራሱ የሆነ ባህርይ ስለሚኖረው፣ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተለየና በራሱ ምርጫ ለሚያደርገው ነገር ለእግዚአብሔር ተጠያቂ ይሆናል።

እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ነገር ለአካላዊ እድገታችን ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ልደታችንም ጭምር ነው። ይህም የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስለ ኃጢአታችን እንድንወቀስና ንስሃ እንድንገባ በማድረግ፥ በውስጣችን ለመኖር ይመጣል፤ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆንም ያደርገናል። ይህም የሚሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስንተባበር ሲሆን፥ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት በማግኘት፣ ሰማያዊ አባታችን ያዘጋጀልንን ርስት ከእርሱ ጋር አብረን እንወርሳለን። መንፈሳዊ ልደት ከዚህ ጋር አብሮ ይዞት የሚመጣው የእርሱን በሕርያት በውስጣችን የማጠናከር ችሎታና እርሱን ወደ መምሰል መለወጥ ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ዳግም እንድንወለድ የሚያደርገን መንፈስ ቅዱስ እንደሆነና በእርሱም በኩል እግዚአብሔር እድንሆን የሚፈልገውን ሁሉ ኃይል እንደምናገኝ እንመለከታለን። የዘላለም ሕይወትን የሚሰጠንና ከአዳኛችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች የሚያደርገን የሕይወት መንፈስ እርሱ ነው።

7. ሀ. መዝ. 119:89፣ ኢሳ. 40:8፣ ማቴ. 5:18፣ 1ጴጥ. 1:25
   ለ. ዘዳ. 8:3፣ መዝ. 119:103፣ 1ጴጥ. 2:2
   ሐ. መዝ. 119:9፣ ዮሐ. 15:13፣ ዮሐ. 17:17፣ 1ጴጥ. 1:22፣ ኤፌ. 5:25-26
   መ. ሮሜ 15:4፣ 1ዮሐ. 5:13
   ሠ. መዝ. 126:6፣ ማር. 4:14-20፣ ማር. 16:15-20
   ረ. 1ነገ. 8:56 (ተጨማሪ ማቴ. 5:18)

16. ክፍል ሀ

    ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅንአት፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነትና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው።

    ክፍል ለ

    ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ደግነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው።

8. ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር፥ ከዚያም መንፈስ ወደ በረሃ እንዲሄድ አነሣሣው።

17. ሀ. ሃሳባችን ሁሉ ኃጢአታዊ ባህሪያችንን ማስደሰት ይሆናል።

    ለ. ሃሳባችን ሁሉ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይሆናል።



# 6
## ትምህርት

# ዳግም ልደት የሚያስገኘው መንፈስ

በጣም ትንሽ ሕፃን ተመልክተህ የመወለድን ነገር በማሰብ ተዓምር ሆኖብህ ተደንቀህ ታውቃለህ? ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ፍጡር በዓይን በማይታይ በሁለት ሴል ውህደት ተጀምሮ ለማደግ፣ ለመብሰልና ሃላፊነት የሚሰማው ጎልማሳ ለመሆን የሚያስችል ነገር በውስጡ አለ። ከሁለ ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ እነዚህ ሁለት ሴሎች በአንድነት ሲዋሃዱና አዲስ ሕይወት ሲፈጠር፣ ህጻኑ የእናቱን ቀይ ጸጉር፣ የአባቱን ቅርጽ፣ የወንድ አያቱን ጸባይና ዝንባሌ፣ የሴት አያቱን ዓይነት ጥርስ፣ እንዲሁም የአጎቱን ሳቂታነት ይዞ ለመውጣት የሚያስችለውን ነገር ሁሉ ማግኘቱ ነው። ቢሆንም ልጁ አንድ ግለሰብ እንዲሆን የሚያደርገውን የራሱ የሆነ ባህርይ ስለሚኖረው፣ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተለየና በራሱ ምርጫ ለሚያደርገው ነገር ለእግዚአብሔር ተጠያቂ ይሆናል።

እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ነገር ለአካላዊ እድገታችን ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ልደታችንም ጭምር ነው። ይህም የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስለ ኃጢአታችን እንድንወቀስና ንስሃ እንድንገባ በማድረግ፥ በውስጣችን ለመኖር ይመጣል፤ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆንንም ያደርገናል። ይህም የሚሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስንተባበር ሲሆን፥ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት በማግኘት፣ ሰማያዊ አባታችን ያዘጋጀልንን ርስት ከእርሱ ጋር አብረን እንወርሳለን። መንፈሳዊ ልደት ከዚህ ጋር አብሮ ይዞት የሚመጣው የእርሱን በሕርያት በውስጣችን የማጠናከር ችሎታና እርሱን ወደ መምሰል መለወጥ ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ዳግም እንድንወለድ የሚያደርገን መንፈስ ቅዱስ እንደሆነና በእርሱም በኩል እግዚአብሔር እድንሆን የሚፈልገውን ሁሉ ኃይል እንደምናገኝ እንመለከታለን። የዘላለም ሕይወትን የሚሰጠንና ከአዳኛችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች የሚያደርገን የሕይወት መንፈስ እርሱ ነው።

### የክፍለ ትምህትቱ አከፋፈል

- የሚወቅስ መንፈስ
- የሕይወት መንፈስ
- የልጅነት መንፈስ

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፡-

- ስለኃጢአት የመውቀስና ወደ ንስሃ የማምጣትን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መግለጽ።

- መንፈስ ቅዱስ ንስሃ ለሚገባ ኃጢአተኛ ሕይወት ሲሰጥና በውስጡ ሲኖር የሚኖረውን ውጤት መግለጽ።

- የቅድስና መንፈስና የልጅነት መንፈስ የተባሉትን መግለጽ።

- በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት የማስገኘት ኃይል ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የተጨመሩ ሰዎች የሚያገኙትን በረከትና ኃላፊነት ለይቶ ማወቅ

---

### የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለክፍለ ትምህርቱ ለመዘጋጀት እንዲረዳህ በትምህርት 3 ውስጥ የሚገኙትንና የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍሎች አንብባቸው። ሁለቱ ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ እንደሚወቅስና ዳግም ልደት እንደሚሰጥ የሚናገሩ ናቸው።

2. በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጡትን የመፅሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች አንብብ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹንም በሙሉ መልስ።

3. ክፍለ ትምህርቱ አጥንተህ ስትጨርስ የሙከራ ፈተናውን በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፍ መጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከለው ካለ አስተካክል።

---



### የትምህርቱ ዝርዝር

## የሚወቅስ መንፈስ

## ስለ ኃጢአት መውቀስ

***ዓላማ 1 ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ የመንፈስ ቅዱስን ስለ ኃጢአት የመውቀስ ኃይል ውጤቶች መግለጽ።***

በሦስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም የተላከው ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅ እና ስለ ፍርድ ለመውቀስና ለማሳመን እንደሆነ ተመልክተናል። ለዚህ ክፍለ ትምህርት መነሻ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት ይወቅሳል፣ ዳግም ልደትን ይሰጣል የሚለውንና በትምህርት 3 ውስጥ የሚገኘውን ክፍል ካላነበብክ አሁኑኑ ደግመህ አንብብ።

አንድን ኃጢአተኛ እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገው ማሳመን የሚችል መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ዳዊት መንፈስ ቅዱስ በወቀሰው ጊዜ በመዝ. 51፥3-4 ላይ "እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፤ ኃጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው። በውሳኔህ ትክክል፣ በምትሰጠው ፍርድም ንጹህ ትሆን ዘንድ፣ አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ፤ በፊትህም ክፉ ነገር አደረግሁ።" በማለት ይናገራል።

መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ለኃጢአተኞች ለመናገር የሚጠቀመው የሰው ምስክሮችን ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ምሳሌዎች ለመጥቀስ ቢያስፈልግ፡-

*1. **ጴጥሮስ፡-*** በበዓለ ሃምሳ ዕለት ኢየሱስ በሰጠው ተስፋ መሠረት ታላቁ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተከናወነ። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ተሰብስቦ ለነበረው ሕዝብ ወንጌልን ሰበከ። የሰበከውም ስብከት በሐዋ. 2፥14-36 ላይ ተጽፎ ይገኛል።

ሕዝቡም የጴጥሮስ ስብከት በሰሙ ጊዜ "ልባቸው በኃዘን ተነካ" (ቁ. 37)። ጴጥሮስ የሰበከው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ቅባት ነበር። የመንፈስ ቅዱስ የማሳመን ኃይል ነበር ልባቸው እንዲነካና "ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?" ብለው እንዲጠይቁ ያደረገው።

*2. **ጳውሎስ፡-*** ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ኃይል ትንቢት በሚናገሩበት ወቅት የማያምን ሰው ሲመጣ ምን እንደሚሆን ይናገራቸዋል። "ነገር ግን ሁሉም ትንቢት በመናገር ላይ ሳሉ፣ እንግዳ ወይም የማያምን ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል፤ በሁሉ ይመረመራል፤ በልቡም የተሰወረው ነገር ይገለጣል፤ እንዲሁም፣

"እግዚአብሔር በመካከላችሁ ነው" በማለት በግንባሩ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።" በማለት ይናገራል። 1ቆሮ. 14፥24-25)

*3. እስጢፋኖስ፦* ከመጀመርያዎቹ ከዲያቆናት አንዱ ይሆን ዘንድ በሐዋርያት የተመረጠው እስጢፋኖስ ሲሆን፣ "በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነበር" (የሐዋ. 6፥5)። እስጢፋኖስ በሕዝቡ መካከል በዙ ታላቅና አስገራሚ ተአምራቶችን በማድረጉ የአይሁድ መሪዎች ይቃወሙት ጀመር። በሐዋ. 6፥9-10 ላይ በሰፈረው ቃል መሠረት፣ እነዚህ ሰዎች እስጢፋኖስን ይከራከሩት እንደነበርና፣ እስጢፋኖስ ይናገርበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ መቋቋም እንዳልቻሉ ይናገራል።

በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 7 ላይ እስጢፋኖስ ለአይሁድ ሸንጎ አባሎች የሰበከውን መልእክት እናገኛለን። በመልእክቱ መጨረሻ ላይ፦ "እናንተ ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፣ አንገተ ደንዳናዎች! ልክ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ" በማለት የተናገረው እንደሚገልጠው የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስና የማሳመን ኃይል ብርቱና ጠንካራ ነበር። (የሐዋ. 7፥51)።

(1). በሐዋ. 2፥41 ለጴጥሮስ መልእክት የተሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

(2). ለመንፈስ ቅዱስ የመውቀስና የማሳመን ኃይል ጴጥሮስን የሰሙት ሁሉ በንሰሃ ተገቢውን ምላሽ ሰጡን?

(3). በሐዋ. 7፥54-60 ለእስጢፋኖስ ስብከት ምላሹ ምን ነበር?

ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳ በጣም የተማረ ሰው ቢሆንም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ አላቸው "ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም፤ ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው።" (1ቆሮ. 2፥4-5) በማለትይናገራል። ጳውሎስ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ከልምምዱ ያገኘው ትምህርት በመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ ኃይል መደገፍ ነበር።

## ወደ ንስሐ ማምጣት

***ዓላማ 2 በተሰጠው ምሳሌዎች መሰረት፤ የንስሐ ትርጉምና ሰዎችን ወደ ንስሐ በማምጣት የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ምን እንደሆነ ለመግለጽ።***

አንድ ኃጢአተኛ እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገው እንዲያምን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ሲሆን፥ ኃጢአተኛውን ግን በግዴታ ንስሐ እንዲገባ አያስገድድም። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኛውን ሰው ስለ ኃጢአቱ በሚወቅስው ጊዜ የእምነት እርምጃን ወዲያው መወሰድ



ይኖርበታል። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ስለዚሁ ሲገልጽ፦ "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ወደ ድነት ለሚያደርስ ንስሐ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበትም" ይላል (2ቆሮ. 7፥10)።

በመዝ. 51፥3-4 ላይ መዝሙረኛው ዳዊት የገለጸው የዚሁ ዓይነት ኃዘን ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ኃጢአተኛው እግዚአብሔር እንደሚያየው ራሱን እንዲያይ ያደርገዋል። እግዚአብሔርም እንደ፡ት እንደሚያየው የሚገልጥለት መንፈስ ቅዱስ ነው (1ቆሮ. 2፥11)።

**ንስሐ ምንድነው?**

ንስሐ ማለት አንድ ሰው ኃጢአትን ለይቶ የሚያውቅበት፣ ከኃጢአቱም የሚመለስበት፣ ለእግዚአብሔርም የሚናዘዝበትና ፈጽሞ ኃጢአቱን የሚተውበት ነው። ንስሐ መግባት፥ አእምሮችንን፣ ስሜታችንን፣ እንደዚሁም ፈቃዳችንን ሁሉ የሚነካ ነው። ንሰሐ መግባት ማለት ለኃጢአት ያለንን ሐሳብ፣ አስተያየትና ባህሪያችንን መቀየር ማለት ነው። ያደረግኸውን ስህተት ማወቅና የእግዚአብሔር ስም በዚህ ምክንያት እንዲነቀፍ በማድረግህ እንደ እርሱ ፈቃድ ማዘንንና መጸጸትን ጭምር የሚያካትት ነው። ስለ ኃጢአት መጸጸት ወይም ኃጢአትን ላለማድረግ ቃል መግባት ብቻ ሳይሆን፥ በጻድቁ እግዚአብሔር ፊት በራስ ላይ መፍረድ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአታችንን ማወቅና ከኃጢአታችን መመለስ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም።

1. ***የሐሳብ ለውጥ፦*** ይህ የሐሳብ ለውጥ የሚመጣው አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የሆነ አቋም እንደሌለው ***ለይቶ በማወቅ*** ነው። በተሳሳተ መንገድ ላይ እየተጓዘ መሆኑንና ይህም ወደ ሞት የሚያደርሰው እንደሆነ ሲያውቅ ሐሳቡን ይለውጣል። ይህን አደገኛ ሁኔታ በመመልከት የጠፋው ልጅ ያደረገውን ነገር በተገነዘበ ጊዜ፣ ተነሥቶ ወደ አባቱ ለመሔድ ወሰነ (ሉቃ. 15፥17-19) ንስሐ መግባት የሚያካትተው ሌላው አስፈላጊ ነገር፣ ለሰው የኃጢአት ችግሮ መፍትሔው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ለይቶ ማወቅ ነው። ከኃጢአት የበደል ስሜት ነፃነት ልናገኝ የምንችለው በእምነት በኩል በክርስቶስ ብቻ ነው።

*2. የስሜት ለውጥ፦* በኃጢአት ውስጥ መሆኑን ማወቅ ኃጢአተኛው እንዲያዝን ያደርገዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 7፥9 ላይ ስለዚሁ ሲናገር፦ "አሁን ግን ደስ ብሎኛል፣ ደስታዬም ስላዘናችሁ ሳይሆን፣ ሐዘናችሁ ንስሐ ለመግባት ስላበቃችሁ ነው፤ ምክንያቱም ሐዘናችሁ እንደ እግዘኢአብሔር ፈቃድ እንጂ ከእኛ የተነሳ ምንም አልተጎዳችሁም" ይላል። ዳዊት በመዝ. 38፥18 ላይ የተሰማውን ሲገልጽ፦ "በደሌን እናዘዛለሁ፣ ኃጢአቴም አውካኛለች" ይላል። አንድ ሰው ከሚሰማውና ከሚገልጸው ሐዘን ባሻገር አስፈላጊው ነገር ኃጢአትን መናዘዝና ለመተው መወሰን ነው። ኃጢአትን ከመናዘዝና ከመተው በስተቀር የሐዘንና የጸጸት ብዛት ለብቻው ፋይዳ የለውም።

3. የባህርይ ለውጥ፦ ኃጢአትን ለይቶ ማወቅና መናዘዝ አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን ኃጢአትን በፍጹም በመተው ከኃጢአት መመለስም የዚያኑ ያህል አስፈላጊ ነው። ለጠፋው ልጅ፣ ከባዱን መከራውን ለይቶ ማወቁና ስለዚሁ የተሰማው መጥፎ ስሜት በቂ አልነበረም። የንስሐው እውነተኛነት የተረጋገጠው በራሱ ፈቃድ ተነስቶ ወደ አባቱ በሄደ ጊዜ ነበር (ሉቃ. 15፥20)። ንስሐ መግባት እያንዳንዱን የሕይወታችን ክፍል የሚዳስስ ነው። ኃጢአትን ለይቶ ማወቅና ስላለፈው ኃጢአታዊ ድርጊት ማዘንና መጸጸት ብቻ ሳይሆን፥ ለወደፊቱም ደግሞ የእኛን ውሳኔ የሚጠይቅ ነው። ለእግዚአብሔር በመታዘዝና ከእርሱ ጋር ሕብረት በማድረግ በእርሱ መንገድ ለመሔድ፣ የራሳችንን መንገድ እርግፍ አድርገን መተው አለብን።

## ንስሐ መግባት ያለበት ማን ነው?

የንስሐ ጥሪ ሰውን ሁሉ የሚመለከት ነው። "ቀደም ሲል እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን አለማወቅ በትዕግሥት ዐልፎአል፤ *አሁን ግን በየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ ያዛል፤* ይህ ጥሪ እያንዳንዱን ሰው ይመለከታል። በክርስቶስ ያላመኑ ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲቀበሉና ልጆቹ እንዲሆኑ ጥሪ ተደርጎላቸዋል" (ዮሐ. 3፥15-17፣ ቲቶ 2፥11) የንስሐ መልዕክት፥ በክርስቶስ ላመኑትና እርሱን ለሚከተሉትም ደግሞ ሁሉ ነው። አማኞች ከተለወጡና ከኃጢአት ቀንበር ነጻ ከወጡ በኋላ፣ መንፈሳዊ ኃላፊነታቸውን የሚዘነጉበት፥ ወይም ለመንፈሳዊ እድገታቸው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሄድ የሚያቅታቸው ወይም ኃጢአት የሚፈጽሙበት ጊዜ አለ። ለኃጢአታቸውና ለውድቀታቸው መፍትሔ የሚሆነው ንስሐ ነው። (ሮሜ 8፥5-11ን ከኤፌ. 4፥17-32 ጋር አወዳድር) በ1ዮሐ. 1፥9 ላይ የሚገኘውና እግዚአብሔር የሰጠው የይቅርታ ተስፋ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተው አማኞችን ነው። ሆኖም ንስሐ ለመግባት ለሚፈልግም ሁሉ ይሠራል።

በራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3 ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አምስቱ ንስሐ እንደገቡት ጥሪ ተደርጎላቸዋል። እነዚህ አምስቱ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ንስሐ ካልገቡ ምስክርነታቸውን እንደሚያጡ፥ እንሚፈረድባቸው፥ መከራ እንደሚያገኛቸው፥ ወይም እንደሚወገዱ ተነግሮአቸዋል። በምዕራፍ 2 ና 3 ሰባት ጊዜ "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!" በማለት ተደጋግሞ ተነግሯል። ይህም በተደጋጋሚ መነገሩ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር መልዕክቱን በጥንቃቄ መስማትና ማስተዋል እንዳለብን አስፈላጊነቱን ለማጠንከር ነው።

(4). ከታች የተገለጹትን፣ ንስሐ ያስፈለገበትን ምክንያቶች ከ1 እስከ 5 ከተሰጡት አብያተ ክርስቲያኖችና የንስሐ መልዕክቶች ጋር አዛምድ። (ይህንን ለማድረግ ይረዳህ ዘንድ ራዕይ 2 እና 3 ተመልከት)።



______ *ሀ. ኤልዛቤልን ችላ ብለሃታል፤ እርስዋ አገልጋዮቼ እንዲሴስኑ... በትምህርትዋ ታስታቸዋለች።*

______ *ለ. ሞተሃል. . .ሥራህ በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ ስላገኘሁትም።*

______ *ሐ. የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል።*

______ *መ. ለብ ያልህ ብቻ እንጂ ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ ስላላሆንህ...*

______ *ሠ. የሐሰት አስተማሪዎችን ተከትለሃል*

1. ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን "ንስሐ ግባ፣ በመጀመሪያ ታደርገው የነበረውን ሥራህን አድርግ።"

2. ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን "ስለዚህ ንስሐ ግባ! ... አለዚያ ቶሎ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም ሰይፍ እወጋቸዋለሁ።"

3. ለትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን "የሚያመነዝሩት ንስሐ ካልገቡ ብርቱ ስቃይ አመጣባቸዋለሁ።"

4. ለሰርዴስ ቤተክርስቲያን "ንቃ! ... ባትነቃ ግን እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ"

5. የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን "እኔ የምወዳቸውን እገሥጻለሁ፤ እቀጣለሁም። ስለዚህ ትጋ፤ ንስሐም ግባ።"

ንስሐ መግባት ለአንድ ወይም ለብዙ ኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል (ማቴ. 18፥21-22)። እግዚአብሔር ኃጢአትን ችላ ብሎ ማለፍ አይችልም። የእግዚአብሔር ይቅርታ የሚለካው በተሠራው ኃጢአት ብዛትና ዓይነት ሳይሆን፣ በንስሐው እውነተኛነት ነው። እውነተኛ ንስሐ ኃጢአትን በተመለከተ የሚታይ የስሜት፣ የአሳብና የባህሪ ለውጥ ነው። ንስሐ የመግቢያው ጊዜ አሁን ነው። እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኞች ስለመታዘዛቸው ንስሐ እንዲገቡና ሕይወታቸውን ለእርሱ እንዲያስረክቡ ኃጢአተኞችን ያለማቋረጥ እየወቀሰ ነው። አማኞችም ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠር እንዲፈቅዱለትና ከእርሱ ጋር እንዲራመዱ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው በሥራ ላይ ነው። (ገላ. 5፥16-18፣ 25)።

ንስሐን እምቢ ማለት የመንፈስ ቅዱስን ልመና አለመቀበል ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው እስጢፋኖስ ላቀረበው መልእክት ያስገኘው ውጤት ተቃውሞና ቁጣ ነበር። ይህም የሚያሳየው ሕይወታቸውን በሙሉ ኃይማኖትን በመከተል ያሳለፉ ሰዎችም ቢሆኑ መንፈስ ቅዱስን ሊቃወሙ እንደሚችሉ ነው (የሐዋ. 7፥51)። በዕብ. 10፥26-31፣ በራእ. 3፥16፣19 እና በምሳሌ 29፥1 ደግመን ብንመለከት እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ሰውን እንደሚወድና ሰው ከጥፋቱ

እንዲታረምና ክርስቶስን ወደ መምሰል እንዲመጣ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ተግሳጹን በመቃወም ሆን ብሎ በኃጢአቱ ለመቀጠል ለፈለገ ሰው ሚጠብቀው የመጨረሻ ነገር አስፈሪ የሆነው የመጨረሻ ፍርድ ነው።

ለዚህ እንደምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል፣ አንድ ሰው በስልክ ደጋግሞ ቢደውልልህና አንተም ለስልኩ ጥሪ ምላሽ ባለመስጠት ችላ ብለህ ትተኸዋል እንበል። ሰውየው በመጨረሻ መደወሉን በማቆም አንተን ለማነጋገር የሚያደርገውን ጥረት ይተዋል። በተመሳሳይ መንገድ መንፈስ ቅዱስን ከጊዜ ወደ ጊዜ የምትቃወም ከሆነ፥ በመጨረሻ ለልብህ ለመናገርና አንተን ወደ ንስሐ ለመጥራት የሚያደርገውን ሙከራ ያቆማል። ያልተናዘዝካቸው ኃጢአቶች ካሉ ንስሐ በመግባት ሙሉ ይቅርታ የምትቀበልበት ጊዜው አሁን ነው።

(5). ስለ ንስሐና መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ወደ ንስሐ ለማምጣት የሚያደርገውን በተመለከተ፣ እውነት የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ንስሐ ስላደረግከው ነገር የሚሰማህ የጥፋተኛነት ስሜት ነው።
ለ. ኃጢአተኛውን ወደ ንስሐ ለማምጣት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ያስገኝ ዘንድ፣ እግዚአብሔር እንደሚያየው አድርጎ ኃጢአተኛው ራሱን እንዲያይ ማድረግ ነው።
ሐ. ንስኃ መግባት ማለት የኃጢአተኛው ሃሳቡን፣ ስሜቱንና ባህርዩን መለወጥ ማለት ነው።
መ. ከድነት በኋላ ንስሐ መግባት አስፈላጊ አይደለም።
ሠ. በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት የተነገረው የመንፈስ ቅዱስ መልዕክት በቅድሚያ ያተኮረው በማያምኑ ሰዎች ላይ ነው።
ረ. የእግዚአብሔር ይቅርታ የተመሠረተው በንስሐው እውነተኛነት ላይ ነው።
ሰ. በመጨረሻ መናገሩን እስከሚተው ድረስ የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ መቃወም የሚቻል ነው።

## የሕይወት መንፈስ

## አዲስ ልደት መስጠት

*ዓላማ 3 በተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ ለኃጢአተኛው ሕይወት በሚሰጥበት ጊዜ ምን እንደሚሆን መግለጽ።*

በአንድ ምሽት ኒቆዲሞስ ኢየሱስን ለማግኘት በመጣ ጊዜ፣ መወለድ እደሚያስፈልገው ነገረው (ዮሐ. 3፥1-12)። ኒቆዲሞስ ወዲያው ስለ ተፈጥሮአዊ ልደቱ በማሰብ "ሰው ካረጀ በኋላ እንዴት እንደገና ሊወለድ



ይችላል?" በማለት ጠየቀ (ቁ. 4)። ኢየሱስም ስለ መንፈሳዊ ልደት እንደሚናገር ሲገልጽለት "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው" በማለት የተናገረው ስለ መንፈሳዊ ልደት እንደሆነ በቁጥር 6 ላይ ለኒቆዲሞስ ገለጸለት።

የመጀመሪያው ሰው አዳም፥ በመጀመሪያ መንፈሳዊ ሕይወት ተሰጥቶት ነበር። ዳሩ ግን ኃጢአት በመስራቱ ይህን መንፈሳዊ ሕይወት አጣ። በአዳም ኃጢአት ምክንያት፣ ጳውሎስ እንደነገረን ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ ከእርሱ ኃጢአት የተነሳ ብቻ ሳይሆን፥ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች በመሆናቸው ሞት ለሰው ሁሉ እንደደረሰ በሮሜ 5፥12 ላይ ይነገረናል።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ፦ "በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ" በማለት ይናገራል (ኤፌ. 2፥1)። ከዚያም በመቀጠል በቁ. 8 ላይ "የዳናችሁት በእምነት በጸጋው ነው" ይላል። እያንዳንዱ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት እንደገና መወለድ የሚገባው ኃጢአተኞች ሁሉ መንፈሳዊ ሞት የሞቱ ስለሆነ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኛውን ወደ ንስሐ የሚያመጣው የእግዚአብሔርን የይቅርታ ጸጋ ኃጢአተኛው እንደሚያስፈልገው በማሳየት እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ኃጢአተኛው ኃጢአቱን በመናዘዝና የእግዚአብሔርን ድነት በመቀበል ተገቢውን ምላሽ ሲሰጥ፥ የሕይወት መንፈስ፥ አዲስ ሕይወትን፥ መንፈሳዊ ሕይወትን ወደ እርሱ ያመጣል። ኃጢአተኛው *እንደገና ተወለደ* እንላለን፥ መንፈሳዊ ልደትን ተለማመደ ማለት ነው። እንዴት አስገራሚ ለውጥ ነው! አሁን እርሱ በውስጡ የእግዚአብሔር መንፈስ አለው፤ ከኃጢአት ከበደል ሽክም ነፃ ነው።

ክርስቲያን ለመሆን ሌላ መንገድ የለም። ከእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ በስተቀር ሌላው የሥጋ ጥረት ነው። ኢየሱስም ሥጋ ሊሰጥ የሚችለው ሥጋዊ ልደትን ብቻ እንደሆነ ተናግሯል። ያለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታ መንፈሳዊ ለውጥ ለማግኘት የማይቻል ነው።

(6). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ ንስሐ ለሚገባው ኃጢአተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በመስጠት በኩል የሚገልጹትን የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ግለጽ።

ሀ. ዮሐ. 6፥63
ለ. ሮሜ 8፥2
ሐ. ገላ. 4፥4-6
መ. ገላ. 5፥16-18፣25

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይገልጻሉ። እኛ ማድረግ ያለብን መተባበርና ይህን የሕይወት ስጦታ መቀበል ነው።

(7). በሮሜ 8፥1-11 ላይ የጻፈውን በማንበብ ክፍቱን ቦታ ሙላ።

ሀ. ከኃጢአትና ከሞት ሕግ በመንፈስ ቅዱስ ነጻ ከወጣህ በኋላ የምትኖረው በኃጢአት ባሕርይ ሳይሆን እንደ __________ ፈቃድ ነው።
ለ. እንደመንፈስ ፈቃድ በምትኖርበት ጊዜ ሐሳብህ የሚያተኩረው በመንፈስ __________ ላይ ነው።
ሐ. እግዚአብሔርን ለማስደሰት ብቸው መንገድ በ _______ ቁጥጥር ስር መሆን ነው።
መ. ማንኛውም ሰው የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው የ _________ አይደለም።

ከእግዚአብሔር የተወለደ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን መንፈስ ይቀበላል። "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል" (ሮሜ. 8፥16) ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔር ያሰበው ይህ ነው። ሰው የእርሱ መቅደስ፥ የእርሱ መኖርያ ስፍራ እንዲሆን ይፈልጋል። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለዚህ ሲያሳስብ "እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን?" (1ቆሮ. 3፥16) በማለት ይጠይቃል።

በሮሜ 8፥9 መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ክርስቶስን ስለሚወክል የክርስቶስ መንፈስ በመባል ነው የተጠቀሰው፥ ይህም ትክክል ነው። በክርስቶስ ፈንታ ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር አብ የተሰጠን እርሱ ነው። ጳውሎስ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን "የልጁ መንፈስ" በማለት ይጠራዋል። (ገላ. 4፥6) "ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ይኖራል" ብሎ ለመናገር የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው (ገላ. 2፥20)።

## *በውስጣችን ማደር*

### *ዓላማ 4 በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን መኖር የሚያረጋግጠው መግለጫወችን ለመስጠት።*

ኢየሱስ በዮሐ. 14፥17 ላይ፡- "እርሱ ከእናንተ ጋር ይኖራል፣ በውስጣችሁም ይሆናል" በማለት ስለመንፈስ ቅዱስ በተናገረ ጊዜ የሰጠውን መግለጫ ደቀ መዛሙርቱ በሚገባ አላስተዋሉም ነበር።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር እንደዚህ ዓይነቱ ዕድል በአማኙ በኩል ኃላፊነት የሚጠይቅ እንደሆነ በመግለጽ ይናገራል (ዮሐ. 14፥16-17፣ 1ቆሮ. 3፥16-17፣ 6፥19-20፣ 2ቆሮ. 6፥16-17)። ይህንን ተበቅ አድርጎ የሚገልጸው በሮሜ 8፥12-17 ላይ "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ግዴታ አለብን፣ ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር ለሥጋ አይደለም" በማለት በሚናገረው ላይ ነው (ቁ. 12)። የመንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን መቆጣጠር ማወቅ ልጆች መሆናችንንና (15-16) ስለ ወደፊቱም መንፈሳዊ ርስታችን እድናውቅ ይረዳናል (17)። የመንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ መኖር ማለት



ሁልጊዜ አለ ማለት ነው። ይህ ከእርሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት ያልተቋረጠ ያደርገዋል። እርሱ ጎብኚ ሳይሆን፣ በእኔ ውስጥ ሙሉ ጊዜውን ይኖራል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ውስጥ የመኖሩን ጥቅም በአጭሩ አጠቃለን እንመልከት።

በውስጣችን የመንፈስ ቅዱስ አንደኛው ሥራ የእኛ አጽኛኝ ወይም አስተማሪ መሆን ነው። በዚህም ምክንያት እውነቱን ለማወቅ እንድንችል በማድረግ፣ የኢየሱስን ትምህርት ወደ አእምሮአችን በማምጣት ያሳስበናል፣ ትምህርቱንም እንድንረዳ ያደርገናል፤ (ዮሐ. 14፥26፣16፥13-15)። በውስጣችን ያለው መንፈስ በድካማችን ይረዳናል ስለእኛም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመቃተት ይጸልያል (ሮሜ 8፥26-27)።

ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውስጥ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆነው አማኝ አዲስ ልደት ካገኘ በኋላ በሕይወቱ ከሚሆነው ነገር ጋር የተዛመደ ነው። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመባል የተጠቀሰው ሲሆን፣ በሰባተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ በጥልቀት እንመለከተዋለን። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ለማረግ ጥቂት ሲቀረው ኃይል ከላይ እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ እንዲቆዩ ነገራቸው (ሉቃ. 24፥49)። በኋላም ነገሩን ግልጽ ሲያደርግላቸው "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ . . . ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" አላቸው። (የሐዋ. 1፥4-5) ከዚህ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቀጥሎ ተከታዮቹ በምድራቸው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በመላው ዓለም ምስክሮቹ ለመሆን ኃይል እንደሚቀበሉ ኢየሱስ ተናገረ (የሐዋ. 1፥8)። የኢየሱስን መግለጫ እውነተኛነት በማረጋገጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች በመላው ዓለም ወንጌልን በማሰራጨት ኃይለኛ መሣሪያዎች እንደነበሩ የሐዋሪያት ሥራ መጸሐፍ አስፍሮታል።

ከዚሁ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በተያያዘ ደግሞ የጸጋ ስጦታዎችም እሠራር አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጸጋ ስጦታዎች የሚጠቅሰው በሮሜ 12፥4-8፣ በ1ቆሮ. 12 እና 14 እና በኤፌ. 4፥11-16 ላይ ነው። እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች የክርስቶስን አካል የሚያንጹና የሚገነቡ ሲሆን በክፍለ ትምህርት 9 ላይ ስንደርስ በጥልቀት እንወያይባቸዋለን።

በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲኖር መንፈሳዊ ፍሬዎችን ያፈራል። አንዳንዶች ይህንን እንደ ክርስቲያናዊ ባህርይ መገንባት አድርገው ይመለከቱታል (ገላ. 5፥16-25)። መንፈሳዊ ፍሬ፥ ከኃጢአት በሕርይ የሚቃረንና በመንፈስ ከመኖርና ከመንፈስ ጋር በመተባበር የሚገኝ ውጤት ነው። የመንፈስ ፍሬን ሰፋ ባለ መልኩ በክፍለ ትምህርት አሥር እንመለከታለን።)

(8). በዚህ ክፍል በተመለከትናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት እውነት የሆኑቱን መግለጫዎች ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ኃጢአተኛው ባይገነዘበውም፣ እርሱ የእግዚአብሔር መቅደስ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ይኖራል።
ለ. አሁን መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ መኖር ስለጀመረ፥ ከእርሱ ፈቃድ ጋር እንዲስማማ አድርገህ ሕይወትህን የማቅረብ ግዴታ አለብህ።
ሐ. የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር የእርሱን አጽናኝነት፣ አስተማሪነትና የጸሎት እርዳታን ያስገኛል።
መ. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተሰጠው አማኞች ከሞት ለተነሣው ጌታቸው ውጤታማ ምስክሮች እንዲሆኑ ኀይል ለመስጠት ነው።
ሠ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የክርስቶስን አካል ለመገንባት ያገለግላሉ።
ረ. የመንፈስ ፍሬ አማኞች ራሳቸውን ተቀባይነት ያለው የክርስትና እምነት ምሳሌ ለማድረግ ካላቸው መልካም ፍላጎት የሚገኝ ውጤት ነው።

## *እኛን መቀደስ*

*ዓላማ 5 በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ ማለት ምን እንደሆነ ለመግለጽ።*

በውስጣችን የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ሌላው ሥራ እኛን መቀደስ ነው። በቀላል አነጋገር ከኃጢአት በመለየትና ለእግዚአብሔር እንዲኖር በማድረግ መንፈስ ቅዱስ አማኙን ይቀድሰዋል ማለት ነው። በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ ማለት አማኙ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲያስገዛና በኃጢአት ቁጥጥር ስር ከመሆን ነጻ ሲወጣ የሚሆን ነገር ነው። (ሮሜ. 8፥2፣9)።

በሮሜ 15፥16 ላይ አህዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው መስዋዕት ስለመሆናቸው ይናገራል። ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም ሲጽፍ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል" (1ቆሮ. 6፥11) በማለት ይናገራል። በተሰሎንቄ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍም

> በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ! እኛ ግን ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያ አንስቶ በመንፈስ ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጦአችኋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ተካፋዮች እንድትሆኑም ጠርቶአችኋል (2ተሰ. 2፥13-14)።

ዳግም ልደትን ስናገኝ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝና ክርስቶስ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ከፈጸመው የመዋጀት ሥራ የተነሳ በፊቱ እንድንቆም ያደርገናል። ጸድቅ ተብለን ስለምንጠራ በእግዚአብሔር ፊት የሚኖረን ስፍራ ምንም ኃጢአት እንዳላደረግን ዓይነት ነው። ቢሆንም እርሱ ጸድቅ አድርጎ ሲቀበለን እኛም የጽድቅ ሕይወትን በመተግባር መኖር አለብን። አዲስ እንደተወለደ መንፈሳዊ ሕጻን ለማደግና ለመጠንከር አስፈላጊው ምክር ተሰጥቶናል (2ጴጥ. 3፥18፣ 2ጢሞ. 2፥15፣ 1ጴጥ. 2፥2-3)። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በውስጣችን ተጀምሮአል



ማለት ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሕያው በመሆናችን፥ ለእግዚአብሔር አስፈላጊውን ምላሽ የመስጠት ችሎታ አለን። ለዘለዘለም ሕይወት የተወሰንንና ወደዚያም ግብ የምንጓዝ ስለሆንን ክርስቶስን ወደ ምምሰል እያደግንና እየበሰልን እንድንሄድ መመሪያ ተሰጥቶናል። ያዳነንንና በውስጣችን የለውን እየመሰል መሄድ አለብን (1ዮሐ. 3፥9)። በኤፌ. 4፥20-32፣ በሮሜ 8፥5-16 ና በገላ. 5፥16-25 እንደተመለከትነው አሮጌውን ሰው በማስወገድ አዲሱን ሰው መልበሳችን እያደገ የሚሄድና ግቡም በእያንዳንዳችን ውስጥ የክርስቶስ አምሳል እንዲያድግ ነው (ሮሜ 8፥29)። አሁን በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ፥ እርሱ ከሚያሳየንና እግዚአብሔርን ከማያስደስቱ፥ ነገሮች በየዕለቱ፥ ራሳችንን መለየት መማር አለብን። ቀስ በቀስም የእርሱ አምሳል እንመስላለን። አንድ ቀንም እርሱን ፊት ለፊት ስለምናየው እንደ እርሱ እንሆናለን (1ዮሐ. 3፥2)። እስከዚያው ድረስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ለመሆን እየተጋን ፍጹም ወደ መሆን ቀስ በቀስ እንጓዛለን።

(9). ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት። በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ ማለት

ሀ. በቅጽበት ፍጹማን ስለምንሆን፣ ከዚያ በኋላ ኃጢአት መሥራት አለ መቻል ነው።
ለ. ከኃጢአት ተለይተን ለእግዚአብሔር የተለየን መሆን ነው።
ሐ. በምናደርገው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን በመፍቀድ ወደ ክርስቶስ አምሳል በየቀኑ መለወጥ ነው።
መ. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ነገሮችን እንድናደርግ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን መፍቀድ ነው።

## የልጅነት መንፈስ

*ዓላማ 6 የዳግም ልደትህን ልምምድና የልጅነት መንፈስ ሥራዎችን ለመመዘን።*

## ወራሾች መሆን

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ልጅነት መንፈስ ሲገልጽ እንደዚህ ይላል።

> ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ግዴታ አለብን፤ ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር ለሥጋ አይደለም። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን በሕይወት ትኖራላችሁ፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። እንደገና የፍርሃት ባርያ የሚያደርጋችሁን መንፈስ ሳይሆን፣ "አባ አባት" ብለን የምንጠራበትን የልጅነት መንፈስ ተቀብላችኋልና፤ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ

መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክርልናል። ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምንባብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን *የልጅነት መንፈስ* ብሎ ሲጠራው ምን ማለቱ ነው? ልጅነት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ፥ የአንድን ሰው ስፍራ የሚመለከት ሲሆን፥ ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ በመሆን ያሉትን መብቶችም ይመለከታል። ለሮማውያን እንደ ልጅ አድርጎ ለመቀበል እንደኛው መንገድ፥ በአንድ ቤተሰብ በሕጋዊ መንገድ የማደጎ ልጅ እንዲሆን ቀባይነት ያገኘ እንደሆን ነው። ብዙ ጊዜ ድሆች ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያሳድጉበት በሚያጡበት ጊዜ አንድ ሐብት ያለው ቤተሰብ ልጃቸውን ወስዶ፥ እንደ ልጁ አድርጎ እንዲያሳድግ ያስጣሉ። ልጁን የተቀበሉትም ወላጆች በልጁ ላይ ሙሉ ሥልጣን አላቸው። ልጁም ከሌሎቹ ልጆች ሳይለይ፣ እኩል መብት ይሰጠዋል። ቢሆንም ልጆች እድሜያቸው ለአካለ መጠን እስከሚደርስ በቤቱ ውስጥ ካሉ አገልጋዮች ብዙም አይለዩም። የልጅነት መብቶችንና ጥቅሞችን የሚያገኙት እድሜያቸው ለአካለ መጠን ሲደርስ ነው። (ገላ. 4፥1-2)።

በዳግም ልደት ምክንያት የሕይወት መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋዮች እንድንሆን ያደርገናል። በልጅነት መንፈስ ምክንያት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ወዳያውኑ ሥፍራ ያስጠናል። ይህ ማለት የቤተሰብ አባላት ያላቸው መብቶች ሁሉ የእኛ ይሆናሉ ማለት ነው። ከሮማውያን ደንብ በተለየ መልኩ የልጅነት በረከቶችን ሙሉ ሰው እስክንሆን እንከለከልም። እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ሲቀበለን ለልጆቹ ያዘጋጀውን ሁሉ በመስጠት እኩል የቤተሰቡ አባል ያደርገናል (ገላ. 4፥1-7)።

ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ የልጅነት ሥልጣን መቀበልን ይጠቅሳል (በገላ. 3፥26-29 እና 4፥1-7 ላይ ተመልከት።) ልጆች የሁሉም ነገር ወራሾች ቢሆኑም ከአገልጋዮች ልዩነት የላቸውም። አባታቸው የሰጠው የጊዜ ገደብ እስኪደርስ ድረስ በሞግዚቶቻቸውና በመጋቢዎቻቸው ሥር ናቸው በማለት ይናገራል። ካደጉት ልጆች እኩል ተቆጥረው ቦታ ይሰጣቸዋል። በአይሁድ ሥርዓት እስራት ውስጥ ገና ነጻ እንዳልወጡ ልጆች የነበሩትን የገላትያ ሰዎች ሙሉ የልጅነት መብት እንደተቀበሉ በመግለጽ፦ " ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባርያ አይደለህም፤ ልጅም ስለሆንክ፣ እግዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል።" በማለት ያስረዳል (ገላ. 4፥6-7)።

እንደ ልጆቹ መቆጠራችን ያስገኘልን አንዱ ጥቅም የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ውስጣዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ ማግኘት ነው። መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክርናል (ሮሜ 8፥12-17) 1ዮሐ. 324፤ 413-14)። በዚህም ምስክርነት የተነሣ እርሱን



አባት ብለን ለመጥራት እንችላለን። ዮሐንስ ይህንኑ በማጠናከር ሲገልጽ፦ "አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን" በማለት ራናገራል (1ዮሐ. 3፥2)። መንፈሳዊ አቋሙን ለመወሰን፣ ክርስቶስ እስኪመጣ ወይም ወደፊት እስከሚመጣው ፍርድ ድረስ ማንም የሚጠብቅ የለም። ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ መንፈስ በውጡ ይመሰክርለታል፤ ዘላለማዊ የሆነውም የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርለታል።

አሁን ሙሉ የመውረስ መብታችን የተጠበቀ የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንም፣ በእግዚአብሔር ፊት ቆመን የከበረ አካል እስክንለብስ ድረስ የልጅነታችን በረከቶች ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ አይውሉም። በሮሜ 8፥23 ጳውሎስ ይህንኑ ሲያረጋግጥ "የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን" ይላል።

በ1ዮሐ. 3፥2 ላይ የተጻፈው ቃል ይህንን በይበልጥ ሲያብራራ፦ "ወዳጆች ሆይ! እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደፊት ምን እንደምንሆንም ገና አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን።" በማለት ይናገራል።

በኋላም ዮሐንስ፣ ወንድሙን የማይወድና ጽድቅን የማያደርግ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም፣ በማለት ይናገራል (1ዮሐ. 3፥10፣ 21-24፣ 5፥1-3)። የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል መሆን መብቶችን የሚያስገኝ ቢሆንም ኃላፊነትንም ደግሞ ያዘለ ነው። እነዚህን ኃላፊነቶች እንድትወጣ የሚያስችልህ በውስጥህ ያለው የእግዘኢብሔር መንፈስ ነው። መለኮታዊ ፍቅር በውስጥህ እንዲፈጠር ከማድረጉም በተጨማሪ ሰማያዊ አባትህን የሚያስደስቱትን ነገሮች እንድታደርግ በውስጥህ ፍላጎት ያሳድራል።

(10). የልጅነት መንፈስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው . . .

ሀ. በዳግም ልደት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ የምሆንበትን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።
ለ. ከሌሎች አማኞች ጋር ባለኝ ግንኙነት በመረጠው ስፍራ የማስቀመጥን የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነው።
ሐ. አዲስ ልደትን ባገኘበት ወቅት በአማኝ ላይ ያለውን ፍጹም የሆነ የመንፈስ ቅዱስን ቁጥጥር ነው።

(11). የእግዚአብሔር ልጅ መሆን የሚከናወነው።

ሀ. የከበረ አካል ስለብስ ስቀበል
ለ. "አባ፣ አባት" ብዬ ስጮሕ
ሐ. አዲስ ልደትን ስቀበል

(12). ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህንና መንፈስ ደግሞ መወለድህን የምታውቅባቸውን ሦስት መንገዶች ጥቀስ (ሮሜ 8፥16፣ 1ዮሐ. 3፥10፣ 21-24፣ 4፥13-14፣ 5፥1-3)።

(13). በተሰጠው በክፍት ስፍራ "አዎን" ወይም "አይደለም" ብለህ በመጻፍ ራስህን መርምር።

ሀ. ኃጢአቴን ተናዝዤአለሁ። ____________
ለ. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀብያለሁ።________
ሐ. ክርስቲያን ብሆንም አልፎ አልፎ የማደርገውን ኃጢአት በመናዘዝ ይቅርታን መቀበል አለብኝ። ____________
መ. ንስሐ መግባት ማለት ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው። ____________
ሠ. ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ ስለወጣሁ መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገውን ማድረግ እፈልጋለሁ። ____________
ረ. በየዕለቱ መንፈስ ቅዱስ እንዲቀድሰኝና በይበልጥ ኢየሱስን እየመሰልኩ እንድሔድ እንዲያደርገኝ እፈልጋለሁ። ____________
ሰ. የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ስለሚመሰክርልኝ ክርስቲያን መሆኔን አውቃለሁ። ____________
ሸ. በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የእግዚብሔር ልጅ በመሆኔ አንዳንድ መብቶችንና ኃላፊነቶችን እንደሚሰጠኝ እገነዘባለሁ። ________

እነዚህን ነገሮች በማሰብ በክርስቶስ አማካኝነት የቀረበልህን በሙሉ መቀበልህን ወይም አለመቀበልህን ለማሰብ አመቺው ጊዜ አሁን ነው። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያለህን ሥፍራ እንደ እግዚአብሔር ልጅነትህ ከመብቶቹና ከኃላፊነቶቹ ሁሉ ጋር እውን እንዲያደርግልህ በጸሎት ጠይቀው።



## የሙከራ ፈተና

ከተሰጡት ሁለት ምርጫዎች ትክክለኛ የሆነውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

*1. ዳግም ልደት*

ሀ. ኃጢአቱን በመናዘዙና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኙ በመቀበል ንስሐ ለሚገባ ኃጢአተኛ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ነው።
ለ. የአንድን ሰው መንፈሳዊነት በተመለከተ የአስተሳሰብና የስሜት ለውጥ፣ ከኃጢአት የነጻ ሕይወት ለመኖር የሚፈጠር ምኞት ነው።

*2. ማሳመንና መውቀስ*

ሀ. የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ ኃይል በጣም ጠንካራ በመሆኑ ከኃጢአቱ ከመመለስና ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ በስተቀር ለአንድ ኃጢአተኛ ሌላ ምንም አማራጭ ያለውም። ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ የበደለኝነት ስሜትና ኃጢአት የሌለበት ሕይወት ለመኖር ፈጽሞ እንደማይቻል ለይቶ ማወቅ ነው።
ለ. መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ ኃጢአተኛውን ሲወቅስና እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገው ሲያሳምነው፥ ብዙ ጊዜ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ በተቀባ ስብከት ወይም በግል ምስክርነት በኩል ለኃጢአተኛው ልብ በመናገር ነው።

*3. ንስሐ*

ሀ. ንስሐ ኃጢአተኛው ራሱን በኃጢአት እንዳለ እንዲያይ የሚያደርግ እንደ እዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ነው። የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ከፈለገ መንገዱን መቀየር እንዳለበት ለይቶ ያውቃል፤ ወደ ዘላለም ሞት የሚወስዱትን ነገሮች ከማድረግ ለመቆጠብ ይሞክራል።
ለ. ንስሐ ስለ ኃጢአት ያለውን ሐሳብ መቀየር፥ ስላለፈው ኃጢአት ከልብ ማዘንና፥ ባህርዩን በመለወጥ ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው። ውስጣዊና ውጫዊ ለውጥ አለው። ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት። አማኙ ወደ ክርስቶስ ከመምሰል የሚያዘገየውና የሚያግዱትን እንቅፋቶች መናዘዝ አለበት።

4. የመንፈሳዊ ሕይወት ውጤቶች

ሀ. ከዲያቢሎስ ፈተና ነፃ ስለወጣሁ፣ ኃጢአት የማድረግ ፍላጎት አያስቸግረኝም።
ለ. በኃጢ ውስጥ አልኖርም፥ አእምሮዬ የሚያስበው መንፈስ ቅዱስ እንዳደርግ የሚፈልገውን ነው።

*5. የመንፈስ ቅዱስ በውስጤ ማደር*

ሀ. መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ሲኖር ብዙ በረከቶችን አገኛለሁ። ልጅነቴን ያረጋግጣል፣ በትክክለኛው መንገድ እንድጸልይ ይረዳኛል፣ ትክክለኛ ስላልሆነው ተግባሬ ይወቅሰኛል፣ ድል እንዳደርግም ይረዳኛል።

ለ. መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ሲኖርና ስውነቴን የእርሱ መቅደስ ሲያደርግ ምርጫዬ፣ ድርጊቴና ሀሳቤ፥ የእርሱ ምርጫ፥ የእርሱ ድርጊትና የእርሱ ሐሳብ እንዲሆን ውስጤን ይቆጣጠራል። እርሱ ሁሉን ከውስጤ ስለሚያስወግድ የሰው ፍላጎቶችና ምኞቶች ፈጽጽ አያስቸግረኝም።

*6. በመንፈስ መቀደስ*

ሀ. በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር እሆን ዘንድ ራሴን ለእርሱ አሳልፌ ስሰጥ፣ ራሴን ከኃጢአት ለይቼ ለእግዚአብሔር እንድኖር ያስችለኛል። ይህም ለመንፈስ ቅዱስ ስታዘዝና በውስጤ የመንፈስ ፍሬዎችን እንዲያፈራ ስፈቅድለት፥ ቀስ በቀስ ክርስቶስን እንድመስል የሚያደርገኝ የእርሱ ሥራ ነው።

ለ. ይህ በድንገት ክርስቶስን እንድመስልና የመንፈስ ፍሬ እንዲኖረኝ የሚያደርግ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።

*7. የልጅነት መንፈስ*

ሀ. በክርስትና ሕይወት ሳድግና በሚገባ ስበስል በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የልጅነት ሥልጣንና የወራሽነት መብትና ኃጢአት የሚገባኝ እሆናለሁ። ለዚህ ተቀባይነት ብቁ የምሆነው መቼ እንደ ሆነ የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን የሚመሰክረው እርሱ ነው።

ለ. መንፈስ ቅዱስ ልደት ሲሰጠኝ፥ የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋይ እንዞሆን ያደርገኛል። ሙሉ የእግዚአብሔር ልጅነት መብቶችን ሰጥቶ ከክርስቶስ ጋር አብሬ እንድወርስ በማድረግ ከእግዚብሔር ቤተሰብ እንድቀላቀል ያደርገኛል። የእርሱ መንፈስ ለእኔ መንፈስ ስለሚመሰክር፥ ትክክለኛ የሆነውን ለማድረግ ስለምፈልግና በክርስቶስም ወንድሞቼና እህቶቼ ለሆኑት ፍቅር ስለሚሰጠኝ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን ዳግመኛ መወለዴን በዚህ አውቃለሁ።



## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. ሀ. መንፈስ
   ለ. ፍላጎት
   ሐ. መንፈስ
   መ. ክርስቶስ

1. ብዙዎች መልእክቱን ተቀብለው ተጠመቁ።

8. ሀ. ሐሰት
   ለ. እውነት
   ሐ. እውነት
   መ. እውነት
   ሠ. እውነት
   ረ. ሐሰት (መንፈሳዊ ፍሬ በመንፈስ ከመኖርና ከመንፈስ ጋር በመተባበር የሚገኝ ውጤት ነው።)

2. አልሰጡም፤ "መልእክቱን የተቀበሉት" የሚለው ቃል (2፥41) አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስን መቃወማቸውን ያመለክታል።

9. ለ፣ ሐ እና መ ትክክለኛ መልስ ናቸው።

3. የለሙት በጣም በመቆጣት የእግዚአብሔርን መንፈስ ተቃወሙ፥ እስኪሞትም ድረስ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወገሩት።

10. ሀ

4. ሀ. 3
   ለ. 4
   ሐ. 1
   መ. 5
   ሠ. 2

11. ሐ

5. ሀ. ሐሰት
   ለ. እውነት
   ሐ. እውነት
   መ. ሐሰት
   ሠ. ሐሰት
   ረ. እውነት
   ሰ. እውነት

12. መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሴ ይመሰክርልኛል፤መልካምን ነገር አደርጋለሁ፤ ክርስቲያኖችን እወዳለሁ።

6. ሀ. መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ይሰጣል።
   ለ. የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ ያወጣል።
   ሐ. መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ያጠነክራል፤ ልጅነታችንንም እውን ያደርጋል።
   መ. በመንፈስ እንኖራለን፤ ተገቢ የክርስትና ሕይወት እንድንኖር ያደርገናል።

13. የአንተ መልስ። ለሁሉም አዎ የሚል መልስ እንደሰጠህ ተስፋ አደርጋለሁ።

# 7
## ትምህርት

# ኃይልን የሚሰጥ መንፈስ

በተማሪዎች ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን ስመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ማስተማር ሁልጊዜ ለእኔ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ነው ያገኘሁት። በተማሪዎች ሕይወት የሚፈጽመው የለውጥ ሥራ ስመሰከት ሳልገረም የቀረሁበት ጊዜ የለም።

ብዙ ተማሪዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሲመጡ ለሚጠብቃቸው የአደባባይ አገልግሎት ምንም ችሎታ ያላቸው ባይመስሉም እግዚአብሔር እንደጠራቸው በማመን ብቻ ይመጣሉ። ከዚያም የእግዚአ ብሔርን ቃል ሲያጠኑ፣ ሲጸልዩና ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ሲሰጡ ቀስ በቀስ በሕይወታቸው ተአምር ይፈጽማል። መንፈስ ቅዱስ ህይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠር ያላቸውን ችሎታ በመቀባትና በጥናታቸው በኩል አዕምሮቻቸውን ብሩህ ሲያደርግ፥ የተለያየ ዓይነት ችሎታዎች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምራሉ። ተማሪዎቹም ከእለት ወደ ዕለት በመንፈስ እያደጉ በመሄድ ትምህራቸውን አጠናቀው በሚመረቁበት ጊዜ እግዚአብሔር ለጠራ ቸው አገልግሎት ዝግጁ ሆነው ይገኛሉ። ከዚያም ጥሩ መጋቢ፣ ወንጌላዊና ሚሲዮናዊ ሆነው ትምህርት ቤቱን ትተው ለአገልግሎት ይሄዳሉ።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ችሎታ የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች ከተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ የታየ ነው። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ያሉት አንዳንዶቹ በጣም የተማሩ ሲሆኑ፣ ብዙዎቹ ግን ከዝቅተኛ ሥፍራ የተነሡ ናቸው። አመጣጣቸው ከየትኛውም ወገን ቢሆን፣ ዓለምን በክርስቶስ ወንጌል እንዲገለብጡ ያስቻላቸው የእነርሱ ዘዴና ጥበብ ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (1ቆሮ. 2፥1-5)።

በዚህ ክፍለ ትምህርት የምትማረው መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወትህ በመም ጣት በጥምቀት ሲሞላህ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ውጤታማ ሠራተኛ እንድትሆን እርሱ ይረዳሃል። ለብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎችና ለአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርት የተሰጠው ኃይል ዛሬም ለአንተ ይሰጥሃል።



### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የብሉይ ኪዳን ባለታሪኮች
- የአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርት
- የሃያኛው ክፍለ ዘመን አማኞች

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በእግዚአብሔር በተመረጡ ሰዎች ላይ ስለ ወረደው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ከብሉይ ኪዳን ምሳሌ መስጠት።
- መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት በደቀ መዛሙርቱ ላይ በወረደ ጊዜ ያስከተለውን ለውጥና የለውጡን ውጤት መግለጽ።
- የአሁኑን ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ዓላማው በመላው ዓ ለም ወንጌል እንዲሰበክና የጌታን መምጫ እንዲፋጠን ከማድረግ ጋር የተያያዘ መሆኑን ማሳየት።

---

### የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በዚህ ክፍለ ትምህርት የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ አንብብና የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን መልስ።
2. የሙከራ ፈተናውን ከወሰድክ በኋላ በመጽሐፍ መጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያት የተሳሳትከው ካለ አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

# የብሉይ ኪዳን ባለታሪኮች

## በፔንታቱክ ውስጥ

***ዓላማ 1 በተመረጡ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በሙሴ ዘመን የላከበትን ዓላማ ለመግለጽ።***

ለመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፔንታቱክ የሚል ስም የተሰጣቸው ሲሆን፣ እነዚህም መጻሕፍት አራት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁና ዘዳግም ናቸው። እነዚህ አምስት መጻሕፍት የተጻፉት በሙሴ ስለሆነ ብዙ ጊዜ የሙሴ መጽሐፍት ተብለው ይጠራሉ። በእነዚህ አምስት መጻህፍትና በሙላው ብሉይ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ በደብልጥ ትኩረት የተሰጠው በተግባሩ ላይ እንጂ በእርሱ ማንነት ላይ አይደለም። ብሉይ ኪዳን ስለመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ምንም የሚናገረው የለም፤ በዘፍጥረት 1 ከሚታየው የመፍጠር ሥራ ጀምሮ፥ በመንፈስ ቅዱስ ታምራዊ ሥራዎች የተሞላ ነው።

በብሉይ ኪዳን አጽንኦት የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ ልዩ አገልግሎት ለማከናወን በሰዎች ላይ መምጣቱ ላይ ነው። የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መገኘት ግን የአዲስ ኪዳንም ክንዋኔ ነበር።

ዮሐንስ በተናረው ቃል ይህንን ሲያረጋግጥ "ኢየሱስ የሚከብርበት ጊዜ ስላልደረሰ፥ መንፈስ ቅዱስ ገና አልተሰጠም ነበር" ብሏል (ዮሐ. 7፥39) ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ መምጣት በሚናገርበት ጊዜ፦ "እናንተ ግን አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ" (ዮሐ. 14፥17) በማለት አስረድቶአል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጡትን ማስረጃዎች ሁሉ በማነጻጸር የብሉይ ኪዳን ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን መገኘት በህይወታቸው የተለማመዱት፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተለየ ተግባር እንዲያከናውኑ ለማስቻል አልፎ አልፎ የሚሆን ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ደግሞ አማኞች ሁል ጊዜ በቋሚነት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ስለሚኖር በእርሱ መኖር ሁልጊዜ ሃሴት ያደርጋሉ። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኙ የሚመጣው ዳግም ልደትን ለመስጠት ሲሆን፤ ከዚያም (በማቴ. 3፥11፤ ማር. 1፥8፤ ዮሐ. 1፥33፤ የሐዋ. 1፥5) ላይ እንደምንመለከተው አማኞች በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ እርሱን በጥምቀት ሙላት ተቀብለውታል።

መንፈስ ቅዱስ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ የጀመረው ወዲያው ከሰው ውድቀት በኋላ ነው። ለእርሱ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጡ እንደ አብርሃም፣ ኖኅ፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ያሉ ሰዎችን አገኘ። እነዚህን ሰዎች በተመለከተ ስለመንፈስ ቅዱስ በተለይ የተነገረው ጥቂት ቢሆንም፥ እነርሱ



ለእግዚአብሔር በሚታዘዙበት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ እንደተመሩ እናውቃለን። የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ሕይወት የሚሠራው የሰዎች ቀልብ ወደ እርሱ እንዲሳብ በማድረግ አልነበረም። በብሉይ ኪዳን የእርሱ ስም በማይጠቀስበት ጊዜ እንኳን ሥራው ይታይ ነበር።

በብሉይ ኪዳን በተለይ በሰዎች ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለሚሠራው ሥራ የተጠቀሱ ነገሮች አሉ። በአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይሉ የተጠቀመባቸው እነማን ናቸው?

1. *ዮሴፍ፦* የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ያለበት ሆኖ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ዮሴፍ ነው (ዘፍ. 41፥38)። ሕልም የመፍታት መለኮታዊ ችሎታ እንዳለው ፈርኦን ተገንዝቦ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ በዮሴፍ ውስጥና በዮሴፍ ላይ ስለ ነበር ፈተናን እንዲቋቋምና የሃገሩና የሕዝቡ ሁሉ ጠባቂ እንዲሆን አደረገው።

2. *ሙሴ፦* እስራኤላውያንን ከግብጽ ለማውጣት በእግዚአብሔር ተመርጠ። ሙሴ የእስራኤል ሕዝብ እረኛ እንደነበረና "መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው እንዲሠራ እንዳደረገ ኢሳይያስ ይነግረናል" (ኢሳ. 63፥11)። "በእግዚአብሔር መንፈስ እረፍትን አገኙ" በማለት በተጨማሪ ኢሳይያስ ይናገራል (ኢሳ. 63፥14)።

የማደሪያው ድንኳን ለጌታ የሚሠራበት ጊዜ ሲደርስ፥ እግዚአብሔር ለሙሴ ሞያተኞችን እንደመረጠ በመግለጽ፦ ሲናገር ስለ ባስልኤል "በሁሉም ዐይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ ብልሃት፣ ችሎታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞልቼዋለሁ" በማለት ይናገራል። የጌታን ቤት ለመሥራት አስፈላጊ በሆነ በማንኛውም ሙያና እውቀት ሁሉ እሠረው መለኮታዊ ችሎታ ተሰጥቶት ነበር።

ሙሴ በህዝቡ ሸከም ምክንያት ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ወደ እግዚአብሔር በጮኸ ጊዜ፥ የሕዝቡን ፍላጎት በማሟላት ሙሴን የሚረዱ፥ ጌታ ለሰባ ሽማግሌዎች መንፈስ ቅዱስን ሰጠ።

(1). ዘኁ. 11፥10-17 እና 24-25 ላይ የተጻፈውን ካነበብህ በኋላ እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ በሙሴ ላይ እንደነበር የሚያመለክተው ጥቅስ የትኛው ነው?
ለ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለሰባዎቹ ሽማግሌዎች ለመስጠት የትኛውን ዘዴ ተጠቀመ?
ሐ. በሰባዎቹ ሽማግሌዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዳረፈ ሁሉም ምን አደረጉ?

3. ኢያሱ፦ ሙሴን እንዲተካ በጌታ የተመረጠው ኢያሱ ነበር። ጌታ ለሙሴ ሲናገር፦ "መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን ጫንበት" አለው። (ዘኁ. 27፥18) ሕዝቡ የተስፋይቱን ምድር እንዲወርሱ ኢያሱ ሊመራቸው የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። በመሪነት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ስለእርሱ የተጻፈው እንደሚነግረን፦ "ሙሴ እጆቹን ጭኖበት ነበርና የነዌ ልጅ ኢያሱ በጥበብ መንፈስ ተሞላ። ስለዚህ እስራኤላውያን አደመጡት፤ እግዚአብሔር ሙሴን አዞት የነበረውንም ሁሉ አደረጉ" በማለት ይገልጻል (ዘዳ. 34፥9)። ስለዚህ ከግብጽ እስከ ከነዓን ድረስ እስራኤላውያን የተመሩት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተሞሉ መሪዎች ነበር።

መንፈስ ቅዱስ ስልዩ አገልግሎት በእግዚአብሔር በተመረጡ የብሉይ ኪዳን ሰዎችና የአዲስ ኪዳን አማኞች ላይ ነበር ማለቱ፣ ጥሩ አገላለጽ ቢሆንም፣ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት አጥጋቢ በሆነ መንገድ አይገልጸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ እንደሚያመለክተውም በብሉይ ኪዳን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ አሠራር፥ ለልዩ አገልግሎት በተመጡ ሰዎች ላይ አልፎ አልፎ በመምጣት የተለየ ችሎታን መስጠት ሲሆን፤ በአዲስ ኪዳን ያለው አሠራር ደግሞ በአጠቃላይ መልኩ ከቋሚነት በሰዎች ውስጥ መኖር ነው። ያየናቸው ምሳሌዎች መንፈስ ቅዱስ በቋሚነት የሚሰጠው ችሎታ ወይም ሥጦታ አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው።

(2). ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሰዎች ላይ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን የላከበት ዓላማ ምን እንደሆነ ግለጽ።

ሀ. ዮሴፍ ______________________
ለ. ሙሴ ______________________
ሐ. ሰባዎቹ ሽማግሌዎች ____________
መ. ኢያሱ ______________________
ሠ. በእያንዳንዱ ላይ የተሰጠው ማስረጃ መሠረት፥ በሰዎቹ ውስጥ የሚገለጠው የመንፈስ ቅዱስ ችሎታ የአጭር ወይስ የረጅም ጊዜ ልምምድ ነበር? __________

## በታሪክ መጽሐፍት ውስጥ

### *ዓላማ 2 ከሳምሶን፣ ከሳኦልና ከዳዊት ሕይወት ለመማር የምንችለውን መርህ ለመግለጽ።*

የኢያሱ መጽሐፍ፥ እስራኤላውያን ወደ ከነአን ምድር ሲጓዙና በኢያሱ መሪነት ምድሩን ሲይዙ የተቀዳጁትን ብዙ ድሎች አስፍሮአል፥ የኢያሱ በመንፈስ የተቀባ መሪነት በኢያሱ 24፥31 ላይ በተጻፈው ቃል ሊጠቃለል ይችላል፦



ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣ ከኢያሱም በኋላ በሕይወት በኖሩትና እግዚአብሔር ለእሥራኤል ያደረገውን ሁሉ በሚያውቁት ሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አመለኩ።

በመሳ. 2፥10-12 ላይ እንዲህ በማለት ይናገራል፦

*ያ ሁሉ ትውልድ ወደ አባቶቹ ከተከማቸ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ ለእሥራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ ተነሣ። ከዚያም እሥራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረጉ፤ የበአል አማልክትንም አመለኩ። ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተው፤ በዙሪያቸው ያሉት ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን አማልክት ተከተሉ፤ ሰገዱላቸውም።*

በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ በእሥራኤላውያን ላይ በረታባቸውና ለመዋጋት ሲሄዱ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው እንዲሸነፉ ፈቀደ። ከዚያም በኋላ ደግሞ "እግዚአብሔርም ከነዚህ ወራሪዎች የሚያድኑአቸውን መሳፍንት አስነሣ" በማለት በመሳ. 2፥16 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

በመሳፍንት ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተለይ ግልጽ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጭቆና ነፃ እንዲያወጡ በተመረጡት ሰዎች በኩል ድካምና ውድቀት ቢታይም፤ እግዚአብሔር ግን ከድካማቸው ጋር መሳፍንቱን ይጠቀምባቸው ነበር።

በጠቅላላው ከ300 ዓመታት ለሚዘልጥ ዘመን እስራኤልን የገዙ 13 መሳፍንት ነበሩ። የጌዲዮንና የሳምሶን ታሪኮች መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በመጣባቸው ጊዜ በሰው ዘንድ የማይቻለውን ለመፈፀም እንደቻሉ።

(3). *መሳፍንት* 6፥11-15 አንብብ። እግዚአብሔር ለጌዲዮን በተገለጠለት ጊዜ ጌድዮን ራሱን ምን ዓይነት ሰው አድርጎ ነው የገለጸው?

ጌድዮን የጌታ መልአክ የሰጠውን መመሪያዎች ተቀብሎ ስለታዘዘ የጌታ መንፈስ በእርሱ ላይ መጣ (መሳ. 6፡34)። በተመረጡ 300 ሰዎች ብቻ፥ ብዛት ካለው ከምድያም ሠራዊት እስራኤልን ነፃ እንዲወጣ እግዚአብሔር ጌዲዮንን ተጠቀመበት።

ለሕይወታቸውና ለአገልግሎት የእግዚአብሔርን ኃይል ለሚቀበሉ ሁሉ ሳምሶን ትልቅ ትምህርት ነው። ከመወለዱ በፊት እንኳ እስራኤልን ለመምራት ተዘጋጅቶ ነበር (መሳ. 13-16 ተመልከት)። ገና ወጣት ልጅ ሳለ "እግዚአብሔርም ባረከው የእግዚአብሔርም መንፈስ . . . ያነቃቃው ጀመር (መሳ. 13፥24-25)።

(4). *መሳፍንት* 14፥6፣19 እና 15፥14 ላይ የተጻፈውን አንብብ። በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ሳምሶን የተጻፈው ምንድን ነው?

ሳምሶን ከመወለዱ ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ነበርና እግዚአብሔርም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን ነጻ እንዲያወጣ ሳምሶንን መረጠው። ዳሩ ግን ሳምሶን ለጌታ ለገባው ቃል ኪዳን ታዛዥ አልነበረም።

(5). *መሳ*. 16፥15-20 አንብብ። ሳምሶን የገባውን ቃል ኪዳን አፍርሶ የኃይሉን ምንጭ በገለጠ ጊዜ ምን ሆነ?

የእስራኤል ሕዝብ እንደ ሰው ለንጉሥነት ተመርጦ እንዲሰጣቸው በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር ሳኦልን ሰጣቸው (1ሳሙ. 8፥4)። ነብዩ ሳሙኤል፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ይወርድብሃል፤ ከእነርሱ ጋር ትንቢት ትናገራለህ፤ እንደ ሌላ ሰውም ሆነህ ትለወጣለህ" በማለት ለሳኦል ነገረው (1ሳሙ. 10፥6)። ይህ ትንቢት በሀያኑ ዕለት ተፈጸመ፤ እግዚአብሔርም የንጉሥነት ተግባሩን በሚጀምርበት ላይ በታላቅ ኃይል ተጠቀመበት። ዳሩ ግን እርሱም እንደ ሳምሶን እግዚአብሔርን በማክበሩና በመታዘዙ አልቀጠለም። ከዚህም የተነሣ በጣም የሚያሳዝኑ ቃላት ስለእርሱ ተጻፉ።

(6). 1ሳሙ. 16፥14 አንብብ። እነዚህ የሚያሳዝኑ ቃላት ምንድን ናቸው?

በዚህን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አንድ እረኛ ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ እያዘጋጀ ነበር። ይህን ልጅ ሳሙኤል እንዴት እንዳገኘውና የዘይቱን ቀንድ ወስዶ እንደቀባው ሲናገር "ሳሙኤልም በወይራ ዘይት የተሞላውን ቀንድ ወስዶ ዳዊትን በወንድሞቹ ፊት ቀባው፤ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት አደረገበት" ይላል( 1ሳሙ. 16፥13)።

የእግዚአብሔር መንፈስ ባላማቋረጥ ካደረባቸው ጥቂት የብሉይ ባለታሪኮች አንዱ ዳዊት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእርሱ ባያድር ኖሮ ብዙ ያከናወናቸው ነገሮች ሊፈጸሙ አይችሉም ነበር።

ዳዊትም የመንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር የመሆኑን አስፈላጊነት ይህና አድርጐ ያውቃል። በኃጢአት ወድቆ በነበረበት ጊዜ እንኳን ንስሐ በመግባት ወደ እግዚአብሔር ሲጮህ፡- "ከፊትህ አታርቀኝ፣ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ አትውሰድብኝ" ይል ነበር (መዝ. 51፥11)።

(7). በህይወታቸው መንፈስ ቅዱስ ኖሮ ሳለ፣ ከሳምሶን፣ ከሳኦልና ከዳዊት ውድቀት ልንማር የምንችለው ትምህርት ምንድን ነው?



## በነብያት መጻሕፍት ውስጥ

***ዓላማ 3 ስለመንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው መገኘት የብሉይ ኪዳን ነብያት አለተያየት የሚያንጸባርቀውንን መግለጫ ለይቶ ለማወቅና ለማስረዳት።***

በእስራኤል የኋለኛው ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀመባቸው መጻሕፍት የጻፉትን ነብያት ነበር። የነዚህ ነብያት ጸሐፎች ከብሉይ ኪዳን መጻሐፍትን ትልቁን ክፍል የያዘ ነው።

ስለ እውነተኛ ነብያት ሁሉ ሊባል የሚቻለውን ነብዩ ሚክያስ ስለራሱ ሲናገር፡- "እኔ ግን እግዚአብሔር በመንፈሱና በኃይሉ ሞልቶኛል" በማለት ይገልጻል (ሚክ. 3፥8)።

ሕዝቅኤል በሰማይን በምድር መካከል መንፈስ እንዴት እንዳነሳውና በራዕይ ወደ ኢየሩሳሌም እንደወሰደው ተናገረ (ሕዝ. 8፥3)።

የመንፈስ ቅዱስ በዳንኤል ውስጥ መኖሩን ንጉሡ ናብከደነጾር ለይቶ በማወቁ "የቅዱሳን አማልክት መንፈስ እንዳለብህና ምስጢር ሁሉ ለአንተ ስውር እንደማይሆንብህ አውቃለሁ" ሲል ለዳንኤል ተናገረ።

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በነብያት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለይቶ መኖሩን በቀላሉ አውቀዋል። ጳውሎስ በሮም ለነበሩ አይሁዶች እንዲህ ብሎ ነገራቸው፡- "መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ አማካኝነት ለአባቶቻችሁ የተናገረው ልክ ነበር" (የሐዋ. 28፥25)።

የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ በምዕራፍ 10፥15-17 ላይ ከትንቢተ ኤርምያስ 31፥33-34 በመጥቀስ፡- "መንፈስ ቅዱስ በዚህ ነገር ይመሰክርልናል" ይላል። በኤርምያስ የተጻፉት ቃላት የመንፈስ ቅዱስ ቃላት እንደሆኑ ተለይተው ይታወቁ ነበር።

በ2ጴጥ. 1፥20-21 ሐዋርያው ጴጥሮስ በነብያት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሲያረጋግጥ፡-

> ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጉመው አይደለም፤ ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።

(8). መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ያለውን አስፈላጊነት በተመለከተ የብሉይ ኪዳንን ነብያት አስተያየት በተሻለ የሚያንጸባርቀው የትኛው መግለጫ ነው?

ሀ. ከፊትህ አትጣለኝ፥ መንፈስ ቅዱስህን ከእኔ አትውሰድብኝ፣ በማለት ዳዊት በመዝ. 51፥11 ላይ የተናገረው።
ለ. በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፣ ይላል ኃያሉ ጌታ በማለት ዘካርያስ 4፥6 ላይ የተነገረው።
ሐ. ሚክ፦ እኔ ግን ኃይልን በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልቻለሁ፤ በማለት ሚክ. 3፥8 ላይ የተነገረው።

## የአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርት

***ዓላማ 4 ሐዋርያው ጴጥሮስ ከበዓለ ሃምሳ በፊትና በበዓለ ሃምሳ ዕለት ምስክርነት ለማነጻጸርና ለመዘርዘር።***

## ከበዓለ ሃምሳ በፊት

ከበዓለ ሃምሳ በፊት የመንፈስ ቅዱስ ዋና ትኩረት በኢየሱስና በሰራው ሥራ ላይ ነበር። ከዚህም ቀደም ሲል በክፍለ ትምህርት አምስት ላይ የኢየሱስ አገልግሎት በተመለከተ *ሕያው ቃል* በሚለው ላይ ስለተወያየንበት በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ እንድገመውም።

ጥቂት የአዲስ ኪዳን ሰዎች ከበዓለ ሃምሳ በፊት ለልዩ አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስን የመስቻል ሃይልን የተቀበሉ ነበሩ፥ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፦

1. *መጥመቁ ዮሐንስ* (ሉቃ. 1፥15)
2. *የመጥመቁ ዮሐንስ ወላጆች* (ሉቃ. 1፥41፣ 67
3. *ማርያም፣ የኢየሰስ እናት ማቴ.* 1፥18፣ 20)
4. *ስምዖን* (ሉቃ. 2፥25)

ለልዩ አገልግሎት በኢየሱስ ከተላኩበት ጊዜ በስተቀር መንፈስ ቅዱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቀጥታ መንገድ አልሠራም (ማቴ. 10፥1፣ ማር. 3፥13-15፣ ማር. 6፥7፣ ሉቃ. 9፥1 እና ሉቃ. 10፥19)። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያመለክቱት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት እንደጠራቸውና በስሙ ተአምራትን እንዲያደርጉ፥ ሥልጣን እንደሰጣቸው ነው። እርሱ ሥልጣኑን የተቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይህንኑ ሥልጣን ለአገልግሎት ዓላማ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው።

ደቀ መዛሙርቱ አብዛኛውን ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ነበሩ። መለኮታዊ መምህራቸውም እርሱ ነበር። እርሱን በመከተልና በማድመጥ እርሱን ለመምሰል ሞከሩ፥ ግን አልሆኑላቸውም። ከእርሱ ጋር በዚያን ጊዜ ለመሆን ቻሉ እንጂ በእርሱ ውስጥ ለመሆን ግን አልቻሉም። እስከ ሞቱና ትንሣኤው ድረስ በእርሱ ላይ የወረደውን ኃይል በሙሉ ለመካፈል



አልቻሉም። ሐዋርያው ዮሐንስ በኋላ እንደጻፈው "ኢየሱስ ገና ስላልከበረ እስከዚያ ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ አልተሰጠም" ነበር (ዮሐ. 7፥39)።

ከበዓለ ሃምሳ በፊትና ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ያለው የደቀ መዛሙርቱ ታሪክ በጣም ያስደንቀኛል። ሁለቱ እጅግ የሚለያዩ ናቸው።

ከበዓለ ሃምሳ በፊትና በኋላ ስለ ሐዋርያዊው ጴጥሮስ የተጻፈው ታሪክ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የተነሳ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚገኘውን ለውጥ የሚያሳየን ማስረጃ ነው። በዚህ ክፍል የምንመለከተው ጴጥሮስ ከበዓለ ሃምሳ በፊት ምን ይመስል እንደነበረ ነው።

**ጴጥሮስ ከባዓለ ሃምሳ በፊት**

1. ሳያስብ በግብታዊነት የሚያደርግ ሰው ነበር ማቴ. 14፥28፣ 17፥47 ዮሐ. 21፥7
2. እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ነገሮች የሚታዩበት ነበር

ሀ. ልበ ሙሉ፥ ማቴ. 16፥22፣ ዮሐ. 13፥8 18፥10 ዓይነ አፋርና ፈሪ፥ ማቴ. 14፥30፣ 26፥69-72

ለ. ራሱን ወዳድና ራሱን መስዋዕት የሚያደርግ ፥ ማቴ 19፥27፣ማር. 1፥18

ሐ. አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ መገለጥ ሲኖረው፣ ሌላ ጊዜ መንፈሳዊ እውነቶች የማይገባው ሰው ዮሐ. 6፥68፣ ማቴ. 15፥15-16

መ. በክርስቶስ ያለውን እምነት ሁለት ጊዜ የመሰከረ ዮሐ. 6፥69 ማቴ. 16፥17 ክፍርሃት የተነሳ የካደ ጥፋተኛ ማር. 14፥67-71 ክርስቶስን በርቀት የተከተለ ማቴ. 26፥58

3. ከክፉ ሰዎች ጋር የተባበረ፦ ዮሐ. 18፥18
4. አላውቀውም ብሎ የካደ፦ ማር. 14፥70-71

በትንሳኤው ምሽት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠና ስለሚመጣው በቅድሚያ እንዲመለከቱ አደረጋቸው፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ በማለት እፍ አለባቸው (ዮሐ. 20፥22)። ብዙዎች ይህን ትእዛዝ የሚመለከቱት የመንፈስ ቅዱስ የዳግም ልደት ሥራ አድርገው ነው፤ ምክንያቱም ዳግም ልደትን የሚያስገኝ እርሱ ስለሆነ። ከላይ የጠቀስነው ድርጊት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስተካከል የሚያስችለውን ተግባር ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደፈጸመ የሚያረጋግጥ ነው። ቢሆንም በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን በመንፈስ ቅዱስ አላጠመቃቸውም። ከዚህ በኋላም

ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር በተገናኘ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ገና እንደሚመጣ ጠቅሶላቸዋል (የሐዋ. 1፥4፣8)።

(9). ደቀ መዛሙርቱ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት ከበዓለ ሃምሳ በፊት እንዴት መጠበቅ እንዲቻሉ የሚያስረዳው የትኛው መግለጫ ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ከማጥናታቸውም በተጨማሪ በየዕለቱ ለመጸለይ ወደ መቅደስ ይሄዱ ነበር።
ለ. ኃይሉ ባይኖርም መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር ነበር።
ሐ. እብዛኛውን ጊዜ ከኢየሱስ ለመማር ከእርሱ ጋር አብረው ነበሩ።

## በበዓለ ሃምሳ ዕለት

በመጨረሻም ኢየሱስ ተስፋ የሰጠው ቀን መጣ። ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች አማኞች በቆይታ ላይ በነበሩበት ክፍል ዓውሎ ነፋስ የመሰለ ድምጽ ከሰማይ መጥቶ የነበሩበትን ክፍል ሞላው። የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች ታዩዋቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ አረፈባቸው። ያን መለኮታዊ መገኘት ወደ ውስጥ ሲተነፍሱ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ባልተማሩት ልዩ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፤ የሚናገሩትንም ቃላት መንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸው ነበር (የሐዋ. 2፥1-4)።

ይህም ልክ መጥምቁ ዮሐንስና ኢየሱስ እንደሰጡት ተስፋ ነበር። በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ተጠመቁ (ማቴ. 3፥11፣ የሐዋ. 1፥5)። በአዲስ ቋንቋ እንደሚናገሩ ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸውን ቃላት ሲናገሩም እርሱ እንደተናገረው ተፈጸመ። (ማር. 16፥17)።

በኢየሩሳሌም ከየአካባቢው አገሮች የመጡ እግዚአብሔርን በሚፈሩ ብዙ አይሁዶች ነበሩ። የመጡትም የበዓለ ሃምሳን በዓል ለማክበር ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ከተሰበሰቡበት ከላይኛው ክፍል ድምጽ በሰሙ ጊዜ ምን ይሆን በማለት ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። እያንዳንዱ ሰው ቋንቋቸውን ሲናገር ስለሰሙ የተሰበሰቡት በመደነቅ ተገረሙ። "እነዚህ እንዲህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ እኛስ በየትውልድ አገራችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው እንዴት ነው? በማለት በመገረምና በመደነቅ ጠየቁ (የሐዋ. 2፥7-8)።

እንዳንዶችም ብዙ ወይን ጠጥተውና ሰክረው ነው በማለት አሾፉባቸው። ጴጥሮስ ግን ቆሞ ምን እንደሆነ ገለጸላቸው። ክርስቶስ ሕያው መሆኑንና ይህን መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ፤ የሰጠው ተስፋ ፍጻሜ እንደሆነ ነገራቸው።

ብዙዎቹም በመንፈስ ቅዱስ ስለተወቀሱ "ምን እናድርግ?" በማለት ተናገሩ። ጴጥሮስም "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይቅር እንዲባልላችሁ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን መንፈስ



ቅዱስንም ትቀበላላችሁ" አላቸው (የሐዋ. 2፥37-38)። በዚያኑ ዕለት ለጴጥሮስ መልእክት ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ሦስት ሺህ ሰዎች ተጠመቁ። ያም ቀን ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ቀን ሲሆን፥ በሌላም በኩል ቤተ ክርስቲያን የተወለደችበት ቀን ነበር (የሐዋ. 2፥1-41)።

(10). የሐዋ. 1 እና 2 ደግመህ አንብብ። ክርስቶስ ካረገ በኋላ መሪነቱን የተረከቡት የትኞቹ ደቀ መዛሙርት ነበሩ?

## ከበዓለ ሃምሳ በኋላ

የበዓለ ሃምሳ ኃይል ቀኑ ሲያልፍ አብሮ አልቆመም። ያዕለት የመንፈስ ቅዱስ ልዩ እንቅስቃሴ የሚሆንበት ዘመን መጀመሪያ ነበር። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፥ መንፈስ ቅዱስ አማኞች ልብ ውስጥ ለመምጣትና ለመኖር መንገድ ተከፈተለት።

በፍርሃት ምክንያት ጌታውን ክዶ የነበረው ጴጥሮስ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ስለ ክርስቶስ የማዳን ጸጋ ኃይለኛና ውጤታማ የሆነ ምስክርነት ለብዙ ሰዎች ለመስጠት በቃ።

ጴጥሮስ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ለተከናወነው ነገር በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው። ከዚህ በታች የቀረበውን ቀደም ሲል ከበዓለ ሃምሳ በፊት በሚለው ሥር ከቀረበው ጋር አወዳድር።

**ጴጥሮስ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ**

1. ኃይለኛ ሰባኪ ሆነ፤ እንዲሁም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ፦ የሐዋ. 1-5 እና 10-12
2. ስለ ክርስቶስ በድፍረት መስከረ - ዮሐ. 1-42፣ ማቴ. 16፥18፣ የሐዋ. 1-8
3. ተአምራትን አደረገ፦ የሐዋ. 3፥7፣ 5፥15 9፥34-40
4. ደፋርና ብርቱ ሆነ፦ የሐዋ. 4፥19-20፣ 5፥28-29፣ 40፣42
5. ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ምሳሌና ማበረታታት በመከራ ውስጥ ላሉ መበረታታት ምክንያት ሆኗል፦ 1ጴጥሮስ
6. ለቤተ ክርስቲያን ሐሰተኛ አስተማሪዎችንና ፌዘኞችን በተመለከተ መመሪያን ሰጥቷል፦ 2ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ኃይለኛ የሆነ መልእክቱን በበዓለ ሀምሳ ዕለት ከሰበከ በኋላ በኢየሩሳሌም የተጀመረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ፊልጶስ በተባለው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ዲያቆን ወደ ሰማርያ ደረሰ። ሰዎች የወንጌልን መልእክት በመቀበል በውሃ ተጠመቁ። ብዙ ተአምራት ቢፈጸምም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ማንም አልነበረም። ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ተላኩ። መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ

በአዲሶቹ አማኞች ላይ እጅ ጭነው ጸለዩላቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (የሐዋ. 8፥4-17)።

መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበል የሚቀጥለው ዘገባ ገና ጌታን የተቀበለው የጠርሴሱ ሳውል፥ ወደ ክርስትና በመመለስ በኋላም ጳውሎስ የተባባው ነበር። አናንያስ ለእርሱ በጸለየ ጊዜ ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፥ ታላቅ ሐዋርያ ሆኖ ወንጌልን ለአሕዛብ አደረሰ (የሐዋ. 9፥17)።

የበዓለ ሃምሳን በረከት ወደ አህዛብ ያደረሰው የመጀመሪያው ሰው ጴጥሮስ ሲሆን፥ ይህም መንፈስ ቅዱስ ያለ ሐዋርያው ፈቃድ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት በላከው ጊዜ ነበር። ለተሰበሰቡት አሕዛቦች ጴጥሮስ ወንጌል ሲሰብክ መልእክቱን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ። ልክ በበዓለ ሃምሳ ዕለት እንደሆነው በልሳን ሲናገሩ በመስማቱ ጴጥሮስ ተገረመ። በኋላም በአይሁድ ወንድሞች ፊት መከላከያ በሚያቀርብበት ወቅት፥ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሚያጠምቃቸው መጥምቁ ዮሐንስ እንዴት ተስፋ እንደሰጠ ጴጥሮስ አስታወሰ። ከዚያ ጥምቀት ጋር ነበር የአሕዛብን ልምምድ ያዛመደው (የሐዋ. 10፥1-11፤18)

ከሃያ ዓመታት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ከተማ ሲጎበኝ ደቀ መዛሙርቶችን በዚያ አገኘ። በመጀመሪያ የጠየቃቸው ጥያቄ፦ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" የሚል ነበር (የሐዋ. 19፥2)። መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ ያልሰሙ መሆናቸውን ተናገሩ። ጳውሎስም እነርሱን አስተማራቸው፥ ከዚያም በኢየሱስ ስም አጠመቃቸውና እጁን ጭኖ ፀለየላቸው። መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መጣ፥ እነርሱም በልሳን ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ (የሐዋ. 19፥1-7)።

ሐዋርያው ጴጥሮስና ጳውሎስ፥ ከያዕቆብ ከዮሐንስና ከይሁዳ ጋር የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመልበስ ነበር የክርስቲያን መመርያ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት በአዲስ ኪዳንን መልእክቶች ውስጥ ያስፈሩት። በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላታቸው የተነሳ የተቀበሉት ኃይለኛ ምስክርነታቸው፥ ዛሬም ለሰዎች ሕይወት አገልግሎትን እያበረከተ ነው።

(11). ከበዓለ ሃምሳ በፊትና በኋላ ያለውን የጴጥሮስ ልምምድ በማነፃፀር ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስፈር አዛምድ

| | | |
|---|---|---|
| ______ | ሀ. ብርቱና ጎበዝ | 1) ከበዓለ ሃምሳ በፊት |
| ______ | ለ. የማይረባ ምሳሌ | 2) ከበዓለ ሃምሳ በኋላ |
| ______ | ሐ. ወላዋይ ምስክር | |
| ______ | መ. ፈሪና ተቃዋሚ | |
| ______ | ሠ. ኃይለኛ መሪና ሰባኪ | |
| ______ | ረ. ፈሪና ከሀዲ | |
| ______ | ሰ. በስሜቱ የሚገፋፋ ችኩል | |
| ______ | ሸ. ምሳሌ የሆነ መንፈሳዊ መሪ | |



# የሃያኛው ክፍለ ዘመን አማኞች

***ዓላማ 5 የሃያኛውን ክፍለ ዘመን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ጋር በመገናኘት ዓላማውን ለመግለጽ።***

ከበዓለ ሃምሳ ዕለት እንሥቶ የመንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ መውረድ ሁል ጊዜ የነበረ ቢሆንም፣ በመጀመሪያዎቹ መቶ ዓመታት በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በጣም የተስፋፋ አልነበረም። የጥንቶቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ተርቱሊያን (160-220)፣ ኦሪገን (185-254)፣ እና ክሪሶስቶም የመሳሰሉት (400)፥ በበዓለ ሃምሳ ዕለት እንደነበረው የመንፈስ ቅዱስ መውረድና በልሳን መናገር እንደተፈጸመ በመጽሐፍ ጽፈዋል። ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ፥ በፕሮቴስታንት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ፥ ጊዜና እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ፥ አልፎ አልፎ በተነሱ ልዩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ከዚህም ጋር አብሮ በልሳን መናገርና ልዩ የምሥክርነት ችሎታዎች ታይተዋል።

በሐዋ. 2 ላይ ጴጥሮስ የኢዮኤልን ትንቢት በመጥቀስ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ታላቁንና አስገራሚውን የጌታን ቃን እንደሚቀድም በሐዋ. 2፥17-21 ላይ ይናገራል። ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቃል የተገባው "ጌታ አምላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ እንደሆነ ይናገራል (የሐዋ. 2፥39)። ይህም የሃያኛውን ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ያካትታል! ከዚህ የምንረዳው ታላቁና አስገራሚው የጌታ ቀን በቶሎ እንደሚመጣ ነው። በዚህ በያዝነውም ክፍለ ዘመን ያሉ ሰዎች ወደ ጌታ እንዲመለሱ በመጠራት ላይ ናቸው።

(12). በሐዋ. 1፥8 ላይ በተጻፈው መሠረት በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ የወረደው ለአማኞች ምን ለመስጠት ነው?

(13). በሐዋ. 2:38-39 ላይ በተፃፈው መሠረት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የሚቀጥለው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

ባሁኑ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የጀመረው በብዙ የዓለም ክፍሎች በተመሳሳይ ወቅት ነው። የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ለምሳሌ በአሜሪካ ውስጥ ካንሳስ በተባለ ስፍራ በሚገኝ አንድ የመፅሐፍ ቅደስ ትምህርት ቤት የነበሩ ተማሪዎች በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የጥንት ክርስቲያኖችን ልምምድ በማጥናትና በማየት ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቀት ያለው ልምምድ ይኖራቸው ዘንድ ጥማት አደረባቸው። ስለዚህ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ በሚገባ ማጥናት ጀመሩ። ለእምነታቸውና ለፀሎታቸው ምላሽ በመስጠት መንፈሳዊ ጥማታቸውን ለማርካት መንፈስ ቅዱስ ወረደ። በጄንዋሪ 1/1901 እ.ኤ.አ. የመጀመሪያው ተማሪ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፣ ከዚያም በኋላ ብዙዎች የመንፈስ ቅዱስን ሙላት አገኙ። በመንፈስ ቅዱስም እንደተጠመቁ መንፈስ እንደሰጣቸው በሌላ ቋንቋዎች ተናገሩ። መንፈሳዊ

እንቅስቃሴው ወደ ሌሎች ስፍራዎች እየተዛመተ በመሄዱ በ1906 መጀመሪያ ገደማ ከ1000 ሰዎች በላይ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

በ1906 ሆስተን በተባለ ሥፍራ የነበረ ሴይሞር የሚባል አንድ ጥቁር ሰባኪ ካሊፎርኒያ ወደ ተባለ ሥፍራ ለመስበክ ሄደ። ከዚያም በዚያው በካሊፎርንያ አዙሳ ጎዳና ሚሽን በተባለ ሥፍራ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ስብሰባው ያለማቋረጥ ቀንና ማታ ለሦስት ዓመታት ያዘል ቆየ። መንፈስ ቅዱስ ያለማቋረጥ ይፈስ ስለነበር በልሳን መናገርንና ተአምራትን ይፈጽም ነበር። ከዚያም መንፈሳዊ እንቅስቃሴው በመላው አሜሪካና ካናዳ እየተስፋፋ ሄደ።

በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በእንግሊዝ ሀገር፣ በኖርዌይ፣ በዴንማርክ፣ በስዊድን፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመንና በሕንድ አገር እንደነበረ ታውቋል። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ የነበረው የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ በኦክቶበር 1907 ወደ ቻይና ምድር መጣ። ይህን ምድር በረገጠ በአምስት ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ 700 ያኀሉ ተወላጆችና ሚሲዮናውያን በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ። በ1909 ይህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወደ ግብፅ፣ ወደ አንዳንድ የአፍሪካ አገሮችና ወደ ደቡብ አሜሪካ ተዛመተ።

በሃያኛው መቶ ዓመት አጋማሽ አካባቢ መንፈስ ቅዱስ በፈውስ ሀይል መንቀሳቀስ ጀመረ። ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያላቸው ወንጌላውያን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የተሳተፉባቸው ታላላቅ መንፈሳዊ ስብሰባዎችን በከተሞች አካባቢ አካሄዱ። ከአዲስ ኪዳን ዘመን ወዲህ በአደባባይ በሕዝብ ፊት የፈውስ ተዓምራቶች ተፈፀሙ። ይህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ደግሞ ዓለም አቀፍ ምስክርነት ነበረው።

እኛ ወዳለንበት ጊዜ ስንመጣ ደግሞ ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔርን መንፈስ መውረድ እየመሰከርን ነው። በዚህ በምዕተ ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ እንደሚታየው ይህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያናት ብቻ የተወሰነ አይደለም። አሁንም የምንመሰክረው በተለያዩ የወንጌላውያን እብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴው መቀጠሉን ነው። በአብዛኛው ትኩረቱ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይም ካሪዝማ ላይ በመሆኑ እንቅስቃሴው ያካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ በመባል ይጠቀሳል። ዋናው ቁም ነገር መንፈስ ቅዱስ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ልምምድን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲያገኙት ማድረጉና ይህም በመላው ዓለም ላይ እየተፈጸመ መሆኑ ነው። ይህም ነገር መንፈስ ቅዱስ እውነተኛይቱን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለእርሱ መምጣት ለማዘጋጀት የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደሆነ ይታመናል።

በበዓለ ሃምሳ ዕለት ጴጥሮስ የሰበከውን መልእክት ስንመለከት በርከት ያሉ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የሚያመለክት ነው። በላይ በሰማይ ድንቅ ነገሮችን



በታች በምድር ተዓምራትን በማሳየት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተው ይድኑ ዘንድ ዓለም አቀፋዊ ፍላጎትን ለመቀስቀስ ነው (የሐዋ 2:17-21 እና ማቴ 24:3-14 አነፃፅር)። በተጨማሪም ኢየሱስ በማቴ 24:14 ላይ ያቀረበውን እውነት ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ከሰበከው መልዕክት ጋር ስናነፃፅረው፣ በመንፈስ ቅዱስ መውረድና ዓለምን በወንጌል ለመድረስ በሚደረገው ጥረት መካከል ጠቃሚ የሆነ ግንኙነት መኖሩን ወደ ማመን እንድንደርስ ያደርገናል። ኢየሱስ ስለዚህ ሲናገር ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግስት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል ብሏል።

(14). በማቴ 24:3-14 በተፃፈው መሠረትና ከዚያ በላይ ባለው ጥቅስ መሠረት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደነገራቸው ምን በተፈጸመ ጊዜ ዳግም ምጽአቱ የከናወናል?

ሀ. ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን በመላው ዓለም ወንጌል ይሰበካል።
ለ. በመላው ዓለም የጦርነት ወሬ ይሰማል፤ ረሃብና የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል።
ሐ. "እኔ ክርስቶስ ነኝ" በማለት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ይመጣሉ።

(15). እስካሁን ባጠናነው መሠረት በአሁኑ ዘመን ያለው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር በማዛመድ ስናየው ዓላማው ምንድን ነው? (የሐዋ 1:8 ተመልከት)

በዚህ በመጨረሻው ዘመን ምድርን ያጥለቀለቀውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ተቀብለሃልን? እግዚአብሔር ባስቀመጠህ ስፍራ ለመመስከር ኃይልን ተቀብለሃልን? የወንጌልን መልእክት ለዓለም የመስጠት ሃላፊነትህን እየተወጣህ ነውን? ወንጌልን በመላው ዓለም የማድረስ ደቀ መዛሙርቱን የላካቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አሁንም ለአንተ ይሰጥሃል። ለሕዝቦች ምስክር ይሆን ዘንድ ወንጌል በመላው ዓለም እንደተሰበከ ኢየሱስ ዳግመኛ ይመጣል። ያንን መልዕክት አደራ የሰጠው ለእኛ ነው። የጌታችንን መመለሻ ለማፋጠን በውስጣችንና በላያችን በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሥራት መቻላችን ምንኛ ደስ የሚያሰኝ ክቡር የሆነ ሃላፊነት ነው!!

# የሙከራ ፈተና

መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል በተሰጠው ስፍራ በማስቀመጥ እመልከት።

_____1. ብሉይ ኪዳን የሚያተኩረው በመንፈስ ቅዱስ ተግባሮች ላይ ሳይሆን በአካላዊነቱ ላይ ነው።

_____2. ከበዓለ ሃምሳ ቀን ጀምሮ የፈሰሰውን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የተለማመዱትን ያህል የብሉይ ኪዳን አማኞች አልተቀበሉም።

_____3. በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ የመጣው ለእግዚአብሔር ልዩ የሆነ ተግባር እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው።

_____4. መንፈስ ቅዱስ ያለማቋረጥ ከእነርሱ ጋር ስለ መኖር ከብሉይ ኪዳን ምሳሌ የሚሆኑን ሳምሶንና ሳኦል ናቸው።

_____5. ዓመፀኛ ከሆነና ከማይታዘዝ ሰው መንፈስ ቅዱስ ይርቃል።

_____6. በመሳፍንት ዘመን እስራኤላውያን በመንፈስ ስለተመሩ ያለማቋረጥ የድል ጊዜ ነበር።

_____7. ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ምንም ማድረግ እንደማይችሉ የብሉይ ኪዳን ነብያት ለይተው ያውቁ ነበረ።

_____8. ከበዓለ ሃምሳ በፊት የመንፈስ ቅዱስ ዋና ትኩረት ኢየሱስ በመረጣቸው አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ላይ ነበር።

_____9. እንዱ ደቀመዝሙር ከበዓለ ሃምሳ በፊትና በኋላ የነበረውን ሕይወት ማጥናት ደካማውን ሰው ኃይለኛ ምስክር እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ እንዴት መለወጥ እንደሚችል ያሳያል።

_____10. ከበዓለ ሃምሳ ዕለት እንሥቶ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ እንደ ቀጠለ ነው።

_____11. እያንዳንዱ ሰው በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ ኢየሱስ ይመለሳል።

_____12. በአሁኑ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በዓለም ላይ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት በመድረሱ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ዳግም ምፅዓት የሚያዘጋጅ ይመስላል።

---



# የጥናቱ ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. ሁሉም መግለጫዎች የነቢያትን በመንፈስ ቅዱስ ላይ መመካት ቢያንፀባርቁም ሀ) እና ሐ) ከነቢያት አገልግሎት ይልቅ በግል ሕይወት ላይ በይበልጥ እንደሚያተኩሩ የሚጠቅስ ይመስላል። የነቢያትን ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መመካት ስለሚገልጥ እኔ የምመርጠው ለ) ነው።

1. ሀ. ቍጥር 17
   ለ. በሙሴ ላይ የነበረውን መንፈስ ወስዶና በእነርሱ ላይ አስቀመጠ (ከዚህም የተነሣ ያው በሙሴ ላይ የነበረው ኃይልና ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ለእነርሱም ተሰጠ)።

   ሐ. በዚህ ጊዜ ሁሉም ትንቢት ተናገሩ።

9. ሐ

2. ሀ. ዘልም ለመፍታት የበላይ ጠባቂ ለመሆን
   ለ. ከግብፅ ሲወጡ ሕዝቡን ለመምራት
   ሐ. የሕዝቡን ፍላጎት ለማሟላት እንዲችል ሙሴን ለመርዳት
   መ. ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ሕዝቡን ለመምራት
   ሠ. በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ የመንፈስን ችሎታ መስጠት የረጅም ጊዜ ልምምድ ነበር።

10. ጴጥሮስ

3. ከደካማ ነገድ ወገን እንደ ነበረና ከቤተሰቡም መካከል በጣም የተናቀና አነስተኛ እንደነበር።

11. ሀ. 2　　መ. 1　　ሰ. 1
    ለ. 1　　ሠ. 2　　ሸ. 2
    ሐ. 1　　ረ. 1

4. የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል በእርሱ ላይ መጣ።

12. በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ኃይል ለመስጠት

5. ውጤቱ ብርቱ ያደረገውና ወደ እርሱ መጥቶ የነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ (13:25.14:6.19:እና 15:14) ጥሎት ሄደ (ቁ.20)።

13. ጌታ ሰዎችን ወደ ራሱ እስከጠራ ድረስ ያም እስከ ታላቁና አስገራሚው የጌታ ቀን መምጫ ድረስ ተሰፋው እንደሚሠራ የሚያመለክት ነው።

6. የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ተለየ።

14. ሀ

7. መልስህ ከዚህኛው ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል። በኃጢያተኛ፣ አመፀኛና ታዛዥ ባልሆነ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ካዘነ በእግዚአብሔር የተመረጠውን ሰው እንኳ ትቶት ይሄዳል። በሰው ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ መኖር ሃላፊነትና ጥንቃቄ ላለበት ሕይወት የሚጋብዝ ነው።

15. የእንተ መልስ የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን እንደሆነ እምናለሁ። የ20ኛው ክፍለ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ዓላማው ወንጌል በመላው ዓለም ይሰብክ ዘንድ እና ለመመስከርም ኃይል ለማግኘት ነው። ለሰዎች ሁሉ ምስክር ይሆን ዘንድ በመላው ዓለም ወንጌል እንደተሰበከ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል።



# 8

## ትምህርት

# በመንፈስ ማምለክ

“እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል” (ዮሐ 4:24) በማለት ኢየሱስ ተናግሯል። እርሱ ይናገር የነበረው ለአንዲት ሳምራዊት ሴት ነበር። ቀደም ብሎም የእግዚአብሔርን ስጦታ ብታውቂና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑን ብትረጂ ኖሮ፣ አንቺው በጠየቅሽው፣ መለመን የሚገባሽ አንቺ ነበርሽ እርሱም የሕይወትን ውሃ ይሰጥሽ ነበር አላት (ዮሐ 4:10)።

ወደ አገልግሎቱ መጨረሻ አካባቢ ስለ ሕይወት ውሃ በተጨማሪ ይህንን ተናግሯል። “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል” (ዮሐ. 7:37-38)። ኢየሱስ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው እርሱ ከከበረ በኋላ ተከታዮቹ ስለሚቀበሉት ስለመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ሐዋርያው ዮሐንስ ይገልጻል (ቁጥሮ 39)። መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውን አገልግሎት ማለትም ከእማኙ ውስጥ እምልኮን ማፍለቅን ይፈጽማል። እውነተኛ እምልኮ የሚገለጠው ቅዱስ በሆነ በእግዚአብሔር ፍርሃትና ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን ከፍ ማድረግ፣ ትዕዛዛቱን መጠበቅና ለመንግሥቱ አገልግሎት ራስን አሳልፎ በመስጠት ነው።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ በኩል እግዚአብሔርን መቀበልና በመንፈሱም አማካኝነት ከእርሱ ጋር ሕብረት ለማድረግ ችሎታ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአሁኑ ዘመን ማብቂያ ላይና ለዘላለም በፍጹም ሕብረትና አንድነት ከክርስቶስ ጋር የሚሆኑ ሰዎችን በማዘጋጀት ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስለሚኖር እስከዚያ ቀን ድረስ እርሱን ለማምለክ፣ ለእርሱም ለመኖር እንሻለን። የዘላለም ሕይወት ይኖረን ዘንድ ራሱን ስለ እኛ አሳልፎ የሰጠውን ለማክበር የተሰጠን መብትና ዕድል እንዴት ታላቅ ነው! በውስጣችን ባለውና የሕይወት ውሃ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ በኩል እርሱን ለማምለክ ሥልጣን ተሰጥቶናል። እርሱን እናምልክ፣ እንፍራው፣ እርሱንም እናገልግል።

## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- እግዚአብሔርን መፍራት
- እግዚአብሔርን ማክበር
- እግዚአብሔርን ማገልገል
- ወደ እግዚአብሔር መጸለይ

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- እግዚአብሔርን በመፍራትና በመንፈስ በማምለክ መካከል ያለውን ግንኙነት መግለጽ።

- እግዚአብሔርን እንድናከብር መንፈስ ቅዱስ እኛን የሚረዳበትን መንገዶች መግለጽ።

- ከመንፈሳዊ አምልኮ ጋር በተገናኘ መልኩ እግዚአብሔርን የማገልገል አስፈላጊነትን መግለጽ።

- በመንፈስና በእውነት ማምለክ የሆነውን የግል የጸሎት ሕይወትንና በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስን ማጎልበት።

---

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ አንብብ፤ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹንም መልስ።

2. ክፍለ ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለህ ስትጨርስ የሙከራ ፈተናውን በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከው ካለ አስተካክል።

---



## የትምህርቱ ዝርዝር

### እግዚአብሔርን መፍራት

***ዓላማ 1 እግዚአብሔርን የማክበርን ወይም የመፍራትን አስፈላጊነት ከቃሉ ለመግለጽ።***

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ

ጠቢቡ ሰለሞን፡- "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" ሲል በምሳ 1:7 ላይ ተናግሯል። አንድ ሰው ይህንኑ ኃሳብ ሰፋ አድርጎ ሲያብራራ ጌታን መፍራት እግዚአብሔርን ከፍ በማድረግ ክብር መስጠት ከመሆኑም በላይ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው በማለት ተናገረ። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ ምን እንዳደረገ ለይተን እናውቅ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል።

የእግዚአብሔርን ታላቅ ክብር፣ የእርሱን ችሎታና ኃይል ስንመለከት፣ እርሱ በእርግጥ የሚያስፈራ እንደሆነ እንገነዘባለን። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ጥልቅ አክብሮትንና አድናቆትን የሚያካትትን ሃሳብ ያዘለ ነው። ይህም ለእርሱ ለመገዛትና እርሱንም ወደ መታዘዝ የሚመራ ነው። ይህም በኢሳያስ የአምልኮ ልምምድ ውስጥ ተገልጾ ይታያል።

(1). በኢሳ 6:1-8 የተጻፈውን ካነበብህ በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. ኢሳያስ ስለ ጌታ ያየውን ራዕይ የገለጸው እንዴት ነው?
ለ. ለዚህ ራዕይ ኢሳያስ የሰጠው ምላሽ እግዚአብሔርን በመፍራት ነው ወይስ ባለመፍራት?
ሐ. ኢሳያስ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ራሱን ያየው እንዴት ነበር?
መ. የነጻው እንዴት ነበር?
ሠ. ከተዘረዘሩት ቃላት ኢሳያስ ለራዕዩ የሰጠውን ምላሽ የሚገልጹት የትኞቹ ናቸው? *ፍርሃት፣ ራስን ማስገዛት፣ ግዴለሽነት*

መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን ስለ መፍራት የሚናገረው እንደ አስፈላጊና ልንሻው የሚገባ አድርጎ ነው። የዚህ እውነተኝነት እስራኤላውያን በኖሩበት በብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን ከጌታ ኢየሱስ ጋር የግል ግንኙነት ባለን በዚህ በአዲስ ኪዳንም ጭምር ነው። ይህም እውነት የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር እኛ እንድናከብረው ስለሚፈልግና በማንነቱና በአድራጎቱ በሕይወታችን የሚገባውን የክብር ስፍራ እንድንሰጠው ስለሚፈልግ ነው። ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደተራ ግንኙነት መቁጠር የለብንም። ወደ እርሱም ስንቀርብ አክብሮት በሌለው ሁኔታ መሆን የለበትም። እርሱ ዓለማትን ሁሉ የፈጠረ ልዑል አምላክ በመሆኑ በእኛ ዘንድ ያለማቋረጥ ሊመለክ ሊከበርና ሊመሰገን ይገባዋል።

## እያደገ የሚሄድ አክብሮት

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና ተዓምራዊ ምልክቶችን ባደረገ ጊዜ ፍርሃትና እድናቆትን ወደ ሰዎች ልብ አመጣ (የሐዋ 2:43)። ቤተ ክርስቲያንም እያደገች ስትሄድ በመንፈስ ቅዱስ እየተበረታታችና እየተጠናከረች፣ ጌታንም በመፍራት ዘኖረች መጠን በቁጥር እየበረከተች ሄደች (ዮሐ 9:41)።

ጌታን መፍራት የሚለው ሃሳብ የሚያካትተው ምን እንደሆነ ቀረብ ብለን እንመልከት። ጌታን መፍራት የሚመጣው ስለሕያው እግዚአብሔር ካለን ሃሳብ ነው። ቅዱስ ፍርሃት በውስጣችን አለ፤ ይህም ቅዱስ የሆነ ፍርሃት የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንድናከብር፣ ትዕዛዛቱን እንድንጠብቅ፣ ቅድስናውንና ክብሩን እንድናደንቅና ክክፉ ነገር እንድንመለስ ያደርገናል (ዘፍ 22:12 1ሳሙ 12:14:20-25 ኢዮብ 28:28 መዝ 111:10 ተመልከት)። እግዚአብሔርን እንደሚገባቸው የሚፈሩ ሰዎች በኢየሱስ ሕይወት ምሳሌነት እንደ ምናየው አምላካዊ ፍርሃት ለእርሱ በአክብሮት መገዛትን ያመጣል (ዕብ 5:7)። ለአምላክ ያላቸውን ፍርሃት ወይም አክብሮት በቅድስና ኑሮ እንዲገልጡ ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞችን ይመክራል (2ቆሮ 7:1፣ ፊል. 2:12)።

የሃናንያና የሰጲራ ምሳሌ እግዚአብሔርን ማክበርና ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ማስጠንቀቂያ ነበር። ለመንፈስ ቅዱስና አብረዋቸው ለነበሩት ክርስቲያኖች በመዋሸታቸው የእግዚአብሔር ፍርድ መጣባቸውና ወድቀው ሞቱ (የሐዋ 5:1-11)።

(2). ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የሰጠችው ምሳሌ ምን ነበር? (የሐዋ. 5:5-11 ተመልከት)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ፦ "እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ! ይህ ሁሉ ተስፋ የተሰጠው ለእኛ ስለሆነ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ከማናቸውም ነገር ራሳችንን እናንፃ። እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችን ፍጹም እንዲሆን እናድርግ" ይላል (2ቆሮ 7:1)። የኤፌሶን ክርስቲያኖችንም ለክርስቶስ ክብር ብለው እንዱ ለሌላው እንዲታዘዝ ደግሞ ይነግራል (ኤፌ 5:21)።

በእግዚአብሔር ፊት መሆንና ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት ለስጋ ፍጹም እንግዳ ነገር ነው። ኢሳያስ ከኃያሉ እግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ራሱን ባስተያየ ጊዜ ንጹህ ባለመሆኑ በፍርሃት ተሞልቶ ነበር። ከመሠዊያው የእሳቱ ፍም በነካው ጊዜ ግን ፈጣሪውን ሲያመልክ በፍርሃት ራሱን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ተለወጠ (ኢሳ 6:5-8)።

በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔርን የማክበር ፍላጎታችን የሚፈጠረው መንፈስ ቅዱስ በሚነካን ጊዜ ነው፤ እኛም እራሳችንን ለእርሱ እሳልፈን በምንሰጥበት ጊዜ እየተጠናከረ ይሄዳል። በዙፋኑ ዙሪያ ሆነው የማያገለግሉ



በእርሱ ፊት በመሆናቸው እየተደሰቱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ ይጮሃሉ (ኢሳ 6:3 ራዕይ 4:8)።

ኢሳያስ በመሲሁ ላይ ስለሚያርፈውና ጌታን መፍራት ስለሚታይበት ሰባት እጥፍ መንፈስ ይናገራል።

> የእግዚአብሔር መንፈስ፣
> የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣
> የምክርና የኃይል መንፈስ
> የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል
> እግዚአብሔርን በመፍራት ደስ ይለዋል። (ኢሳ 11:2-3)።

የጌታ መንፈስ አሁን በእኛ ውስጥ ስለሚኖር የእርሱን ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ምክር፣ ኃይልና እውቀት በእኛ ውስጥ ሆኖ እንዲገለጥ ሲያደርግ ማየት እንችላለን። በመንፈስ ቅዱስም ዕርዳታ እግዚአብሔርን መፍራትና ማክበርን እንማራለን። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የምናገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ቅርበት ወደ እርሱ እየቀረብን በሄድን ቁጥር ይበልጥ እግዚአብሔርን እያከበርን እንድንሄድ ያደርገናል።

## እግዚአብሔርን ማክበር አስፈላጊነት

ኃጢአተኞች እግዚአብሔርን እንደማይፈሩ ጳውሎስ በሮሜ 3:18 ላይ ይናገራል። ከሌሎች ኃይሎች በላይ ሊፈራ የሚገባው ቢኖር ኃያሉ እግዚአብሔር ነው። የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ ስለዚሁ ሲናገር፦

> "የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን በኃጢአት ጸንተን ብንመላለስ፣ ከእንግዲህ ለኃጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፤ የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሔርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ ነው። የሙሴን ሕግ የናቀ ማንኛውም ሰው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ከመሰከሩበት ያለ ምሕረት ይገደል ነበር። ታዲያ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደተራ ነገር የቆጠረ፣ የጸጋንም መንፈስ ያክፋፋ እንደምን ያለ የባሰ ቅጣት ይገባው ይመስላችኋል? "በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ያለውን እናውቀዋለንና፤ ደግሞም፣ "ጌታ በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል" ይላል። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው።" (ዕብ 10:26-31)።

ጴጥሮስ "እግዚአብሔርን ፍሩ ንጉስን አክብሩ" በማለት ጽፎአል (1ጴጥ 2:17)። መሆን የሚገባውም እንደዚህ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ስለ እኛ ምን እንደሚሰማው ሳናውቅ ወይም ምን እንደሚያደርገን ግራ በመጋባት እርሱን ከመፍራት የተነሣ በስጋት እንኖራለን ማለት እይደለም። በከፍተኛ አክብሮት የምንቀርበው አባት ሆኖ ለእኛ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦልናል። መንፈሳዊ አምልኮ የሚጀምረው እግዚአብሔርን በማክበር

ነው። ጌታን ከፍ ከፍ ለማድረግና ለእርሱ ለመታዘዝ ራሳችንን እሳልፈን እንድንሰጥ የሚያደርገን ለእርሱ ያለን እክብሮት ነው።

(3). ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የብሉይና የአዲስ ኪዳን ክፍሎች እግዚአብሔርን ስለመፍራትና ስለማክበር ምን እንደሚናገሩ በአጭሩ ግለጽ።

ሀ. ዘፀ. 20:20
ለ. ዘዳ. 5:29
ሐ. ኢዮ. 28:28
መ. መዝ. 19:9
ሠ. መዝ. 33:18-19
ረ. መዝ. 85:9
ሰ. መዝ. 103:11
ሸ. ምሳ. 14:27
ቀ. ሚል. 4:2
በ. ሉቃ. 1:50
ተ. ፊል. 2:12-13
ቸ. ራዕ. 11:18

## እግዚአብሔርን ማክበር

### በመንፈስና በእውነት

*ዓላማ 2 እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ ማለት ምን እንደሆነ ለመግለጽ።*

በክፍለ ትምህርቱ መጀመሪያ ላይ በጠቀስነው ታሪክ ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ያደረገው ንግግር በቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ ምሳሌ የሚሆነውን እስቀምጦእል።

"በእውነት የሚሰግዱ ለእብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። አሁንም መጥቶእል እብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል። እግዚእብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስባ በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል" በማለት ነበር የተናገረው (ዮሐ 4:23-24)።

በኋላም ኢየሱስ የእውነት መንፈስ በሚመጣበት ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው። ከዚያም እንዲህ እለ፦ "የእ ውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ እይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል።



የእብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው። እንግዲህ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል ያልኋችሁ ለዚሁ ነው" በማለት ተናገረ (ዮሐ. 16:13-15)።

ለእግዚአብሔር አምልኮአችንን በምንገልጽበት ጊዜ ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ የመጣው ጌታን እንድናከብር ሊረዳን ነው። የእርሱን ግርማ፣ ሞገስና ውበት ለእኛ በማሳየት በአምልኮአችን እርሱ እኛን ይረዳናል። የጌታን የቅድስናውን ውበት በመረዳት በምናመልክበት ጊዜ ስለ ሥነ ምግባራዊ ልቀቱና ስለንጽህናው እርሱን እናመሰግናለን። ምክንያቱም ቅድስናው ለሌቹን የእግዚአብሔር ባህርያቶች ሁሉ የሚጠቀልል ነው።

የተለያዩ የቀለማት ዓይነቶች በፀሐይ ብርሃን ውስጥ በአንድነት ተጣምረው እንደሚፈነጥቁ የእግዚአብሔርም ባሕርያት በሙሉ በቅድስና ተጠቃለው ይገለጣሉ። እርሱ ብቻ ክፋት ፈጽሞ የሌለበት ቅዱስ ነው (1ሳሙ 2:2)። ሥራዎቹ ማንነቱን የሚገልጹ እንደመሆናቸው፣ የሚሠራቸው በሙሉ ትክክል ናቸው። ልጁን በመስጠትና በጸጋው ብቻ ወደራሱ ሊያቀርበን ስለመረጠ የሕዝቡን ውዳሴ እንደሚቀበልና የልባቸውን ምኞት እንደሚሰጥ በማወቅ እክብሮት በተሞላበት እምነት በየዕለቱ ወደ እርሱ መቅረብ እንችላለን። በመንፈስ ቅዱስ ካልተገለጠልን በስተቀር ስለ እውነተኛው ቅድስና ምንም ሃሳብ አይኖረንም።

ክርስቲያን በሆንኩባቸው በመጀመሪያ ጊዜያት በጣም አይን አፋር ስለነበርሁ በሕዝብ ፊት ቆሞ ማገልገል ገና ሳስበው በጣም ያስፈራኝ ነበር። ብቻዬን በቤቴ አኮርዲዮን ደህና አድርጌ እጫወታለሁ። ሰዎች በተሰበሰቡበት ስፍራ ለመጫወት ግን ስለሚያርበተብተኝ አንድ መዝሙር እንኳን ጨርሼ መጫወት አልችልም ነበር ።

ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቅሁ። መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ በመጣበት ምሽት በሺህ በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ቆሜ ለመጫወት እንደምችል ተሰማኝ። ስለዚህ በእሁድ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ ለመጫወትና ለመዘመር ተስማማሁ።

በአኮርዲዮን የምዘምርበት ጊዜ ሲደርስ ግን መንፈስ በእኔ ላይ በወረደበት ጊዜ የተሰማኝ ድፍረት ጠፋና መንቀጥቀጥ ጀመርሁ። ውድቀት በፊቴ የሚጠብቀኝ መሰለኝ፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመተማመን ወደ መድረኩ ወጣሁ። አኮርዲዮን መጫወት ስጀምር እንደገና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለተሰማኝ እየተጫወትኩ መዘመር ቻልኩኝ። ቢሆንም መዝሙሩን ስጨርስ አንድ የተለየ ነገር እንደነበር ተረዳሁ። በአኮርዲዮን ጨዋታዬና በመዝሙር ችሎታዬ የተደሰተ ማንም ያለ አይመስልም። ከጉባኤው መካከል አብዛኞዎቹ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው እጆቻቸውን ወደ ላይ አንስተው ነበር። መንፈስ ቅዱስ እየተጠቀመብኝ ነበር ክብሩን ግን የተቀበለው ጌታ ነበር።

ባለፈው ክፍል ትምህርት ላይ እንደገለጥነው መንፈስ ቅዱስ ያለ ማቋረጥ ካረፈባቸው ጥቂት የብሉይ ኪዳን ባለታሪኮች አንዱ ዳዊት ነው። የዳዊት መዝሙሮች እግዚአብሔርን ሊያከብር መንፈስ በእርሱ ላይ እንደ ሚንቀሳቀስ የሚያንጸባርቁ ናቸው። መዝሙሮቹ መልካም ነገሮችን ሁሉ በልግስና የሚሰጠውን ኃያሉን እግዚአብሔርን በማመስገን የተሞሉ ናቸው። የእርሱን ውበትና ራሱን መሥዋዕት ማድረጉን በማሰብ የጌታችንና የአዳኛችንን ስም ድምጻችንን ከፍ አድርገን በምስጋና ለማክበር፣ መንፈስ በእኛ ላይ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ መዝሙሮቹ የሚያሳዩ ናቸው።

(4). እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ለማምለክ ከሚከተሉት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መታዘዝ
ለ. ምስጋና
ሐ. ድፍረት
መ. ቅድስና
ሠ. አክብሮት
ረ. በመንፈስ መሞላት
ሰ. የአደባባይ አገልግሎት

## በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ

*ዓላማ 3 በመንፈስ ቋንቋ የማምለክን ሁለት መንገዶች ለመዘርዘርና የእያንዳንዱን ጥቅም ለመግለጽ።*

መንፈስ ቅዱስ የቅድስናን ውበት ለአማኞች በሚገለጥበት ጊዜ ይህንን ውበት ለመግለፅ ቃላት ያጥሩቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ተቀባይነት ያለውን አምልኮ በእኛ አንደበት ለመግለጽ ቃላቶችን ማግኘት ያቅተናል። መንፈስ ቅዱስ እንደገና የመንፈስን ቋንቋ በመስጠት ይረዳናል።

*በመንፈስ መፀለይ፡-* አንድ ጓደኛችን ለብዙ ዓመታት የመንፈስ ቅዱስን ቋንቋ እንደተቃወመ ነገረን። ቢሆንም የመንፈስ ቅዱስን ሙላት አጥብቆ የሚፈልግና እግዚአብሔርን በተመኘው መጠንና መንገድ ለማምለክ እንዳልቻለ ይናገር ነበር። በመጨረሻ ምንም አጥጋቢ መልስ እንዳላገኘ በተረዳ ጊዜ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት እንዳለበት ተገነዘበ። "የመንፈስ ሙላትን ስጠኝ። የማልረዳውን ቋንቋ መናገር አይደለም" እያለ አጥብቆ እግዚአብሔርን ይለምን ነበር።

ከመጀመሪያው በመንፈስ የማምለክ ልምምዱ በኋላ የተሰማውን ሲመሰክር ለእግዚአብሔር ስመናገር ይሞክር የነበረውን ሁሉ የሚያፈስ ምንጭ በመንፈሱ ውስጥ እንደፈለቀ የተሰማውን መስከረ። ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት በማምለኩ እርካታ እንዳገኘም መስከረ።

*በመንፈስ መዘመር፡-* መዝሙር እግዚአብሔር የሚከበርበት ዋናው ክፍል ነው። አንድ ሰው እንደተናገረው መዝሙር ወይም መንፈሳዊ ሙዚቃ



የነፍስ ቋንቋ ነው። መንፈሳዊ መዝሙሮችን ለጌታ እንደንዘምር መጽሐፍ ቅዱስ ያሳስበናል።

> በመዝሙርና በውዳሴ በመንፈሳዊም ዝማሬ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፣ በልባችሁ ለጌታ ተቀኙ፣ አዚሙም። በዚህም እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር ሁልጊዜ አመስግኑ። (ቆላ. 5:19-20)

> የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፣ ተመካከሩ፣ በመዝሙርና በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ (ቆላ. 3:16)።

መንፈሳዊ መዝሙሮችና መንፈሳዊ ዜማ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጹና ለማያምኑ ለዎች ምስክር የሚሆኑ ናቸው (1ቆሮ 14 ተመልከት)። በመንፈስ መዘመር ወይም መንፈሳዊ መዝሙር ውስጣዊ ደስታችንን፣ ስሜታችንን፣ ምስጋናችንንና አክብሮታችንን በመንፈስ ቋንቋ ለመግለጽ ይረዳናል። ለአምልኮአችን ሁለቱም አስፈላጊ ነገሮች ሲሆኑ ሁለቱም በመንፈስ የተቀቡ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ሲገልጽ፡- "በመንፈሴ እፀልያለሁ በአእምሮዬ ደግሞ እፀልያለሁ በመንፈሴ እዘምራለሁ በአዕምሮዬ ደግሞ እዘምራለሁ" ይላል።

(5). በመንፈስ ቋንቋ የምናመልክበትን ሁለቱን መንገዶች በመዘርዝር የእያንዳንዱ ጥቅም ግለጽ።

ሀ. ________________________________

ለ. ________________________________

ስታንሌይ ኤም ሆርትን የተባሉ ሰው በመጽሐፋቸው ላይ እንዳስፈሩት "የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በራሳቸው ጌታን ለማመስገንና ለማክበር ብቃት እንደሌላቸው ያውቁ ነበር። በመንፈስ መዘመርን፣ በመንፈስ መፀለይን፣ የመንፈስን ስጦታዎችና አገልግሎቶች በጉጉት ይጠብቁ ነበር። በየዕለቱ በመንፈስ በመመላለስ ኖሩ" በማለት ተናግረዋል (ሆርትን 1976፡ ገፅ 12)።

## እግዚአብሔርን ማገልገል

*ዓላማ 4 እግዚአብሔርን በማገልገልና በመንፈሳዊ አምልኮ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ።*

አምልኮ ተብለው የተተረጎሙት አንዳንድ የግሪክ ቃላቶች አገልግሎት በመባልም ሊተረጎሙ ይችላሉ። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን በሮሜ 12:1 ላይ የተጻፈው ነው።

እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለአእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው።

"ሌላ ትርጉም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ..."ብሎ ይገልጸዋል።

እግዚአብሔርን እንድታገለግል መንፈስ ቅዱስ ከሚረዳህ መንገዶች አንዱ ሙሉ በሙሉ ራስህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ እንድትሰጥ በማስቻል ነው። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ተመሳሳይ አባባልን ተጠቅሟል፡ "እኛ በእውነት የተገረዝን በእግዚአብሔር መንፈስ የምናመልክ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የምንመካ፣ በሥጋም የማንታመን ነንና" ይላል።

ሃና በመቅደስ ያደረገችው ጾምና ጸሎት ሁለቱም በተለያዩ ትርጉሞች *ማገለገልና ማምለክ* ተብለው ይጠራሉ። በታላቅ ትህትናና በእንባ ጌታን ስለማገልገል ጳውሎስ ሲናገር "ማገልገል" "ማምለክ" በሚለው ቃል ሊተረጎም ይችላል።

መጾምና መጸለይን እንዲሁም ማንባትን ከአምልኮ ጋር አያይዞ ማየቱ አስቸጋሪ ባይሆንም አምልኮ ግን ከዚያ በላይ ነው። በዕብ 9፡14 ላይ፡- "በዘላለም መንፈስ አማካኝነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናገለግል (እንድናመልክ) ሕሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን" ብሎ ይናገራል። በሌላ አባባል በየዕለቱ በመንፈስ የምንኖረው ኑሮ እግዚአብሔርን የማምለክ ድርጊት ነው። የምንናገረውና የምናደገው ሁሉ የመንፈሳዊ አምልኮ መንገድ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በታች የሰፈሩትን ቃላት ለቆላስያስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ ሐዋርያው ጳውሎስ ለማለት የፈለገው ይህንኑ ነበር።

"በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ ለጌታ እንደምታደርጉት ቆጥራችሁ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፤ ከጌታ ዘንድ እንደብድራት የምትቀበሉት ርስት እንዳለ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነው" (ቆላ. 3፡17፣ 23-24)።



(6). ሮሜ 12 ላይ የተጻፈውን በማንበብና በሕይወታችን በሥራ በመተርጎም ስለ መንፈሳዊ አምልኮ፣ አንዳንድ ነገሮችን ለመማር እንችላለን። በግራ በኩል አታድርጉ የሚለው የሰፈረ ሲሆን አድርጎ የሚለውን በቀኝ በኩል በተሰጠው ስፍራ ሙላ።

| አታድርጉ | አድርጉ |
|---|---|
| ሀ. ይህን ዓለም አትምሰሉ (ቁ.2) | |
| ለ. ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ አታስቡ (ቁ.3) | |
| ሐ. ከትጋት ወደ ኋላ አትበሉ (በንፍናን አስወግዱ) (ቁ.11) | |
| መ. አትኩራሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ (ቁ.16) | |
| ሠ. ክፉን በክፉ አትመልሱ (ቁ.17) | |
| ረ. አትበቀሉ (ቁ.19) | |

(7). በሮሜ 12 ላይ የተጻፈው፣ በተጨማሪ እንዴት ማገልገል እንደሚገባን ይነግረናል። ከቁጥር 6-8፣ 20 ላይ በተጻፈው መሠረት ዓረፍተ ነገሩን የተሟላ አድርግ።

ሀ. የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ ____________
ለ. ማገልገል ከሆነ ____________
ሐ. ማስተማርም ከሆነ____________
መ. መምከር ከሆነ ____________
ሠ. ለሌላቸው መለገስ ከሆነ____________
ረ. ማስተዳደር ከሆነ ____________
ሰ. ምሕረት ማድረግ ከሆነ ____________
ሸ. ጠላትህ ቢራብ ____________
ቀ. ጠላትህ ቢጠማ ____________

ኢየሱስ የመንፈሳዊ አምልኮን ትርጉም በአገልግሎት ውስጥ ምን እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረው በማቴ 25፡31-46 ላይ ስለ በጎችና ፍየሎች በሰጠው ምሳሌ ላይ ይገኛል። የሌሎችን ችግር እንድናቃልል እርሱ እኛን ወደ ዓለም ልኮናል። እኛ ከእርሱ የተቀበልነውን የሕይወት ውሃ እንዲጠጡ ልንሰጣቸው ይገባል። በኃጢአት ለጠፉትም የሕይወት እንጀራ የሆነውን ዘላለማዊ ቃሉን ልናካፍላቸው ይገባል። ለጌታ እንደምናደርገው አድርገን በአካላዊ ፍላጎታቸውም በኩል ደግሞ ልናገለግላቸው ይገባል። ይህ መንፈሳዊ አምልኮን በተግባር መተርጎም ነው።

(8). በማቴዎስ 25፡31-46 ላይ የተጻፈውን በጥንቃቄ አንብብ። ከዚያም መግለጫውን የተሟላ የሚያደርገውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

በዚህ ምንባብ ውስጥ ከፍርድ መሠረት የሆነው
- ሀ. ለተመለከቱት ችግሮች አድማጮች የሰጡት ምላሽ ለመማር ወይም
- ለ. እውቀት ለማግኘት የአድመጮች ችሎታ ማነስ

ሽልማት ለተቀበሉት የሰው ልጅ የነበረውን ምላሽ ከማየት የምንረዳው
- ሐ. ድነትን ለምግኘት አንድ ሰው በትጋት መሥራት እንዳለበት
- መ. ሌሎችን በችግራቸው ማገልገል እርሱን ማገልገል እንደሆነ

ለቅጣቱ አፈጻጸም መሠረት የሆነው
- ሠ. ሰው ያደረገው ነገር፣ ሊያደርግ ከሚችለው ጋር ተመዛዝኖ ነው።
- ረ. ለክርስቶስ እንደሚያደረግ አድርጎ ለሰዎች ችግር ምላሽ አለመስጠትን ነው።

በዚህ ሃሳብ በሚቀሰቅስ ምሳሌ ውስጥ ኢየሱስ ሊናገር የፈለገው
- ሰ. አምልኮ እንደ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር በተግባር የሚያሳ ይበት ካልሆነ በቀር የሞተ ነው።
- ሸ. አምልኮ በተግባር ቢደገፍም ባይደገፍም በማንኛውም መልኩ ተቀባ ይነት አለው።

## ወደ እግዚአብሔር መጸለይ

አዲስ ኪዳን በመንፈስ ስለ መጸለይ የሚያስተምረውን መንገድ ከተከተልህ ጸሎትህ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል። "በጸሎትና በልመና ሁሉ፣ በማንኛ ውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ" (ኤፌ.6:18) በማለት ጳውሎስ ይናገራል። ይህ በመንፈስ መጸለይ ብሎ ስለሚጠራው ሰፋ ያለ ሀሳብን ያዘለ ነው። ጳውሎስ "በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለፍሬ ነው። ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ? በመንፈስ እጸልያለሁ፤ በአእምሮዬም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ" (1ቆሮ 14:14-15) በማለት ይናገራል። እነዚህ ሁለቱም በመንፈስ መጸለይ ሊሆኑ ይችላሉ። እዚህ ላይ በተጻፈው መሠረት መጸለይ ልመናን ከማቅረብ በተጨማሪ ማመስገንና ውዳሴን ማቅረብን ጭምር የሚያካትት ነው (ቁ. 16)።

በማቴ 6:9-13 ላይ *የጌታ ጸሎት* ብለን በምንጠራው በጸሎት ውስጥ ያለውን የመንፈሳዊ አምልኮ ትርጉምን አስተምሮናል።

> በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግስትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን። የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን። በደላችንን ይቅር በለን፣ እኛም የበደሉንን የቅር እንደምንል። ወደ ፈተናም አታግባን፣ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ። መንግስት ያንተ ናትና፣ ኃይልም፣ ክብርም፣ ለዘላለሙ አሜን።

የዚህን ጸሎት የመጀመሪያ ሀረጎች በመመልከት ስለ መንፈሳዊ አምልኮ ከተናገርነው ጋር እንዴት ግንኙነት እንዳላቸው እንመለከታለን።



## ስምህ ይቀደስ - አክብሮት

***ዓላማ 5 መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምን እንደሚል ለመጥቀስና ይህንን ከእርሱ ጋር ካለን ግንኙነት ጋር ለማገናኘት።***

የጌታችን ጸሎት የሚጀምረው ለእግዚአብሔር ስም ሊሰጥ ስለሚገባው መንፈሳዊ ክብር ለይቶ በማስረዳት ነው። እግዚአብሔር በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ፣ ለቅድስና ኑሮ መለኪያውን በሰጠ ጊዜ ስሙ መከበር እንዳለበት አጥብቆ ገልጾአል። "የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ያለአግባብ አታንሳ፤ እግዚአብሔር ስሙን ያለአግባብ የሚያነሳውን በደል አልባ አያደርገውም" ይላል (ዘፀ.20:7)።

ወደ መንገድ ወጣ ብለህ የዓለም ሰዎች የሚነጋገሩትን ብትሰማ የጌታን ስም የማክበርን አስፈላጊነት እንድትረዳ ያደርግሃል። በምትዘዋወርበት ስፍራ ሁሉ የቅዱሱን የእግዚአብሔር አብንና የልጁን የኢየሱስን ስም ሰዎች በከንቱ ሲያነሱ ትሰማለህ።

ስሙ ቅዱስ ነው። የኢየሱስ ስም ሲጠራ ሲሰሙ አጋንንት ይንቀጠቀጣሉ (ሉቃ. 10:17፤ የሐዋ. 16:18 ተመልከት)። ድነት የሚገኘው በኢየሱስ ስም ብቻ ነው (ሐዋ. 4:12)። ፊልጵ. 2:6-11 ከስም ሁሉ በላይ የኢየሱስን ስም ለምን ማክበር እንዳለብን ይገልጻል።

> እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።
>
> *ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።*

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ጌታን በአንድነት ያመልኩ በነበሩ አማኞች ላይ የኢየሱስ ስም የሚሰጣቸውን ትርጉም አንድ በአንድ መግለጽ ሲጀምሩ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ። አንዱ የእግዚአብሔር ሰው ጮኾ በማለት "የኢየሱስ ስም ድንቅ ነው! ስሙ አማኑኤል፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" በማለት ተናገረ። ሌላው ሲመልስም "ስሙ አጽናኝና የሰላም አለቃ ነው" ሲል፤ ሌላው ደግሞ "ስሙ አዳኝ፣ አጥማቂና ፈዋሽ ነው" በማለት፣ የኢየሱስ ስም ምን ትርጉም እንደሚሰጣቸው መናገራቸውን ቀጠሉ። በእርግጥ የእርሱ ስም ምስጋናና ውዳሴ የሚገባው ነው! የእርሱ ስም የተቀደሰ ነው።

(9). **ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ እያንዳንዳቸው ስለ ኢየሱስ ስም የሚናገሩትንና በግልህ ለአንተ ምን ማለት እንደሆኑ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።**

ሀ. **ኢሳያስ** 9:6
ለ. **ማርቆስ** 16:17
ሐ. **ዮሐንስ** 1:12
መ. **ዮሐንስ** 14:13-14፡ 16:24
ሠ. **የሐዋ**.3:16 **ያዕ**.5:14
ረ. **የሐዋ**.4:12 **ሮሜ** 10:13
ሰ. **ራዕ** 19:16

## *መንግሥትህ ትምጣ - ክብር*

### *ዓላማ 6 መንግስቱ እንዲመጣ በማፋጠን እግዚአብሔርን በማክበር እንዴት መሳተፍ እንደምትችል ለመግለጽ።*

ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል የሰበከው ስብከት ዋና መሪ ሃሳብ መንግሥተ ሰማይ የሚል ነው። "መንግሥተ ሰማይ በእርሻ ውስጥ የተደበቀ ሀብት ትመስላለች፤ አንድ ሰው ባገኛት ጊዜ መልሶ ሸሸጋት፤ የተነሳ ሄዶ፣ ያለውን ሁሉ በመሸጥ ያንን የእርሻ ቦታ ገዛ" በማለት ኢየሱስ አስተማረ (ማቴ. 13:44)።

በምሳሌው ውስጥ ያለው ሰው ኢየሱስ ሲሆን እርሻው ዓለም ነበር። ሀብቱም መንግግሥቱ ነበር። ኢየሱስ ዓለምን የገዛው ውድ በሆነው ደሙ ነበር፤ ነገር ግን ገና የራሱ ንብረት አድርጎ አልወሰደውም። ከዓለም ዓይን የተሸሸገው ሀብት፣ መንፈስ ቅዱስ አሁን በአማኞች ልብ ውስጥ ፍጹም በማድረግ ላይ ያለው መንግሥቱ ነው። ክርስቶስ መንግሥቱን ለማቋቋም በሚመለስበት ጊዜ እነርሱ ገዢ እንዲሆኑ በማዘጋጀት ላይ ነው።

ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ስለሚመጣው ስለ ክርስቶስ ክብር ሲናገር "ዓይን ያላየው፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቷል" (1ቆሮ. 2:9) ይላል። ቀጥሎም በቁጥር 10 ላይ "እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል" በማለት ይናገራል። አእምሮአችን ከክርስቶስ ጋር ፊት ለፊት የምንገናኝበትንና መዋጀታችን ሁሉ ሲፈጸም የምንቀበለውን በረከት፣ ተድላና ደስታ በመናፈቅ ቢዝልም ስለሚገለጠው ክብር በቅድሚያ በጥቂቱ እንድንመለከት ለማድረግ እግዚአብሔር መጋረጃውን ገልጦአል (ራዕይ 21 እና 22)። ስለዚህም የእግዚአብሔርን የማዳን ፕሮግራም እስኪፈጸም በናፍቆት ብንጠብቀው የሚያስደንቅ አይደለም።

(10). *የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ለማፋጠን ድርሻ እንዳለህ ታውቃለህ? ማቴ*.24:14 **ከዚያም ማቴ**. 9:37-38 **እና ሉቃስ** 10:2 **ላይ** የተጻፈው ካነበብህ በኋላ የመንግሥቱን መምጫ ለማፋጠን እግዚአብሔርን በማክበር እንዴት ተሳትፎ ማድረግ እንደምትችል ግለጽ።



ኢየሱስ መንግሥቱን ሲመሠረትና እኛም ከመላዕክቱ ጋር በዙፋኑ ዙሪያ ሆነን ስንዘምር ያ ቀን ምንኛ ደስ የሚያሰኝና የተባረከ ቀን ይሆን! በታላቅ ድምፅ፡- "የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት፣ ጥበብና ብርታት፣ ክብርና ሞገስ፣ ምስጋና ለመቀበል የተገባው ነው። በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉም ምስጋናም ሊቀበል ይገባዋል" እያልን እንዘምራለን (ራዕ.5:12-13)። እስከዚያ ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ሆነን "መንግሥትህ ትምጣ" እያልን መጸለያችንን እንቀጥል።

## *ፈቃድህ ይሁን - አገልግሎት*

### *ዓለማ 7 የምታመልከው በመንፈስና በእውነት መሆኑን ለማወቅ የራስህን የአምልኮ ልምምድ ለመገምገም።*

እንድንፀልይ ኢየሱስ የነገረን ሦስተኛው ነገር "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" በማለት እንድንጸልይ ነው። የእግዚአብሔርን ሃሳብና ፈቃድ ከመንፈስ ቅዱስ የተሻለ ማን ያውቃል? በ1ቆሮ. 2:9-11 ላይ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለእኛ የሚገልጠው በመንፈሱ እንደሆነ ይነግረናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጸለይ እርሱ ሊረዳን ይችላል። ከዚያም ቃሉ ሲሰበክ ጸሎታችን ይመለሳል።

እግዚአብሔርን ለማገልገል ታላቁ መንገድ የእርሱን ፈቃድ ማድረግ እንደሆነ የኢየሱስ ሕይወት ምሳሌአችን ነው። የኢየሱስ ፍላጎት የአባቱን ፈቃድ ማድረግ ነበር (ሉቃ. 22:42 ተመልከት)። መንፈስ ቅዱስም እርሱን ሲረዳ ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር ነበር (ሉቃ. 4:1፤ 14:18-19)። አንተም ኢየሱስ እንደኖረው መኖር ትችላለህ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድታደርግ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ ብታደርግ ሕይወትህ ደግሞ ለእግዚአብሔር በረከት ይሆናል።

በሮሜ 8:27 ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚረዳን ሲናገር "ልባችንን የሚመረምረው እርሱ የመንፈስ ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና" ይላል። እንዴት እንደምንጸልይ በማናውቅበት ጊዜ እንኳ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈፀም ዘንድ እርሱ ለእኛ የፀልያል።

(11). *የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን ይፈጸም ዘንድ የምንጸልይ ከሆነ እርሱን ለመታዘዝና ለማገልገል ዝግጁዎች መሆን አለብን። በማቴ*. 9:36-38 *ላይ ተጨማሪ ሠራተኞችን ወደ መከሩ ሥራ እንዲልክ የመከሩን ጌታ እንዲለምኑ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው።*

*ሀ. ፀሎታቸውን ለመመለስ እርሱ ማንን ላከ?*

ሰ. አንተ በምትመኘው ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ያህንን በሥራ ለመተርጎም እንዴት ትችላለህ?

(12). በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለመንፈሳዊ አምልኮ ወይም በመንፈስ ስለ ማምለክ ተነጋግረናል። እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ለማምለክ እርሱን መታዘዝን፣ እርሱን ማክበርንና ማመስገንን፣ ስሙን ከፍ ከፍ ማድረግንና ለእርሱ ፈቃድ ራስን አሳልፎ መስጠትን የሚጠይቅ ነው። ንጹህና የቅድስና ሕይወት እንደዚሁም ለእርሱ መንግሥት ማገልገልን የሚጠይቅ ነው። የራስህን አምልኮ የምትመለከትበት ጊዜው አሁን ነው። አምልኮህ እውነተኛ መንፈሳዊ አምልኮ ነው? ወይስ ያለምንም ትርጉም የአምልኮን መልክ የያዘ ብቻ ነው? እግዚአብሔርን በተሻለ መንገድ ልታስደስት የምትችልበት መንገድ እርሱን በመንፈስና በእውነት ስታመልክ ነው። ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ምሪት አሳልፈህ ስትሰጥ የአምልኮን እውነተኛ ትርጉም መንፈስ ቅዱስ ያስተምርሃል።

---

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ፡ ትክክል የሆነውን መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

1. በዮሐ. 7:37-39 ላይ በተጻፈው መሠረት ኢየሱስ የሚሰጠው የሕይወት ውሃ:-

ሀ. ቁሳቁሳዊ በረከት ነው።
ለ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት ናቸው።
ሐ. ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ ነው።
መ. መንፈስ ቅዱስ ነው።

2. እግዚአብሔርን የመፍራት ትርጉም ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ስጋት
ለ. አክብሮት
ሐ. ከፍ ማድረግ
መ. መታዘዝ

3. በኢሳ 6:1-6 ላይ የተጻፈው እንደሚያስተምረን በህልዎት (መገኘት) እግዚአብሔር በምንነካበት ጊዜ የምንፈልገው:-

ሀ. ከእግዚአብሔር ፍርድ መሸሽ
ለ. እግዚአብሔርን ማክበርና ራሳችንን ለእርሱ መስጠት
ሐ. የራሳችንን ምኞት መከተል



4. እግዚአብሔርን መፍራት የመንፈሳዊ አምልኮ አስፈላጊ ክፍል የሆነው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. እለመታዘዝን ስለምንፈራ እንድንታዘዝ ስሚያደርገን ነው።
ለ. የእርሱን ቅድስና ስለምንረዳና የእኛ ፍቅርና መታዘዝ እንደሚገባው ስለምንረዳ እርሱን በአክብሮት እንድንቀርብ ያደርገናል።
ሐ. ያለ ፍርሃት ለመታዘዝ ችሎታ ስለሌለን፣ እኛን ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠር የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ነው።

5. በመንፈስ መዘመር:-

ሀ. በአእምሮ የምናመልክበት መንገድ ነው።
ለ. የመንፈስን ሃሳብ የምናሳውቅበት መንገድ ነው።
ሐ. እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ነው።

6. አምልኮን የሚተካው ሌላው ቃል

ሀ. አገልግሎት ነው።
ለ. መታዘዝ ነው።
ሐ. መታነጽ ነው።

7. የአገልግሎት መሠረት ሃሳብ እንደ አምልኮ ይቆጠራል ማለት

ሀ. የምናደርገው ነገር ሁሉ ለመንፈሳዊ አምልኮ መንገድ ሊሆን ይችላል።
ለ. አምልኮ ሊካሄድ የሚችለው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ብቻ ነው።
ሐ. በአፍ ከምንገልጸው ይልቅ በድርጊት የምንገልጠው አምልኮ የበለጠ አስፈላጊ ነው።

"እውነት" ወይም "ሀሰት"። መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሀሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" በመጻፍ አመልክት።

_____ 8. ሮሜ 12 ስለ መንፈሳዊ አምልኮ ብዙ አስፈላጊ ትምህርቶች ይሰጣል።

_____ 9. የበጎቹና የፍየሎቹ ምሳሌ የሚያመለክተው በችግር ላይ ያለን መርዳት ኢየሱስን እንደመረዳት ነው።

_____ 10. በአእምሮ መጸለይ አስፈላጊ ቢሆንም መንፈሳዊነት፣ ግን በመንፈስ ከመጸለይ ዝቅተኛ ነው።

_____ 11. አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍርሃት ለመወሰን የሚቻለው የእግዚአብሔርን ስም እንዴት እንደሚያነሳ በመመዘን ማወቅ ይችላል።

_____ 12. አያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን እስኪያመልክ ድረስ የእግዚአብሔር መንግሥት አትመጣም።

______13. በእርሻ የተደበቀው ሀብት ምሳሌ ውስጥ ሀብቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ነበር።
______14. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ብቸኛው መንገድ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ነው።
______15. እግዚአብሔርን መፍራት መልካም ነገር ነው።
______16. ሳንታዘዝ በመንፈስና በእውነት ማምለክ አንችልም።
______17. ተቀባይነት እንዲኖረው አምልኮ በራስ ቋንቋ መገለጥ አለበት።
______18. በመንፈስ ከመዘመር ይልቅ መዝሙር መዘመር አስፈላጊነቱ ዝቅተኛ ነው።
______19. መጾምና መጸለይ ብዙ ጊዜ ከመንፈሳዊ አምልኮ ጋር ይያያዛሉ።
______20. በየዕለቱ በመንፈስ የምንኖረው ሕይወት የአምልኮ ድርጊት ነው።

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. ሀ. በእምነታችን መጠን ትንቢትን እንናገር።
   ለ. በትጋት እናገልግል።
   ሐ. እናስተምር።
   መ. እንምከር።
   ሠ. በደስታ እንለግስ
   ረ. በትጋት እናስተዳድር
   ሰ. በደስታ ምህረት ማድረግ
   ሸ. አብላው
   ቀ. አጠጣው።

1. ሀ. ከፍ ብሎ ልዕልና ባለው ዙፋን ላይ ተቀምጦ
   ለ. እግዚአብሔርን በመፍራት።
   ሐ. ንጹሕ እንዳልሆን
   መ. ከመስዊያው በተወሰደ የእሳት ፍም

8. ሀ፣ መ፣ ረ እና ሰ

2. በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሁሉና በእናንያና ሰጲራ ላይ የሆነውን የሰሙ ሁሉ ታላቅ ፍርሃት ያዛቸው።

9. ሀ. ስሙ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል።
   ለ. አጋንንት በስሙ ይወጣሉ።
   ሐ. በስሙ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን።
   መ. በስሙ በምንጠይቅበት ጊዜ ጸሎታችን ይመለሳል፤ ችግራችን ይቃለላል።
   ሠ. በስሙ ፈውስ አለ።
   ረ. በስሙ ድነትን እናገኛለን።
   ሰ. እርሱ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ ነው።



3. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

ሀ. እግዚአብሔርን መፍራት ኃጢያት ከማድረግ ይጠብቀኛል።
ለ. እግዚአብሔርን ቢፈሩ እነርሱና ልጆቻቸው ለዘላለም በመልካም ሁኔታ ይከናወንላቸው ነበር።
ሐ. እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው።
መ. እግዚአብሔርን መፍራት ንጹሕ፥ ለዘላለም የሚጸና
ሠ. እግዚአብሔር የሚፈሩትን ከሞት ነጻ ያወጣቸዋል።
ረ. እግዚአብሔርን የሚፈሩ ድነትን
ሰ. እግዚአብሔር የሚፈሩትን ያፈቅራል ወይም ምሕረት ያደርጋል
ሸ. እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት ምንጭ ነው።
ቀ. እግዚአብሔርን ለሚፈሩ በክንፎቹ ፈውስ አለ።
በ. እግዚአብሔር ለሚፈሩት ምሕረቱን ያደርጋል።
ተ. በእናንተ የሚሠራ
ቸ. ሽልማታቸውን

10. የአንተ መልስ። አማኞች ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን እንዲሰብኩና ሰዎች ሁሉ የመስማት እድል አግኝተው ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው የመቀበል እድል እንዲያገኙ እጸልያለሁ ብለህ ለመመለስ ትችላለህ።

4. ሐ. ከድፍረትና
   ሰ. ከአደባባይ አገልግሎት በስተቀር ሁሉም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

11. ሀ. ይጸልዩ የነበሩትን ደቀ መዛሙርት ላካቸው።
   ለ. የአንተ መልስ። በምድር ላይ የእርሱ ፈቃድ እንዲሆን ከጸለይሁ ፈቃዱን ለመፈጸም ሊጠቀምብኝ እንደሚፈልግ በማሰብ እርሱን ለማገልገል ዝግጁ መሆን አለብኝ።

   ሀ. *በመንፈስ መጸለይ*- ሐዋርያው፡- "በመንፈሴ እጸልያለሁ" ይላል። ይህም የሚያመለክተው አምልኮውን ለመግለጽ በቂ ቃላት ለማግኘት በማይችልበት ጊዜ በማይታወቅ ቋንቋ እንደሚጸልይ ነው።
   ለ. *በመንፈስ መዘመር*፡- ውስጣዊ ደስታችንን፣ ምስጋናችንንና የአክብሮት ስሜታችንን በዝማሬ ለመግለጽ ይረዳናል።

12. የአንተ መልስ

6. ሀ. በእእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ።
   ለ. እግዚአብሔር እንደሰጣችሁ እምነት መጠን ስለ ራሳችሁ አስቡ።
   ሐ. ጌታን በማገልገል መንፈሳዊ አድናቆትህን ቀጥል።
   መ. ከዝቅተኛ ሰዎች ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ ሁን።
   ሠ. በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አድርጉ።
   ረ. በቀልን ለእግዚአብሔር ተዉ (ራሳችሁ አትበቀሉ)።

# 9
ትምህርት

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተስፋ በሰጣቸው ጊዜ በእነርሱ ውስጥ ይኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል እንደገባላቸው ታስታውሳለህ? በዮሐ.16:14 ላይ "የእኔ ከሆነው ወስዶ ስለሚነግራችሁ እኔን ያከብረኛል" ሲል ነገራቸው። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ለዓለም ይገልጣል።

ይህን ከሚያደርግባቸው መንገዶች አንደኛው እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለውን ለዓለም በማሳየት ነው። ይህንንም የሚያደርገው በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካኝነት ነው። ቀደም ባለው የትምህርታችን ክፍል እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የማወቅ፣ ሁሉን ቻይነትና በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ የመገኘት ባሕርያት አላቸው። እነዚህ ሁሉ ባሕርያት የተገለጡት በ1ኛ ቆሮ.12:8-10 ላይ በተዘረዘሩትና መንፈስ ቅዱስ ራሱን በሚገልጽባቸው መንገዶች ነው። እነዚህ ልዕለ ተፈጥሮአዊ መገለጾች እግዚአብሔር ሕያው መሆኑንና ለሰዎችም ችግሮች የሚገደው መሆኑን ይመሠክራሉ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት የክርስቶስን አካል ለማነጽ ነው።

*ስጦታዎችና መገለጦች* የሚሉትን ቃላት በማፈራረቅ እንደምንጠቀምባቸው ልብ በል። ሁለቱም የሚያመለክቱት ያንኑ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ነው። እርሱ እንደወደደ መለኮታዊ ስጦታዎቹን ይሰጣል፤ በሚቀበለው ሰው በኩልም ስጦታዎቹ ይገለጻሉ። የስጦታዎቹም ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን ቤተ ክርስቲያንን ወይም አማኞችን ለማነጽና ክርስቶስን ለማክበር ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት በመጠኑ የምንዳስሰው ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና የኢየሱስን ኃይል ለቤተ ክርስቲያንና፣ በእርሷም በኩል ለዓለም የሚገለጥባቸውን መንገዶች ነው።



## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች
- የመናገር ስጦታዎች
- የኃይል ስጦታዎች
- የመገለጥ ስጦታዎች

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በ1ቆሮ.12 የተጠቀሱትን ዘጠኙን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መዘርዘርና ለእያንዳንዱ አጠር ያለ መግለጫ መስጠት።
- የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ዓላማ መግለጽ።
- የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የሚቀበል ማን እንደሆነ መግለጽ።
- በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ስለሚታየው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንቅስቃሴ ማመስገንና ስጦታዎቹን ለመቀበል መሻት።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የተሰጡትን የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ አንብብ። ከዚያም የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን መልስ።
2. ለክፍለ ትምህርቱ መዘጋጃ ይሆንህ ዘንድ 1ቆሮ. 12 እና14 እንዲሁም ሮሜ 12 አንብብ። የሙከራ ፈተናውን ወስደህ መልሶችህን አመሳክር።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

## *ዓላማ 1 ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጠቀሱትን ለመዘርዘር።*

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና የጳውሎስ መልዕክቶች እንደሚገልጹት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን መገለጥ በቋሚነት ትለማመድ ነበር። ቤተ ክርስቲያንን በጋራ ለማነጽና ለኢየሱስ ክብር ለማስገኘት የሚውሉ ነበሩ። ቢሆንም ስጦታዎቹ የሚገለጡት በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በሰጡና በእነርሱ ውስጥ እንዲሠራ በፈቀዱ አማኞች በኩል ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ወይም ስለጸጋ ስጦታዎች የተጻፉ በርከት ያሉ መግለጫዎች አሉ። የተሟላ መግለጫ ከሁሉም ይበልጥ ይዘው የሚገኙት በ1ቆሮ 12 እና 14 ላይ የሰፈሩት ናቸው። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ስጦታዎቹ አጠቃቀም አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል። በ1ቆሮ.12:4-11 ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተጠቅሰዋል።

> ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው። ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያወ መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ መንፈስ መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤ ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ይሰጠዋል። እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደፈቀደ ይሰጠዋል።

ስለሥጦታዎቹ የሚናገረው ሁለተኛ ምንባብ ቁ.28 ሲሆን፣ በዚህም ላይ ስምንት ስጦታዎች ተጠቅሰዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ከነዚህ አንዳንዶቹ "የአገልግሎት ስጦታዎች" ተብለው የጠራሉ።

> እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንደኛ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያትን፣ ሦስተኛ መምህራንን፣ ቀጥሎም ታምራት አድራጊዎችን፣ የመፈወስ ስጦታዎች ያላቸውን፣ ሌሎችን የመርዳት ስጦታ ያላቸውን፣ የማስተዳደር ስጦታ ያላቸውንና በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች መድቦአል።



በ1ቆሮ.12:4-11 የተጠቀሱትን ዘጠኙን የፀጋ ስጦታዎች ማንሳት ወይም ለሁለተኛ ጊዜ በቁ.28 የተጠቀሰው ስጦታዎቹን የተቀበሉትን ሰዎች አትልቶ እንደሚያመለክት አድርጎ ማስቀመጥ ብዙም ልዩነት አያመጣም።

(1). በሁለተኛው ዝርዝር ላይ የተጠቀሱት ሦስቱ ስጦታዎች በመጀመሪያው ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሱም። ያልተጠቀሱት የትኞቹ ናቸው?

ጳውሎስ በቁጥር 28 ላይ ያስፈረውን በማብራራት በቁጥር 29-30 እንደዚህ በማለት ይቀጥላል።

ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ መምህራን ናቸውን? ሁሉስ ታምራት ያደርጋሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታዎች አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ስለ ፀጋ ስጦታዎች ሊጠቀሱ የሚገባ ሁለት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። የመጀመሪያውን በክፍለ ትምህርት ስምንት ላይ የክርስቲያን አገልግሎት የሆነውን የአምልኮን ተግባር ስንነጋገር የተመለከትነውና በሮሜ 12:6-8 ላይ የተጻፈው ነው።

> እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር። ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መስጠት ከሆነም አብዝቶ ይስጥ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤ ምህረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር።

አራተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጠቀሰው በኤፌ. 4:11-13 ላይ ሲሆን ስጦታዎቹ በቤተ ክርስቲያን የተሰጡበትን ዓላማ የሚያሳትት ነው።

> አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች ሌሎች ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው። ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክንደርስ ነው።

የስጦታዎቹ ሦስት ዓላማዎች እዚህ ላይ ተጠቅሰዋል፦

1. የክርስቶስን አካል ማነጽና መገንባት

2. ኢየሱስን በማወቅ የሚገኝ የእምነት አንድነት
3. ክርስቶስን በመምሰል ወደ በሰለ ክርስትና መምጣት

(2). በእነዚህ አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጠቀሱትን ስጦታዎች ማስታወሻ ደብተር ላይ ዘርዝር። ለምሳሌ ያህል፡-

| 1ቆሮ.12፡7-11 | 1ቆሮ.12፡28-30 | ሮሜ.12፡6-8 | ኤፌ.4፡11 |
|---|---|---|---|
| የፈውስ ስጦታዎች | የፈውስ ስጦታዎች | የተጠቀሰ የለም | የተጠቀሰ የለም |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

ስታንለይ ሆርተን ዝርዝሩን በአንድ ላይ አቀናጅተን ብናየው ከ18 እስከ 20 የሚደርሱ ስጦታዎች አሉ ብለዋል (ሆርተን፣ 1976 ገጽ 210)።

እንዱ ዝርዝር ውስጥ ያሉ አንዳንድ ስጦታዎች በሌላው ውስጥ በድጋሚ እንደተጠቀሱ እንደሚደራረቡ ግልጽ የሆነ ነገር ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚያምኑት፣ የአገልግሎት ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ለጥናታችን አመቺ ይሆን ዘንድ በ1ቆሮ 12፡7-11 ላይ የሰፈሩትን ዘጠኙን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በዝርዝር እንጠቀምባቸዋለን። እነዚህንም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደሚከተለው በሦስት ከፍለናቸዋል።

1. የንግግር ስጦታዎች፡- በልሳን መናገር፡ በልሳን የተነገረውን መተርጎምና ትንቢት
2. የኃይል ስጦታዎች፡- የእምነት፣ የፈውስና ተዓምራት የማድረግ ስጦታዎች
3. የመገለጥ ስጦታዎች፡- መናፍስትን መለየት፣ የዕውቀት ቃልና የጥበብ ቃል

በቀረው ሃሳብ መሠረት የንግግር ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስን በሁሉ ቦታ የመገኘት በሕርይ ሲያጠናክሩ፣ የኃይል ስጦታዎች የእርሱን ወሰን የሌለው ኃይል የሚገልጹ ናቸው። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው አስፈላጊው ቁም ነገር የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ በመንፈስ በተሞላ አማኝ በኩል የሚገለጡ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ናቸው።

## የመናገር ስጦታዎች

*ዓላማ 2 ስለ ልሳን ስጦታዎች አስፈላጊውን ማብራሪያ ለመስጠት*

### የመቀበል ልሳን



“ንግግር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጮክ ባለ ድምጽ የተነገረውን የቃል መግለጫ ነው። በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ የሚያስረዳው መንፈስ ቅዱስ ችሎታን ሲሰጥ ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችን መናገር እንደሚሰጥ ነው። አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቁ የመጀመሪያው አካላዊ ማስረጃ የአቀባበል ልሳን ተብሎ ሊጠራ ይችላል። አንድ ሰው ኢየሱስ ተስፋ የሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መቀበሉን የመጀመሪያው አካላዊ ምልክት እንደሆነ የሚገመት ነው። ተቀባዩ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት በሚገባ ያውቃል። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ሲያመልክና ሲያከብር ደስታ፣ ምስጋናና ኃይል፣ .እንደዚሁም ቅዱስ የሆነ ድፍረት ስለሚሰጠው ነው። በአዲስ ልደት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እንድናውቅ አድርጎናል (ሮሜ. 8፡5-16)፤ ለአሮጌው ሕይወታችንም አስፈላጊ ስፍራ እንድንሰጥ ያስችለናል (ኤፌ. 4፡17-32)። በኋላ በጥምቀት ሙላት ሲመጣ በአዲስ አስገራሚ መንገድ ለመመስከር ኃይል ይሰጠናል። ይህ ኃይል በበዓለ ሃምሳ ዕለት የክርስቶስ ለነበሩት ለደቀመዛሙርቱ መጣ። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከዚያም በኋላ በተከታታይ የመጣ ልምምድ ነበር። (የሐዋ. 8፡14-17፣ 19፡1-7 በማነጻጸር ተመልከት)።

በበዓለ ሃምሳ ዕለት በልሳን ሲናገሩ የሰሙ ሰዎች ተገረሙ፤ ከየስፍራው የተሰበሰቡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁዶች ድምፁን ሰምተው ተሰበሰቡ። የእግዚአብሔር አስገራሚ ሥራዎች በቋንቋቸው ሲነገር በመስማታቸው ተገረሙ። ለመግለጽ አስቸጋሪ የነበረውን ይህን ሁኔታ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ገለጻ ሰጠ። ውጤቱም ኃይለኛ የሆነ መንፈሳዊ ምላሽን ያስገኘ ነበር። በዚህ ቦታ የልሳን ስጦታዎች ለማያምኑ ሰዎች ምልክት ይሆን ዘንድ የተሰጡ የሚታዩ መለኮታዊ ምልክቶች ነበሩ።

(3). በልሳን መናገር አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን ለመቀበሉ ለሌሎች ምልክት ነው። በሐዋ.10 ላይ ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአሕዛብ የሰጠው አገልግሎት ሰፍሮ እናገኛለን። በቁ. 44-46 ያለውን አንብብ። እዚህ ላይ ጴጥሮስና ሌሎቹ አማኞች እነዚህ አሕዛቦች መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ያስተዋሉት ምን ላይ ነበር? (የአንዱን መልስ ምረጥ።)

ሀ. በውሃ በተጠመቁ ጊዜ
ለ. የንስሃ ጸሎት በጸለዩ ጊዜ
ሐ. በልሳን እየተናገሩ ማመስገን በጀመሩ ጊዜ
መ. ቃሉን በሰሙ ጊዜ ተገቢውን ምላሽ ሲሰጡ

አብዛኛውን ጊዜ የሚነገረው ልሳን በሰሚዎቹም ሆነ በተናጋሪው ዘንድ ሊገባ የማይችል ነው። የአቀባበል ልሳን ዓላማው የስጦታውን ሰጪ ከፍ ማድረግ ስለሆነ አስተርጓሚ አያስፈልገውም። ትርጉሙ የማይታወቅ ልሳን ተቀባይነት ያለው ልምምድ ቢሆንም የአማኞቹ መለወጥን ምስክርነት ከማንኛውም የበለጠ የማያምኑትን ሰዎች ያስደንቃቸዋል (የሐ. 4፡13)።

## የግል የሚነገር ልሳን

በሕዝብ ፊት የሚነገሩና በግል የሚነገሩ የተለያዩ ልሳኖች ዓላማቸውና ልዩነታቸው እስካልገባን ድረስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተለያዩ ዓይነት ልሳኖች የሚናገረው ግራ የሚያጋባ ሊሆንብን ይችላል። በ1ቆሮ 12፡10 ላይ የተጠቀሰው ልሳን መገለጥ ለጋራ ጥቅም የሚሆን ነው (ቁ.7 ተመልከት)። ይህ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ የሚሆን እስከሆነ ድረስ ሰሚዎቹ እንዲታነጹ መተርጎም ይኖርበታል።

የግል ልሳን በሌላ በኩል ለአማኙ የግል መታነጽ የሚውሉ ናቸው። በግል አምልኮ ጊዜ በመንፈስ ስትጸልይ ወይም በመንፈስ ስትዘምር በልሳን የተነገረውን መተርጎም አስፈላጊ አይደለም። ይህ አማኙን የሚያንጽ በልሳን የመናገር ድርጊት ነው (1ቆሮ. 14፡2-4)። መጸለይ በማይቻልበት መንገድ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መጸለይ ትችላለህ፣ ምክንያቱም በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በመንፈስ በመጸለይ ምስጢራትን ትቃትታለህ።

ከግል ልሳን በረከቶች አንደኛው ጌታን በመንፈስ በምታገለግልበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ከአንተ ጋር መኖር መገንዘብህ ነው። "ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋቸሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ" በማለት በዮሐ. 4፡18 ላይ የተናገረውን የኢየሱስን ተስፋ እየተለማመድክ ነው።

የግል ልሳን እግዚአብሔርን በግልህ ስታመልክ ለራስህ ብቻ የምትናገረው ነው። ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚነገሩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ራሱን እንዲገልጥ እስከፈቀድክለት ድረስ ይህንን ልትለማመደው ትችላለህ። ጳውሎሱ ከሁላችሁም አብልጬ በልሳን እናገራለሁ በማለት ሲና ገር በግል አምልኮው ጊዜ በልሳን ይጸልይ እንደነበረ ግልጽ ነው (1ቆሮ. 14፡18)። በቁ.19 ላይ በቤተ ክርስቲያን ከነበረው ሁኔታ ጋር በተቃርኖ ይገልጻል።

(4). (አንድ መልስ ምረጥ)። የግል ልሳንና በማኅበር ፊት የሚነገር ልሳን ዋና ልዩነት

ሀ. በማኅበር መካከል የሚነገር ልሳን ቤተ ክርስቲያንን ሲያንጽ፣ በግል የሚነገረው ማንንም ለማነጽ የታሰበ አይደለም።
ለ. በማኅበር ወይም በጉባዔ ፊት የሚነገር ልሳን መተርጎም ሲገባው፥ በግል የሚነገረው ልሳን ግን መተርጎም አያስፈልገውም።
ሐ. የግል ልሳን ስጦታ ማንም ሰው ሊኖረው ሲችል፣ በማኅበር ፊት የሚነገ ረው ልሳን የተሰጠው ግን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ነው።

### በማኅበር የሚነገር ልሳን

በማኅበር ፊት የሚነገሩ ልሳን ተብለው የሚገመቱ ሦስት የመንፈስ መገለጦች አሉ። እነርሱም በልሳን መናገር፣ በልሳን የተነገረውን መተርጎምና ትንቢት ናቸው።



1. ***በልሳን መናገር፡-*** ***በሕዝብ ፊት የሚነገር ልሳን*** ሁልጊዜ ለተናጋሪውም ሆነ ለሰሚዎቹ ትርጉሙ የማይታወቅ ነው። ሁልጊዜ የተነገረው ልሳን መተርጎም አለበት።

2. ***በልሳን የተነገረውን መተርጎም፡-*** በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ሲሆን፥ ተርጓሚው በራሱ ቋንቋ እንዲናገር ያስጠዋል። ተርጓሚው በልሳን የተነገረበትን ቋንቋ አያውቀውም። ተርጓሚው ራሱ በልሳን የተናገረው ሰው፣ ወይም ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል።

3. ***ትንቢት፡-*** በመንፈስ አነሳሽነት በማኅበር ፊት የሚነገር ሲሆን፥ የሚነገረውም ሰሚዎቹ በሚያውቁት ቋንቋ ነው።

የልሳንና የትርጉም ዓላማው የተናጋሪውን የግል ሕይወት ለማነጽ ሳይሆን ቤተክርስቲያንን ለማነጽ ነው። ትንቢትም እንዲሁ ዓላማው ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ሲሆን፥ እንግዶች ባሉበትና ተርጓሚ በሌለበት ጊዜ የሚመረጥ የመንፈስ መገለጥ ነው።

5. 1ቆሮ. 14፡1-5 አንብብ። ልሳን የማይተረጎም ከሆነ ከልሳኑ ይልቅ ትንቢት የበለጠ የሚመረጠው ለምንድን ነው?

የትንቢትና የሚተረጎም ልሳን ዓላማ አንድ ዓይነት ነው። እነዚህን ስጦታዎች በመለማመድ ቤተ ክርስቲያን ልትበረታታ፣ ልትታነጽና መንፈስ ቅዱስ የእርሱን ግልጽ ፍላጎቶች ሲናገር ምሪትን ማግኘት ትችላለች (ሮሜ 8፡26-27፣ 1ቆሮ 2፡10-15)። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ታነጸች ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም ለጠፉት ነፍሳት ወንጌልን ስለመሰበክ፣ ቀደም ሲል የተሰጠውን ትእዛዝ በተግባር ላይ እንድታውል ልዩ ምሪት ታገኛለች (የሐዋ. 1፡8 ከ13፡1-3 ጋር አነጻጽር)። በሌላ ጊዜያት ደግሞ አገልጋዮቹን ከአንዳንድ እንቅስቃሴዎች በመከልከል ዓላማውን ግልጽ አድርጎ ይናገራል። (የሐዋ. 16፡6-10)። የትንቢት ሌላው ዓላማ በግልጽ የሚታየው በሐዋ. 21፡10-11 ላይ መንፈስ "ስለሚመጡት ነገሮች" (ዮሐ. 16፡13) ለጳውሎስ ባሳየው ላይ ነው። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚገኙት ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሐዋርያው ጳውሎስ በቀጥታ ከጌታ መልዕክት እንደሚቀበል (የሐዋ. 23፡11)፥ በተዘዋዋሪ መንገድ ደግሞ በመልአክ አማካኝነት መልዕክት እንደሚቀበል ነው (የሐዋ. 27፡23-24)። እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት ጌታ ለቤተ ክርስቲያን፥ መንፈሳዊ ህይወት፣ እድገትና መስፋፋት እንደሚገደው ነው።

በልሳን የተነገረውን ስለመተርጎም በአዲስ ኪዳን የተጻፉና እንደምሳሌ የሚጠቀሱ የሉም፣ ዳሩ ግን ትንቢታዊ ንግግር ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ በርከት ያሉ ጸሎቶች አሉ (ሉቃ. 1፡47-55፣ 68-79 እና 2፡29-32 ተመልከት)። የሆነው ሆኖ፥ በ1ቆሮ. 14 ስለልሳን ስጦታዎች ሐዋርያው ጳውሎስ በሰፋት በመናገሩ፣ የልሳን ስጦታዎች በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው የሚነገር ነበር በማለት ለማጠቃለል እንችላለን።

ስለዚህ ትንቢት ወይም ልሳን ከትርጉም ጋር ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ናቸው። ምናልባት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰባኪ ሲሰብክ ሳለ ትንቢታዊ ንግግር ሲናገር ሰምተክ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያንም በዚህ መንገድ ስትታነጽ ልዩ በረከትን ተለማምደህ ይሆናል።

የእነዚህ ስጦታዎች በተግባር ላይ መዋል፥ አማኞች በተሰበሰቡበት የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና በረከት ስለሚሆን የሚበረታታ ነው። ሆኖም ሰው ለመንፈስ ቅዱስ ራሱን አሳልፎ በመስጠትና ማስገዛት፣ ሰዎች ወደራሱ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር እንዲሳቡ ማድረግ አለበት።

ሐዋርያው ጳውሎስ 14ኛውን ምዕራፍ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጻፈው እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ስጦታዎች አማኞች በማይገባ መንገድ ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ለይቶ ስላወቀ ነው። ልሳን ወይም ትርጉም ወይም ትንቢት በማንኛውም መንገድ የመንፈስን እንቅስቃሴ በአማኞች መካከል የሚያግድ ከሆነ፣ ወይም እነዚህ ስጦታዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ካልሆኑ፣ የመንፈስ ሳይሆን የሥጋ ሥራ መሆናቸውን ታውቃለህ። መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአግባቡ ስላለመጠቀም በይበልጥ ለመረዳት ስለጸጋ ስጦታዎች የተጻፉ የተለያዩ መጽሐፍትን መመልከት ይጠቅማል።

ጳውሎስ የፀጋ ስጦታዎችን እንደ‘ንሻ ሲመክር፦ "ነገር ግን ከሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" (1ቆሮ. 12፥31) "ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፣ በተለይም ትንቢት የመናገርን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" በማለት ይናገራል (1ቆሮ. 14፥1)።

(6). ስለ ልሳን ስጦታዎች "እውነት" የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት፦

ሀ. "የመቀበል ልሳን" የሚያመለክተው ልሳንን ከትርጉም ጋር ነው።
ለ. በግል የተነገረ ልሳን ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚነገር ነው።
ሐ. ሰው የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ለመቀበሉ የመጀመሪያው ተጨባጭ ምልክት በማይታወቅ ልሳን መናገር መጀመሩ ነው።
መ. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለሚቀበለው ሰው በረከት ያለውን የመንፈስ ቅዱስን መገኘት ያመጣል፤ እንደዚሁም ደግሞ ታላቅ ደስታንና ቅዱስ ድፍረትን ያስገኛል።
ሠ. በማህበር የሚነገር ልሳን በጣም አስፈላጊው በልሳን መናገር ነው።
ረ. ልሳን ከትርጉም ጋር ሲሆን ከትንቢት ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።
ሰ. ሐዋርያው ጳውሎስ ትንቢት ዋና ከሆኑ ስጦታዎች አንዱ እንዲሆን ይቆጥራል።
ሸ. የማኅበር ልሳን ዓላማ የቤተ ክርስቲያን መታነጽ ነው።
ቀ. አንድ ሰው በልሳን ሲናገር የሚናገራቸው ቃላት ፈጽሞ አይገቡትም።



በ. የመናገር ስጦታዎች ዓላማ እግዚአብሔርን ለማክበርና አማኞችን ለማጠናከር ስለሆነ፥ እነዚህ ስጦታዎች ሁልጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር መስማማት አለባቸው።
ተ. በትንቢት መልክ የተናገረ ቃል በእግዚአብሔር ቃል ያልተደገፈ ወቅታዊ መልዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያመጣል።

## የኃይል ስጦታዎች

መጽሐፍ ቅዱስ ድርጊት የሞላበት መጽሐፍ ነው። በወንዶችና በሴቶች መካከል የተፈጸመውን የእግዚአብሔርን ድርጊቶች አስፍሮአል። የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ የሚያከናውን ወኪል መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ባለፉት ክፍለ ትምህርቶች ተመልክተናል። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በፍጥረት ሥራ ውስጥ ሲንቀሳቀስ ተመልክተናል። ከዚያም በብሉይ ኪዳን በተመረጡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ በተአምራዊ አሰራር በኃይል ሲንቀሳቀስ ተመልክተናል። ቀጥሎም፥ ኢየሱስ በሰዎች መካከል ሲያገለግል፣ ኃይለኛ ተግባሮችን እንዲያከናውን ሲቀባው ተመልክተናል።

ኢየሱስ ይህችን ዓለም ትቶ በሄደ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ካደረጋቸው የበለጡ ነገሮች እንደሚያደርጉ ተናግሯል (ዮሐ. 14፥12)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ኢየሱስ በሰጠው ተስፋ መሠረት የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና ተአምራዊ ሥራዎችን ያሰፈረ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ኃይለኛ ተአምራዊ ተግባሮችን በምድር ላይ ለማከናውን በመንቀሳቀስ ላይ ነው። ስጦታዎቹን በሚሹት አማኞች ሕይወት ውስጥ በኃይል በመሥራት ላይ ነው። የእነዚህ ስጦታዎች ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽና እግዚአብሔርን ለማክበር ነው። ስጦታዎቹም የእምነት፣ የፈውስና ተአምራት የማድረግ ስጦታዎች ናቸው።

## የእምነት ስጦታ

***ዓላማ 3 አንድ ሰው ሊኖረው የሚችለውን የእምነት ዓይነቶች ለመግለጽ።***

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው የእምነት ስጦታ ልዩ እምነት ስለሆነ በሰው ውስጥ ከሚታየው ከተራው እምነት ጋር መምታታት የለበትም። በወንበር ላይ በምንቀመጥበት ጊዜ ወንበሩ እንደሚሸከመን ተራ በሆነ እምነት እናምናለን። የኢየሱስን እንደግል አዳኛችን አድርገን በምንቀበልበት ጊዜ እግዚአብሔር በውስጣችን የሚያስቀምጠው እምነት ሳይሆን፥ ወይንም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለን ግንኙነት የምናፈራው የእምነት ፍሬ፣ ወይንም በክርስቲያናዊ እርምጃችን በየዕለቱ እግዚአብሔር እንደሚመራን በውስጣችን ያለ እምነት አይደለም።

የእምነት ስጦታ ይልቁንም ተራራን ሊያፈርስ የሚችልና ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ልዩ እምነት ሲሆን፥ በሚያስፈልግ ወቅትና ጊዜ እግዚአብሔር የሚሰጠው የማይነቃነቅ እምነት ነው። ወደ እሳት ነበልባል በተጣሉ ጊዜ የታየው የሦስቱ ዕብራዊያን እምነት ነው (ዳን. 3፥16-18)። ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ ያሳየው እምነት ነው (ዳን. 6፥21-22)። አንገቱ በሚቆረጥበት ምሽት፥ ጸጥ ብሎ በሰላም በመተኛት ጴጥሮስ ያሳየው እምነት ነው (የሐዋ. 12፥6)።

ጴጥሮስ ለሽባው ሰው፦ "ብርና ወርቅ የለኝም፤ ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሳና ተመላለስ" (የሐዋ. 3፥6) በማለት እንዲናገር ያስቻለው እምነት ነው። ሰውየውም ወዲያውኑ ተነስቶ ተራመደ። ጳውሎስ በልስጥራ ሽባው ሰው ለመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ ንቁ ከመሆኑ የተነሣ ለመፈወስ እምነት እንደነበረው አውቆ "ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም" ሲል ተናገረ (የሐዋ. 14፥8-10)።

ምንም እንኳ የእምነት ስጦታ ተመልካችን በመሳብ ከኃይል ስጦታዎች ሁሉ አነስተኛ ቢሆንም፥ ለፈውስና ለተአምራት አስፈላጊ ነው። ይህ ልዩ እምነት በመንፈስ ቅዱስ ለተመረጡ አንዳንድ ግለሰቦች የተሰጠው፣ እንደሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ ነው።

(7). የእምነት ስጦታ በድርጊት የሚያሳይ አንዳንድ ምሳሌዎችን ከራስህ ልምምድ ስጥ።

(8). ቁጥሩን በሰጠው ስፍራ በማስፈር በስተቀኝ የተፃፈውን የእምነት ዓ ይነት በስተግራ ካለው ማብራሪያ ጋር አባምድ።

________ ሀ. በዕለታዊ የክርስትና ሕይወት እርምጃህ እግዚአብሔር እንደሚመራህ ማመን

________ ለ. በብስክሌት ላይ ወጥተህ ስትነዳ ተሸክሞ የምትፈልገው ቦታ እንደሚያደርስህ ማመን

________ ሐ. ኃጢአትህን በመናዘዝ ክርስቶስን ስትቀበል ከዘላለም ፍርድ እንደሚያድንህ ማመን

________ መ. በኢየሱስ ስም የምትጠይቀው ማንኛውም ነገር እንደሚደረግ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ልዩ እምነት

1. የመዳን እምነት
2. የእምነት ስጦታ
3. የእምነት ፍሬ
4. ተራ እምነት



## የፈውስ ስጦታዎች

### *ዓላማ 4 በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የፈውስ ዓላማ ምን እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት መግለጫ ለመስጠት።*

በ1ቆሮ. 12፥9 እና 30 ላይ የተዘረዘሩት የፈውስ ስጦታዎች ብዙ እንደሆኑ ልብ ብለህ አስተውለሃልን? ለእያንዳንዱ ዓይነት በሽታ ፈውስን ለመስጠት በቂ ስጦታዎች መኖራቸውን እያንዳንዱ ሰው እንዲያውቅ መንፈስ ቅዱስ ይፈልጋል።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ስጦታዎች ለክርስቶስ አካል ከመሆን ይልቅ ይበልጥ ወንጌል ለማስፋፋት የተሰጡ ይመስላል። ፈውስ የተከናወነው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይከብር ዘንድ ነበር (የሐዋ. 3፥1-13)። በያዕ.5፥14-15 በቤተ ክርስቲያን ላሉት የተሰጠው የታመመ አባል ካለ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እነርሱም በሽታኛውን በጌታ ስም በዘይት ቀብተው እንዲጸልዩለት ሲሆን፣ በእንዲህ ዓይነቱ እምነት የተመሠረተ ጸሎት በሽተኛውን እንደሚፈውሰው ነው።

ክርስቲያኖች ለመፈወስ ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና አንዱ ለሌላው እንዲጸልይ ይመከራል። የክርስቲያን መፈወስ ስጦታ ያለው ወንጌላዊ እጁን ከመጫን የበለጠ የሚጠይቅ ነው። በአማኞች መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ሊቃለሉ የሚገባቸው መንፈሳዊ ችግሮች እንዳሉ የሚያመለክት ነው።

(9). የሐዋ. 3፥1-13 አንብብ። ሰዎች ለዚህ ፈውስ የሰጡት ምላሽ እንዴት ነበር?
(10). ጴጥሮስ እንዳለው የፈውሱ ዓላማ ምን ነበር?

(11). የሐዋ. 14፥8-18 አንብብ። ስለ ሽባው ሰው መፈወስ "እውነት" የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስና ሽባው ሰው ሁለቱም እምነት እንደነበራቸው የተጻፈው ቃል ያመለክታል።
ለ. ፈውሱ የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ሰዎቹ ወዲያው ለይተው አወቁ።
ሐ. ጳውሎስና በርናባስ የፈውሱ መፈጸም የእነርሱ ጥረት ተደርጎ እንዳይወሰድ አደረጉ።
መ. የፈውሱ ዓላማ ሐዋርያቱ ክርስቶስን ለማክበርና የወንጌልን የምሥራች ቃል እንዲናገሩ እድል ለመስጠት ነበር።
ሠ. ይህንን ከገለጹ በኋላ ሰዎቹ፥ እነርሱን ማምለክ አቆሙ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች ቤተ ክርስቲያን የፈውስ ስጦታዎችን ለማየት ከመንፈስ ቅዱስ ብትጠብቅም ማንኛውም ስጦታውን የተቀበለ ሁሉ ነጻ ለማውጣት ፍጹም ኃይል አለው ማለት አይደለም። ስጦታዎቹን መንፈስ ቅዱስ እንደፈቃዱ ይሰጣል፥ እኛም የእርሱን ስጦታዎች እንድንጠማ ተመክረናል። ዓላማው ሁልጊዜ ሰውን ለማክበር ሳይሆን ክርስቶስን ለማክበር ነው። አስፈላጊው ነገር ለመንፈስ ቅዱስ ቅስቀሳ ንቁ ሆኖ መገኘት ነው። መንፈሳዊ ስጦታን እንድትለማመድ ከቀሰቀሰህ እርሱን በፍጹም መታዘዝ ይኖርብሃል።

## ተአምራትን ማድረግ

*ዓላማ 5 የላቀ ጥቅም ያላቸው ተአምራቶች የትኞቹ እደሆኑ ለመግለጽ።*

ተአምር ማለት የተለመደውን የተፈጥሮ ሂደት እግዚአብሔር ሲለውጠው ወይም ሲገድበው ማለት ነው። ተፈጥሮ የተወሰኑ ሕጎችን እንደሚከተል፣ እግዚአብሔር ግን ተፈጥሮን እንደሚቆጣጠርና አንዳንድ ጊዜም የራሱን ዓ ላማ ለማከናወን እነዚህን ሕጎች ለጊዜው እንደሚሰውጥ ይህ አገላለጸ እውነት አድርጎ ይቀበላል።

ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በላይ ተመልካችን የሚስብ ተአምራት ማድረግ ነው። ይህ በተለይ በግልጽ ይታይ የነበረው በብሉይ ኪዳን በተመረጡ ሰዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜና በሰው ዘንድ የማይቻሉ ነገሮችን በፈጸሙ ጊዜነበር።

(12). ከዚህ በታች የተሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ካነበብህ በኋላ በእያንዳንዱ ድርጊት ምን ተአምር እንደተፈጸመና እግዚአብሔር የተጠቀመበትን ሰው ስም በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

| | |
|---|---|
| ሀ. ዘጸ 14፥21 | መ. መሳ 15፥14 |
| ለ. ዘጸ 17፥6-7 | ሠ. 1ነገ 18፥38 |
| ሐ. ኢያሱ 10፥12 | ረ. 2ነገ 4፥35 |

የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎትም ደግሞ በተአምራት የተሞላ ነበር። የጀመረው በሰርግ ቤት ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በለወጠ ጊዜ ሲሆን (ዮሐ. 2፥9) ያበቃው ደግሞ በአካል ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ነበር። (የሐዋ. 1፥9)። በአገልግሎቱ ዘመን ኢየሱስ በውኃ ላይ ተራምዶአል፣ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሳ አምስት ሺህ ሰዎችን መግቦአል እንዲሁም ሙታንን አስነስቶአል፣ ድውያንን ፈውሶአል፣ አጋንንትን አውጥቶአል፣ ሌሎችንም ተአምራዊ ተግባሮችን አከናውኗል። ወንጌላት በእርሱ ተአምራት የተሞሉ ናቸው።

ኢየሱስ ወደ አባቱ በሄደ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ። ደቀመዛሙርቱ ቃሉን ሲሰብኩ እንደዚሁ ዓይነትና ከዚህም የበለጠ



ተአምራት እንደሚፈጸም ለመጠበቅ ቻሉ። እነዚህ ተአምራቶች በራሳቸው የመጨረሻ ሆነው መታየት የለባቸውም። የወንጌልን መሠረታዊነት የሚያረጋግጡና ወደ ልዑል እግዚአብሔር ኃይል የሚያመለክቱ ናቸው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደቀ መዛሙርቱ የፈጸሙትን ብዙ ተአምራት አስፍሮአል። በርግጥ በአዲስ ኪዳን የሰፈሩት ኢየሱስ "የሚያምኑትም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል" በማለት የተናገራቸውን ቃላት የሚያረጋግጡ ናቸው (ማር. 16፥17)። እነዚህ ተአምራዊ ምልክቶችና ድንቆች በሐዋርያት ሥራ ላይ (5፥12-16) ተመልከት። በጥንቃቄ ስናጠና ከፍ ያለ ተአምራዊ እንቅስቃሴ እንደነበረ መረዳት ይቻላል። የዕብራውያንን ፀሐፊ ሲናገር ወንጌል በተሰበከበት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በምልክቶች፣ በተአምራትና በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተደገፈ እንደነበር ያመለክታል (ዕብ. 2፥4)። እነዚህም ተአምራት ሙታንን ማስነሳትን የሚያካትቱ ነበር (የሐዋ. 9፥40፤ 20፥10)፤ በተአምራዊ መንገድ ከእስር ቤት መለቀቅን (5፥19፤12፥6-10)፤ ተቃውሞ የተረጋጋበት (12፥23)፣ በተቃውሞ ላይ የመታወር ፍርድ የመጣበት (13፥9-12)፣ እንካሶች የተፈወሱበት (3፥6-10፣ 14፥8-10)፤ አጋንንት የወጡበት (16፥18-18) የእስር ሰንሰለት የተበጠሰበት (16፥25-28)። ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ዛሬም ወንጌል ሲሰበክ ብዙ ተአምራት እንደሚከተሉ ማወቅ የሚያስገርም ነው። የእግዚአብሔር ተአምር ሠሪ ኃይሉ ዛሬም ከእኛ ጋር ነው።

(13). ከላይ እንደተመለከትነው በአዲስ ኪዳን በጣም በግልጽ የሚታዩ ተአምራቶች ተቀዳሚ ዓላማቸው

ሀ. የሚገባቸውን ግለሰቦች ችግር ለማቃለል ነው።
ለ. የወንጌላዊያንን፣ የመጋብያንን፣ የአስተማሪዎችን ኃይል ለማሳየትና ሕይወታቸውን ለመቆጣጠር ነው።
ሐ. እግዚአብሔር በመረጠው መንገድ የወንጌልን እውነተኝነት ለማረጋገጥ።
መ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለኮታዊ ምልክትን ለሚሹ ፍላጎታቸውን ለማርካት ነው።

## የመግለጥ ስጦታዎች

*ዓላማ 6 ስለ እያንዳንዱ የመገለጥ ስጦታ ትርጉሙንና ምሳሌ ለመስጠት።*

በዚህ ክፍል የሚገኙት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ውስጥ በሚያስፈልጉ ጊዜ ልዩ መለኮታዊ ማስተዋልን የሚያስገኙ ናቸው። የእግዚአብሔር እውቀት ገደብ የሌለው ነው። የሚያጋጥምህን እያንዳንዱን ሁኔታ በፍጹም ያውቃል። የሰው ማስተዋል ብቃት ሲጎድለው በመገለጥ ስጦታ አማካኝነት መለኮታዊ እርዳታውን ይሰጠናል።

እነዚህን ስጦታዎች የተፈጥሮ ወይም የመንፈሳዊ ስልጠናን ስፍራ ሊተኩ እንደማይችሉ ጠበቅ አድርገን መግለጽ ይገባናል። በመንፈስ የተሞሉ አማኞች ትምህርት ያስፈልጋቸዋል፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በታማኝነት ማጥናት አለባቸው። ቢሆንም ግን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማግኘት ልዩ መገለጥ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል። እነዚህ መለኮታዊ መገለጦች መናፍስትን መለየት፣ የእውቀት ቃልና የጥበብ ቃል በተባሉት የፀጋ ስጦታዎች አማካኝነት የሚሰጡ ናቸው።

## መናፍስትን መለየት

### *ዓላማ 7 ስለመንፈስ አሠራርና መናፍስትን ስለ መለየት አስፈላጊውን መግለጫ ለመስጠት።*

*መለየት* ማለት "አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ማመዛዘን" ማለት ነው። እዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትርጉም "በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት የማወቅ ችሎታ" ማለት ነው (1ቆሮ. 12፥10)። መለየት የመያስፈልገን ሦስት የመንፈስ ዓይነቶች አሉ።

1. *የእግዚአብሔር መንፈስ*፦ እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ከእርሱ ጋር እንተባበር ዘንድ እርሱ በሚንቀሳቀስ ጊዜ ለይተን ማወቅ ያስፈልገናል። እርሱ የሚንቀሳቀሰው ራሳቸውን ለእርሱ ባስገዙና በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች በኩል ነው። አንዳንድ ጊዜም ተግባሩን ለማከናወን መልካም መናፍስት በሆኑት መላእክት ይጠቀማል።

2. *እርኩሳን መናፍስት*፦ በመጨረሻው ዘመን የአጋንንት መናፍስት ተአምራትን እንደሚፈጽሙ በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ይናገራል (ራእ. 16፥14)። በአሁኑ ጊዜ የአጋንንት አምልኮ፣ እንደ ጥንቆላና ኮከብ ቆጠራ ያለው ስውር ሰይጣናዊ የአምልኮ እንቅስቄ በጣም እየተስፋፋ ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን የአጋንንትን መናፍስት እንቅስቃሴዎች ለይቶ ካላወቀ ሊታለል ይችላል።

3. *የሰው መንፈስ*፦ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አማኖች ከእግዚአብሔር መንፈስ ይልቅ በራሳቸው መንፈስ ሊወሰዱ ይችላሉ። መንፈስ ቅዱስ መናፍስትን የመለየት ችሎታ ስለሚሰጥ የመንፈስ መገለጥ የመጣው ከእርሱ ወይም ከአጋንንት መንፈስ ወይም ከሥጋ እንደሆነ በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት እንድንረዳ ያስችለናል።

በአዲስ ኪዳን በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ስለማወቅ የተሰጡ በርከት ያሉ ምሳሌዎች አሉ። ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ኢየሱስ ቀደም ብሎ አወቀ (ዮሐ. 13፥21-26)። በፈተና ጊዜ የዲያብሎስን የማታለል ዘዴ ለይቶ አወቀ (ሉቃ. 4፥1-12)። እንደገናም ሰይጣን የበሽታ መነሻ የሆነበትን ጊዜ አወቀ (ሉቃ. 4፥33-35፣ ዮሐ. 5፥4)። ሲሞን በእርኩስ መንፈስ መያዙን ጴጥሮስ ለይቶ አወቀ (የሐዋ. 8፥18-23)።



በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት የማወቅ ስጦታ አደገኛ ስህተት ላይ ከመውደቅ ይጠብቀናል። ይህ ስጦታ ሊሠራ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ አማኝ በኩል ብቻ ነው (1ቆሮ. 2፥12-15)። መናፍስትን መለየት ተፈጥሮአዊ ከሆንና ከመንፈስ ሳይሆን ከስጋ ከሆን ከተቺነት መንፈስ ጋር መምታታት የለበትም።

ከመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው ከገቡት የስህተት ትምህርቶች የሚረዳን ማስተዋልን እናገኛለን። ዮሐንስ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ከእኛ ወጥተው ሄደዋል ይላል (2፥18-19)። እነርሱ እግዚአብሔርንና ልጁን ክርስቶስን ክደዋል (ቁ. 22)። ወደ ተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በመምጣት ትንቢታዊ መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአማኞች የሚያመጡ በማስመሰል እነዚህ ቅድስና የሌላቸው ችግር ፈጣሪዎች አማኞችን ለማስኮብለል ሞክረዋል (ቁ. 26 ከራእ. 2፥14-16፥ 20-23፥ 3፥9 ጋር አነጻጽር)። ዮሐንስ አማኞች መንፈስን። እንዲሰዩ ይናገራል (4፥1)፤ የእውነትን መንፈስ ከሐሰት መንፈስ እንድንለይ፣ ለይተንም ለማወቅም እንድንችል አንዳንድ መመዘኛዎች ይሰጣል (4፥6)።

1. እነዚህ ሰዎች በጽድቅ ሕጉን በመጠበቅና ከኃጢአት በመራቅ ይኖራሉ? (3፥4-10)።
2. ወንድሞቻቸውን ይወዳሉ? (3፥10)።
3. የክርስቶስን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር መምጣት ይክዳሉ? (2፥22 እና 4፥2)።
4. በሐዋርያት የተሰጠውን ትክክለኛውን አስተምህሮ ይጠብቃሉ? (2፥18-19)።
5. የወንድሞቻቸውን ችግር ይካፈላሉ? (3፥16-20)
6. የሐዋርያትን መልእክት ያደምጣሉን? (4፥6)።
7. የጌታን ትእዛዝ ይጠብቃሉ? (5፥1-3) የቤተ ክርስቲያን ጌታ የሆነው ኢየሱስ እውነተኛውን ትምህርት የምንመዝንበት መመዘኛ ሰጥቶናል። መልካምና ጠቃሚ በሆነውና ሐሰት በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ስንሻ በውስጣችን የመንፈስ ሐሳብ ቶሎ እንዲሰማን ነቅቶ መጠበቁ የእኛ ፈንታ ነው።

(14). ስለመንፈስ ተግባርና መናፍስትን ስለ መለየት "እውነት" የሆኑት መግለጫዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችለው ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።
ለ. እርኩሳን መናፍስት አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ማታለል ይችላሉ፣ ከእውነትም እንዲርቁ ይመሩአቸዋል።
ሐ. መናፍስት የመለየት ስጦታ ያለው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ በእውነት መንፈስና በሐሰት መንፈስ መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ለማወቅ እንዲችል ያደርገዋል።
መ. የሥጋ መንፈስ አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ መገለጥ አስመስሎ ሊከሰት ይችላል።

ሠ. በመንፈስ የተሞሉ አማኞች መታለልን ለማስወገድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ንቁ መሆንና በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ መመዘኛውን ደኅና አድርገው ማወቅ አለባቸው።
ረ. ተገልጦ በመስራት ላይ ያለው መንፈስ ምን እንደሆነ ማንም ሰው ለይቶ ሊያውቅ ይችላል።

## የእውቀት ቃል

*ዓላማ 8 ስለ እውቀት ቃልና ስለ ጥበብ ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መግለጫ ለመስጠት።*

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሐሳብ እንደሚያውቅ ቀደም ብለን ተምረናል። በሚያስፈልግ ጊዜ የእግዚአብሔርን እውቀት ለአንተ ሊገልጥ ይችላል። ወደፊት ስለሚፈጸም ነገር ሊሆን ይችላል፣ አሁን በሌላ ስፍራ ስለሚፈጸም ነገር ሊሆን ይችላል ወይም ማስታወስ ስላለብህ ስላለፈ ነገር ሊሆን ይችላል። ሁሉን ነገሮች ታውቅ ዘንድ የእውቀት ስጦታ አይሰጥህም፥ ነገር ግን በሚያስፈልግ ጊዜ የሚሆን የእውቀት ቃል ብቻ ነው ይሰጥሃል።

የምትሠራውን ሥራ አቁመህ በሩቅ ስፍራ ላለ ሌላ ሰው እንድትጸልይ አስፈላጊ ሆኖ ተሰምቶህ ያውቃል? ከዚያም ስለዚያ ሰው በጸለይክበት ወቅት ሰውየው በአንድ ዓይነት ችግር ውስጥ ገብቶ የአንተ ጸሎት እንዳስፈለገው በኋላ ለመረዳት ችለሃል? ይህ ምሪቱን ለመቀበል ዝግጁ ለሆነ መንፈስ ቅዱስ ለተሞላ አማኝ? የሚሰጠው የእውቀት ቃል ነው።

በብሉይ ኪዳን የእውቀት ስጦታ ምሳሌ በ2ነገ. 6፥9-10 ላይ ይገኛል። የእግዚአብሔር ሰው ተብሎ ይጠራ የነበረው ነብዩ ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ ጠላት በነበረበት ሥፍራ እንዳያልፍ አስጠነቀቀው። በቁ.10 ላይ የተጻፈው ቃል ስለዚሁ ሲገልጽ "ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ የእግዚአብሔር ሰው የነገረውን ቦታ አሰቃኘ፤ ኤልሳዕም ንጉሡን እንደዚህ ካሉት ቦታዎች ራሱን እንዲጠብቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በላይ አስጠነቀቀው" ይላል።

## የጥበብ ቃል

በችግር ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብህ ታውቅ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የጥበብ ቃል ይሰጥሃል። ይህ ባለፈው ልምምድ ላይ የተመሠረተ የሰው የጥበብ ቃል ሳይሆን፥ ለልዩ ችግር መፍትሔ ይሆን ዘንድ የተሰጠ ልዩ የጥበብ ቃል ነው። የእውቀት ቃልን ሊያከትት ወይም ላያከትት ይችላል። እዚህ ላይም፥ እንደገና ስጦታው የጥበብ ቃል ብቻ ነው። ይህ ማለት ለአንድ አጋጣሚ ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ትቀበላለህ ማለት ነው። የጥበብ ቃል በቤተክርስቲያን በመሪነት ስፍራ ላይ ለተቀመጡ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ቃል በስብሰባ ወቅት በመሪዎች መካከል አንድነትን ሊያመጣ ይችላል። በክርስቶስ ላይ ባለህ እምነት



ምክንያት በዓለም የፍርድ ሸንጎ ፊት ብትቀርብ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር በመሆን የሚያስፈልግህን ጥበብ እንደሚሰጥህ ማወቁ የሚያበረታታ ነው።

በሐዋ. 15 ላይ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ተሰባስበው እንደ አይሁድ ሕግ ሥርዓት አሕዛብ መገረዝ ይገባቸዋል ወይም አይገባቸውም በሚለው ጥያቄ ላይ ለመወያየት በኢየሩሳሌም ጉባዔ እንደተቀመጡ እናነባለን። መሪዎቹ ለአሕዛብ አማኞች በገለጹት መሠረት "ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች በስተቀር ሌላ ተጨማሪ ሸክም እንዳንጭንባችሁ ለመንፈስ ቅዱስም እኛም መልካም መስሎ ታይቶናል" (የሐዋ. 15፥28) በማለት ያስተላለፉት ውሳኔ የጥበብን ቃል በግልጽ የሚያሳይ ነው።

(15). *የእውቀት ቃል* በሚያሳዩት "1" ቁጥር፣ *የጥበብ ቃልን* በሚያሳዩት መግለጫዎች ደግሞ "2" ቁጥርን በተሰጠው ስፍራ ላይ በመጻፍ አመልክት።

_____ሀ. ዮሐ. 4፥7-17 ኢየሱስ ለአንዲት ሴት ስላለፈ ሕይወቷ ነገራት።
_____ለ. የሐዋ. 5፥27-29 ጴጥሮስ ለአንድ ችግር መፍትሔ ሰጠ።
_____ሐ. የሐዋ. 5፥3 ሃናንያና ሰጲራ ስለሃብታቸው መዋሸታቸውን ጴጥሮስ አወቀ።
_____መ. በሐዋ. 10፥19 ጴጥሮስ በሌላ በኩል ሊያውቀው የማይችለውን መንፈስ ቅዱስ እንዲያውቅ አደረገው።
_____ሠ. የሐዋ. 28፥26፡- አይሁዶች ለወንጌል እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ መንፈስ ቅዱስ ለኢሳይያስ መልእክት ሰጠው።

(16). በሚከተሉት መልመጃዎች ውስጥ የትኛው የመገለጥ ስጦታ እንደ ሚሠራ ግለጽ።

ሀ. በችግር ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብህ እንድታውቅ የሚያደርግህ ልዩ ቃል።
ለ. የሚታየው መንፈሳዊ መገለጥ ከእግዚአብሔር ወይም ከርኩስ መንፈስ፣ ወይም ከሥጋ እንደሆነ የማወቅ ስጦታ።
ሐ. በአንድ የተለየ ጊዜ ማወቅ ስለሚያስፈልግህ አንድ ነገር ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ መገለጥ።
መ. በአንዲት ገረድ ውስጥ ርኩስ መንፈስ እንደነበረ ጳውሎስ ለይቶ እንዲያውቅ ያደረገው ስጦታ (የሐዋ. 16፥16-18)።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ዓላማቸው የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ወይም ለመገንባት እንደሆነ አትዘንጋ። መንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንደፈቃዱ የሚሰጠው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እድገትን በማግኘት እንድትጠነክር ነው።

## የሙከራ ፈተና

1. አዛምድ፦ በስቀኝ የተፃፉት በ1ቆሮ. 12፥7-11 ላይ ያሉትን ዘጠኙን የፀጋ ስጦታዎች በስተግራ ካሉት ማብራሪያዎች ጋር አዛምድ። አብሮ የሚሄደውን ቁጥሩን በባዶው ስፍራ በማስፈር አመልክት።

| | |
|---|---|
| ___ ሀ. መገለጥ ከመንፈስ ቅዱስ ወይም ከሌላ መንፈስ እንደሆነ የሚያሳይ ስጦታ | 1. ልሳን |
| ___ ለ. የጠየቅኸውን ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔር ሊያደርግ እንደሚችል የሚያስተማምን ስጦታ | 2. ልሳንን መተርጎም |
| | 3. ትንቢት |
| ___ ሐ. ሳይታሰብ ለገጠመህ ችግር ልዩ የሆነ ማስተዋል እንድታገኝና ካለፈው ነገር እንድታስታውስ የሚያደርግ ስጣ | 4. እምነት |
| ___ መ. በማይታወቅ ቋንቋ የመናገር ስጦታ | 5. ፈውስ |
| ___ ሠ. የተፈጥሮን ሂደት የሚያዛባ ስጦታ | |
| ___ ረ. በልሳን የተነገረውን መልእክት አድማጮች በሚረዱት ቋንቋ የሚገልጥ ስጦታ | 6. ተአምራት |
| ___ ሰ. ለበሽታ ፈውስ የሚያመጣ ስጦታ | 7. መናፍስትን መለየት |
| ___ ሸ. አድማጮቹ በሚረዱት ቋንቋ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት የማምጣት ስጦታ | 8. የእውቀት ቃል |
| ___ ቀ. በችግር ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብህ የሚያሳይ ስጦታ | 9. የጥበብ ቃል |

አጭር መልስ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ።

2. በዚህ ክፍለ ትምህርት የተገለጸውን ሶስቱን የስጦታዎች አከፋፈል ግለጽ፡

3. የፀጋ ስጦታዎችን ሁለት አስፈላጊ ዓላማዎች ግለፅ።

4. የፀጋ ስጦታዎች ሊቀበል የሚችል ማን ነው?



## የጥናት ማጠናከከሪያ ጥያቄ መልሶች

9. የእግዚአብሔር ሰዎች በመሆናቸው ጴጥሮስና ዮሐንስ በራሳቸው ለመፈወስ ሃይል ያላቸው መስላቸው።

1. ሐዋርያት፣ አስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች (ሌሎችንም ለመርዳት የሚችሉትን ጨምሮ)።

10. ጌታን ኢየሱስን ለማክበር

2.

| 2.1ቆሮ. 12፥7-11 | 1ቆሮ. 12፥28-30 | ሮሜ. 12፥6-8 | ኤፌ. 4፥11 |
|---|---|---|---|
| ጥበብ | | | |
| እውቀት | | | |
| እምነት | | | |
| የፈውስ ስጦታ | የፈውስ ስጦታ | አልተጠቀሰም | አልተጠቀሰም |
| ተአምራዊ ኃይል | ተአምራት ማድረግ | | |
| ትንቢት | ነቢያት | መተንበይ | ነቢያት |
| መናፍስትን መለየት | | | |
| በልሳን መናገር | በልሳን መናገር | | |
| ልሳንን መተርጎም | ልሳንን መተርጎም | | |
| | ሐዋርያት | | ሐዋርያት |
| | አስተማሪዎች | ማስተማር | አስተማሪዎች |
| | መርዳት/ ረዳቶች | ማበረታታት ማገልገል | |
| | አስተዳዳሪዎች | መሪነት | መጋቢዎች |
| | | መስጠት | |
| | | ምሕረትን ማሳየት | |
| | | | ወንጌላውያን |

11. ሀ. እውነት
ለ. ሐሰት
ሐ. እውነት
መ. እውነት
ሠ. ሐሰት

3. ሐ

12. ሀ. ባሕሩ ተከፈለ - ሙሴ
ለ. ከዓለት ውሃ ፈለቀ - ሙሴ
ሐ. ፀሐይና ጨረቃ ቀጥ አሉ - ኢያሱ
መ. 1000 ፍልስጥኤማውያን ተገደሉ - ሳምሶን
ሠ. ምሥዋዕት በእሳት ተቃጥለ - ኤልያስ
ረ. ልጅ ከሞት ተነሣ - ኤልሳዕ

4. ለ

13. ሐ

5. ልሳን ብቻውን ተናጋሪውን ከማነጽ በስተቀር ሌላውን አያንጽም። ትንቢትና ልሳን ከትርጉም ጋር አብሮ መላውን ቤተ ክርስቲያን ያንጻል። (ይህንን በስፋት ለመረዳት 14ኛው ምዕራፍ በጥንቃቄ አንብብ)

14. ሀ. ሐሰት
ለ. እውነት
ሐ. እውነት
መ. እውነት
ሠ. እውነት
ረ. ሐሰት

6. ሀ. ሐሰት
ለ. እውነት
ሐ. እውነት
መ. እውነት
ሠ. ሐሰት
ረ. ሐሰት
ሰ. እውነት
ሸ. እውነት
ቀ. እውነት
በ. እውነት
ተ. ሐሰት

15. ሀ. 1
ለ. 2
ሐ. 1
መ. 1
ሠ. 2

7. የአንተ መልስ።

16. ሀ. የጥበብ ቃል
ለ. መናፍስትን መለየት
ሐ. የእውቀት ቃል
መ. መናፍስትን መለየት

8. ሀ. 3
ለ. 4
ሐ. 1
መ. 2



# 10
## ትምህርት

# የመንፈስ ፍሬ

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ደግነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች የሚቃረን ሕግ የለም (ገላ. 22-23)።

ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ፍቅር ደግ ነው፤ ፍቅር አይመቀኝም፤ ፍቅር አይታበይም፤ ፍቅር አይኮራም፤ ፍቅር ሥርዓተ ቢስ አይደለም፣ ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ አይደለም፣ ፍቅር አይበሳጭም፣ ፍቅር ቢበደልም በደልን እንደበደል አይቆጥረውም፤ ፍቅር እውነት በሆነ ነገር ይደሰታል እንጂ ክፋት በሆነ ነገር አይደሰትም፤ ፍቅር ሁሉን ችሎ" ይታገሳል ፍቅር በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል፤ ፍቅር በሁሉ ላይ ተስፋ ያደርጋል፤ ፍቅር በሁሉ ነገር ይጸናል (1ቆሮ. 13:4-8)።

ኢየሱስ ያረገው ከ2000 ዓመታት በፊት ወደ ሰማይ አርጓል። ደቀ መዛሙርቱ ለእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን እውነተኛ ምሳሌ እንደሆነ በመናገር እርሱን ከፍ አድርገውታል። አንዳንዶች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እርሱን የሚመስል ባህርይ አዳብረዋል፤ በዚህም የእርሱን ማንነት ለሌች ያስታውሳሉ። ምንም እንኳን ዛሬ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋዊ ዓ ይናቸው ባይመለከቱትም የእርሱ ማንነትና ባህሃያችን በሕይወታቸው በመግለጥና እርሱን በመምሰል በሚመላለሱ አማኞች ሕይወት ውስጥ ይመለከቱታል።

በዚህ በመጨረሻው ትምህርት ላይ የኢየሱስን እውነተኛ ተከታይ ባሕርያትና እነዚህንም ባህርያት በውስጡ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ እንዴት እያዳበረ እንደሚሄድ መመልከት ተገቢ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ባህርያት የመንፈስ ፍሬ ብሎ ይጠራቸዋል። ሁሉም "ፍቅር" በሚለው ቃል ሊጠቃለሉ ይችላሉ። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚገኙ የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው ብዬ ብጠራቸው እወዳለሁ። ይህን ክፍለ ትምህርት ስትከታተል ሌሎች ኢየሱስን በአንተ ውስጥ ማየት ይችሉ እንደሆነ ራስህን መርምር።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- ፍሬ ማፍራት ያስፈልጋል
- ፍሬ ሲመረመር
- ፍሬ ዋጋ ያስገኛል

---

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ የሚከተለውን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በ1ቆሮ. 13 እና በገላ. 5፥22-23 ላይ በተጻፈው መሠረት የመንፈስ ፍሬ የሚለውን ቃል ትርጉም መግለጽ።
- ንግግራችን፥ አገልግሎታችን፥ መሥዋዕታችን ውጤታማ እንዲሆን ፍሬ ለምን እንደሚያስፈልግ መግለጽ።
- ክርስቲያናዊ ባሕርይህን በመገምገም ለመንፈሳዊ እድገትህ የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ መወሰን።
- መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን መምሰል በአንተ ውስጥ እንዲያዳብር መፍቀድ የሚኖረውን ዘላለማዊ ዋጋ በጉጉት መጠባበቅ።

---

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1. በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በጥንቃቄ አንብብ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹንም በሙሉ መልስ።
2. ለዚህ ክፍለ ትምህርት መንደርደሪያ ይሆንህ ዘንድ ዮሐ. 15፣ 1ቆሮ. 13፣ ገላ. 5 እና 2ጴጥ. 1፡5-11 በጥንቃቄ አንብብ።
3. የሙከራ ፈተናውን ወስደህ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት አመሳክር።



**የትምህርቱ ዝርዝር**

## ፍሬ ማፍራት ያስፈልጋል

*ዓላማ 1 በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ ለምን እንደሚያስፈልግ ለመግለጽ።*

ክፍለ ትምህርት ዘጠኝን ስታጠና፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 12 እና 14. ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲጽፍ ለምን በመካከል ምዕራፍ 13ን በማስገባት ለየት ያለ ሃሳብ እንደጻፈ ይገርምህ ይሆናል፤ ለዚህ ጥያቄ መልስ የምታገኘው ምዕራፍ 13ን ስትመለከት ነው። የዚህን ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ቁጥሮች አንብብ። በእነዚህ ሦስት ቁጥሮች ውስጥ የምታገኛቸውን ተውላጠ ስሞች ቁጠራቸው። እኔ በማነበው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፥ "እኔ" የሚለው ተውላጠ ስም 8 ጊዜያት ተጠቅሷል።

ጳውሎስ ሊነግረን የሚሞክረው ምንድን ነው? እዚህ ላይ የእርሱ ትኩረት በራሱ ላይ ነው። የሚለውም "ያልሁትንም ሆነ ያደረግሁትን ሁሉ ውስጤ፤ ብቻዬን ቆሜ ታገኙኛላችሁ። በዚያን ጊዜ ከተናገርኩት ወይም ካደረግሁት ይልቅ የእኔ ማንነት የበለጠ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል" የሚል ነው።
በዘጠነኛው ክፍለ ትምህርት ላይ እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር እንድንኖር ሊረዳን ይመጣል። እግዚአብሔር እንድሆነው የሚፈልገውን እንድሆን ይረዳኛል። ለእግዚአብሔር መኖር ሌሎችን የበለጠ ይጠቅማል። እግዚአብሔርን መምሰል መሆን እኔን ከሁሉም በላይ ይጠቅመኛል። ሁለቱም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ቢሆኑም መሆን የሌለበት ማድረግ ግን ባዶ እና ትርጉም የሌለው ይሆናል።

ሐዋርያወ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ፍሬ ወይም ስለ ክርስቲያናዊ ባህርይ አስፈላጊነት የሚናገረውን በጥልቀት እንመርምር። ይህንንም ስናደርግ ፍቺር በማለት የተጠቀመውን ቃል ክርስቲያናዊ ባህርይ በማለት እንተካዋለን።

## በንግግር

*ዓላማ 2 ምስክርነታችንን የሚደግፍ እውነተኛ የክርስቲያን ባሕርይ ማለት ምን እንደሆነ ለመግለጽ።*

በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብናገር፣ ነገር ግን ምስክርነቴን የሚደግፍ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ባህርይ ከሌለኝ፣ እንደሚጮህ ነሐስ እንደሚንሽዋሸው ጽናጽል ያሰበት የአሕዛብ መቅደስ እመስላለሁ። ምስክርነቴ ሰዎች እግዚአብሔርን ፍለጋ ወደ መቅደሴ እንዲመጡ ያደርጋቸዋል። የእርሱ ባሕርይ በውስጤ ካልታየ ግን አዝነው ይመለሳሉ። የእኔ ምስክርነት ወደ ባዶው የአሕዛብ መቅደስ ሰዎችን ከሚጠሩት ናስና ከሚንሽዋሸው ጸናጽል የተሻለ አይደለም። እውነተኛ ባሕርዩ ከምስክርነቴ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ መቅደስ ወደሆነው ሰውነትህ ገብቶ የመንፈስን ፍሬ ለማፍራት ይፈልጋል። ከዚያም እርሱን በሚቀበሉት ሰዎች ሕይወት እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚችል በምትመሰክርበት ጊዜ ለምስክርነትህ ሕያው ምሳሌ ትሆናለህ። ሰዎች "እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አውቃለሁ፣ አንተን ይመስላል" በማለት ይናገራሉ።

(1). ምስክርነትህን ለመደገፍ እውነተኛ የክርስቲያን ባህርይ እንዲኖርህ ያስፈልጋል ስንል ምን ማለታችን ነው? (አንዱን መልስ ምረጥ)

ሀ. ምንም ዓይነት ኑሮ ብትኖር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚስብ ኃይለኛ መልዕክት ይኖርሃል ማለት ነው።
ለ. በማንኛውም ጊዜ የክርስቶስን ፍቅር ታሳያለህ፥ በአንተነትህና በምትናገረው መልዕክት ሰዎች ወደ ክርስቶስ ይሳባሉ ማለት ነው።

## በአገልግሎት

*ዓላማ 3 የመሆንና የማድረግን አስፈላጊነት ጠቅለል ባለ መልኩ ለመግለጽ*

ከመናገር ስጦታዎች መካከል የበለጠውን፥ ትንቢት የመናገር ስጦታ ቢኖረኝ፥ ከመገለጥም ስጦታዎች መካከል ከፍተኛ የሆነውን ምስጢርን ሁሉ ብረዳና ዕውቀትም ሁሉ ቢኖረኝ፥ ከኃይል ስጦታዎችም የበለጠውን ተራራን የሚያፈልስ እምነትም ሁሉ ቢኖረኝ፥ የክርስቲያን ባህርይ ከሌለኝ ግን ከንቱ ነኝ።

ጳውሎስ ስጦታዎችን ለማሳነስ ያደረገው ጥረት የለም። እነዚህ ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስ ናቸው። እነርሱ የሰው ልጅ የሚለማመዳቸው፥ ከፍተኛ የሆኑ የእግዚአብሔር ሐሳብና ኃይል የሚገለጥባቸው ናቸው። የሰዎችን ፍላጎትና ችግር በከፍተኛ ደረጃ ሊደርሱ የሚችሉ ናቸው። የቤተክርስቲያን አባላት የሚታነጹት በእነርሱ ነው። መለኮታዊ ጥበብና እውቀት ያከፍላሉ። ተራራ የሚፈልስበት ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገናል፥ እንደገናም እግዚአብሔር የቀባው የእርሱ አገልጋይ ተብዬ ልቆጠር እችላለሁ። *ሆኖም ግን፥ ፍሬ ያለው የክርስቲያን ባህርይ ከሌለኝ፤ በእግዚአብሔር ፊት ባዶ ሆኜ እቀርባለሁ።*

ኢየሱስ ስለዚህ ሲያረጋግጥ፦ "በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" (ማቴ. 7፥16) አለ። በተጨማሪም እንዲህ አለ፦ በዚያ ቀን ብዙዎች፣ "ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን?" ይሉኛል። በዚያ ጊዜ "ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች ከእኔ ራቁ! ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ።" (ማቴ. 7፥22-23)

ለእግዚአብሔር የምናቀርበው አገልግሎት የአምልኮአችን ክፍልና ሰው ለእግዚአብሔር መስራት የሚችለው ትልቁ ሥራ ነው። በጌታው ፊት



በሚቆምበት ጊዜ እንደማንነቱ ፍርድን ይቀበላል፤ ስለ ስራውም ሥራ ሽልማቱን ይቀበላል።

ለዚህም ምክንያት አለ። መንፈስ ቅዱስ ለሚመጣው የክርስቶስ መንግስት ገዢዎችን እያዘጋጀ ነው። ከክርስቶስ ጋር ስለሚነግሱ፥ እርሱን መምሰል አለባቸው። ቦታው የሚደለደለው ከሥራችን አኳያ ከመሆን ይልቅ ክርስቶስን ከመምሰላችን አኳያ ይሆናል። ክርስቶስም አድልዎ በሌለበት፣ የጽድቅና የፍቅር ምሳሌ በሆነው በብረት በትር ይገዛቸዋል። ስለዚህ ክርስቶስ ንጹህ የክርስቲያን አመለካከትና እርሱን የሚመስል ባህርይ ያላቸውን ገዢዎች ይፈልጋል (ራዕይ 2፥26-27 ተመልከት)።

የፖለቲካ ስልጣን አብዛኛውን ጊዜ የሚገኘው እግዚአብሔርን በመምሰል ላይ በተመሠረተ ባህርይ ሳይሆን ብዙ ተስፋዎችን በመስጠትና እንዲህና እንዲህ ነኝ ብሎ ራስን በማሞካሸት ነው። በክርስቶስ መንግስት ግን፥ ከምታደርገው ነገር ይልቅ የሆንከው የበለጠ ግምት ይሰጠዋል። ይህ የ1ቆሮ. 13 መልዕክት ይኸው ነው።

ይህም ሁሉን እማኝ? እኩል ያደርገዋል። የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ ቤተ ክርስቲያን ባለስልጣናት ክርስቶስን ለመምሰል እኩል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሆነው አካላቸው መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አለ፥ እርሱም በእነርሱ ውስጥ የመንፈስ ፍሬን ለማፍራት ይፈልጋል።

(2). ዓረፍተ ነገሮችን የተሟላ ለማድረግ ባዶ ቦታውን ሙላ።

ሀ. 1ቆሮ. 13፥ ላይ ______ይልቅ_____የበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል።
ለ. ከክርስቶስ ጋር መግዛት የሚፈልጉ ሁሉ ____________ አለባቸው።
ሐ. ኢየሱስ ሲናገር እኛ የምንታወቀው ________ነው። ይህም ማለት ምን እንደሆንን የምናሳየው ___________________ በማሳየት ነው።

## በመሥዋዕት

***ዓላማ 4 በ1ቆሮ. 13:3 መሠረት መስዋዕት በማቅረብና በክርስቲያናዊ ባህርይ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት።***

በመስዋዕትነት ያለኝን ሁሉ ለድሆች ብሰጥ፣ ሥጋዬን እንኳ ሳይቀር በእሳት እንዲቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፣ የክርስቲያን ባህሪይ ከሌለኝ ግን የማተርፈው ምንም ነገር የለም።

እግዚአብሔር ድሆችን ይወዳል። ሐዋርያው ያዕቆብ በጻፈው መልእክት፥ በመጨረሻው ዘመን ሀብታሞች ለዎች ድሆችን የጨቆኑባቸው መንገዶች ትገዝ ሲላቸው እንደሚያለቅሱና ዋይ ዋይ እንደሚሉ፥ የሠሩበትን ደሞዝ በመከልከል ስላሰቃዩአቸው ዋጋቸውን እንደሚያገኙ ያስጠነቅቃል (ያዕ. 5፥1-4)። እግዚአብሔር ለሌላቸው ሰዎች ሃብት ሲካፈል ደስ ይለዋል።

ለድሆች መስጠት፣ ለእግዚአብሔር ከመናገርና ስጦታዎችን ከመለማመድ ይልቅ ክርስቲያናዊ ባህርይን መግለጥ የሚችል ነው። ለድሆች የምትሰጠው ለጊዜውም ቢሆን ድሆችን በእርግጥ ይጠቅማል። ለመስጠት የሚገፋፋህ ዝንባሌህ በክርስቶስ ፊት በምትቆምበት ጊዜ ዋጋ ይኖረው ዘንድ በውስጥህ ካለው ከክርስቶስ ባሕርይ የተነሳ መሆን አለበት።

ጳውሎስ *ሥጋን* በእሳት እንዲቃጠል አሳልፎ ስለመስጠት በ1ቆሮ. 13፥3 ላይ ሲናገር የሚጠቅሰው ስለሰማዕታት ይሁን ወይም በእርሱ ዘመን ስለነበረው ከኃይማኖታዊ ምክንያት ጋር ስለተያያዘ ራስን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ በግልጽ አናውቅም። የሆነው ሆኖ ምንም አይነት ምክንያት ይሁን፣ ኃይማኖታዊ ግዴታዬን ለመወጣትም ሆነ ለሌላ ራሴን አስቃቂ ለሆነ ሞትና *ሥቃይ* አሳልፌ ብሰጥ፥ የክርስቲያን ባህርይ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ከሌለኝ *ምንም አይጠቀመኝ* በማለት ተናገረ።

(3). የመንፈስ ፍሬ መለኪያው ምንድን ነው?

(4). ለድሆች መስጠት ወይም ራስን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው መቼ ነው?

(5). ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ፍሬ እንዲኖረን ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ አጥብቆ ለመናገር *ሥጋን* በእሳት እንዲቃጠል አሳልፎ ስለመስጠት ምሳሌ የሰጠበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?

(6). በአንድ ክርስቲያን ህይወት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ የሚገልጸውን እውነተኛ የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳመለከተው ከምናገረውና ከምናደርገው ይልቅ ማንነታችን ይበልጥ አስፈላጊ ነው።
ለ. ከመንፈሳዊ ፍሬ ጋር ሲነጻጸር በልሳን መናገር ጥቅሙ እምብዛም፣ ወይም ምንም ያህል ጥቅም የለውም።
ሐ. የክርስቶስ ባህርይ ከሌለኝ የማደርገው ሁሉ ትርጉም አይኖረውም።
መ. ከእኔነቴ ይልቅ በምናገረው ነገር ሰዎች ወደ ክርስቶስ በይበልጥ ይሳባሉ።
ሠ. የመንፈስን ስጦታዎች ሁሉ ይገፎ ምንም የማልጠቅም ልሆን እችላለሁ።
ረ. በእግዚአብሔር ፊት ባዶ ሆኜ እንዳዳገኝ የመንፈስ ፍሬ መያዝ አለብኝ፡
ሰ. ደቀ መዛሙርቱ በስጦታቸው እንደሚታወቁ ኢየሱስ ተናገረ።
ሸ. በእግዚአብሔር መንግስት የወደፊት ስፍራችን የሚወሰነው ክርስቶስን በመምሰላችን ነው።





## ትርጉም

*ዓለማ 5 ፍቅር ምን እንደሆነና ምን እንደሚያደርግ ለመግለጽ።*

ክርስቲያናዊ ባህርይ አስፈላጊ ነው። ይህ ክርስቲያናዊ ባህርይ ግን ምንድን ነው? ይህ ባህርይ እንዳለኝ የማውቀው እንዴት ነው? ይህን ክፍለ ትምህርት የጀመርንበት ጥቅስ የዚህን ጥያቄ መልስ ይሰጠናል። በጥቅሱ ውስጥ የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን የተለያዩ የክርስቲያን ባሕርይ ገጽታዎች እናገኛለን። እነርሱን ስታጠና እነዚህን የክርስቶስን ባህርያት ይዘህ እንደሆነ ራስህን ጠይቅ።

(7). በገላ. 5፥22-23 ላይ የሠፈሩትን ዘጠኙን የመንፈስ ፍሬዎችን አስፍር።

እውነተኛ የክርስቲያን ባህርይ ራሱን የሚገልጠው በመንፈስ ፍሬ ነው፤ ይህም የሚጠቃለለው በፍቅር ነው። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ሲኖር የሚዳብሩት ሌሎቹ የእግዘአብሔር ባሕርያት ሁሉ የሚመጡት ከፍቅር ነው። ስለዚህ ነው በ1ቆሮ. 13፥4-8 ያለው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ የእውነተኛ ክርስቲያን መለኪያ ተብሎ የሚጠራው።

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ፍቅር የሚለው ቃል አጋፔ ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ይህ ፍቅር በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚፈስ ነው "እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና" ይላል። (ሮሜ 5፥5) እንደዚህ ዓይነቱ ጥልቀት ያለው ፍቅር ነው እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ስለኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ እንዲሰጥ ያደረገው (ዮሐ. 3፥16)። ኢየሱስ ለእኛ ያለው ፍቅር ነው እኛ ሌሎችን እንድንወድ የሚያደርገን "ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደሆነ በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል።" (1የሐ. 3፥16፣ ዮሐ. 15፥12-13) ተመልከት።

*ኤ.ቲ. ፒርሰን የተባለ ሰው እንደሚከተለው ብለዋል፦*

*ደስታ የሚደሰት ፍቅር ነው፣*
*ሰላም በእምነት የማረፍ ፍቅር ነው፣*
*ትዕግስት በፈተና ውስጥ የሚያልፍ ፍቅር ነው፣*
*ቸርነት በሕብረተሰብ መካከል ያለ ፍቅር ነው፣*
*መልካምነት በሥራ የሚታይ ፍቅር ነው፣*
*ታማኝነት የፍቅር ጽናት ነው፣*
*ገርነት በሥልጠና ላይ ያለ ፍቅር ነው፣*
*ራስን መግዛት በዲሲፕሊን ውስጥ የሚታይ ፍቅር ነው።*

እውነተኛ የክርስቲያን ባህርይ የሆነው፣ የዚህ ዓይነቱ ፍቅር ካለህ ታጋሽ ትሆናለህ (1ቆሮ. 13፥4-7)። በማንኛውም መጽናት ባለብህ ሁኔታዎች ውስጥ፥ ቶሎ በመናደድ በኋላ የምትጸጸትባቸውን ነገሮች አትናገርም፥ አታደርግምም።

- ሊሚጎዱህ ሰዎች ቸር ትሆናለህ።
- እግዚአብሔር ለአንተ በሰጠህ በመርካት፣ የሌሎችን ስልጣን ወይም ሐብት አትመቀኝም።
- ስለላከናወንካቸው ነገሮች ሌሎች አንተን ሲያመሠግኑ እግዚአብሔርን ታከብራለህ እንጂ አትመካም።
- የምታደርገው ሁሉ በእርሱ ኃይል ስለሆነና ያለህ ማንኛውም ነገር ከእግዚአብሔር የተሰጠህ በመሆኑ አትታበይም።
- *የማይገባውን አታደርግም፤* እውነተኛ ክርስቲያን፥ ሰዎች በየትኛውም ደረጃ ላይ ይሁኑ እያንዳንዱን ሰው ያከብራል።
- *ራስ ወዳድ አትሆንም*፣ ከአንተ በፊት በመጀመሪያ እግዚአብሔርን፥ ከዚያም ሌሎችን ታስቀድማለህ።
- በቀላሉ አትበሳጭም፥ በቀላሉ አትጎዳም፤ ይልቁንም የማይጎዳ ትሆናለህ።
- ሰዎች በአንተ ላይ የሰሩትን በደል ይቅር ትላለህ እንጂ በደልን አትቆጥርም።
- *በማናቸውም ዓይነት ክፋት አትሰኝም*፣ ከዚህ ይልቅ ከክፋት የተነሳ ክርስቶስ ስቃይ ለመቀበል እንዴት ፈቃደኛ እንደሆነ ታስባለህ።
- *በእውነት ደስ ይልሃል*።
- ሁልጊዜ ትክክል የሆነውን *ትጠብቃለህ*።
- ሁልጊዜ እውነት የሆነውን ተቀብለህ *ታምናለህ*።
- ሁልጊዜ እግዚአብሔር የሰጠውን *ተስፋ ታደርጋለህ*።
- ሁልጊዜ *ትታገሳለሁ*፥ የተሰጠህን ተስፋ እስክትጨብጥ፣ ተስፋ ያረግኸው እውን እስኪሆን ትጸናለህ ።

(8). ፍቅር ምን እንደሚያደርግና ምን እንደሆነ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

| | |
|---|---|
| ሀ. ራሱን ይገዛል | ቀ. ስላማዊ |
| ለ. የራሱን አይፈልግም | በ. ቀናተኛ |
| ሐ. ራሱን መስዋዕት ያደርጋል | ተ. በቶሎ የሚቆጣ |
| መ. ገር | ቸ. የሚጸና |
| ሠ. ትሁት | ኀ. እውነትን የሚጠብቅ |
| ረ. ሥርዓት የሌለው | ነ. ትዕቢተኛ |
| ሰ. ታጋሽ | አ. ተስፋ የሚያደርግ |
| ሸ. ሁልጊዜ ደስተኛ | ከ. መልካም |



# በሥራ ላይ ማዋል

***ዓላማ 6 የመንፈስ ፍሬ በክርስቶስ ሕይወት እንደታየው፣ በአንተ ህይወት እንዴት እንደምታሳይ ለመግለጽ።***

በዚህ መስፈርት ወይም መመዘኛ ማን ሊለካ ይችላል ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። በዚህ መስፈርት ተለክቶ መስፈርቱን ያሟላ አንድ ብቻ ነው። እርሱም ኢየሱስ ነው። ስሙን በእያንዳንዱ የመንፈስ ፍሬ ፊት ብታስቀምጠው ፍጹምና የሚስማማ ሆኖ ልታገኘው ትችላለህ። ኢየሱስ እርሱ ያላደረገውን እኛ እንድናደርግ አይጠይቀንም። እርሱ ያደረገውም በውስጣችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

ክርስቶስ ምሳሌአችን ነው። በራሳችን ኃይል እርሱን መምሰል አንችልም። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ አምሳል ቀርጾ እንዲያወጣን መፍቀድ አለብን። እኛ የእርሱ ባህርይ ተካፋዮች ነን (2ጴጥ. 1፥4)። የተካፋይነታችን መጠን የሚወሰነው መለኪያ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ፍጹም ስብዕና በቀረብን መጠን ነው።

(9). በክርስቶስ ምድራዊ ሕይወቱ፥ የተገለጡ መለኮታዊ ባሕርያት ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጥንቂ በማንበብ፥ አብሮ ከሚሄደው የመንፈስ ፍሬ ጋር አዛምድ። ቁጥሩን በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ሙላ።

| | |
|---|---|
| ______ ሀ. ዮሐ. 14፥27 | 1. ፍቅር |
| ______ ለ. ኢሳ. 53፥7 | 2. ደስታ |
| ______ ሐ. ዕብ. 4፥15 | 3. ሰላም |
| ______ መ. 2ጴጥ. 3፥9 | 4. ትዕግስት |
| ______ ሠ. ሉቃ. 22፥42 | 5. ቸርነት |
| ______ ረ. 1ዮሐ. 3፥16 | 6. በጎነት |
| ______ ሰ. ማቴ. 4፥1-11 | 7. ታማኝነት |
| ______ ሸ. ዮሐ. 8፥3-11 | 8. የዋኅት/ ገርነት |
| ______ ቀ. ዮሐ. 8፥3-11 | 9. ራስን መግዛት |
| ______ በ. ዕብ. 12፥2 | |
| ______ ተ. የሐዋ. 10፥38 | |
| ______ ቸ. ማቴ. 18፥21-22 | |

እንግዲህ ራሳችንን እንመርምር። ብዙዎቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤታችን ተማሪ የነበረን አንድ ወጣት በጥቂቱ እንመስላለን። ሮቤል የተባለው ይህ ተማሪ ፈተናን በጣም አድርጎ ይጠላል። በፈተና ሰዓት በመቃተት ዓይነት ከውስጡ ይተነፍሳል። ሁሉንም ጥያቄዎች የሚመልሰው አልፎ

በክርስቶስ በኩል በወንጌሉ እንደሚፈረድብን ጳውሎስ ይነግረናል። (ሮሜ 2፥16) ምናልባትም በ1ቆሮ. 13ኛው ምዕራፍ ላይ የተጻፈው ቃል ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት የሚጠቀምባቸው ቃላት ሳይሆኑ አይቀሩም፥ ማለትም ለሚመጣው ምንግስት የኃለፊት ስፍራ ሊይዙ የሚችሉትን የሚመርጥበት መሠረት ይሆናል። ይህ ጳውሎስ የሚሰጠን የመንፈስ ፍሬ ትርጉም በየጊዜው እያጠናን ለመጨረሻ ፈተናችን እንድንዘጋጅ ያደርገናል።

በክርስቲያን ባሕርይ እግዚአብሔር የሚጠይቀው ሁሉ የመንፈስ ፍሬ ብለን ባጠናነው የመጻሐፍ ቅዱስ ክፍል ተሰጥተዋል። ሁሉም የእግዚአብሔርን ባሕርያትና ጠባይ የሚያንጸባርቁ ናቸው። እነዚህን ፍሬዎች በራስህ ልታፈራቸው አትችልም። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለህ የግል ግንኙነት በሕይወትህ እያደጉ እንዲሄዱ መፍቀድ አለብህ። እርሱ እነዚህን ፍሬዎች በአንተ ውስጥ ያፈራል።

(10). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ፥ በገላ. 5፥22-23 እና በ1ቆሮ. 13 ላይ የተጻፈቱን የመንፈስ ፍሬዎች አስፍር። እነዚህን ፍረሬዎች በሕይወ ትህ በማፍራት ረገድ ጠንካራና ደካማ ጎንህን በመገምገም መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ እያንዳንዱን ፍሬ እንዲያፈራ፥ በክርስቶስ ያፈራውን ያህል፥ በአንተም ውስጥ እንዲያፈራ በመጠየቅ ራስህን አሳለፈህ ስጥ።

## ፍሬ ዋጋ ያስገኛል

*ዓላማ 7 በመጽሐፍ ቅዱስ በመደገፍ ፍሬ ማፍራት የሚያስገኘውን ሦስት ዋጋዎች ለመጥቀስ።*

አንድ ጊዜ ከሃያ ዓመት በታች የነበርሁ ወጣት ነበርሁ አሁን ግን አያት ሆኛለሁ። በሁለቱ መካከል ብዙ የመማር ልመመዶች የሚይካድ ነው። አንዳንዶቹ የሚያስደስቱ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የማያስደስቱ ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም አስፈላጊዎች ነበሩ።

ለምን ያስፈልጋሉ? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። አስፈላጊነታቸው ለዚህ ሕይወት ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ለመኖር ዝግጁ በምሆንበት ጊዜ ሕይወት ወደ ፍጻሜ ይደርሳል! ነገር ግን፥ መንፈስ ቅዱስ ወደፊት ለሚሆን ለአንድ ትልቅ ነገር እያዘጋጀኝ ነው። የሚያዘጋጀኝም እኔ ከማስበው በላይ ለሆነ ትልቅ ነገር ነው። የመንፈስ ፍሬ የሆነው ክርስቲያናዊ ባሕርዬ በመንፈስ ቅዱስ በውስጤ ለዘላለማዊ መኖሪያዬ እያዘጋጀኝ ነው።

ከ1ቆሮ. 13 ላይ የመጨረሻዎቹን ስድስት ቁጥሮች እንመልከትና እነዚህን ዘላለማዊ ጥቅሞች ልብ ብለን እናስተውል።



## ጊዜ አይወስነውም

የክርስቲያን ባህርይ አሁን ልታገኘው የምትችለው የዘላለማዊ ሕይወት አንዱ ክፍል ነው፤ የቀረው ሁሉ ያልፋል። "ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል" (ቁ.8) ይላል።

ኢየሱስን ፊት ለፊት በምናይበት ጊዜ ትንቢት ያንጊዜ ስለማያስፈል ያበቃል። ከተፈጸመ በኋላ ትዝታ ብቻ ይሆናል። በመንፈስ በኩል የሚሆን የበለጠ ተግባቦት በሚኖረን ጊዜ የሚታወቅና የማይታወቅ ልሳን፥ ሁለቱም ጸጥ ይላሉ። የቋንቋ ልዩነትም አይኖርም።

ያለን የተወሰነ ዕውቀትም ያልፋል፥ ምክንያቱም ትንቢት፣ ልሳንና የአሁኑ ዕውቀት ለዚህ ለአሁኑ ሕይወት እግዚአብሔርን በከፊል የሚገልጡልን ናቸው። በዚህ ሕይወት መጨረሻ ላይ እንዳለ የሚቆየው የባህርይ እድገታችን ብቻ ነው። "ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ጸንቶ ይኖራል።" የክርስቲያን ባህርይ በጊዜ አይገደብም። (1ቆሮ. 13፥8፣ 13)።

(11). (ትክክለኛውን መልስ ምረጥ) በክርስቶስ ዘላለማዊ መንግስት፥ ልሳን፣ ትንቢትና ከፊል ዕውቀት የማያስፈልግበት ምክንያት

ሀ. በእርሱ ፊት ስንሆን ይህ ከፊል መገለጥ የማያስፈልግት ምክንያት እርሱን እንዳለ ስለምናየውና ስለምናውቀው ነው።
ለ. በእርሱ መንግስት ተግባቦት አስፈላጊነት አይኖረውም።
ሐ. ከእርሱ ጋር ስንነግስ በእኛ ውስጥ የሚሠራ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አያስፈልገንም።

## ብስለት ወይም ዕድገትን ያመጣል

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በመንፈሳዊ ሕይወት መኖር የምንጀምረው በአዲስ ልደት ነው። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂነት በቃሉ እየታነጽን በዕውቀትና በልምምድ እናድጋለን፤ አዲሱን ልደት ከተለማመድን በኋላ ሁላችንም በተለያዩ የመንፈሳዊ ዕድገት ደረጃዎች ላይ ያለን የእግዚአብሔር ልጆች ነን። ክርስቲያን የሆንበት የጊዜ ርዝመት ከክርስቲያናዊ ዕድገታችን ጋር ያለው ግንኙነት በጣም ትንሽ ነው።

ከእርሱ ጋር እስከተባበርን ድረስ፣ መንፈስ ቅዱስ የክርስቲያን ባህርይ ፍሬን በሕይወታችን ያፈራል። አንዳንድ በመንፈስ የተሞሉ አማኞች ጥቂት ትምህርቶችን በመማር ብዙ ዓመታት ያባክናሉ። ልሳን፣ ትንቢትና ዕውቀት ጠቃሚና አስደናቂ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ የእነርሱ በሕይወታችን መኖር ሁልጊዜ ክርስቲያናዊ ብስለታችንን የሚያመለክት አይደለም። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ዕድገታችን

የሚለካው፥ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ባህርያት በሕይወታችን እንዲያፈራ በፈቀድንለት መጠን ነው።

(12). ዮሐ.15፥1-5 ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ ፍሬ እንድታፈራ አስፈላጊው ሁኔታ ምንድን ነው?

በክርስቶስ መኖር ከክርስቶስ ጋር መተባበርን (ቁ. 1-2)፣ በአብ መገረዝንና (ቁ. 2) ፍሬ ማፍራትን (ቁ. 5) ያመጣል። የፍሬያማነት ሁኔታዎች እነዚህ ናቸው።

(13). በ2ጴጥ.1፥5-8 ላይ የመንፈስ ፍሬን የማሳደግ ሂደት ተፅፎ እናገኛለን። ክርስቲያናዊ ብስለትን ለማጠናከር ደረጃ በደረጃ ልንከተል የሚገባውን ቅደም ተከተል ዘርዝር።

ጴጥሮስም በመቀጠል "እነዚህ ባህርያት ተትረፍርፈው ቢኖሯችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ዳተኞችና ፍሬ ቢሶች ከመሆን ይጠብቋችኋል። እነዚህ ባህርያት የሌሉት ግን የሩቁን የማያይ ወይም ዕውር ነው፤ ከቀድሞው ኃጢአቱ መንጻቱን ረስቶአል።" ይላል (2ጴጥ. 1፥8-9)።

## ሙላትን ያመጣል

ምሳሌአችን በሆነው በኢየሱስ ፊት በመጨረሻ ስንቆም፥ሙሉ በሙሉ ያደገ ክርስቲያን ምን መምሰል እንደሚገባው እናውቃለን። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው፦ "አሁን በመስታወት እንደምናየው ዓይነት በድንግዝግዝ እናያለን፣ በዚያን ጊዜ ግን በግልጥ እናያለን" (1ቆሮ. 13፥12)። አሁን በድንግዝግዝ መስተዋት እንደማየት ነው ከዚያ በሃላ ግን እግዚአብሔር እንደሚያየን ራሳችንን እናያለን። አሁን የሚረዳን እምነት፥ ወደ ፊትም እንድንገነዘ የሚገፋፋን ተስፋ አለን። እነዚህ ግን ዘላለማዊ አይደሉም። ኢየሱስን በምናይበት ጊዜ ሁለቱም ያልፋሉ።

ሽልማታችንን በሙላት ለማግኘት ብቸኛው መንገድ በሕይወታችን የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለዚሁ ሲያሳስብ "እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም፤ በዚህም ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋል" ይላል (2ጴጥ.1፥10-11)።

(14). ፍሬ ማፍራት የሚያስገኘውን ሦስት ዋጋዎች፣ እያንዳንዱን በቃሉ በማስደገፍ ጥቀስ።



## የሙከራ ፈተና

የተሻለውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

1. የመንፈስ ፍሬ የሚለው ቃል የሚያመለክተው

ሀ. መንፈሳዊ ስጦታዎችን ነው።
ለ. ትንቢትና መሥዋዕትን ነው።
ሐ. ክርስቶስን መምሰልን ነው።

2. የመንፈሳዊ ፍሬ ባሕርያት በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚዳብሩት

ሀ. በመንፈስ ቅዱስ ነው።
ለ. በትምህርትና በልምምድ ነው።
ሐ. ኢየሱስን ለመምሰል በሚያደርገው በራሱ ጥረት ነው።

3. ክርስቲያናዊ ባሕርይን ለማጎልበት የአማኙ ድርሻ

ሀ. ክርስቶስን ለመምሰል መሞከር
ለ. በሕጉ መሠረት መኖር
ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በእርሱ ውስጥ እንዲጎለብት መፍቀድ

4. የመንፈስ ፍሬ ወይም የክርስቲያን ባህርይ በተሻለ መንገድ ጠቅለል አድርጎ ሊገልጸው የሚችለው ቃል፡

ሀ. አጋፔ (ፍቅር)
ለ. አገልግሎት
ሐ. እምነት
መ. ምስክርነት

5. ለክርስቲያን ከሁሉም ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የምናገረው
ለ. ማንነቴ
ሐ. የማደርገው
መ. የሚሰማኝ

6. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ኖረውኝ፣ ከንቱ የምሆነው ግን

ሀ. ኃይል ከሌለኝ ነው።
ለ. ልሳን ከሌለኝ ነው።
ሐ. መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሌለኝ ነው።
መ. ፍቅር ከሌለኝ ነው።

7. በእግዚአብሔር መንግሥት ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት አማኞች የሚሰጣቸው የሥልጣን ቦታ በምን መሠረት ነው?

ሀ. በፈጸሙት ድርጊት
ለ. በምኞታቸው
ሐ. ክርስቶስን በመምሰላቸው
መ. በአምልኮ ልምምዳቸው

8. እራስን መግዛት ____________ ፍቅር ነው።

ሀ. የድርጊት
ለ. የዲሲፕሊን
ሐ. የፈተና
መ. የሕብረት

9. ለዘላለም ሊቆይ የሚችለው ብቸኛ ነገር

ሀ. ተስፋ
ለ. ትንቢት
ሐ. እምነት
መ. ክርስቲያናዊ ባህርይ

10. በ2ጴጥ. 1፥5-8 ላይ በተሰጠው መሠረት የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ የማሳደግ ሂደት፥ ጀምሮ የሚጨርሰው በየትኞቹ ሁለት ቃላት ነው?

ሀ. እምነት - ራስን መግዛት
ለ. መልካምነት - እግዚአብሔርን መምሰል
ሐ. እምነት- ፍቅር
መ. ፍቅር - ጽናት



## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

8. ከ "ረ" "በ" "ተ" "ነ"፥ በስተቀር ሌሎቹን መከበብ አለብህ።

1. ለ

9. እኔ የማዛምዳቸው በሚከተለው መንገድ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 3 | ሠ. 7 | ቀ. 5 |
| ለ. 8 | ረ. 1 | በ. 2 |
| ሐ. 9 | ሰ. 9 | ተ. 6 |
| መ. 4 | ሸ. 6 | ቸ. 4 |

2. ሀ. ከምናደርገው፥ የሆንነው ለ. እርሱን መምሰል
ሐ. በፍሬአችን፥ ክርስቲያናዊ ባህርይ

10. የአንተ መልስ።

3. ፍቅር ወይም የክርስቲያን ባህርይ ነው።

11. ሀ

4. ክርስቶስ ለእኛ ባለው ዓይነት ፍቅር ስናደርግ

12. ፍሬ እንድታፈራ በእርሱ መኖር አለብህ።

5. የአንተ መልስ። እኔ እንደምለው ክርስቶስ ያሳየውን ፍቅር ማሳየት ዘላለማዊ ዋጋ የሚያስገኝ እንደሆነ እንድንረዳ ስለፈለገ ነው። ራስን መስዋዕት ማድረግ ሰው ሊያደርገው የሚችለው የመጨረሻ ትልቁ ነገር ነው።

13. በእምነት ላይ በጎነት
በበጎነት ላይ ዕውቀት
በዕውቀት ላይ ራስን መግዛት
ራስን በመግዛት ላይ መጽናትን
በመጽናት ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነትን
በእውነተኛ መንፈሳዊነት ላይ ወንድማዊ መተሳሰብን
በወንድማዊ መተሳሰብ ላይ ፍቅርን ጨምሩ።

6. ሀ. እውነት
ለ. ሐሰት
ሐ. እውነት
መ. ሐሰት
ሠ. እውነት
ረ. እውነት
ሰ. ሐሰት
ሸ. እውነት

14. መንፈሳዊ ፍሬ ወይም ፍቅር በጊዜ አይገደብም። 1ቆሮ.13፥8፣ 13። መንፈሳዊ ብስለትን ወይም ክርስቶስን መምሰልን ያስገኛል 2ጴጥ.1፥8። ሙላትን ያስገኛል 2ጴጥ.1 10-11።

7. ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ እምነት፣ የዋሃት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት።

---

# የሙከራ ፈተና መልስ

## ትምህርት 1

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እወነት
4. እውነት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት
11. ችግሮች
12. ፍላጎቶች
13. ልምምድ
14. ግንኙነት
15. ብስለት

16. ፍጹም
17. የስሜት፥ የማወቅና የመምረጥ ችሎታ
18. እርሱ አካል ስላለው ሊወደኝ ይችላል። እኔም ለፍቅሩ ምላሽ መስጠት እችላለሁ። በእኔ በኩልም ሌሎችን ሊወድ ይችላል።
19. ከእነዚህ የትኛውም ሊሆን ይችላል - ሊዋሽ፣ ሊቃወሙት፣ ሊሰደብ፣ ኃጢአት ሊደረግበት ይችላል።

## ትምህርት 2

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት
11. ሐሰት
12. እውነት

13. ከለ፥ መ፥ በ፥ በስተቀር የቀሩትን መክበብ አለብህ።
14. እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱ መተባበር ስላለው።
15. መለኮታዊ ባሕሪይ ስላለው፥ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ኃይል፣ ቅድስናና ሕብረትን ይሰጠኛል።



## ትምህርት 3

1. ሐ)
2. መ)
3. ለ)
4. ሀ)
5. ሐ)
6. ሀ)
7. መ)
8. ሐ)
9. ሀ)

10. ከነዚህ ሁለቱ፡ መልስ ይሆናል። የክርስቶስን ነገሮች እንድናስታውስ ወደ ሃሳባችን ያመጣል። ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል፥ ክርስቶስን ያከብራል፥ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ወደፊት ስለሚፈጸሙት ነገሮች እንድናውቅ ያደርገናል።

11. ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስና አማኝ

## ትምህርት 4

1. ለ)
2. ሐ)
3. ሀ)
4. ለ)
5. ሀ)
6. ሐ)
7. ሐ)
8. ሀ)
9. ለ)
10. ለ)
11. ለ)
12. ለ)

## ትምህርት 5

1. ሐ)
2. ለ)
3. መ)
4. ለ)
5. ሀ)
6. ሐ)
7. ሀ)
8. ሐ)
9. ሐ)
10. ለ)
11. ሠ)
12. ሀ)

## ትምህርት 6

1. ሀ)
2. ለ)
3. ለ)
4. ለ)
5. ሀ)
6. ሀ)
7. ለ)

## ትምህርት 7

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት
11. ሐሰት
12. እውነት

## ትምህርት 8

1. መ)
2. ሀ)
3. ለ)
4. ለ)
5. ሐ)
6. ሀ)
7. ሀ)
8. እውነት
9. እውነት
10. ሐሰት
11. እውነት
12. ሐሰት
13. እውነት
14. እውነት
15. እውነት
16. እውነት
17. ሐሰት
18. ሐሰት
19. እውነት
20. እውነት

## ትምህርት 9

1. ሀ. 7)
   ለ. 4)
   ሐ. 8)
   መ. 1)
   ሠ. 6)
   ረ. 2)
   ሰ. 5)
   ሸ. 3)
   ቀ. 9)

2. የንግግር ስጦታዎች፥ የኃይል ስጦታዎች እና የመገለጥ ስጦታዎች

3. ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽና፥ ክርስቶስን ለማክበር

4. ማንኛውም በመንፈስ የተሞላ አማኝ። (የሚሰጡት ግን እንደ መንፈስ ቅዱስ ምርጫ ነው። እኛ የመንፈስን ስጦታዎች እንድንሻ ተነግሮናል። ይህ የሚያሳየን መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ከልብ የሚሹትን እንደሚመርጣቸው ነው)።

## ትምህርት. 10

1. ሐ)
2. ሀ)
3. ሐ)
4. ሀ)
5. ለ)
6. መ)
7. ሐ)
8. ለ)
9. መ)
10. ሐ)